ክክ ሄ ዲ ዐ

HICKORY DICKORY DO

A HERCULE POIROT MYSTERY

ከአጋታ - ክርስቲ



ካነ
556/2000

ጮ ዳ ና ው

ማዳበ አበባ

HICKORY DICKORY DOCK

AGATHA CHRISTIE

Addis Ababa City Government
Culture & Information Bureau
Public Library

- HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA

የሕዝብ ቤተ

ትርጉም በጊታቸው መኩንን ሐሰን (ሊ/ኮ)

በተፈራ በላቸው

ሰኔ 1984

“ በጣም ይቅርታ የኔ ጌታ ” አለች ። ቀጥላም “ እንዴት እን ደሆነ — ማወቅ ነበረብኝ ፣ ግን አላወቅሁም ። ብቻ በእህቴ ምክንያት ነው ” ስትል ነገረችው ።

“ እህትሽ ? ”

እንደገና ደነገጠች ። ፖይሮት ፍጹም ሚስስ ሊመን እህት ይኖራታል ብሎም አላሰበም ። እስከነአካቴውም አባት ፣ እናት ፣ ወይ ንም አያት ይኑራት አይኑራት እርሱ የሚያውቀው ነገር የለም ። ብቻ ሚስስ ሊመን ፍጹም መሣሪያ የፈበረካት ነገር ናት ። እውነቱን ለመ ናገር በሥራዋ ፍጹም ናት — ፍቅር ፣ የቤተሰብ ናፍቆት ፣ ሀሳብ አለባት ሲባል አስቂኝ ይሆናል ። ሚስስ ሊመን ልቧና ጭን ቅላቷ በሙሉ ሥራ በሌላት ጊዜ እንኳ ስሟን ለሚያሞግስላትና ክብሯን ለሚጠብቅላት አዲስ የማህደር አሠራርና ሌሎች ሥራዎች መሻሻልና የፈጠራ ተግባር የሚውል መሆኑ የታወቀ ነው ።

“ እህቴ ? ” ሲል ሔርኩሌ ፖይሮት ደገመው ። ከአነጋገሩ የተነ ገረውን እንዳላመነ ለመረዳት ይቻላል ።

ሚስስ ሊመን ኮስተር ብላ ራሷን ነቀነቀች ።

“ አዎን ” አለች ። “ ስለ‘ርሷ አንስቼልህ የማውቅም አይመስ ለኝም ። አብዛኛውን የሕይወቷን ዘመን ያሳለፈችው ሲንጋፖር ነበር ። ባሏ ከዚያው ሀገር በጎማ ፋብሪካ ይሰራ ነበር ። ”

ሔርኩሌ ፖይሮት በገባው ሰው አኳኋን ራሱን ነቀነቀ ። የሚስስ ሊመን እህት አብዛኛውን የሕይወቷን ጊዜ ሲንጋፖር ማሳለፏ ትክክል ሆኖ ተሰማው ። እንደ ሲንጋፖር ዓይነቶቹ ቦታዎች ጥቅም እንደዚህ ላሉ ጉዳዮች ነው ። እንደ ሚስስ ሊመን ዓይነቶቹ ሴቶች በንግድ ሥራ ሲንጋፖር የተሠማሩ ወንዶች ሚስቶች ነበሩ ። ስለዚህ ነው መሰል የወዲህኛው ዓለሞቹ ሚስስ ሊመኖች ራሳቸውን ለአለቆቻቸውና ቀጣ ሪዎቻቸው ልዩ መሣሪያ አድርገው የሚያቀርቡት ። (በእረፍት ጊዜያ ቸው እንኳ ሳይቀር አዳዲስ የማህደር አያያዝ ስልቶችን ይፈጥራሉ)

“ ደህና ገንዘብ አላት — ምንም እንኳ ገንዘብ ማድረግ የሚ ችለውን ባያደርግም ፣ ፍላጎቷና ምኞቷ ግን እስከዚህም ብዙ የሚያ ስወጣት አይደለም ። ከተጨነቀች ብዙ ጊዜ ያለ ችግር መኖርም ትችላለች ። ”

ሚስስ ሊመን ለትንሽ ጊዜ ንግግሯን ካቋረጠች በኋላ ቀጠለች ።

“ በእርግጥ እውነተኛው ችግሯ ብቸኛ መሆኗ ነው ። ከእን ግሊዝ ውስጥ ፍጹም ኖራም አታውቅ ፣ አብሮ አደጎችና የልብ ወዳ ጆች የሏትም ፣ በዚሁ ላይ ብዙ ጊዜ ያለምንም ሥራ ነው የምታሳል ፈው ። ብቻ ከስድስት ወራት በፊት ይህን ሥራ ለመያዝ እንዳሰበች ነገረችኝ ” አለች ።

“ሥራ ? ”

“ምንድነው የሚሉት እኒህ - አስተናጋጅ ? ወይንስ አስተናባሪ ? ከአንድ የተማሪዎች ሆስቴል ነው ። ሆስቴሉ በከፊል የአንዲት ግሪ ካዊት ነው ። አንድ በሀላፊነት የሚሠራላት ሰው ትፈልግ ነበር ። ምግ ብና ሌሎች ነገሮችን በሚመለከት ሥራው በሚገባ እንዲካሄድ ታደ ርጋለች ፣ ጥንታዊነት ያለው ብዙ ክፍሎች የሚገኙበት ከ ሒኮሪ ጎዳና የሚገኝ ቤት ነው ። ሒኮሪ ጎዳናን ካወቅከው ማለቴ ነው ።” ፖይ ሮት ግን አያውቀውም ነበር ። “በአንድ ወቅት በጣም የተከበረ አካባቢ ነበረ ። የቤቶቹም አሠራር ልዩ ነው ። እህቴም በጣም ምቾት ያለ ውን ማለፊያ መኝታ ቤት ፣ እንግዳ ቤትና ትንሽ መታጠቢያ ያላት ወጥ ቤት ልታገኝ ነው ። ”

ሚስስ ሊመን ንግግሯን አቋረጠች ። ፖይሮት ግን አበረታ ታት ። ጉዳዩ እስከፊ መስሎ እስካልታየው ድረስ ማበረታታትም ነበ ረበት ።

“ እኔም ራሴ ስለነገሩ ርግጠኛ አልነበርኩም ። ነገር ግን የእህ ቴን ምክንያት ተረዳሁት ። እጆቿን አጣጥፋ የምትቀመጥ ሰው አልነ በረችም ። ከዚህ በተጨማሪ ሥራ ወዳድ ከመሆኗም በላይ ችግሮችን መፍታትና ምን መደረግ እንደሚገባ አሳምራ የምታውቅ ነበረች ። ገንዘብ ማውጣትና የመሳሰለውን ብኩንነት አትወደውም ። ሥፍራው እንኳ ገንዘብ የሚገኝበት ነበረ ፤ በርግጥ ከፍተኛ ደሞወዝ አልነበረም። ‘ርሷ ግን ያንን አልፈለገችውም ። ጉልበት የሚጠይቅም ሥራ አል ነበረም ። ወጣቶችን ከበፊት ጀምሮ ትወዳቸዋለች ፣ ትግባባቸዋለች ፣ ትስማማለች ። ከምሥራቁ የዓለም ክፍል ስለኖረች የዘር ልዩነት ንና ደካማ ስሜትን በሚገባ መረዳት ትችላለች ። ምክንያቱም እነ ዚህ ከሆስቴሉ የሚኖሩ ተማሪዎች ከብዙ የተለያዩ ዜጐች የተውጣጡ ናቸው ። አብዛኛዎቹ እንግሊዛዊያን ሲሆኑ ጥቂቶቹ ጥቁሮች ናቸው ።

“የተለመደ ነው ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ።

“ዛሬ ከሆስፒታል ያሉት ነርሶቻችን በከፊል ጥቁሮች ናቸው ፣” አለች ሚስስ ሊመን ርግጠኛነቷን እየተጠራጠረች ። ቀጠል አድርጋም ፣ “ ከእንግሊዛዊያት ይልቅ የበለጠ ተግባቢዎችና ሰው አክ

ባሪዎች ናቸው ብዬ አስባለሁ ። ይህ ሁኔታ ግን ከሁለቱም ዘንድ የለም። በመጨረሻ ላይ በጉዳዩ በደንብ ከተወያየንበት በኋላ እህቱ ገባች ። እኔም ሆንኩኝ ' ርሷ ለባለ ሀብቷ ለሚስ ኒኮሊተስ ለዚያች መላቅጥ ባህርይዋ ለማይታወቅ ሴት ፡ ለዚያች አንዳንዴ ደስተኛ ፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፡ ብቻ ይህን በመናገሬ አዝናለሁ ፡ ፍጹም ተቃራኒ ሁኔታ ለም ታሳየዋ እመቤት ብዙም ዋጋ አንሰጣትም። ሁለቱንም አንድ የሚያ ደርጋቸው የገንዘብ ስስት ባህሪያቸው ነው ። እውነቱን ለመናገር ብቁና ቀልጣፋ ሰው ብትሆን ኖሮ ሪዳትም አያስፈልጋትም ነበር ። እህቱ ለማንም መጥፎ ባህርይና ብስጭት ሥፍራ የምትሰጥ አልነበረችም ። ከማንም በሆን መነታረክ የማትፈልግና ክብሯንም የማታስ ነካ ነበረች ። ”

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ። የወይዘሪት ሊመን እህት ከሞላ ጎደል እንደ እህቷ ሆና ታየችው — በጋብቻና በሲንጋፖር ባህል የበሰለች ፡ ነገር ግን ያው የለመደው የስሜት ጉጥ ያላት ሆና ተሰማችው ።

“ ታዲያ እህትሽ ሥራውን ያዘች ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ አዎን ፡ ከቁጥር 26 ሔኮሪ ጎዳና ከስድስት ወራት በፊት ገባች ። በአጠቃላይ ሥፍራውንም ሥራውንም ወደደችው ። ”

ሔርኩሌ ፖይሮት አዳመጣት ። እስካሁን የተተረከው ሚስስ ሊመን እህት ጅብድ የሚያናድድና የሚያሰለች ነበር ።

ለጥቂት ጊዜ በጣም በማሰብ ላይ ሆና ትታይ ነበር ። ጭንቅቷ ከፊቷ ይነበባል ።

“ ለምን ? ”

“ አየህ መሴ ፖይሮት ፡ የምታያቸውን አንዳንድ ነገሮች አልወ ደደቻቸውም ። ”

“ ተማሪዎቹ ከሁለቱም ጸታዎች ነበሩ ? ” ሲል ፖይሮት ጠየቀ ።

“ የለም ፡ መሴ ፖይሮት እንደዚያ ማለቴ አይደለም ! አንድ ሰው እንደዚያ ስላለው ችግር ሁልጊዜም ቢሆን መዘጋጀት አለበት ። እንደዚህ የመሳሰሉ ነገሮችን መጠበቅ ይኖርበታል ! የለም ፡ አየህ ? ዕቃዎች እየጠፉ ነው ። ”

“ እየጠፉ ነው ? ”

“ አዎን ፡ ሁሉም ነገር ባልታሰበ መንገድ ሲፈጸም . . . ግራ የሚ ገባ ነገር ሆኗል . . . ”

‘‘ዕቃዎች እየጠፉ ነው ስትይ ዕቃዎች እየተሠረቁ ማለትሽ ነው?’’

‘‘ አዎን ። ’’

‘‘ ፖሊስ ተጠርቶ ነበር ? ’’

‘‘ የለም ፣ ገና አልተነገረም ። እህቴም አስፈላጊ ሆኖ አላገኘች ውም። እነዚህን ወጣት ልጆች ትወዳቸዋለች ፣ ጥቂቶቹን ማለቴ ነው ። አዎን ! ራሷ ችግሩን ለማቃለል ትሞክራለች ። ’’

‘‘ አዎን ’’ አለ ፖይሮት በሀሳብ እንደተዋጠ ። ‘‘ ነገሩ በር ግጥ ይገባኛል ፣ ግን እንደዚያ ማለቴ ሀሳቤን አይገልጸውም ። የአንቺ ችግር ያው የእህትሽም እንደሆነ አድርጌ አስባለሁ ። ’’

‘‘ መሲ ፖይሮት ሁኔታውን አልወደድኩትም ። ፍጹም አልወ ደድኩትም ። አንዳች ልረዳው የማልችለው ነገር እየተካሔደ እንዳለ ያለኝን ስሜት መግታት አልችልም ። ምንም ዓይነት ተራ ገለጻ እው ነቱን ሊደብቀው አይችልም ። ደግሞ ሌላ ምክንያት መኖር አለመኖ ኖሩን ለመገንዘብ ያዳግተኛል ። ’’

ፖይሮት በሀሳብ ተዋጠ ። ራሱን በአንድ ነገር ላይ እንዳተኮረ ሰው ሆኖ ይነቀንቃል ።

ሚስስ ሊመን ያለባት ደካማ ጎን ይሆናል ብሎ ማመኑ ነው ። ሌላ የሚያስከፋ ጎን የላትም ። የማስረጃ ጉዳይ ሲሆን የምትበገር አይ ደለችም ። የይሆናል ነገር ሲሆን ግን ከሀሳብ ባህር ትሰጥማለች ። ማንም የሚስተካክላት ሰው የለም ።

‘‘ ተራ ሥርቆት አይደለም ? እንዲያው የሥርቆት ሱስ በሽታ ይሆን ? ’’

‘‘ የለም አይመስለኝም ። ስለዚህ ጉዳይ እንብቤ ነበር ’’ አለች ሊመን በጠንቃቃና በእውነተኛ አገላለጽ ። ቀጥላም ፣ ‘‘ከኢንሳይክሎ ፒዲያ ብሪታኒካና ከአንድ የሕክምና ጽሑፍ እንብቤ ነበር ። ነገር ግን አልረካሁበትም ስትል አከለችበት ። ’’

ለአንድ ለሁለት ደቂቃ ሔርኩሌ ፖይሮት ጸጥ ብሎ ቆየ ።

እንዴት ዝም ብሎ ለሚስስ ሊመን እህትና ለአንድ የዘር ስብጥር ናሙና ሆስቴል የውስጥ ችግርና ብጥብጥ ዘሎ ራሱን ይነክ ራል ? ከሁሉም በላይ ሚስስ ሊመን በደብዳቤው አተያየብ ላይ የሠ ራችው ስህተት የሚያበሳጭና የሚያናድድ ነበር ። ‘ርሱንም ከችግሩ ዘሎ ጥልቅ እንዲል የሚያበቃው ይኸው ብቻ ነው ። በዚህ የሚያስለ

ችና የማይረባ ነገር ዘሎ ጥልቅ እንዲል የሚያበቃው ይኸው ብቻ ነው ። ይህን የሚያሰለችና የማይረባ ጉዳይ እንዲት ሊያስበው እንደ ቻለ ራሱንም አላመነው ።

“ ውሀ ሲወስድ እያሣሣቀ ነው ” አለ ለራሱ በማጒተም ተም ።

“ ውሀ ? መጣቅ ?” አለች ሊመን አፍጥጣ እየተመለከተችው ።

“ ከጥንታዊ ጽሑፎች ውስጥ የተጻፈ ጥቅስ ነው ። ” ቀጠል አድርጎም ፣ “ ካለ ጥርጥር መቼም አብዛኛዎቹን የሽርሎክ ሆልምስን ጀብድ ሳታነቢ አልቀረሽም ” አላት ።

“ እ . . . እነዚህን የቤከር ጎዳና ተዋናዮች ምናምን ነው የም ትለኝ ? ” አለች ሊመን ። “ትላልቅ ሰዎች እንደዚህ የማይረቡ ሆነው ሲገኙ የሚያስገርም ነው ! ግን ይህ ደግሞ ከሁሉም ሥፍራ ነው ። ልክ እንደአሻንጉሊቶቹ ባቡሮች መሥመር ላይ እንደሚተውት ሆኖ ነው የሚሰማኝ ። ጊዜ ኖሮኝ አንብቤያቸዋለሁ አልልም ። ለማንበብ ጊዜ ሳገኝ ሁልጊዜም ቢሆን የምመርጠው ሥራዬን የሚያሻሽሉል ኝን መጽሐፍትን ነው ። ”

ሔርኩሌ ፖይሮት በአክብሮት ከእንጉቱ እጅ ነሳ ።

“ እንዴት መሰሎ ይታይሻል ሚስስ ሊመን ? አንድ ጊዜ እንዳው ትንሽ እንድትዝናና እህትሽን ምናልባት ለከሰዓት በኋላ ሻይ ብትጋብዣት ትንሽ ልረዳት እችል ይሆናል ። ”

“ በጣም አመሰግናለሁ መሲ ፖይሮት ። በእውነት ነው የምልህ ባለውለተኛዬ ነህ ። እህቴ ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ረፍት ናት ። ”

“ አንቺ ልታዘጋጅው ከቻልሽ ለነገ ብናደርገውስ ? ”

በዚሁ አጋጣሚ ታማኙና ታዛዥ ጆርጅ አራት ማዕዘን ጣፋጭ ያልሆኑ በቅቤ የራሱ ኬኮች ፣ ሶስት ማዕዘን ሳንድዊቾች ሌሎችም ከሰዓት በኋላ ድል ተደርገው ለሚደገሱ የእንግሊዝ ባሕል ሻይ ግብዣዎች የሚቀርቡት አስፈላጊ ምግቦች ሁሉ እንዲያዘጋጅ ተነ ገረው ።

— 2 —

ሚስ ሀበርድ የተባለችው የሚስስ ሊመን እህት ከእህቷ በጣም ትመሳሰላለች ። የቆዳዋ ቀለም ወደ ብጫው ያደላል ። ድምቡሽቡሽ ያለች፣ ጸጉሯን ለቅንጦት የተሠራች፣ በአኳኋኗ ሁሉ የተቀላጠፈች እመ ቤት ትመስላለች ። እኒያ ርህራሔና ቀና መንፈስ የሰፈነባቸው ውብ ዓይኖቿ ግን ከሚስስ ሊመን አፍንጫ የተለጠፈውን ክብ መነጽር ዘልቀው በሽሙጥ የሚታዘዙት ያው የተለመደ ገጿን የሚሸሽጉ አል ሆኑም ።

“ በጣም ከፍተኛ መስተንግዶ ነው መሴ ፖይሮት ፣ እግዜር ይስ ጥልኝ ። እንዴት በጣም ግሩም ጣዕም ያለው ሻይ ነው ? አቅሜ በላይ ነው የበላሁት ። ምናልባት አንድ ሳንድዊችና አንድ ስኒ ሻይ ሳል ደግም አልቀርም ። እስኪ ግማሽ ሻይ ድገሙኝ ? ”

“ በመጀመሪያ ቁርስ መጣይ ከቀማመስን ቀጥለን ወደሥራ ችን ማምራት ብቻ ነው ” አለ ፖይሮት ።

በወዳጅነት መንፈስ ፈገግ በማለት ጺሙን ቋጨት አደረገ ። ሚስ ሀበርድ ፣ “ ልክ ከፊሲሊቲ አገላለጽ እንመትደገኩህ ሆነህ ነው ያገኘሁህ ፣ ታውቃለህ ? ” አለች ።

ከጥቂት ጊዜ ትውስት በኋላ ፊሊሲቲ ሚስስ ሊመን የክር ስትና ስም መሆኑን በማስታወስ ፣ ራሱም ፖይሮት በተመሳሳይ የወይዘሪት ሊመንን አገላለጽ በመጠቀም ከገመተው በላይ እንዳል ሆነችበት አጫወታት ።

በሀሳብ ተውጣ ሚስ ሀበርድ ሁለተኛዋን ሳንድዊች እየበላች ፣ “ፊሊሲቲ ለሰው ደንታም ኖሯት አያውቅ ። እኔ በጣም ነው የምቸ ገረው ። ለዚህ ነው ጭንቀት ውስጥ የገባሁት ” አለች ።

“ ምን እንደሚያስጨንቅሽ በትክክል ልትነግሪኝ ትችያለሽ ?”

“ አዎን ፣ እችላለሁ ። ገንዘብ እንኳ ቢወሰድ የተለመደ ነገር ነው ። ትንሽ ገንዘብ ከዚህም ከዚያም ይጠፋል ። ጌጣጌጦችም ቢሆኑ

ግልጽ ነው - ማሰቱ ግልጽ ነው ስል ትክክል ለማለት አይደለም - በታ አለ አይደለም ? ለሥርቆት ሱስ ወይንም ለእምነተቢስነት ያህል የማ ደረግ ይሆናል ። ግን እስኪ የተወሰዱትን ቁሳቁሶች ዝርዝር ከወረቀት ያስፈርኳቸውን ላንብብልህ ። ''

ሚስ ሀበርድ ቦርሳዋን በመክፈት ትንሽ ማስታወሻ ደብተር አወጣች ።

የምሽት ጫማ (አዲስ ጥንድ)
የእጅ አምባር (ጥንታዊ ጌጥ)
የአልማዝ ቀለበት (ከሾርባ ማህን የተገኘ)
የፊት ፓውደር
ሊፕስቲክ
የልብ ምት መመርመሪያ
የጆሮ ጉትቻዎች
የሲጋራ መለኮሻዎች
የሱፍ ሱሪ (አሮጌ)
የኤሌክትሪክ አምፑሎች
አንድ ፓኬት ቸኮሌት
የሐር ሻርፕ (ተቆራርጦ የተገኘ)
የጆርባ ሻንጣ ?
ቦሪክ አሲድ ዱቄት
የመታጠቢያ ጨው እና
የምግብ ማዘጋጃ መጽሐፍ ናቸው ።
ሔርኩሌ ፖይሮት በረጂሙ ተነፈሰ ።

''የሚገርም ነው'' አለና ፣ ''እውነትም — የሚያስደንቅ ነው'' አለ ። ከሕልም ውስጥ እንዳለ ሰው ሁሉ በሀሳብ ሰጠመ ። ከዚያ ምንም ከማይቀበለው የተከሳተረ የሊመን ፊት ዓይኖቹን በማንሳት ያን ሀዘ ነተኛ የሚስ ሀቦርድን ገጽታ ቃኘ ።

'' እንኳን ደስ ያለሽ '' አላት ሁለተኛዋን በጋለ ስሜት ።
አተኩራ ተመለከተችው ።
''ግን ለምኑ መሴ ፖይሮት ? ''

“እንኳን ደስ አለሽ ያልኩሽ እንዲህ ዓይነቱ የተለየና ውብ ችግር ስለገጠመኝ ነው ። ”

“ ምናልባት ነገሩ ለእንተ ስሜት ሰጥቶህ ይሆናል ፣ መሲ ፖይሮት ፣ ግን . . . ”

“ ምንም ስሜት አልሰጠኝም ። በልደት በዓል አካባቢ በአንዳንድ ወጣት ጓደኞቹ እየተገደድኩኝ በቅርቡ መጫወት ከጀመርኩት የጥሎ ማለፍ ጨዋታ ያህል እንኳ የሚያስታውስ አይደለም። ባልሳሳት ጫወታው፣ ባለ ሶስት ቀንዲ እመቤት ይባላል ። እያንዳንዱ ሰው በተራው ይህን ቃል መናገር ነበረበት ፣ ‘ወደ ፓሪስ ሔጄ-ገዛሁ!’ ይላል አንዳንድ የዕቃ ስም በመጨመር ። የሚቀጥለውም ሰው ያንን ይናገርና ሌላ ዕቃ ይጨምርበታል ። የጨዋታው ዓላማ የተጠቀሱትን ዕቃዎች በትክክል ቅደም ተከተላቸው መጥራት ሲሆን አንዳንዶቹ እውነቱን ነው ለመያዝ የሚያስቸግሩና የሚያስቁም ነበሩ ። ቁራጭ ሣሙና፣ ነጭ ዝሆን ፣ ባለተንቃይ እግር ጠረጴዛ ፣ የሩሲያ ዳክዬ ናቸው ። አንዳንዶቹን እንደማስታውሳቸው የማስታወሱ ችግር የሚፈጠረው በዕቃዎቹ አለመመሳሰል ምክንያት ነበር ። የቅደም ተከተሉ ግድፈት ማለቴ ነው። ልክ አንቺ ለኔ ካሳየሽኝ ዝርዝር እንደተጻፈው ማለት ነው። ምናልባት አንድ አሥራ ሁለት ነገሮች ተዘርዝረው ይሆናል ። እነዚህን በቅደም ተከተላቸው መጥራት በጣም አስቸጋሪ ነው ። እንዲህ የማድረጉ ጥረት ለተወዳዳሪ የወረቀት ቀንድ ይሰጥና እርሷ ወይንም እርሱ ያን ዝርዝር ‘እኔ ባለ አንዲ ቀንድ እመቤት ፣ ፓሪስ ሔጄ ’ በሚል ጀምሮ ወ.ዘ.ተ... መድገም ነው ።ሶስቱ ቀንዶች ከተወጡ በኋላ የግዴታ ከጫወታው ውጭ መሆን ይኖራል ፣ በመጨረሻ የሚቀረው አሸናፊው ይሆናል ። ”

“ አሸናፊው አንተ እንደነበርክ እርግጠኛ ነኝ፣ መሲ ፖይሮት” አለች ሚስስ ሊመን በታማኝ ሠራተኛ መንፈስ ።

ፖይሮት በደስታ ፈካ ።

“ ነገሩስ እንደዚያ ነበር ” አለ ። “ እንዲያው እንደ አጋጣሚም እንኳ ቢሆን አንድ ሰው ጥቂት ብልሃት በመጠቀም ዕቃዎቹን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይቻለዋል ። ማለት ፣ አንድ ሰው በአዕምሮው ውስጥ ‘ በአንዲት ቁራጭ ሳሙና አንድ ትልቅ የእብነበረድ ዝሆን ከባለተንቃይ እግር ጠረጴዛው አቁሜ አጠብኩኝ ፣ ማለት ይችላል ’ አለ ። ”

ሚስ ሀበርድ በአክብሮት ፣ “ ምናልባት በነዚህ በሰጠሁህ የዕቃ ዝርዝሮች ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ትችል ይሆናል ” አለችው ።

“ ያለ ጥርጥር እችላለሁ ። እመቤቲቱ ቀኝ ጫማ ለብሳ በግራ እጅዋ አምባር አድርጋለች ። ፓውደር ተቀብታ፣ ከንፈሯን በሊፕስቲክ አቅልማ ከግብጣ ትሄድና ከመረቅ ሣህን ውስጥ ቀለበቷን ትጥላለች ፣ ወዘተ... በማለት ዝርዝርሽን ለማስታወስ እችላለሁ ። የእኛ ችግር ግን ያ አይደለም ። የምንፈልገውም እርሱን አይደለም ። ለምንድነው ይህን የመሳሰሉ የዕቃ ግብስብሶች የተሠረቁት? ከበስተጀርባው አንዳች ሚስጥር ይኖር ይሆን ? አንዳች በአንድ ነገር ላይ የተደረገ ትኩረት ይኖር ይሆን ? በመጀመሪያ የሚኖረን የትንተና ሂደት ነው ። ማድረግ የሚገባን የዕቃዎቹን ዝርዝር በጥንቃቄ ማጥናት ነው ። ”

ፖይሮት ማንሰላሰል በጀመረበት ወቅት ጸጥታ ሰፈነ ። ሚስ ሀበርድ አንድ ህጻን ፈጣን ምትሃተኛ እየተመለከተ በተስፋ አንዲት ጥንቸል ዘላ ስትወጣ ወይንም ቢያንስ ብዙ ቀለማት ያላቸው ሰንደቆችን እንደሚጠባበቅ ሁሉ በሀሳብ እልም ፣ ጭልጥ ብላ መመልከት ጀመረች ። ሚስስ ሊመን ጉዳዩን ከግምትም ሳታገባው የማሀደር አያያዟን አዳዲስ ስልቶች ለመመራረጥና ለማጥናት ወደ ሥራዋ ተመለሰች ።

በመጨረሻ ፖይሮት ሲናገር ሀበርድ ባነነች ።

“ በመጀመሪያ ደረጃ ከአዕምሮዬ የተፈጠረው ሀሳብ እንዲህ ነው ” አለ ፖይሮት ። “ ከጠፉት ሁሉ ነገሮች ውስጥ የሁሉም ዋጋ በጣም ቀላል ነው፣ (አንዳንዱ ጭራሹንም ከቁጥርም የሚገባ አይደለም) ከሁለቱ በስተቀር—የልብ ምት መለኪያውንና የአልማዝ ቀለበቱን ማለቴ ነው። የልብ ምት መለኪያውን ለጊዜው ወደ ጎን እንተወውና በቀለበቱ ላይ ለማተኮር እፈልጋለሁ ። ምን ያህል ዋጋ ያለው ነው ? ”

“ አምን መሲ ፖይሮት፡ትክክለኛውን እንኳ መናገር አልችልም። ባለአንድ ፈርጥ አልማዝ መሰለኝ ። ሌሎችም ከላይና ከታች ጥቂት ተለጣፊዎች ሳይኖሩት አይቀሩም ። እንደሚገባኝ የሚስስ ሌኒ እናት የጋብቻ ቀለበት ነው ። በጠፋበት ወቅት በጣም ነው የተረበሸችው ። በሁለተኛው ምሽት ከሚስስ ሆብሐውስ የሾርባ ሣህን ስናገኘው ደግሞ በጣም ነው የተደሰትነው ። በቃ የማይረባ ድብብቆሽ አድርገን ነው የወሰድነው ። ”

“ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን እራሴ ሠርቄ እንደገና መመለሱ ቁም ነገር ያለው ይመስለኛል ። የፕላስቲክ ወይንም የፓውደር መያዣ ወይንም መጽሐፍ ቢጠፋ ፖሊስ ለመጥራት በቂ ምክንያት የሚሆን አይመስለኝም ። ነገር ግን በጣም ውድ የሆነ የአልማዝ ቀለበት መጥፋት የተለየ ነገር ነው ። ፖሊስ ለመጥራት የሚያስችልሽም ነው ። ስለዚህ ቀለበቱ ተመለሰ ። ”

“ ግን ለመመለስ ከፈለግህ ለምን ትወስደዋለህ ? ” ስትል ሚስስ ሊመን ተኰሳትራ ጠየቀቸው ።

“ ለምን ? የሚለው ተገቢ ጥያቄ ነው ፣ ” አለ ፖይሮት ። “ ለጊዜው ጥያቄዎቹን እንተዋቸዋለን ። አሁን ግን የተሠረቁትን ዕቃዎች እስኪ በመልክ በመልካቸው ለማጥናት ልሞክር ። በመጀመሪያም ቀለበቱን እንውሰድ ። ለመሆኑ ይህች የተሠረቀባት ወይዘሪት ማን ናት ? ”

“ ፖትሪሺያ ሌኒ ? በጣም ግሩም ልጅ ናት ። ይኼ ምንድነው የምትሉት ፣ የታሪክ ወይንስ የአርኪኦሎጂ ? ዲፕሎማዋን ለማግኘት የደረሰች ልጅ ናት ። ”

“ ሀብታም ናት ? ”

“ የለም ፣ አይደለችም ። በርግጥ ትንሽ ገንዘብ አላት ። ነገር ግን ሁልጊዜም ቢሆን ጠንቃቃ ናት ። ቀለበቱ እንዳልኩህ የእናቷ ነው ። አንድ ሁለት ጌጣጌጦች አታጣም ። ነገር ግን በብዛት ይህና ልብሶች የሏትም ፣ ማጨስም ያቆመችው በቅርቡ ነው ። ”

“ መልኳን ልትገልጭልኝ ትችያለሽ ? እስኪ በራስሽ አገላለጽ አቅርቢልኝ ? ”

“ አለ አይደል ፣ መካከለኛ ነገር ናት ። ያልተዋጣላት ዓይነት ሰው ነች ። ዝምተኛ ሴት ፣ ወይዘሮ መሳይ ፣ እምብዛም ደስተኝነትና ርካታ የማይታይባት ናት ። አለ አይደለም የዋህ ዓይነት ሴት ነች ። ”

“ ቀለበቱ ሚስስ ሆብሐውስ የሾርባ ማሀን ውስጥ ነው የተገኘው ? ለመሆኑ ይህች ሆብሐውስ ማንናት ? ”

“ ቫለሪ ሆብሐውስ ? በጣም ብልህ የማይጠበቅ ድብቅ ችሎታና አሽሟጣጭ የአነጋገር ፈሊጥ ያላት ሰው ናት ። ከአንድ የቁንጅና ሳሎን ነው የምትሠራው ። ሳብሪና ፈየር — ሳታውቀው ‘ምትቀር አይመስለኝም ። ”

“ እነዚህ ሁለቱ ልጃገረዶች ባልንጀራሞች ናቸው ? ”

ሚስ ሀበርድ አምሰለሰለች ።

“ ይመስለኛል — አዎን ። ብቻ እስከዚህም የሚያቀራርባቸው ነገር የለም ። ፖትሪሺያ ከሁሉም ሰው ትግባባለች ፣ ታዋቂም ባት ሆን አዎን እንደዚያ ዓይነት ሰው ናት ማለት እችላለሁ ። ቫለሪ በም

ላሷ ምክንያት ብዙ ጠላቶች አፍርታለች - እንዲያም ብትሆን ተከታይ የምታጣ አይደለችም የምናገረው የሚገባህ ከሆነ ። ''

'' የሚገባኝ መሰለኝ '' አለ ፖይሮት ።

ፖትሪሺያ ሌኒ ጥሩ ሰው ብትሆንም ነገር ግን ደደብ ናት ። ቫሌሪ ሆብሐውስ ግን ተከለ ሰውነቷን ትጠብቃለች ። ወደ ተሠረቁት ነገሮች ጥናቱ ተመለሰ ።

''የሚያታልሉት ነገሮች ከዚህ የተዘረዘሩት የተለያዩ ዕቃዎቹ እነናቸው ። አንዲት ክብሯን የማትጠብቅ ፣ ስሜት የማይሰጣትን ግድየለሽ ልጃገረድ ሊያሳስቱ የሚችሉ ጥቃቅን ነገሮች እንደ ሊፕስቲክ ፣ ጥንታዊ ጌጣጌጥ ፣ የፖውደር መያዣ — የመታጠቢያ ጨው — ፖኬት ቸኮሌት፣ምናልባትም ሌሎች ነገሮችም ሊሆን ይችላሉ። ግን የልብ-ምት መለኪያን ዓይነት መሣሪያ ሊሸጥ ወይንም በመያዣነት ሊሰጥ የሚችለው የሽያጩን ወይንም የማስያዣውን ሥፍራ የሚያውቅ ሰው ነው ። ለመሆኑ የማን ነበር ? ''

'' የሚስተር ባትሰን ነው ። በጣም ተግባቢ ወጣት ነው ። ''

'' የህክምና ተማሪ ነው ? ''

'' አዎን ። ''

'' እንዴት ነው ፣ በመጥፋቱ ተበሳጭቶ ነበር ? ''

'' አዎን ፣ እጅግ ተናድዶ ነበር ሙሴ ፖይሮት ። አለ አይደለም ይኼ ቶሎ የመፍላት ፣ የመጨስ ባህሪ አለበት ። ሰጊዜው የሆነ ያልሆነውን ይቀበጣጥርና ወዲያውኑ ይረሳዋል ። ዕቃዎቹ ሲሠረቁበት በዝምታ የሚያልፍ ዓይነት ሰው አይደለም ። ''

'' ሌላስ ? ''

'' አዎን ፣ ሚስተር ጎፖል ራም ሕንዳዊው ተማሪም አለ ። ዘለ ዓለም ፈገግታ የማይለየው ሰው ነው።እጁን እያወዛወዘ ይኼን ተውት! ይኼ የሥርቆቱ ጉዳይ እንኳ ምንም አይደለም ይላል ። ''

'' የተሠረቀበት ንብረት ነበር ? ''

'' የለም ! ''

'' አሀ ! የሱፍ ሱሪውስ የማን ነበር ? ''

'' የሚስተር ማክናብ ። በጣም አሮጌ ስለሆነ የሚፈልገውም የለ። ነገር ግን ሚስተር ማክናብ ከአረጁ ልብሶቹ የተያያዙ ትዝታዎች ስለ አሉት ምንም ነገር መጣል አይፈልግም ። ''

“ እንግዲህ በውይይታችን መሠረት ስሥርቆትም የማይበቁ ነገሮች ላይ ደርሰናል ። ያረጀ የሱፍ ሱሪ ፣ የኤሌክትሪክ አምፑሎች ፣ ቦሪክ አሲድ ዱቄት ፣ የመታጠቢያ ጨው ፣ የምግብ ማዘጋጃ መጽሐፍ ናቸው ። ምናልባት ጠቃሚ ነገሮች ይሆኑ ይሆናል ። ግን አይደሉም ። ቦሪክ አሲዱ ምናልባት በሥህተት ተነስቶ ሊሆን ይችላል ። የተታጠለውን አምፑል አንዱን በሌላ ለመተካት አውጥቶት ይሆናል ። የምግብ ማዘጋጃውንም መጽሐፍ አንዱ ተውሶ ላይመልሰው ይችላል ። ሱሪ ውንም እንደሌሎቹ ሁሉ የጽዳት ሠራተኛዋ ልትወስደው ትችላለች ።”

“ የለም ሁለት የምንተማመንባቸውን ሰዎች ነው የምንጠቀመው ። ባንጠይቃቸውም ሁለቱም እንዲህ ዓይነት ሥራ እንደማይሠሩ ርግጠኛ ነኝ ። ”

“ ትክክል ልትሆኚ ትችያለሽ ! የምሽት አዲስ ጥንድ ጫማ ዎችም ያሉ መሰለኝ ፣ አይደለም ? የማን ነበሩ ? ”

“ የሳሊ ፊንች ነው ። በፋልበራይት ነጻ ትምህርት ለመጠቀም የመጣች አሜሪካዊት ወይዘሪት ናት ። ”

“ ይህ የምሽት ጫማ አንድ ሥፍራ የተሰወረ አይመስልሽም ? ለማንም ቢሆንአንድ ጫማ ምን እንደሚሠራለት መገንዘብ አልችልም ። ”

“ የለም ፣ የትም አልተሰወረ መሴ ፖይሮት ። ሁላችንም በሚቻለን ፈልገነዋል ። ወይዘሪት ፊንች ወደ አንድ ፓርቲ ‘ የግዴታ አስፈላጊ ’ በምትላቸው በእነዚህ የምሽት ልብሶች መሔድ ነበረባት ። ጫማዎቹ ደግሞ የበለጠ አስፈላጊ ነበሩ ። ያሉዋት የምሽት ልብሶች እነዚህ ብቻ ናቸው ። ”

“ በጣም አበሳጫት ፣ ቅር አሰኛት - አዎን . . . አዎን ይገባኛል ። ምናልባት አንድ ነገር ይኖራል . . . ”

ለደቂቃ ያህል ትንሽ ጸጥ ካለ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ ።

“ ደግሞ ሌሎች ሁለት ዕቃዎች አሉ ። የጀርባ ሻንጣ የተቆራረጠና የሐር ሻርፕ እንደዚያው ከጥቅም ውጭ የተደረገ አለ ። ይህ ለጥፋትም ሆነ ለትርፍ የሆነ ነገር አይደለም — ነገር ግን ለቂም በቀል ሆን ተብሎ የታሰበ ነው ። የጀርባ ሻንጣው የማን ነበረ ? ”

“ በሙሉ ማለት ይቻላል ፣ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የጀርባ ሻንጣ አሉዋቸው ። ያው እንደምታ ውቀው ተሽከርካሪዎችን እየለመኑና ነጻ ጉዞ እየጠየቁ እንደሚዞሩ ግልጽ ነው ። አብዛኛዎቹ የጀርባ ሻንጣዎች ተመሣሣይ ናቸው ። ከአንድ ሥፍራ የሚገዙ በመሆናቸው አንዱን

ከአንዱ መለየት ይከብዳል ። ነገር ግን ይህ የሊዎናርድ ባትሰን ወይ ንም ኮሊን ማክናብ ነው ማለቱ የሚከብድ ጉዳይ አይሆንም ። ”

“ የሐር ሻርፑም — የተቆራረጠው ፣ የማን ይመስልሻል ? ”

“ የቫሌሪ ሆብሐውስ ነው ። በገና ሥጦታ ያገኘችው ነው ። አረ ንጓዴ ዕንቁ ቀለም ያለው በጣም ግሩም ውድ ጨርቅ ነው ። ”

“ የሚስስ ሆብሐውስ . . . ገባኝ ። ”

ፖይሮት ዓይኖቹን ጨፈናቸው ። ከዓይነ ሕሊናው የተሳለው ከቱቦ ውስጥ መስታወትና ትናንሽ ባለቀለም ብርጭቆዎች ተደርጎ ቱቦው ሲገለበጥ እንደሚታየው ዓይነት ጥለት ነው ። የካሊዲስኮፕ ዓይነት ማለት ነው ። የተቆራረጡ ሻርፖች ፣ የጀርባ ሻንጣ ፣ የምግብ ማዘጋጃ መጽሐፍ ፣ ሊፕስቲኮች ፣ የመታጠቢያ ጨው ፣ ስሞችና የአውራ ጣት ጥፍሮች ያልታወቁ ተማሪዎች ምስል ንድፎቻቸው ናቸው ። ነገር ግን ሀብሪያና ቅርጽ ከየትኛውም ሥፍራ ላይ አይታይም ። የማይገናኙ ሁኔታዎችና ሰዎች ከሀዋው በፍጥነት ይዘዟራሉ ። ፖይሮት ግን እንደምንም ከአንድ ሥፍራ ላይ አንድ ጥለት መኖር እንዳለበት አሣምሮ ያውቃል ። አዎን ብዙ ጥለቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። በእያንዳንዱ ወቅት የጥለት መነጽሩን ወይንም ካሊዲስኮፑን ሲነቀንቀው አንድ ሰው የተለያዩ ጥለቶችን ማየት ይቻለዋል . . . ነገር ግን ከጥለቶቹ አንዱ ትክክለኛ ጥለት ነው . . . ጥያቄው ግን የት እንጀምረው ነው ። . . . ”

ዐይኖቹን ገለጠ ።

“ይህ እንግዲህ ብዙ ማሰብን የሚይጠይቅ ጉዳይ ነው ። ብዙ ማሰብን ። ”

“ አዎን ፣ በትክክል እንደዚያ ይመስለኛል መሴ ፖይሮት ” ልትል ሚስ ሀበርድ ተስማማች ። “ እውነቱን ነው ላስቸግርህ አልፈልግም ። ” አለችው እንደገና ።

“ የለም ፣ አታስቸግሪኝም ። ግን ስለተታለልኩኝ ነው። ነገር ግን እያሰብኩኝ ባለሁበት ሠዓት ማድረግ ከምችለው መጀመሩን መረጥኩኝ ። በመጀሪያ . . . በጫማው ፣ በምሽት ጫማው . . . አዎን ፣ ከዚያ መጀመር እንችላለን ። ሚስስ ሊመን ። ”

“ አቤት መሴ ፖይሮት ” ሚስስ ሊመን የማህደሩን ሥራ ከአዕምሮዋ አጠፋችው ። በበለጠ ቀጥ ብላ ተቀመጠች ፣ ጊዜም ሳትሰጥ ማስታወሻና እርሳስ አነሳች ።

“ ሚስ ሀበርድ ምናልባት የተቀረውን ጫማ ትሰጥሽ ይሆናል! ወደ ቤከር ጎዳና ከጣቢያው ሔጄ ከጠፉ ዕቃዎች መምሪያ ማለቴ ነው ። መቼ ነው ይህ የሆነው ? ”

ሚስ ሀበርድ ትንሽ አሰበች ።

“ በትክክል አሁን ለማስታወስ አልችልም መሲ ፓይሮት ። ምናልባት ከሁለቱ ወራት በፊት ነበር ። ከዚያ ወዲህ መሆን አይችልም ። ነገር ግን የግብግቦውን ቀን ከሳሊ ፊንች ማግኘት እችላለሁ። ”

“ መልካም ጥሩ ነው — ” አለ ። ለአንድ ጊዜ በድጋሚም ወደ ሚስስ ሊመን ፊቱን አዙረ ። “ ትንሽ ግልጽ ላይሆንልሽ ይችል ይሆናል ። ጫማዬን ከባቡሩ ውስጥ ጣልኩት በያቸው ። እንደዚያ ማለቱ የተሻለ ነው ። ወይንም ከአንድ ከሆነ ባቡር ላይ ብለሽ ንገሪ ። ካለ በለዚያም ከአውቶቡስ ላይ በያቸው ። ለመሆኑ ከሒኮሪ ጎዳና አካባቢ ስንት አውቶቡሶች ናቸው የሚሰማሩት ? ”

“ ሁለት ብቻ ናቸው መሲ ፖይሮት ። ”

“ መልካም፡ከቤከር ጎዳና ውጤት ካላገኘሽ ወደ ስኮትላንድያርድ ሒጂና ሞከሪ ። ከታክሲ ረስቼው ነው ብለሽ ንገሪያቸው ። ”

“ ልምቤዝ ” ስትል ወይዘሪት ሊመን አረመች ።

ፖይሮት እጁን አወዛወዘ ።

“ እነዚህን ነገሮች በደንብ ታውቂያቸዋለሽ ? ”

“ ሚስ ሀበርድ ግን ለምን አሰብከው — ” ስትል ፣ ፖይሮት ንግግሯን አቋረጣት ።

“ እስኪ በመጀመሪያ ምን ዐይነት ውጤት እንደምናገኝ እንወቅ ። አገኘንም አላገኘን እኔና ሚስ ሀበርድ እንደገና መነጋገር ይኖርብናል ። ከዚያ እኔ ማወቅ የሚኖርብኝን አንዳንድ ነገሮች ትነግረኛለች ። ”

“እንደሚመስለኝ መናገር የሚገባኝን ነገር በሙሉ ነግሬሀለሁ።”

“ የለም ፣ የለም ፣ አልስማማበትም። ከዚህ ሥፍራ የተለያዩ የወጣት ስሜቶችና ባህርያት ያሉዋቸው ፣ የተለያዩ ጾታዎች ይኖራሉ። ሀ—ለን ያፈቅራል ፣ ለ ግን መን ታፈቅራለች ፣ ሰ ና ረ ምናልባት በሀ ምክንያት ዱላ እስከመማዘዝ ደርሰው ይሆናል ። ይህንን ሁሉ ነው ማወቅ የፈለኩት ። የሰውን ልጅ የስሜት ጨወታ ማለቴ ነው ። ጸቦቹ ፣ ቅንዓቶቹ ፣ ባልንጀራነቱ ፣ ምቀኝነቱና ርህራሔ ቢስነቱን በአጠቃላይ ማለቴ ነው ። ”

“ በርግጥ ” አለች ሀበርድ በቅሬታ ። “ እንደዚያ ስላለው ነገር ምንም አላውቅ ፣ በፍጹም ከነርሱ የሚያገናኝንም ነገር የለም ። የኔ ድርሻ ሥራዬን በተሰጠኝ ሀላፊነት መምራትና የምግብ አቅርቦቱን መቆጣጠር ብቻ ነው ። ”

“ በሰዎች ላይ ያለሽን አመለካከት ነግረሽኝ ነበር ። ወጣቶችን ትወጂለሽ ። ይህንን ሥራ የተቀበልሽው ለገንዘቡ ትኩረት ስለሰጠሽው አይደለም ። ነገር ግን እንዳልሽው ከሆነ ከሰው ልጅ ችግር ሊያገኝሽ ስለሚችል ነው ። ከተማሪዎቹ የምትወጂቸውና የማትወጂቸው ቸውም አሉ ። ይህንንም ትነግሪኛለሽ ። አዎን ትነግሪኛለሽ ! አንድ በጣም ያሳሰበኝ ነገር አለ ። ይህ ነገር አሁን ያለው ሁኔታ አይደለም ። ያ ደግሞ ቢያሳስብሽ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መሔድ ትችያለሽ . . . ”

“ ሚስ ኒኮላቲስ ፖሊስ በዚህ ጉዳይ እጁን እንዲያስገባ አትፈልግም ! እውነቴን ነው የምልህ ። ”

ንግግሯን ማቋረጡ ብዙም ሳይሰማው ፖይሮት ቀጠለ ። “ የለም ፣ አንድ ሰው በጣም አሳስቦሻል — እንዳንቺ ሀሳብ አንድ ለዚህ ጉዳይ በሀላፊነት የሚጠየቅ ወይንም በጉዳዩ ውስጥ እጁን ያስጋባ ሰው አለ። ይህ ሰው አንቺ የምትወጂው ሰው መሆን አለበት ! ”

“ እውነት ! መሴ ፖይሮት ? ”

“ አዎን ፣ እውነት ። እንደሚመስለኝ መጨነቅሽ ትክክል ነው። የዚያ የሐር ሻርፕ መቆራረጥ የጤና አይመስለኝም ። ያ የተቀዳደደው የጀርባ ሻንጣም ጥሩ አይመስለኝም። የተቀረው እንኳን የሕጻን ጨዋታ የሚመስል ነው ። ግን ደግሞ ርግጠኛ አይደለሁም ። የለም ፣ ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ አይደለሁም ! ”

— 3 —

ደረጃውን እየተቻኮለች በመውጣት ሚስ ሀበርድ ከቁጥር 26 ሔኮሪ ጎዳና በር ቁልፉን አስገባች ። ልክ በሩ እንደተከፈተ አንድ የወላፈን ቀለም ጸጉር ያለው ወጣት ጀሚሳ ከበስተኋላ ደረጃውን ወጣ።

" ታዲያስ እንዴ ? " አላት ሌን ባትሰን ሁልጊዜ ሊጠራት በሚ ጠቀምበት መንገድ ። በጣም ተግባቢ ነው ። የድምፅ አሰባበሩ ከም ሥራቅ ለንደን የመጣ ሰው መሆኑን ይመሰክርለታል ። ከማናቸውም የበታችነት ስሜት ነጻ ነው ። " እግርሽን ለማፍታታት ወጥተሽ ነበር?" አላት ።

" ሻይ ልጠጣ ነበር የወጣሁት ሚስተር ባትሰን ። አሁን ጊዜ ዬን አትግደልብኝ ፡ እቸኩላለሁ ። "

" ይኸውልሽ ዛሬ አንድ አስክሬን ስቆራርጥ አረፈድኩኝ " አለ ሌን ። ቀጥሎም " በፍጥፈጣ እኮ ነው " አላት ።

" አንተ የማትረባ ልጅ ! አታስፈራራኝ ብዬሃለሁ ። እንዲህም አድርጎ የለ ! ውብ አስክሬን ይሁንልህ ! ሀሳብህ መቅፈፉ ! ስው ነት ይዘገንናል ። "

ሌን ባትሰን ተንከተከተ ፡ አዳራሹም አብሮት አስተጋባ ።

" ለሴሊያ ከእንግዲህ ምንም ነገር አበቃ ። አየሽ ወደ መድሐ ሒኒት ማከፋፈያው ሔድኩኝና ስለአስክሬን ለመነጋገር ነበር የመ ጣሁት አልኩኝ ። ፊቷ በአንድ ጊዜ በድንጋጤ ኖራ መስሎ ሕይ ወቷ ሊያልፍ ምንም ያህል አልቀራት ። ምን ይመስልሻል እስኪ እንዴ ሀበርድ ? "

" አልደነቅበትም " አለች ሚስ ሀበርድ ። " ነገሩ ! ሴልያ ምናልባት እውነተኛውን የተናገርክ መስሏት ይሆናል ! "

" እውነተኛውን ስትይ ምን ማለትሽ ነው? የእኛ አስክሬኖች ምንድን ነው የሚመስሉሽ ? ተራ አሻንጉሊቶች ? "

አንድ ቀጭን ወጣት ረጅም ቆሻሻ ጸጉር ያለው ከበስተቀኝ ከምትገኝ አንዲት ክፍል ብቅ ብሎ በብስጭት ፡

ETY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA

“ እንዴ ! አንቺ ነሽና ፤ ብዙ ወታደሮች መስለውኝ ነበር ። ከውጭ አንድ ሰው ብቻ ነው ፤ ውስጥ ሆነው ሲሰሙት የአሥር ሰው ነው የሚመስለው ። ”

“ ይህን ያህል የሚያበሳጭ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ ። ”

“ ከወትሮው በላይ እንኳ አይደለም ” ብሏት ኒዬል ቻፕማን እንደገና ወደ ውስጥ ገባ ።

“ የኛ አትንኩኝ — ባይ አበባ ! ” አለ ሌን ።

“ አሁን አምባሳራችሁን ተዉ ! ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ መልካም ጸባይ ብቻ ! ያንን ነው እኔ የምፈልገው ። አለ አይደለም ፤ ሰጥቶ እንደ መቀበል ዓይነት ? ”

ጆዊሳው ወጣት ወደታች እያያት በፍቅር ፈገግ አለ ። “ እንዴ ሙች ! እኔ ስለ ኒዬል ግድ የለኝም ” አላት ።

አንዲት እንደአጋጣሚ ደረጃውን በመውረድ ላይ የነበረች ልጃ ገረድ ፤ “እንዴ ሚስ ሀበርድ ! ሚስ ኒኮሊተስ ከክፍላቸው ሆነው እንደ ተመለሰች በፍጥነት እንድታነጋግረኝ ብለዋል እኮ ” አለች ።

ሜስ ሀበርድ በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ደረጃውን መውጣት ጀመረች ። ረጅሟ መልዕክቱን ያመጣችላት ጅንን ልጅ ከግድግዳው በመጠጋት አሳለፈቻት ።

ሌን ባትሰን የዝናብ ጃኬቱን እያወላለቀ ፤ “ ምንድነው ቫለሪ ? ስለእኛ ጸባይ ጉድለት በእንዴ ሀበርድ በኩል የሚተላለፍልን ነገር ይኖር ይሆን ? ” ሲል ጠየቃት ።

ልጅቱ ትከሻዋን በመነቅነቅ ደረጃውን እየተጀነነች ወርዳ ወደ አዳራሹ አለፈች ።

“ አሁንስ ይህ ሥፍራ ከቀን ወደ ቀን የእብድ ቤት እየመሰለ መጣ ” አለች ዝቅ ባለ ድምፅ ።

እያንተመተመች በቀኝ በኩል በበሩ አልፋ ገባች ። የምትራመደው በዚያ በታወቁ ባለሙያ ፋሺን ተዋንያን የንቀትና የኩራት አረማመድ እየተጀነነች ብዙም ሳትቸገር ነበር ።

ቁጥር 26 ሔኮሪ ጎዳና መኖሪያ እውነቱን ለመናገር ያህል ሁለት ትላልቅ ክንፎች አሉት ። እነዚህ 24 እና 26 ተብለው የተከፋፈሉ ነበሩ ። ከምድር ወለሉ ላይ አንድ ናቸው ። ከዚሁ ወለል የጋራ-ሰፊ ሣሎንና የጋራ ሰፊ አዳራሽ አሉዋቸው ። ሁለት የኮት ፤ የባርኔጣ የምርኩዝ ...

ማስቀመጫ ክፍሎችና ከበስተጀርባ አንዲት ጽሕፈት ቤት አሉ ። ለየብቻቸው ወደ ላይኞቹ የተለያዩ ክፍሎች የሚወስዱ ሁለት የተለያዩ ደረጃዎች አሉት ። ልጃገረዶቹ የያዙዋቸው መኝታ ክፍሎች በስተቀኝ ያሉትን ሲሆን ወንዶቹ ግን በሌላኛው ወገን ያለውን ቁጥር 24ትን ነው ።

ሚስ ሀበርድ የኮሊታዋን ቁልፍ እየከፋፈተች ወደ ላይ ወጣች ። ወደ ኒኮሊተስ መኖሪያ ስታመራ በረጅሙ ተነፈሰች ።

" ያው እንደተለመደው ሆና ነው እንግዲህ " ስትል አጉተ መተመች ። በሩን እንኳኩታ ገባች ።

የሚስ ኒኮሊተስ እንግዳ መቀበያ በጣም ይሞቅ ነበር ። ትልቁ የኤሌክትሪክ መሞቂያ እስከ መጨረሻው ተከፍቶ መስኩቱ በመላ ተዘጋግቷል ። ሚስ ኒኮሊተስ ከአንድ ዙሪያውን በሐርና በሱፍ በተለበጡ የቆሸሹ መከዳዎች ከተከበበ ትልቅ ሶፋ ላይ ሆና ታጨሳ ለች ። ለዓይን የምትከብድ ወፍራም መልክ መልካም ፣ ተናጋሪ ፣ ትላልቅ ቡናማ ቀለም ዓይኖች ያሏት እመቤት ናት ።

" እ. . . መጣሽ እንዴ ? " አለች ኒኮሊተስ በቅሬታ ።

ያች የሊመን የደም ክፋይ ሚስ ሀበርድ ሳትፈራና ሳትረበሽ መልስ ሰጠች ።

" አዎን ፣ እዚሁ ነበርኩኝ " አለች ኮስተር ብላ ። ቀጥላም ፣ " በጣም ትፈልጊኛለሽ ማለትን ሰምቼ ነው የመጣሁት " አለች ።

" አዎን ! በጣም ነበር የፈለኩሽ ። እውነት ነው ። ከአውሬነት የማያንስ ነው ! "

" የምን አውሬነት ? "

" እነዚህን የወጪ ሰነዶች ተመልከች ? ያንቺን ደረሰኞች ! " ሚስ ኒኮሊተስ በቅልጥፍና እንደሚያስመስል አጭበርባሪ ሁሉ ከመ ከዳው ሥር የወረቀት ረብጣ መንጭቃ አወጣች ። " እነዚህን ችግረኛ ተማሪዎች ምንድነው የምንቀልባቸው ? ኮስታራ ዶሮና ቆቅ ? እነመኳንንት ? እንዳው እኚህ ተማሪዎች ምንድናት ብለው ያስቡ ይሆን ?"

" ጤነኛ የምግብ ፍላጎት ያላቸው ጤነኛ ወጣቶች ! " አለች ሀበርድ።"ጥሩ ቁርስ - ማለፊያ ራት - ያገኛሉ ። ምግቡ ተራ ነው። ግን ለስውነት ጠቃሚ ነው ። በጥንቃቄ በቁጠባ ነው የሚሠራው ። "

" በቁጠባ ? ቁጠባ ? እንዴት እንዲህ ደፍረሽ ትነግሪኛለሽ? እንደ ዚህ እየከሰርኩኝ ? "

“ ሚስ ኒኮሊተስ ከዚህ ሥፍራ ጥሩ ትርፍ እያገኘሽ ነው ያለ ሽው ። በዚህ ላይ ደግሞ ከፍያው ለተማሪዎቹ በጣም ከባድ ነው ።”

“ መቼ ነው ሰው አጥቼ የማውቀውን ከሦስት ጊዜ በላይ ሳይያዝ የቀረ ሥፍራ ኖሮ ያውቃል ? በብሪትሽ ካውንስል ፡ በለንደን ዩኒቨርስቲ የምግብና የመኝታ ቦርድ ፡ በኤምባሲዎች - በፈረንሣይ ሊሰና በመሳሰሉት ተማሪዎች ሳይላኩልኝ መቼ ቀርቶ ያውቅና ? ”

“ ያ የበዛበት ምክንያት ምግቦቹ የሚበሉና ብቁ በመሆናቸው ነው ። ወጣቶች በሚገባ መመገብ አለባቸው ። ”

“ ተይኝ ወዲያ ! ይህ ወጪ የሚያሳማ ነው ። ምክንያቶቹ ደግሞ ያቺ ጣሊያናዊቷ ወጥ ቤትና ባለቤቷ ናቸው ። እነሱ በምግቡ እያ ጭበረበሩ ነው ። ”

“የለም ! ሚስ ኒኮሊተስ ፍጹም አያጭበረብሩም ። ማንኛውም የውጭ ዜጋ አንቺ ነሽ እንዲህ ያደረግሽ እንደማይለኝ አረጋግጥል ሻለሁ ። ”

“እንግዲያውስ አንቺው ራስሽ ነሽ የምትዘርፊኝ ! አንቺ ነሽ! ” አለች ሚስ ሀበርድ ። ግን ምንም አልተጨነቀችበትም ።

“እንደዚያ ያለ ነገር እንድትናገሪ እንኳ አልፈቅድልሽም!” አለች የቆየ ሠራተኛ ለአሳዳሪዋ በምሬት እንደምትናገረው ዓይነት ። “ እንደ ዚያ ማድረጉ ጥሩ አይመስለኝም ። በዚህ ላይ በዛሬው ጊዜ እንደዚህ የማይገባ ነገር ማድረጉ ላንቺ ጥሩ አይመስለኝም ” አለቻት ።

“ እንዲያነው ! ” አለችና ሚስ ኒኮሊተስ ያን የደረሰኝ ወረቀት ከአየር ስትበትነው የክፍሉን ወለል በመላ አለበሰው ። ሚስ ሀበ ርድ አጎንብሳ ሰበሰበቻቸው ። ከንፈሯን በሃዘን እየመጠጠች ሳለች ፡ “ በጣም ነው የምታናድጂኝ ! ” አለች ቀጣሪዋ በጩኸት ።

“እውነቴን ነው የምልሽ ” አለች ሚስ ሀበርድ። “እንዲህ መሆኑ ላንቺ መጥፎ ነው ። ንዴት ለደም ብዛት በጣም መጥፎ ነገር ነው ” ስትል መለሰች ።

“ይህ የዛሬው ሒሳብ ካለፈው ሣምንት የበለጠ መሆኑን አት ቀበይም ? ”

“ በርግጥ አምን ፡ ከላምፕሰን መደብሮች በጣም ከፍተኛ ቅናሽ ነበረ ። ያንን እድል ተጠቅሜ ነው ። በሚቀጥለው ሣምንት ጠቅላላ ሒሳቡ ከማዕከላዊ ተመን በታች ይሆናል ። ”

ሚስ ኒኮሊተስ በጣም ተናደደች ።

“ደግሞ ሁሉንም ነገር ልክ እንዳልተሳሳትሽ ነው የምትገልጪው!” አለች ።

“ ሌላስ ? ” አለች ሚስ ሀበርድ ደረሰኞቹን በሥነ ሥርዓት ከጠረጴዛው ካስቀመጠች በኋላ ። “ ሌላ ጉዳይ አለ ? ” አለች ደግማ ።

“ አሜሪካዊቷ ሚስስ ሳሊ ፊንች እሔዳለሁ ትላለች ። እኔ ግን እንድትሔድብኝ አልፈልግም ። እርሷ የመጣችው በፉልበርት የነጻ ትምህርት እድል ነው ። ሌሎች የፉልበርት የነጻ ትምህርት ተማሪዎችን ታመጣለች ። ስለዚህ ከዚህ መሔድ የለባትም ። ”

“ ልትሔድ የፈለገችበት ምክንያት ምንድነው ? ”

ሚስ ኒኮሊተስ ትከሻዋን እንደ ሐውልት ሁሉ ባንድ ላይ ሰበሰበችው ።

“ እንዴት ማስታወስ እችላለሁ ? እውነት አይደለም ። እውነቱን ነው ‘ምልሽ አውቃለሁ ። ”

ሀበርድ በሀሳብ ተደምማ ራሷን ነቀነቀች ። ሚስ ኒኮሊተስ የምት ናገረውን ማመን የሚያስቸግራት አይሆንም ።

“ ሳሊ ለኔ ምንም አልነገረችኝም ” አለች ።

“ ግን ልታነጋግሪያት ትችያለሽ ? ”

“ አዎን ፥ በሚገባ ። ”

“ እነዚህ ነጭ ያልሆኑት ሀንዶቹ ከሆኑ ፥ እነዚህ ጥቁሮቹ ከሆኑ በሙሉ መሔድ ይችላሉ ፥ ገባሽ ? ይህ የቀለም እቀባ ለነዚህ ለአሜሪካኖች ከሁሉም ነገር በላይ ነው ። ለኔ ግን ከአሜሪካኖቹ የሚበልጥብኝ ነገር ምንም የለም ። ለነዚህ ለጥቋቁሮቹና ለክልሶቹ ዋጋም አልሰጣቸውም ። ቢፈልጉ ገደል ይግቡ ! ”

ስትናገር በትወና መልክ ነበር ።

“እኔ በሀላፊነት እያለሁ ይህ አይሆንም ! ” አለች ሀበርድ በግድ የለሽነት ። “ ብቻ ለማንኛውም ተሳስተሻል ። ከእዚህ ሥፍራ ከተማሪዎቹ መካከል እንዲህ ያለ ስሜት የለም ። እውነቱን ለመናገር ሳሊ ደግሞ እንደዚያ ያለች ሰው አይደለችም ። እርሷና ሚስተር አኪቦምቦ አብዛኛውን ጊዜ ምሣ አብረው ይበላሉ ። ከርሱ በላይ የጠቆረ ደግሞ ለአሳር ነው ። ”

“ እንግዲያውስ ኮሚኒስቶቹ ናቸው — አሜሪካኖች ስለ ኮሚኒስቶች የሚኖራቸውን አመለካከት ታውቂዋለሽ ? ኒጌል ቻፕማን-ኮሚኒስት ነው ። ”

“ እጠራጠራለሁ ! ”

“ አዎን ፣ አዎን . . አንድ ምሽት ሲናገር የነበረውን ሳትሰሚ አትቀሪም ? ”

“ ኒጌል እናዳጅ ፍጡር ነው ። በጣም የሚሠለች ችኩ ነው ።”

“ ሁሉንም በደንብ ታውቂያቸዋለሽ ። ውድ ሀበርድ ፣ አንቺ ልዩ ሰው ነሽ ! ለራሴም ፣ ለብቻዬ እያለሁ ‘ይህቺ ሀበርድ ባትኖር ኖሮ ምን ላደርግ እችል ነበር ?’ እያልኩኝ ዘወትር አስባለሁ ። የምትማሙ ነው በአንቺ ብቻ ነው ። አንቺ ልዩ ፍጡር ነሽ ፣ በጣም ነው የማደንቅሽ ።”

“ ከዱቄቱ በኋላ ሊጡ ፣ ” አለች ሀበርድ ።

“ ምን ማለትሽ ነው ? ”

“ አታስቢ ፣ የምንችለውን ያህል አደርጋለሁ ። ”

በችኮላ በማመስገን ክፍሉን ጥላ ወጣች ።

ለብቻዋ ፣ ‘ጊዜዬን የምታባክንብኝ-ምን ዓይነት እብድ ሰው ናት!’ እያለች በማጉተምተም በመተላለፊያው አድርጋ ወደራሷ ክፍል ተመለሰች ።

ነገር ግን ለሚስ ሀበርድ ገና ሰላም አልሰፈነላትም ። አንዲት ረጅም ሴት ገና ሚስ ሀበርድ ከክፍሏ ከመግባቷ በፊት ከፊቷ በመቆም፡

“ ለጥቂት ደቂቃዎች ባነጋግርሽ በጣም ደስተኛ ነበርኩኝ ” አለቻት ።

“ በሚገባ እንጂ ኤልሳቤጥ ። ”

ሚስ ሀበርድ የተገረመች ትመስላለች ። ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ከዊስት ኤንዲስ የመጣች የሕግ ትምህርት የምትከታተል ወይዘሪት ናት ። በጣም ጠንካራ ሠራተኛ ናት ። ምኞቷና ተስፋዋ የሰፋ ፣ እምብዛም ከሰው መዳራትን የማትፈልግ ናት ። አርቆ አስተዋይ ብልህና ብቁ ናት ። ሚስ ሀበርድ ዘወትር ከሆስቴሉ ከሚኖሩት ተማሪዎች ሁሉ ጸባየ ምስጉን አድርጋ ነው የምትመለከታት ።

አሁን ግን ፍጹም ተናድዳለች ። ምንም እንኳ ከፊቷ መረዳት ባይቻልም ከድምጿ መቆራረጥ ለማወቅ ስለማያዳግት ሚስ ሀበርድ ፣

“ ምነው የሆንሽው ነገር አለ ? ” ስትል ጠየቀቻት ።

“ አዎን ፤ ከመኝታ ቤቴ አብረሽኝ አንድ ጊዜ ልትመጪ ትችያለሽ ? ” አለቻት ።

“ ለአንድ ጊዜ ቆይኝ ” አለችና ሀበርድ ኮቷንና የእጇን ጓንት አውጥታ ከወረወረች በኋላ ልጅቷን ተከትላ ወደ ላይ ደረጃውን መውጣት ጀመረች ። የልጂቷ መኝታ ቤት ከላይኛው ክፍል ነው ። በሩን ከፍታ ከመስኮቱ አጠገብ ወዳለው ጠረጴዛ ሔደች ።

“ ይኸውልሽ ጽሑፎቹን ተመልከች ” አለቻት ። “ ይህ እንግዲህ ለብዙ ወራት የለፋሁበት የጥናት ውጤቴ ነው ። ምን እንደተደረገ ይታይሻል ? ”

ሚስ ሀበርድ ትንፋኟን ዋጥ አደረገች ።

ከጠረጴዛው ላይ ቀለም ፈሶበታል ። ወረቀቶቹን በሙሉ አበላሽቷቸዋል ። በጣም አርጥቧቸዋል ። ሚስ ሀበርድ በጣቷ ጫፍ ነካችው ። በጣም ርሶ ነበር ።

ጥያቄዋ የማይገባ መሆኑን ብታውቀውም ፣ እንዲህ ስትል ጠየቀች

“ ቀለሙን ያፈሰስሽው አንቺ አይደለሽም ? ”

“ እኔ ከቤት ወጥቼ እያለሁ ነው የተደፋው ። ”

“ ሚስ ቢግስ ትሆን ? ”

ሚስ ቢግስ ከላይኛው ደርብ ያሉትን መኝታ ቤቶች የምታጸዳ ጻዋ ሴትዮ ነች ።

“ የለም ! ሚስ ቢግስ አይደለችም። የኔ የራሴም ቀለም እንኳ አይደለም ። ይኸው እዚህ ከመጽሐፍ መደርደሪያው ፤ ከአልጋዬ አጠገብ ፍጹም በእጅም አልተነካ ። የሆነ ቀለም ይዞ በገባ ሰው ነው እንዲህ የተደረገው ። ”

ሚስ ሀበርድ በጣም ደነገጠች ።

“ ምን ዓይነቱ የማይረባ — አረመኔ ሥራ ነው ? ”

“ አዎን በጣም መጥፎ ሥራ ነው ። ”

ልጅቱ ስትናገር በጽሞናና በትህትና ነበር ። ሚስ ሀበርድ ስሜቷ በሚገባ ገብቷታል ።

“ ገባኝ ኤልሳቤጥ ፣ ምን እንደምናገርም ለራሴም ጨንቆኝ ነው። በጣም ነው የደነገጥኩት ። እውነቴን ነው ፣ ከው ነው ያልኩት ። በተቻለኝና አቅሜ በፈቀደ ይህ የምቀኝነትና የማይረባ ሥራ በማን እንደተደረገ ለማወቅ ጥረት አደርጋለሁ። አንቺስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲያውም ምንም ሀሳብ የለሽም ? ”

ልጂቱ ሊጥያቂዋ ወዲያውኑ መልስ ሰጠቻት ።

“ ይህ አረንጓዴ ቀለም ነው ፣ አይተሽዋል ? ”

“ አዎን ! ተመልክቸዋለሁ ። ”

“ ይህ አረንጓዴ ቀለም ርካሽ ነገር አይደለም ። በዚህ ዓይነት ቀለም ከዚህ የሚጠቀም አንድ ሰው ብቻ ነው። ርሱም ኂጌል ቻፕማን ነው ። ”

“ ኂጌል ? ኂጌል እንዲህ ያለ ሥራ ይሠራል ብለሽ ታስቢያለሽ ?”

“ የለም — ማሰብ እንኳ አልነበረብኝም ። ነገር ግን ደብዳቤዎቹንና ማስታወሻዎቹን የሚጽፈው በአረንጓዴ ቀለም ነው ።”

“ ብዙ ጥያቂዎችን መጠየቅ አለብኝ ። በጣም አዝናለሁ ኤል ሳቤጥ ። እንዲህ ዓይነት ድርጊቶች ከዚህ ቤት ውስጥ ሲፈጸሙ ዝም ብዬ አላይም ። እስከመጨረሻው የተቻለኝን በማድረግ እውነቱን ለማግኘት እሞክራለሁ ። ”

“ አመሰግናለሁ ሚስ ሀበርድ ፣ ሌሎች ነገሮችም ነበሩ ። አል ነበሩም ? ”

“ አ - አአ - አዎን ። ”

ሚስ ሀበርድ መኝታ ክፍሏን ለቃ በመውጣት ደረጃዎቹን መውረድ ጀመረች ። ነገር ግን ከመቀጠሏ በፊት በድንገት ሀሳቧን በመለወጥ ከመተላለፊያው መጨረሻ ካለችው ክፍል ተጓዘችና አንኳኳች። የሚስስ ሳሊ ፊንች ድምፅ እንድትገባ ጋበዛት ።

የክፍሉ አያያዝ ደስ ይላል ። ከሳሊ ፊንችም ገጽታ ደስተኛነት ይነበባል ።

ከአንድ የማስታወሻ መጻፊያ ወረቀት ላይ አቀርቅራ እየጻፈች ነበረች ቀናስ ቅል በነዚያ ብርቱካን ጉንጮቿ ላይ ደስታን አፈ ካችባቸው ። አንድ የጣፋጭ ሣጥን በመክፈት ፣

“ ከሀገሬ የተላከሉኝ ከረሚላዎች ናቸው ። ጥቂት ያኽ ” አለቻት ።

“ አመሰግናለሁ ሳሊ ፣ አራን ምንም አያስፈልግኝም ። ይልቁንስ ተናድጃለሁ ” አለችና ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች ። “ ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ምን እንደደረሰባት ታውቂያለሽ ? ”

“ ምን ሆነች ብላክ ቢስ ? ”

ይህ የቅጽል ስሟ ተወዳጅነትዋን ለመግለጽ በአካባቢዋ ነዋሪዎች የወጣላት ነው ። እርሷም ያለ ተቃውሞ ተቀብላዋለች ።

ሚስ ሀበርድ የሆነውን ሁሉ ገለጸችላት ። ሳሊ የመቆጨት ንዴት አላየች ። በጣም አዘነችላት ።

“ በጣም ደካማ ምቀኝነት ነው ! በእኛይቱ ቢስ ፡ በተወዳጇቱ ላይ ማንም ቢሆን እንደዚያ ዓይነት የማይረባ ሥራ አይፈጽምም ! ሁሉም ሰው ይወዳታል ። በጣም ዝምተኛ ከመሆኗም በላይ ብዙም መግባባት አታበዛም ። አንድ የሚጠላት ሰው እንዳለ ግን ርግጠኛ ነኝ ”

“ እኔም'ኮ የምለው ይህንኑ ነው ። ”

“ ይህ እንኳ ምንም አይደል አንድ ነገር ነው ። ሌሎችንስ ዕቃ ምቿን ? ስለዚያ ነው - ” አለችና አቆመች ።

“ ስለዚያ ምን ? ” ሚስ ሀበርድ አቋርጣ ጠየቀቻት ። ሳሊ በዝ ቅተኛ ድምጽ ።

“ ስለዚያ ነው እኔም ከዚህ የምለቀው ። ሚስ ኒክ ነግራሻለች ?”

“ አዎን ! በጣም ነው የተናደደችው ። ትክክለኛውን ምክንያት ያስረዳሻት አይመስለኝም ። ”

“ አዎን ! አልነገርኳትም ። እንድትጨስ የማደርግበት ምንም ምክንያት የለኝም ። ጸባይዋን ታውቂዋለሽ ። ነገር ግን ምክንያቱ ይሄ ብቻ ነው ። ከዚህ ሥፍራ እየተደረገ ያለውን ነገር አልወደድኩ ትም ። ጫማዬን ማጣቱ ለራሴውም ገርሞኛል ። ደግሞ የቫለሪ ሻርፕ መቆራረጥ - የሌን የጀርባ ሻንጣ . . . ብዙ ዕቃዎች መሠረቃ ቸው አይደለም ? ከዚህም በላይ አሁንም በማንኛውም ጊዜ ሊፈጸም ይችላል - ጥሩ ነገር እንኳ አይመስለኝም ። ግን የተለመደ ነገር ነው። በዚህ ላይ ከሁሉም ደግሞ ይህ አሁን የተፈጸመው ጉዳይ የተለየ ነው ” አለችና ለጊዜው ንግግሯን አቋርጣ ጥቂት ጊዜ ቆየች ። ፈገግ ካለች በኋላ ሳታስበው ጥርሷን አሳየች ። “ አኪቦምቦ በጣም ፈርቷል ” አለች ። “ ሁልጊዜም የማይበት በጣም ማወቁንና መስል ጠኑን ነው ። ነገር ግን በጥንታዊ የምዕራብ አፍሪካዊያን የአስ ማት እምነት ሊደረግ የሚቻል ነገር አለ ብሎኛል ” አለች ።

“ ወዲያልኝ ! ” አለች ሚስ ሀበርድ ሀሳቡን በመቃወም። “እኔ ለላዕላይ አምልኮት ደንታም የለኝ ። በቃ አንድ ተራ የሰው ልጅ ለሚ ሠራው አሰልቺ ቀልድ ማለቴ ነው ። በቃ ይኸው ነው ። ”

የሳሊ ዐይን እንደ ድመት በስፋት ግማሽ ክብ ሠራ ።

“ አገላለጹና የሚሰጠው ትኩረት ” አለች ፡“አዎን ተራ ነው። ነገር ግን ከዚህ ቤት ውስጥ አንድ ፍጹም ተራ ያልሆነ ሰው አለ ! ” ስትል ደመደመች ።

ሚስ ሀበርድ በደረጃው ወረደች ። ከምድር ቤቱ ወደ ተማሪዎቹ የጋራ መዝናኛ ገባች ። ከክፍሉ ውስጥ አራት ሰዎች ተቀምጠዋል ። ቫለሪ ሆብሐውስ ያን ትንሽ ውብ እግሯን ከመደገፊያው ላይ አድርጋ ከሶፋ ተቀምጣለች ። ኒጌል ቻፕማን ከአንድ ጠረጴዛ ትልቅ መጽሐፍ ከፊት ለፊቱ ከፍቶ ያመለክታል ። ፖትሪሺያ ሌን ከእሳቱ አጠገብ ካለው እብነ በረድ አጠገብ ተደግፋበት ተቀምጣለች ። ሌላኛይቱ የዝናብ ልብስ የለበሰችዋ የሱፍ ባርኔጣዋን ሚስ ሀበርድ በመግባት ላይ እያለች ስታወጣ የነበረችይቱ ልጅ ነች ። መልክ መልካም ፡ ወፈር ያለች ቡናማ ሠፋፊ ዓይኖችና በጥቂቱ ከፊት ያለ የመገረም ሁኔታን የሚ ያሳይ የአፍ ቅርጽ ያላት መስላ ትታይ ነበር ።

ቫሌሪ ከአፏ ሲጋራውን እያላቀቀች በሰነፈና የተንቀረፈፈ ድምጽ፡

“ ታዲያስ እንዴ ! ለተቀደሰችው ባለቤት ፡ ለአሮጊቷ ሰይጣን የመታሻ ሳይሩፕ ሰጥተሻታል ? ” አለች ።

ፖትሪሺያ ሌን “ ስትደባደብ ነበረች ? ” ስትል ጠየቀች ።

“ እንዴ ! ” አለች ቫሌሪ አፍን ይዛ እየሣቀች ።

“አንድ የሆነ መጥፎ ድርጊት ተፈጽሟል ” አለች ሀበርድ ። “ኒጌል እንድትረዳኝ ‘ ፈልጋለሁ ” አለች እንደገና ።

“እኔ?... እንዴ?” አሉና ኒጌል አየት አድርጓት መጽሐፉን ዘጋው።

ቀጭንና ተንኰለኛ የሆነው ፊቱ በድንገት በሸረኛ ግን በሚያ ስገርም ጣፋጭ ረገግታ ፈካ ። “ ምን አድርጌያለሁ ? ” አላት ።

“ ምንም እንዳላደረግህ ተስፋ አደርጋለሁ ” አለች ሀበርድ ። “ግን እኮ ለምቀኝነት ሆነ ተብሎ ከኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ማስታወሻ ደብተር ላይ ቀለም ፈስሷል።ቀለሙ ደግሞ አረንጓዴ ነው ። አንተ የም ትጠቀመው በአረንጓዴ ቀለም ነው ኒጌል ? ”

ትኩር ብሎ ተመለከታት ። ከፊቱ ላይ ፈገግታው ጠፋ ።

“ አዎን ፡ የምጠቀመው አረንጓዴ ቀለም ነው ” አለ ።

“ የሚቀፍ ነገር ” አለች ፖትሪሺያ ። “ አንተ ባትጠቀምበት እመኝ ነበር ኒጌል ፤ ሁልጊዜ እነግርህ ነበር ኒጌል ። እስኪ ምኑ ነው የሚፈቀረው ? ” አለችው ።

“ ወድጄው ነው ” አለ ኒጌል ። “ ሀምራዊ ወይን ጠጅ የበለጠ የተሻለ ይመስለኛል ። እስኪ ትንሽ ለማግኘት እሞክራለሁ ። ግን እውነትሽን ነው እንዴ? ይህን የተሠራውን ሽር ማለቴ ነው ” አላት ።

“ አዎን ! እውነቴን ነው ። የአንተ ሥራ ነው ኒጌል ? ”

“ የለም ፤ አይደለም ። ሰዎችን ማበሳጨት ደስ ይለኛል ። ታውቂ ያለሽ ። ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት የማይረባ የጅል ሥራ አልሠሪ ም ። በእውነት ደግሞ በማንም ሥራ ውስጥ ጣልቃ የማትገባና በምሣሌነት የምጠቅሳትን ውድ ብላክ ቢስ እንደዚህ ዓይነት የማይጠቅማትን ሥራ ፍጹም አላደርግባትም ። የትአለ የኔ ቀለም ? ብዕሬን የሞላሁት ትላንትና ምሽት ነው ። አስታውሳለሁ ። የማስቀምጠውም ያው ከመ ጽሐፍት መደርደሪያው ላይ ነው ። ” ከመቀመጫው ዘሎ በመነሳት ከፍሉን አቋርጦ ሔደ ። “ ይኸውና ! ” የቀለሙን ቢልቃጥ አን ስቶ አቃጨ ። “ ትክክል ነሽ ! ቢልቃጡ ባዶ ነው ፤ ሙሉ ነበር ። ”

የዝናብ ልብስ የለበሰችው ልጅ ትንፋሽ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ፣ “የማ ያሳዝን ነው ፤ ምስኪን ! ” አለች ። “ ምስኪን ፣ ጥሩ ሥራ አይደለም ” አለች ።

ኒጌል በቁጣ ገረመመማት ።

“ ማስረጃ አለሽ ሴሊያ?” ሲል እንደ ጣዕረ መንፈስ ጮኸባት ። ልጅቱ አሁንም ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ።

“ እኔ አይደለሁም ! እኔ ፍጹም አላደረግሁትም ! ለማንኛውም እኔ ቀኑን በመላ ሆስፒታል ነበርኩኝ ፤ ለማድረግም አልችልም ነበር!”

“ አሁን በቃ ኒጌል ” አለች ሀበርድ ። “ሴሊያን አታላግጥባት!” አለች ፖትሪሺያ ሌን በቁጣ ፣

“ ኒጌል ለምንና እንዴት እንደተጠረጠረ አልገባኝም ። በቃ ቀለሙ ብቻ ስለተወሰደ ? ” አለች ።

ቫሌሪ በዚያ ሸረኛ ድምጿ ። “ ትክክል ነሽ የኔ ወለላ ፤ ፍቅረኛ ሽን ተከላከይላት ” አለቻት ።

“ ነገር ግን ትክክል አይደለም ! ” ።

“ እውነቱን ለመናገር እኔ እንዲህ ካለው ሥራ በምንም ዓይነት የሚያያዝ ጉዳይ አይኖረኝም ” አለች ሴሊያ እየተንገፈገፈች ።

“ ማንም አንቺን የጠረጠረ የለም ፣ ጨቅላ !” አለች ቫሌሪ በር ጋታ ። “ ያው እንደምናውቀው ነው ” አለችና ዐይኗ ከሚስ ሀበርድ ዐይኖች ተገጣጠሙ ። በጥቅሻ መልዕክት ተለዋወጡ ። “ይህ ነገር ከቀ ልድ በላይ እየሆነ ስመጣ ። አንድ ነገር መደረግ አለበት ” አለች ።

“ አንድ ነገር መደረግ አለበት ? ” አለች ሚስ ሀበርድ ኮምጨጭ ብላ ።

— 4 —

“ ይኸውና መሴ ፖይሮት ። ”

ሚስስ ሊመን አንድ ቡናማ የወረቀት ጥቅልል በማውጣት ከፖይሮት ፊት አስቀመጠች ። ከላዩ ያለውን ሽፋን በማንሳት በጥሩ ባለሞያ እጅ የተሠራውን የምሽት ጫማ ዋጋውን እንደሚተምን ሰው ሁሉ አተኩሮ ተመለከተው ።

“ አንተው እንዳልከው ከቢከር ጎዳና ነበር ። ”

“ ከቺግር አድናናል ” አለ ፖይሮት ። “ ሀሳቤንም ያረጋግ ጥልኛል ። ”

“ በትክክል ! ” አለች በተፈጥሮም ለምንም ጉዳይ የማትበገረዋ ሚስስ ሊመን ።

ያም ሆኖ ለቤተሰብ ፍቅር የምትሰጠው ሥፍራ ከፍተኛ ነው ።

“ በጣም የማያስቸግርህ ከሆነ መሴ ፖይሮት ከእህቴ ዘንድ አንድ ደብዳቤ ደርሶኝ ነበር ። አንዳንድ በቅርቡ የተፈጸሙ ጉዳዮች ነበሩ ። ”

“ እንዳነበው ፈቃድሽ ቢሆን ? ”

ሰጠችው ። ካነበበ በኋላ ሚስስ ሊመንን ከእህቷ በስልክ እንድ ታገናኘው አዘዛት ። ወዲያውኑ ከመሥመር ላይ መሆኗን ገለጸችለት ። ፖይሮት መነጋገሪያውን አነሳ ።

“ ሚስ ሀበርድ ነሽ ? ”

“ አዎን ፡ መሴ ፖይሮት ። ሳትዘገይ ስለደወልክልኝ በጣም አመ ሰግናለሁ ። በእውነት በጣም — ። ”

ፖይሮት ንግግሯን አቋረጣት ።

“ ለመሆኑ የት ሆነሽ ነው የምታነጋግሪኝ ? ”

“ እንዴ ፡ ከቁጥር 26 ሒኮሪ ጎዳና ነዋ ። አዎን ፡ ምን ማለት እንደ ፈለግህ ገባኝ ። ከራሴ ክፍል ሆኜ ነው ። ”

“ የውስጥ መሥመር አለ ? ”

“ ይህ የውስጥ መሥመር ነው ። ዋናው ስልክ ከአዳራሹ ውስጥ ከታች ነው ። ”

“ ሊሰማ የሚችል ከቤት የቀረ ሰው አለ ? ”

“ በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ በሙሉ አይገኙም ወጥተዋል ። ወጥ - - ቤቷ ወደ ገበያ ወጥታለች ። ባለቤቷ ጆርሚኖ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው አነስተኛ ነው ። ዕዳት ሠራተኛዋ አለች ። ጆሮ ደንቆሮ ስለሆነች እንደማትሰማን ርግጠኛ ነኝ ። ”

“ መልካም ፣ በጣም ጥሩ ። አሁን ነጻ ሆኜ ማውራት እችላለሁ ። አንዳንዴ ትምህርታዊ ንግግሮች ይደረጋሉ ? ወይንም ምሽት ፊልሞች ይታያሉ ? ማለቴ አዝናኝ የሆኑ ዝግጅቶች ? ”

“ ትምህርታዊ ንግግሮች እንኳ አልፎ አልፎ ይሰጣሉ ። ሚስስ ባልትራውት አገር አጥኚዋ ተመራማሪ በቅርቡ ቀለም ፎቶግራፎቿን ይዛ መጥታ ነበር ። ለሩቅ ምሥራቅ ተልዕኮዎች ጥያቄ አቅርበን ነበር ። ምናልባት በዚያን ምሽት ብዙ ተማሪዎች አይገኙም ብዬ ፈርቻለሁ ። ”

“ አሀ ! በዚህ ምሽት መሴ ፖይሮትን የእህትሽን አለቃ ካከና ወናቸው የወንጀል ክትትሎች በጣም አስደናቂ ከሆኑት መካከል ለተማሪዎችሽ ለማቅረብ እንዲመጣ አስቸግረሽዋል አሉ ። ”

“ በጣም ግሩም ይሆናል ! ርግጠኛ ነኝ ። ግን ይመስልሀል ? ” ።

“ የለም ፤ የመምሰል ጥያቄ ሳይሆን ርግጠኛ ነኝ ! ”

በዚያን ምሽት ወደ ጋራ - አዳራሹ የሚገቡ ተማሪዎች ከማስታወቂያ ሰሌዳው ከበሩ ውስጥ ማስታወቂያ ተለጥፎ ተመለከቱ ።

መሴ ሔርኩሌ ፖይሮት እወቁ ስውርወንጀልን በግል ተከታታይ የሆኑት ሰው በዚህ ምሽት በከተተል ፅንሰ ሀሳብ ላይ ከታወቁ የወንጀል ድርጊቶች በመ ጥቀስ ንግግር ስለሚያደርጉ ሁላችሁም ተጋብዛችኋል ።

በመመለስ ላይ የነበሩ ተማሪዎች የተለያዩ አስተያየቶችን ሰነ ዘሩ ።

“ ይኼ የግል ጆሮ ማነው ? ” “ በፍጹም ስሙንም ሰምቼ አላ ውቅ ። ” “ እኔ ሰምቼለታለሁ ። አንድ ሰው ዕዳት ሠራተኛ በመግደል ወንጀል ሞት የተፈረደበት ነበር ። ወንጀሉን የሠራውን ሰው በማ ግኘት ይኸው ሰው ከሞት አትርፎታል ። ” “ እንዲያው ጊዜ ማጥ ፊያ ነገር መሰለኝ።”“እንዲያውም የሚያሥቅ፣ለቀልዳቀልድ ብሎ መሰ

CITY - HALL LIBRARY
OF
ADDIS ABABA

ለኝ ። ” “ ኮሊን በጣም ነው ደስ የሚለው ፣ የወንጀል ሳይኮሎጂ ሲሉት ልቡ ነው የሚጠፋው ። ” “ እኔ እንኳ እንደዚያ በትክክል መናገር አልችልም ፤ ነገር ግን ከወንጀለኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሰው ማነጋገር የሚያጓጓ መሆኑን አልጠራጠርም ። ”

በአንድ ተኩል ላይ አብዛኞቹ ተማሪዎች ሚስ ሀበርድ ስት መጣ ከራት ላይ ነበሩ ። ከ’ራሷ ክፍል ነበር የምትመጣው ። (ለተከ በረው እንግዳ የደቡብ ስፓር ወይን ጠጅ ቀርቦለታል) አብሯት ከሰውነቱ አነስ ብሎ ጠና ያለ የሚመስል ጥቁር ፀጉርና ብልህ ተክለ ሰውነቱን የሚያጎላ በጥንቃቄ የተቋጨ ዒም ያለው ሰው ተከትሏ ታል ።

“ እነዚህ ከተማሪዎቻችን ጥቂቶቹ ናቸው መሲ ፖይሮት ። እኚህ ከ’ራት በኋላ ንግግር የሚያደርጉልን ሰው መሲ ሔርኩይሌ ፖይ ሮት ናቸው ። ”

ሰላምታዎች ተለዋወጡ ። ፖይሮት ከሚስ ሀበርድ ጎን ተቀምጦ በምስጉኑ ጣሊያናዊ ወጥ - ቤት ከአንድ ከትልቅ ጉድጓዳ ሣህን የሚወ ጣው ሚኒስትሮኒ ዒሙን እንዳያበላሽበት ጥንቃቄ በማድረግ ላይ ነው ።

ወዲያው ትኩስ የስፓጌቲና የድብልብል ሥጋ ሣህኖች ተከታ ተሉ ። በዚያን ጊዜ ነበር ከፖይሮት በስተግራ የተቀመጠችዋ ወይ ዘሪት በዓይነ አፋርነት እየተሽኮረመመች ያነጋገረችው ።

“የሚስ ሀበርድ እህት በእውነት ከርሶ ዘንድ ነው የምትሠራው?”

ፖይሮት ወደ’ርሷ ዞረ ።

“ እንዴ ፣ አዎን ። ሚስስ ሊመን ለብዙ ዓመታት ጸሐፊዬ ሆና ቆይታለች ። በጣም ብቃት ካላቸው ሴቶች አንዷ ናት ። አንዳንድ ጊዜ እፈራታለሁ ። ”

“ ገባኝ ፤ በጣም ነው የተገረምኩት — ”

“ የምን መገረም ነው ወይዘሪት ? ” አላት ።

አባታዊ ፈገግታ እያሳያትና ከሀሳቧ ሁኔታዎቿን በማጠናናት ላይ ነበር ።

“ ውበት ፣ ጭንቀት ፣ በአዕምሮ ፈጣን አለመሆን ፣ ፍራት ...”

“ የምታጠኝውን ትምህርትና ስምሽን ልትነግሪኝ ትችያለሽ ?”

“ ሴሊያ አውስቲን ። አልማርም ! ከቅድስት ካታሪን ሆስፒታል መድሐኒት አከፋፋይ ነኝ ። ”

“ በጣም የሚያስደስት ሥራ ነው ያለሽ ፣ አይደለም ? ”

“ እኔ እንጃ — ምናልባት ሊሆን ይችላል ። ” ርግጠኛ አለመሆኗ ይንጸባረቃል ።

“ እነዚህስ? ስለነሱ ምናልባት አንዳንድ ነገሮችን ልትነግሪኝ ትችያለሽ? እንደገባኝ ይህ ቤት ለውጪ ዜጋ ተማሪዎች ነበረ ። ነገር ግን በአብዛኛው እንግሊዛዊያን መሰሉኝ ። ”

“ አብዛኛዎቹ መጤዎች ወጥተዋል ። ሚስተር ቻንድራ ላልና ሚስተር ጎፖል ራም - ሕንዶች ናቸው - ሚስስ ሪንጂር ደች - ሚስ ተር አህመድ አሊ ግብጻዊና የፖለቲካ ሰው ናቸው ! ”

“ ከዚህስ ያሉት ? እስኪ ስለነ‘ሱ ንገሪኝ ? ”

“ መልካም ፣ ከሚስ ሀበርድ በስተግራ ያለው ኒጌል ቻፕማን ነው ። የሚያጠናውም የመካከለኛውን ዘመን ታሪክና ጣሊያንኛ ከለንደን ዩኒቨርስቲ ነው ። ቀጥላ የተቀመጠችው የዓይን መነጽር ያደረገችው ፖትሪሺያ ሌን ናት ። በአሁኑ ወቅት በአርኪዮሎጂ ዲፕሎማዋን ታገኛለች ። ያ ጎላ ያለው ባለቀይ ፀጉሩ ሊን ባትሰን ነው ። የህክምና ተማሪ ነው ። ከርሱ ቀጥላ ያለችዋ ቫለሪ ሆብሐውስ ናት ። በውበት ሣሎን ሠራተኛ ናት ። ከርሷ ጎን ኮሊን ማክናብ ነው ። በአሁኑ ወቅት ለድህረ ምረቃ በማጥናት ላይ ነው ። ሳይካትሪ ነው የሚያጠናው ። ”

ስለ ኮሊን ስትናገር ድምጿ ትንሽ ለውጥ ይታይበታል ። ፖይሮ ትም ፊቷ ሲለዋወጥ ተመለከተ ።

ለራሱም ፣ “ ፍቅር ስለያዛት ነው ። ራሷን መቆጣጠርና ስሜቷን መሸፈን አትችልም ” ሲል አሰበ ።

ከአጠገቡ ከነበረች አንዲት የምትንከተከት ባለቀይ ፀጉር ወይ ዘሪት በማውራት ላይ የሚገኘው ወጣቱ ማክናብ ራቅ በማለቱና ከጠ ረጴዛውም አሻግሮ መመልከት ባለመቻሉም ይሆናል ። ሔርኩሌ ፖይ ሮት ግን ለልጂቱ ትኩረት ያልሰጣት መሆኑን ተመለከተ ።

“ያቺ ደግሞ ሳለ. ፊንች ናት ። አሜሪካዊት ሴት ነች ። በፋልበር የነጻ ትምህርት እድል ለመማር የመጣች ናት ። ቀጥላ ያለችው ጂኔ ቬይቭ ማሪኩድ ናት ። እንግሊዝኛ ነው የምታጠናው ። ከአጠገቧ ያለው ሬኒ ሀሌ ነው ። ትንሿ ልጃገረድ ጄን ቶሚልሰን ናት ፣ እርሷም ከቅድ ስት ካታሪን ትሰራለች ። ፊዚዮቴራፒስት ናት ። ጥቁሩ ሰው አኪ

ቦምቦ ይባላል ። ከምዕራብ አፍሪካ ነው የመጣው ። በጣም ጥሩ ሰው ነው። ያቺ ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ትባላለች። ከጀማይካ ነው የመጣችው። የሕግ ተማሪ ናት ። ከእኛ በስተቀኝ ያሉት ከሣምንት በፊት የመጡ የቱርክ ተማሪዎች ናቸው ። ፍጹም የእንግሊዝኛ ቋንቋ አይችሉም ።''

'' እመሰግናለሁ እንዴት ነው ትስማማላችሁ ? ወይንስ ትጣላላችሁ ? '' አነጋገሩ የፊቱን ኮስታራነት ያጣፋዋል ።

'' ለመጣላት ጊዜ አናገኝም። ሥራ ይበዛብናል። ምንም እንኳ—'' አለች ሴሊያ ።

'' ምንም እንኳ—ምን ወይዘሪት አውስቲን ? ''

'' አዎን — ኒጌል - ከሚስ ሀበርድ አጠገብ የተቀመጠው ሰው ችን በመነካካት ማበሳጨት ይወዳል ። ሌን ባትሰንም ቁጡ ነው ። አንዳንዴ በደምፍላት ነው የሚንተከተከው ። ነገር ግን በጣም ተወዳጅ ሰው ነው ። ''

'' ኮሊን ማክናብስ ፡ እርሱም ይናደዳል ? ''

'' የለም ! ኮሊን ቅንድቡን ወደ ላይ እያነሳ መሣቅ ብቻ ነው ።''

'' ገባኝ ! ወጣቶቹ ሴቶችስ ? ርስ በርሳችሁ ትጣላላችሁ ? ''

'' የለም ! ተስማምተን ነው የምንኖረው ። ጂኔቪቭ አንዳንዴ ይሰማታል ። እንደሚመስለኝ ፈረንሣዮች ቶሎ ወደሚሰማቸው ሰዎች ሚያዘነብሉ ሳይሆኑ አይቀሩም - በጣም ይቅርታ — ማለቴ — ። ''

ሴሊያ ግራ የመጋባት መልክ ይታይባታል ።

'' እ ፡ ያ — ምንም — ምንም አይደል በእውነት — ቢቃ ፡ አንዳንድ ቀልዶች አሉ አይደል? — ሚስ ሀበርድ ይመስለኛል — ግን የራሴው ጅልነት ነው ። ሌላ ነገር እንኳ መናገሬ አልነበረም ። ''

ፖይሮት ብዙም ሳይገፋበት ተወው ። ወደ ሚስ ሀበርድ በመዞር ፡ ከርሷና ከኒጌል ቻፕማን ወንጀል የፈጠራ ጥበብ ነው ። እኒያ ገልቱዎች በሀቡዕ - ፍቅረ - ሥቃይ ብቻ ወደ ሙያው ስለሚገቡት ፖሊሶች ፡ በሚለው የኒጌል አከራካሪ ርዕስ ላይ በሦስቱ መካከል በሚደረገው ውይይት እየተሣተፈ ነው ። ፖይሮት በጥርጣሬ ፍርሃት ተውጣ መነጽሯን ካፍንጫዋ ሰክታ ተስፋ እንደቆረጠ ሰው ሁሉ ከጎኑ እርሱ የሰነዘረውን ሀሳብ ማብራሪያ በምትሰጠዋ ወይዘሪት በጣም የተደነቀ ይመስላል ። ኒጌል ቀና እንኳ ብሎ የሚመለከታት አይመስልም ።

ሚስ ሀበርድ የተገረመች ትመስላለች ።

“ የዛሬዎቹ ወጣቶች በቃ ካለ ፖለቲካና ሳይኮሎጂ ሌላ ሀሳብ የላችሁም ? ” አለች ። “ እኔ ልጃገረድ ሳለሁ አብዛኞቻችን ደስተኞች ነበርን ። በቃ መደነስ መጨፈር ብቻ ! ይህን ከጋራ - አዳራሹ ያለ ውጋ ምንጣፍ ብትጠቀልሉት ጥሩ ወለል ታገኛላችሁ ። ከዚያ ሬዲዮ ከፍቶ ማስነካት ብቻ ነው ። እናንተ ግን አትፈልጉትም ። ”

ሴሊያ በትንሹ ቅንዓት የተቀላቀለበት ሣቅ ሣቀች ።

“ ነገር ግን ኒጌል ስትደንስ አልነበርክም ? ምንም እንኳ ታስ ታውሰዋለህ ብዬ ባልጠብቅም አንድ ጊዜ እኔ ራሴ አብሬህ ስደንስ ነበር ። ”

“ እምን ! ከኔ ደንሰሽ ነበር ” አለ በሚያፈዝ ሰው አኳኋን ። “ ግን የትኛው ሥፍራ ? ” ሲል እንደገና ጠየቃት ።

“ ከካምብሪጅ በግንቦቱ ሣምንት የጸደይ ክብረ በዓል ላይ ።”

“ አስታወስኩኝ የጸደይ ክብረ በዓል ! ” ኒጌል ያን የልጅነት ጨዋታ በእጁ ተወነ ። “ አምን፣ አንድ ሰው በዚያ ዓይነቱ አቅመ አዳም የደረሰ ዕድሜ ውስጥ ማለፉ ግዴታው ነው ። ደግሞ ወቅቱ ሲያበቃ ሁሉም ያልፋል ። ”

ኒጌል አሁንም ከሀያ - አምስቱ የዘለለው መስሎ አይታይም ። ፖይሮት ሣቁን በጺሙ ሸፈነው ።

ፖትሪሺያ ሌን ከልቧ ፡ “ አየሽ ሚስ ሀበርድ ! ብዙ የሚ ወራ ነገር አለ ። ሌክቸር መከታተል ፡ ማስታወሻዎች መጻፍ ፡ ምንም ሌላ ጊዜ አይኖርሽም ። ለዚሁ መሯሯጥ ብቻ ! ” አለች ።

“ አምን የኔ ወሰላ ፡ እውነት ነው ። ነገር ግን አንድ ሰው ወጣት የሚሆነው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ” አለች ሀበርድ ።

ከስፖንጊቲው ቀጥሎ ቸኮሌት ተከተለ ። ከዚያ በኋላ ወደ የጋራ- አዳራሽ በመግባት ከጠረጴዛው ከተቀመጠው ሙቀት መጠበቂያ ጀበኛ ቡና እየቀዱ መጠጣት ቀጠሉ ። ፖይሮት ንግግሩን እንዲጀምር ተጋበዘ ። ሁለቱ የቱርክ ዜጎች ይቅርታ ጠይቀው ወጡ ። ሌሎቹ ፣ ቀ ምጠው በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር ።

ፖይሮት ከመቀመጫው ተነስቶ በመቆም በተለመደው ሁኔታ ያለችግር ንግግሩን ቀጠለ ። የ‘ራሱ ድምጽ ምንጊዜም ያስደስተው ነበር ። ለአርባ አምስት ደቂቃዎች በሚገባና በሚያስደንቅ አኳኋን የሥራ - ልምዱንና ያጋጠመውን ድርጊት በመዘርዘር በተከታታዮቹ

ዘንድ ከፍተኛ መገረምን አስከተለ ። አነጋገሩ ያሳምናል ። ምናልባት ትንሽ ኮስተር ብሎ የማይጠቅሙ መድሐኒቶችን እንኳ ሰመሸጥ ቢሞክር የሚቃወመው ሰው አይኖርም ።

“ እና አያችሁ ” አለ ሲጨርስ ፡ “ ለዚህ የተከበረ ኩባንያ ከሲጅ ስለማውቀው አንድ ለውብ ጸሐፊው ፍቅር ሲል ሚስቱን ስለ መረዛት የሣሙና ፋብሪካ ባለቤት አስታወስኩት ። በቀስታ ፡ በቀላሉ አጫወትኩት ። ወዲያው አንድ ውጤት አገኘሁ ። ያገኘሁለትን የተሠረቀውን ገንዘብ ከእጇ ላይ ወረወረው ። ተሠርቆ ያስመለስኩት ሁለት ገንዘብ ነበር ። ፊቱ ገረጣ ፡ ከዓይኖቹ ፍርሃት ይነበባል ። ‘ ይህን ገንዘብ ፡ ለአንድ በጎ አድራጎት እመጸውታዋለሁ ’ ባልኩት ጊዜ እርሱ ደግሞ ፡ ‘ የፈለከውን አድርግበት ’ አለኝ ። እኔም መልሼ በቁም ነገር ፡ ‘ ጌታዬ በጣም ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል ’ አልኩት ። ካለምንም ቃል ራሱን ሲነቀንቅ ቆየ ። በመሐድ ላይ እያለሁ ዞር ብዬ ስመለከተው ከግንባሩ የተንቸረፈፈውን ላብ በመጠራረግ ላይ ነበር ። በጣም ፍርሃት ውጦት ነበር ። ነፍሱን አድኛታለሁ ። ከዚያች ንጹህ አውሮፓዊት ጸሐፊው ለያዘው የዓይን ፍቅር ሲል ያቺን ደደብና ጨቅጫቃ ሚስቱን ለመመረዝ ከእንግዲህ አይሞክርም ። ከሕክምናው ይልቅ ሁልጊዜም ቢሆን አስቀድሞ መከላከሉ ይሻላል ። የግድያ ወንጀሎች እስከሚፈጸሙ መጠበቅ አይኖርብንም ። ”

እጅ በመንሳት እጆቹን ዘረጋችው ።

“ መቼም እንዳሰለቸኋችሁ አልጠራጠርም ” አለ ።

ተማሪዎቹ አድናቆታቸውን በጭብጨባ ገለጹለት ። ፖይሮት እንደገና እጅ ነስቶ ሊቀመጥ ሲል ኮሊን ማክናብ ፒፖውን በጥርሶቹ መካከል አድርጎ ፡ “ ቀጥሎ ምናልባት እዚህ ሥፍራ የመጣህበትን ምክንያት ትገልጽልን ይሆናል ! ” አለው ።

ሩጥቂት ጊዜ ጸጥታ ሠፈነ ። ፖትሪሺያ በቁጣ አገላለጽ “ኮሊን !” ስትል ጠራችው ።

“አምን ! አንድ ነገር ሁላችንም የተረዳን መሰለኝ ። አይደለም?” በንቀት መንፈስ በዙሪያው ያሉትን ተመለከተ ። “ መሴ ፖይሮት አስ ገራሚ የሆነ ትንሽ ንግግር አድርጎልናል ። ነገር ግን እዚህ የመጣበት ጉዳይ ለዚህ አይመስለኝም ። እ‘ሱ ሥራውን እየሠራ ነው ። እውነትም መሴ ፖይሮት ይህን የማይገምቱ ናቸው ብለህ ታስባለህ ? ” አለ ።

“ ይህን ለራስህ ተወው ኮሊን ” አለች ሳሊ ።

“ እውነት ነው ፡ አይደለም ? ” ሲል ጠየቀ ኮሊን ።

ፖይሮት እንዶገና እጆቹን ዘረጋ ። በትህትና የመቀበል ዓይነት ነበር ።

‘‘ ተቀብያለሁ ’’ አለ ። ‘‘ የተከበረችው አስተናጋጅ አንዳች ነገር በጣም እንዳሳሰባት አጫውታኝ ነበር ። ’’

ሊን ባትሰን ከመቀመጫው ተነሳ ። ፊቱ ከብዶታል ። ለጸብ የተ ዘጋጀ ሰው ይመስላል ።

‘‘ እኔ የምለው ’’ አለ ። ‘‘ ለመሆኑ ይኼ ሁሉ ምንድነው? እኛን ለመወንጀል የተሠራ ሥራ ነው ? ’’

‘‘ በእውነት እንዲህ በንዴት የሚያንጨረጭር ነገር ነው ባት ሰን ? ’’ ሲል ኒጌል በሚያስደስት አኳኋን ጠየቀው ።

ሴሊያ በፍርሃት ከተነፈሰች በኃላ ‘‘ ትክክለኛ ነበርኩ ! ’’ አለች ።

ሚስ ሀበርድ በሀላፊነት ድምፅ በመጀነን ፡ ‘‘ መሴ ፖይሮትን ንግግር እንዲያደርግልን የጠየቅሁት እኔ ነኝ ። በተጨማሪ ባለፈው ጊዜ ስለተፈጠሩ አንዳንድ ነገሮች እንዲያማክረኝ ጠየቅሁት ። አንድ ነገር መደረግ ነበረበት ። ያለው አማራጭ ፖሊስ ብቻ መስሎ ታየኝ ’’ አለች ።

በአንድ ጊዜ ትልቅ አምባጓሮ ተፈጠረ ። ጄኒፌቭ በፈረንሣይኛ ታስነካው ጀመር ። ‘‘ ወደ ፖሊስ መሔዱ በጣም የሚያሳፍር ወራዳ ተግባር ነው ! ’’ ሌሎችም ድምጾች በተቃውሞና በድጋፍ ተሰሙ ። በመጨረሻ በስንት እሸሩሩና ማባበል የሊዎናርድ ባትሰን በወ ሳኝነት ላቅ ብሎ መስማት ቀጠለ ።

‘‘እስኪ መሴ ፖይሮት ስለ ችግራችን የሚናገረውን እናዳምጥ’’አለ።

ሚስ ሀበርድ ፡ ‘‘ ለመሴ ፖይሮት የሆነውን ሁሉ ማስረጃውን ሰጥቼዋለሁ ። ጥያቄዎች መጠየቅ ከፈለገ ማንኛችሁም እንደማትቃ ወሙ ርግጠኛ ነኝ ’’ አለች ።

ፖይሮት እጅ ነሳት ።

‘‘ አመሰግናለሁ ’’ አለና በአስተማማኝ አኳኃን ጥንድ የምሽት ጫማዎች አውጥቶ ለሳሊ ፊንች ሰጣት ።

‘‘ ጫማዎችሽ ናቸው ወይዘሪት ? ’’ አላት ።

‘‘ እንዴ - አዎን - ሁለቱም ? የጠፋው ከየት መጣ ? ’’

‘‘ ከቤከር ጣቢያ ከጠፋ ዕቃዎች ጽሕፈት ቤት ነው የተገኘው ።’’

‘‘ ግን እንዴት ከዚያ መኖሩን ማሰብ ቻልክ መሴ ፖይሮት ? ’’

‘‘ በጣም ቀላል ነው ። አንድ ሰው ከክፍልሽ ጫማ ይወስዳል ። ለምን? ለማድረግም ሆነ ለመሸጥ አይደለም ። ቤቱ በሁሉም ሰው ዕቃው እስኪተገኝ ስለሚፈተሽ ከቤት ወጥቶ ሌላ ሥፍራ መቀመጥ አለበት ። ካልሆነም መጥፋት ይኖርበታል ። ቀላሉ መንገድ በጣም ሰው በሚ በዛበት የችኮላ ጊዜ ከአውቶቡስ ወይንም ከባቡር ውስጥ በአንድ ነገር ጠቅልሎ ከመቀመጫ ሥር ጥሎ መውጣት ብቻ ነው ። ያ እን ግዲህ በመጀመሪያ ላይ በሀሳቤ የመጣ መላ ምት ነው ። ትክክል ሆኖ አገኘሁት ። ስለዚህ ሀሳቤ ሁሉ እንደሚሳካልኝ አወቅሁ ። እኒህ ጫማ ዎች የስነ ግጥሙ ሰው እንዳለው ሁሉ የተወሰዱት ‘‘ የሚያላግጡ መሆናቸውን ስለሚያውቅ ለማናደድ ነው ’’ አለ ።

ቫሌሪ ትንሽ ፈገግ አለች ።

‘‘ ወዳጄ ኒጌል ያለምንም ጥርጥር ይህ አንተን የሚመለከት ጉዳይ ነው ። ’’

ኒጌል በቁላቂል አሣሣቅ፡‘‘ ጫማው የሚሆንሽ ከሆነ አድርጊው ’’ አላት። ‘‘ ደደብ! ’’ አለች ሳሊ። ‘‘ኒጌል ጫማዬን አልወሰደም!’’ አለች።

‘‘ በርግጥ እ‘ሱ አልወሰደም ! ’’ አለች ፖትሪሺያ በቁጣ ። ‘‘በጣም የተሣሣቱ አስተሳሰብ ነው ፡ ’’ ስትል አከለች ።

‘‘ እኔ ስለ ስህተት አላውቅም ’’ አለ ኒጌል ። ‘‘ ለማንኛውም እኔ እንደዚያ ዓይነት ሥራ ሠርቼ አላውቅም — ሁላችንም ካለጥርጥር እንደምናምነው ማለቴ ነው ። ’’

ፖይሮት እነዚህን ቃላት እንደሚጠብቅ ሁሉ ልክ አንድ ተዋ ናይ የራሱን ክፍል ለመተመን የሌላውን ወይንም ሌላይቷን የመጨረሻ ደርጊት ወይንም ንግግር እንደሚጠባበቅ መስሎ ይታይ ነበር ። ዓይ ኖቹ ቦሀሳብ ከሊን ባትሰን የቀላ ፊት ላይ ዓረፉ ። ቀጥለው ከቀሩት ተማ ሪዎች ላይ ተንከራተቱ ።

ሆነ ተብሎ በሚደረግ የባዕድ የእጅ አወነጫጨፍ እጁን ተወነ ጨፈ ። ።

‘‘ የኔ አቋም ግልጽ ነው ። ከዚህ እንግዳ ሆኜ ነው የመጣሁት ። በሚስሀበርድ ቲጋብኜ ። አንድ አስደሳች ምሽት ለማሳለፍ ነው የመ ጣሁት ። በቃ ! እግረ — መንገዴንም በጣም ደስ የሚሉ የምሽት ጫማ ዎችም ለወይዘሪቷ ለመመለስ ነው ። ከዚህ በተረፈ - ’’ ብሎ ትንሽ

ዝም አለ ። ቀጥሎም “ መሴ ባትሰን ? አምን ባትሰን እኔ ራሴ ስለ ዚህ ችግር ምን እንደማስብ ጠይቆኛል ። ነገር ግን በአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን በሁሉም እስካልተጠየቅሁኝ ድረስ መናገሩ ለ‘ኔ ተገቢ አይደለም ። ”

ሚስተር አኪቦምቦ ያን ጥቁር ራሱን ኮስተር ብሎ በነገሩ ውስጥ አለመኖሩን በሚገልጽ አኳኋን ነቀነቀ ።

“ አምን ! ይህ ነው ትክክለኛው ሥነ - ሥርዓት ” አለ ። “ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ሒደት ችግሩን ለመላው ተሳታፊ ማቅረብ ነው ። ”

የሳሊ ፊንች ድምጽ በትዕግሥት ማጣት ሲቻኮል ይሰማል ።

“ባዶ ኮፈን ብቻ ” አለች ። “ በቃ ይኼ ነው ስብሰባው? እስኪ ባልንጀሮቼ ሀሳባችን አንድ ይሁን ። የማይረባ እሰጥ—አገባ እንተውና መሴ ፖይሮት የሚሰጠንን ምክር እንስማው ። ”

“ ሳሊ ከእንግዲህ ብዙ መግባባት አንችልም ” አለ ኒጌል ።

ፖይሮት እጅ ነሳ ።

“ መልካም ” አለ ። “ ሁላችሁም ይህን ጥያቄ እስካቀረባች ሁልኝ መልሱን እሰጣለሁ ። ምክሬ በጣም ቀላል ነው ። ሚስ ሀበርድ ወይንም ሚስ ኒኮሊተስ - ከኔ ይልቅ በአንድ ጊዜ ፖሊስ ለመጥራት አያዳግታቸውም ። ጊዜ መጥፋት የለበትም ። ”

— 5 —

የፖይሮት ንግግር ያልተጠበቀ ዱብ ዕዳ መሆኑ የማያጠራጥር ነበር ። ምንም ተታወሞም ሆነ ጭቅጭቅ አልፈጠረም ። ያፈራው ጭንት የሚል ድንገተኛ ፀጥታ ነበር ።

በዚያ የጥቂት ጊዜ አምባጓሮ በመከለል አጋጣሚውን ለመጠቀም ፖይሮት በሚስ ሀበርድ ወደ ራሷ ክፍል ‘‘መልካም ምሽት ለሁላችሁም ! ’’ በሚል የቸኰላ ትሕትና ስንብት ወሰደ ።

ሚስ ሀበርድ መብራቱን አበራች ። በሩን ዘጋችና መሲ ፖይሮትን ከመሞቂያው ምድጃ አካባቢ ካለው ወንበር እንዲቀመጥ ጋበዘችው ። ያ የደስ ደስ ያለው ኮስታራ ፊቷ በጥርጣሬና ፍርሃት ደፍርሷል ። ለእንግዳዋ ሲጋራ ጋበዘችው።ፖይሮት ግን የራሱን ማጤስ እንደሚፈልግ በትህትና በመግለጽ አልተቀበለውም ። ርሱም ቢጋብዛት ለወጥ ባለ ድምጽ ፥ ‘‘ አላጤስም መሲ ፖይሮት ! ’’ በማለት መለሰችው ።

ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ ከጥቂት ማመነታታት በኋላ ፡

‘‘ ትክክል ነህ መሲ ፖይሮት ! ምናልባት በአሁኑ ወቅት ከዚህ የቀለም ማፍሰስ የምቀኝነት ሥራ በኋላ ፖሊስ መጥራት እንችላለን። ነገር ግን ፊት ለፊት እንደዚያ ባትናገር እመርጥ ነበር ’’ አለች ።

‘‘ አሀ ! ’’ አሰ ፖይሮት ቀጭኗንና ትንሿን ሲጋራውን በማቀጣጠል ወደ ላይ የሚወጣውን ጭስ እየተመለከተ ። ‘‘ መደረግ ነበረበት ብለሽ ታስቢያለሽ ? ’’ አላት ።

‘‘ በርግጥ ግልጽ መሆኑ እንኳ ትክክል ነው ። ለ’ኔ ግን እንደሚመስ ኝ ዝም ብሎ አንድ መኰንን በመጥራት በግል ነገሩን ማስረዳት የተሻለ ነበር ። ማለት የፈለግኩት ይህን ይደብ ሥራ የሚሠራ ማንም ይሁን ግን አሁን ማስጠንቀቂያ አገኘ ማለት ነው ። ’’

‘‘ ምናልባት ይሆናል ። ’’

‘‘ እንደዚያ መናገር እችላለሁ ’’ አለች ሚስ ሀበርድ ቅጭም ብላ ። ‘‘ ምናልባት የሚባል አይደለም ! በዚህ ምሽት አብረውን ያል

ነበሩ የቤት ሠራተኞች ወይንም ሌሎች ተማሪዎች እንኳ ቢሆኑ ወሬ ው ይደርሳቸዋል ። ሁልጊዜም እንደዚሁ ነው የሚሆነው ። ''

'' ትክክል ነው ። ሁልጊዜም እንደዚሁ ነው ። ''

'' በዚህ ላይ ደግሞ ሚስ ኒኮተሊስም አለች ። ምን ሀሳብ እንደ ሚኖራት በርግጥ ለማወቅ አልችልም ። እንዲህ በቀላሉ ሀሳቧን ለመረዳት የሚቻል ሰው አይደለችም ። ''

'' ለማወቅ ጥረት ማድረጉ የሚያዓዓ ነው ። ''

''ርዒ እስካልተስማማችበት ፖሊስ መጥራትም አንችልም ። ማነው ደግሞ ይኼ ? ''

ከበሩ ላይ ትምክህት የተሞላው የመንኳኳት ድምጽ ይሰማል ። ሚስ ሀበርድ በንዴት ፡ '' ይግቡ ! '' ከማለቷ አስቀድሞ በሩን በመበ ርገዱ ከጥርሶቹ መካከል የትምባሆ ፒፓውን እንደያዘ አስከፊ የፊት ገጽታ ከክፍሉ ገባ ።

ከጥርሶቹ ፒፓውን አላቆ በሩን ከበስተጀርባው ዘጋው ።

''ይቅርታ ታደርጊልኛለሽ ፡ ከመሴ ፖይሮት ጋር ጥቂት ነገ ሮችን ለመነጋገር ፈልጌ ነበር '' አለ ።

'' ከ'ኔ? '' ሲል ጠየቀው በየዋህነት የመገረም መንፈስ ራሱን ያዞረው ፖይሮት ።

'' አዎን ፡ ከአንቱ '' አለ ኮሊን እየከበደው ።

አንድ ምቾት የሌለው ወንበር ስቦ ፊቱን በመመለስ በሔርኩሌ ፖይሮት ፊት ለፊት ተቀመጠ ።

'' ዛሬ ምሽት ላይ የሚያስገርም ንግግር ነው ያደረከልን '' አለው በማመስገን መልክ ። ቀጥሎም ፡ '' በርግጥ የተለያየና የረ ጂም ጊዜ ልምድ ያለህ ሰው መሆንህን አልክድም ። ነገር ግን ይህን በመናገሬ ይቅርታ የምታደርግልኝ ከሆነ ስልቶችህና ሀሳቦችህ ሁለ ቱም ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው '' አለው ።

'' እውነቴን ነው የምልህ ኮሊን ! '' አለች ሚስ ሀበርድ ፊቷ እየቀላ ፡ '' ከመጠን በላይ ባለጌ ነህ !'' አለች ።

'' መሳደቢ አይደለም ። ነገር ግን ጉዳዩን ግልጽ ማድረግ ስለፈ ለግኩኝ ነው ። ወንጀልና ቅጣት መሴ ፖይሮት — የአስተሳሰብ አድ ማስህ ስሩት የሚወስነው ነገር ነው ።''

“ ለኔ የተፈጥሮ ቅደም ተከተል ነው የሚመስለኝ ” አለ ፖይሮት ።

“ በጣም የጠበበውን የሕግ አመለካከት ነው የወሰድከው — ሌላስ በተጨማሪ እዎን ! በጣም ሁዋላ የቀረውን ሕግ ። በዛሬው ዘመን ራሱም ሕጉም ቢሆን የወንጀል መንስኤዎች ምንድናቸው ? ከሚሉት ዘመናዊ ጽንስ - ሀሳቦች ተስማምቶ መጓዝ ይኖርበታል ። ዋጋ የሚሰጣቸው መሴ ፖይሮት ፣ መንስኤዎቹ ናቸው ። ”

“ ወዳጄ ! በእንተ ዘመናዊ አነጋገር ለመጠቀም ያህል ከዚህ በላይ ከእንተ እንደማልስማማ ገልጽልሃለሁ ! ”

“ ከዚህ ቤት እየተፈጸመ ስላለው ጉዳይ መንስኤውን መፈለግ ይኖርብሃል ። እነዚህ ነገሮች ለምን እንደተደረጉ ማወቅ አለብህ ! ”

“አሁንም ቢሆን በሀሳብህ እስማማለሁ።ያ በጣም አስፈላጊ ነው።”

“ ሁልጊዜም ቢሆን’ኮ ካለምክንያት የሚሠራ ነገር የለም ። ይህን የሚፈጽመው ሰው አጥጋቢ ምክንያት ይኖረዋል ። ”

በዚህ አነጋገር ራሷን ለመቆጣጠር ያልቻለችዋ ሚስ ሀበርድ ፣ “የማይረባ ! ” ስትል አምባረቀች ።

“እዚያ ላይ ነው የተሳሳትሽው” አለ ኮሊን ፣ ራሱን ወደ ርሷ ትንሽ ዘወር በማድረግ ። “ሳይኮሎጂካዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት አለብሽ ”—አለ ደገመና ። ”

“ ሳይኮሎጂካዊ ቅብጥር ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ “ እንደዚያ ላለው ንግግር ትዕግሥት የለኝም ! ”

“ እንደዚያ የምትይው በትክክል ምን ማለት እንደሆነ ስለማታውቂ ብቻ ነው ” አለ ኮሊን ንዴቱ ከፊቱ እንደ እሳት እየተንቀለቀለበት ። ፊቱን ወደ ፖይሮት መለሰ ።

“ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ከፍተኛ ጉጉት ስላለኝ ነው ። በአሁኑ ወቅት በሳይኮሎጂና ሳይካትሪ ላይ የድህረ ምረቃ ጥናት እያደረግሁኝ ነኝ ። በዚህ አጋጣሚ በጣም በሚዘገንኑና ሥር በሰደዱ ጉዳዮች ላይ ጥናት ወስደን ነበር ። ለአንተ መጠቆም የምፈልገው መሴ ፖይሮት አንድ ወንጀለኛ በሚመለከት በቅደመ ጥፋት መርሆዎች ወይንም ከግል ፍላጎት በሚመነጭ ለሀገሪቱ ሕጎችና ደንቦች ተገዥ ባለመሆን አታሰናብተውም ። የችግሩን ሥረ — መሠረት ማወቅና የወጣት ጋጠ - ወጡን ባህርይ ማረም አስፈላጊ ነው ። እነዚህም ዓላማዎች በአንተ ጊዜ የማይታሰቡና የማይታወቁ ስለነበሩ ለመቀበል እንደሚያዳግቱህ ፍጹም አልጠራጠርም — ። ”

“ ሥርቆት ሥርቆት ነው ” አለች ኮስተር ብላ ሀበርድ ። ኮሊንም ትዕግሥቱ — አልቆ ፣ በንዴት ገረመማት ። ፖይሮት በርጋታ ፡

“ አዎን ! አስተሳሰቦቹ ያለጥርጥር ጎላ ቀሮች ናቸው ። ነገር ግን በሚገባ ሀሳብህን ለመስማት ዝግጁ ነኝ ሚስተር ማከናብ ” አለ ።

ኮሊን በጣም ተገረመ ።

“ አዎን መሲ ፖይሮት ! ነገሩ እንኳ እንዲያው ዝም ብለህ የተና ናገርከው ነገር ነው ። አሁን ግን በጣም ቀላል ቃላትን በመጠቀም ጉዳዩን ለማብራራት እሞክራለሁ ። ”

“ አመሰግናለሁ ” አለ ፖይሮት በርጋታ ።

“ለማስረዳት ስል ፣ በዛሬው ምሽት ይዘህ በመምጣት ለሳሊፊንች በመለስካቸው ጥንድ ጫማዎች እጅምራለሁ ። የምታስታውስ ከሆነ የተሠረቀው የአንድ እግር ጫማ ብቻ ነው ፤ የአንድ እግር ብቻ ! ”

“ አዎን ! በጉዳዩ መደነቄን አስታውሳለሁ ” አለ ፖይሮት ።

ኮሊን ማከናብ ወደፊት አጎነበሰ ። የማይበገረው ነገር ግን ውብ ገጽታው ለማወቅ በነበረው ጉጉት ተለሳለሰ ።

“ አዎን ! ግን ምንም ዋጋ አልሰጠሽውም ነበር ። በጣም ከሚያረኩትና ከሚያስገርሙት ምሣሌዎች ማንም ሰው ቢሆን ከሚጓጓላቸው መካከል አንዱ ነው ። በግልጽ ይህ የገጠመን ጉዳይ ከሲንድሬላ ውስብስብ የተመሳሰለ ነው ። ምናልባት ይህ ልብ ወለድ ትረካ ለአንተ እንግዳ አይሆን ይሆናል ። ”

“ የፈረንሳይ ነው — አዎን ። ”

“ ሲንድሬላ ያቺ የማይከፈልባት አሰልቺ ሥራ ያጣመናት ልጅ ከሳቱ ተቀምጣለች ። እህቶቿ በውብ ልብሶቻቸው ተሸሞንሙነውና ተጊጠው ወደ ልዑሉ ግብዣ ሔደዋል ። የዓይን - እናቷ ሲንድሬላን ወደ ብጣው ሥፍራ ዘግይታ ትልካታለች ። በአፍላ ሌሊት ደማቅ ጨረቃ ላይ ነበረ ። ያ የበዓል ልብሷ ወደ ብጥስጣሽ ጨርቃ ጭርቅ ይለወጣል ። የሞት የሽረቷን እንዱን ነጠላ ጫማዋን ጥላ እግሬ አውጭኝ ብላ ትሸሻለች ። እዚህም ይህን ሁኔታ ከሲንድሬላ ለማወዳደር የሚያስችል ጭንቅላት አለን ። (ነገር ግን ሳናስበው ነው ።) ከ‘ዚህ ላይ ልሸቀት ፡ ቅንዓት፡ የበታችነት ስሜት እንዳለ እንረዳለን ፡ እንመለከታለን ። ልጅቷ ነጠላ ጫማ ትሠርቃለች። ለምን ? ”

“ ልጅቷ ? ”

“ ያው እንደምናውቀው አንዲት ልጅ ” አለ ኮሊን በማረጋገጥ ፡ “ ይህ በጣም ደካማ ሰው ሆነ ሰው እንኳ የሚሠወር አይደለም ” አለ ።

“ እውነት ? ኮሊን ! ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

“ ‘ባክህን ቀጥል ” አለ ፖይሮት በአክብሮት ።

“ ምናልባት ርሷ ራሷም ለምን እንዳደረገችው አታውቅም — ውስጣዊ ፍላጎቱ ግልጽ ነው ። ልዕልት መሆን ትፈልጋለች ። በሁሉ መታወቅና መደነቅ ትፈልጋለች ። ሌላው የማይናቅ ጉዳይ ነጠላ ጫማው የተሠረቀው ወደ ምሽት ግብግቡ ከምትሔደው ውብ ወይዘሪት ላይ ነው ። ”

የኮሊን ፒፖ እሳት ከጠፋ ብዙ ጊዜ ሆኖታል ። በመገረም ስሜት ከእጁ ላይ አወዛወዘው ።

“ እስኪ አሁን ደግሞ ሌሎቹን ጉዳዮች እንመልከት ። ሰዓይን የሚያስደስቱ አንዳንድነገሮችን ስለምትጠልፈዋ ጭልፊት ማለቴ ነው። ሁሉም ዕቃዎች ከሴቶች ፍላጎት የተያያዙ ናቸው ። የፖውደር መያዣ፡ ሊፕስቲክ፡የጆሮ ጌጥ ፡ የእጅ አምባር ፡ ቀለበት ናቸው ። እዚህ ላይ እጥፍ ድርብ ዋጋ ሚሰጣቸው ጉዳዮች ይታያሉ ። ልጂቱ መታወቅ ፡ መታየትን ትፈልጋለች ። ከዚያም በላይ መቀጣትም ትፈልግ ይሆናል — አንዳንዴ ወጣት ጋጠ — ወጦች እንደሚያደርጉት ማለት ነው ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱም ቢሆን ከተራ የወንጀል ሥርቆት የሚመደቡ አይደሉም። የነዚህ ነገሮች ዋጋ አይደለም የሚፈለገው ። እንዲህ ባሉ ተመሳሳይ መንገዶች ነው ደህና ኑሮ የሚኖሩ ሴቶችም ከመደብሮች በመሔድ ከፍለው ለመግዛት የሚችሏቸውን ዕቃዎች የሚሠርቁት ። ”

“ ደደብ ! ” አለች ሚስ ሀበርድ በቁጣ ” አንዳንድ ሰዎች በግልጽ እምነተቢሶች ናቸው ። ይኸው ነው በቃ ። ”

“ ነገር ግን ከተሠረቁት ነገሮች ውስጥ የአልማዝ ቀለበትም አለበት ” አለ ፖይሮት የሚስ ሀበርድን ተጨማሪ ሀሳብ ወደ ኑን በመተው ።

“ ያ እንኳ ተመልሷል ። ”

“ አሁን በእውነት ሚስተር ማክናብ የልብ ምት — መለኪያ የሴቶች መዋቢያ መጌጫ ነው ብለህ ታሳምነናለህ ? ”

“ ያ እንኳ ጠለቅ ያለ ቁም ነገር ያለው ነው ። ለሴቶች ፍላጎት ግድ የለሽ ነን የሚሉ ሴቶች ይህን ጉድለት በአንድ ሙያ ማረጋገጥ ይፈልጋሉ ። ”

“ የምግብ ማዘጋጃ መጽሐፉስ ? ”

“ የባልና የቤተሰብ ፡ የግል ሕይወት ምልክት ነው ። ”

“ የቦሪክ አሲዱ ዱቄትስ ? ”

ኮሊን በንዴት ፡ “ ወዳጄ መሴ ፖይሮት ማንም ቦሪክ አሲድ ፓወደር የሚሠርቅ የለም ! ለምን ይሁንኝ ብለው ?” ሲል ጠየቀ ።

“ ይህ ለራሴም ያቀረብኩት ጥያቄ ነው ። ያን መቀበል ይኖር ብኛል መሴ ማክናብ ። ለሁሉም ነገር መልስ ያለህ ይመስለኛል ። በል የአንድን አሮጌ የሱፍ ሱሪ መጥፉት ምክንያት አብራራልኝ ? አዎን የሱፍ ሱሪዎች ፡ እንደሚገባኝ —”

ለመጀመሪያ ጊዜ ኮሊን ትንሽ ጨነቀው ። አፈር በማለት ምራቁን ዋጥ አደረገ ።

“ ያን እንኳ አብራራዋለሁ ። ነገር ግን ከጉዳዩ የተያያዘ ወይንም ሌላ ችግር ሊኖር ይችላል ። ”

“ ከሀፍረት አዳንከኝ ። ”

በድንገት ፖይሮት ወደፊት በማጎንበስ የወጣቱን ጉልበት ቸብ አደረገው ።

“ ከሌላይቱ ተማሪ ጽሑፍ ላይ የፈሰሰው ቀለም ፡ እንዲሁም የተ ቆራረጠ የሐር ሻርፕ ነበረ ። እነዚህ ነገሮች ትንሽ አያሳስቡህም ? ”

ያ ርካታና የበላይነት የሚታይበት የኮሊን ሁኔታ ሊሆን የሚ ችል ነገር ግን ድንገተኛ ለውጥ አሳየ ።

“ አዎን ! የሚያሳስቡ ናቸው ። እመነኝ የሚያሳስቡ ናቸው። ትኩ ረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው ። ሕክምና ማግኘት ይገባታል ። ብዙ መዘግየት አይኖርበትም ። ነገር ግን የመድሐኒት ሕክምና መሆን አለበት ። ለፖሊስ የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም ። ትንሿ ምስኪን ሠይ ጣን ይህ ሁሉ ስለምን እንደሆነም ጭርሱኑ አታውቅም ። በችግሮች ተወጥራለች ። እኔ ያ . . . ”

ፖይሮት አቋረጠው ።

“ ማን መሆኗን ታውቃለህ ማለት ነው ? ”

“ አዎን ! ጠንከር ያለ ጥርጣሬ ነው ያለኝ ።

ፖይሮት የተነገሩትን ዋና ዋና ነጥቦች በድጋሚ እንደሚያስታ ውስ ሰው ሁሉ በማጉመትመት ፡

“ ከተቃራኒ ጾታ ምንም ዓይነት ግንኙነት መፍጠር ያልቻለች ወይዘሪት ። ዐይን አፋር ልጃገረድ ። ፍትር የያዛት ወይዘሪት ። አዕም ምሮዋ ለማንኛውም መልስ ምት የሚዘገይ ችሎታ ያላት ወይዘሪት ፣ በጣም ልሽቀት ያጠቃትና ብትኛ ወይዘሪት ፣ አንድ ወይዘሪት . . . ”

በሩ ተንኳኳ ። ፖይሮት ንግግሩን አቋረጠ ። በሩ እንደገና ተንኳኳ . . .

“ ይግቡ ! ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

በሩ ተከፈተ ። ሴሊያ አውስቲን ገባች ።

“ ታዲያስ ! ” አለ ፖይሮት ራሱን እየነቀነቀ ። “ በትክክል ። ወይዘሪት ሴሊያ አውስቲን ” አለ ።

ሴሊያ በድንጋጤ ዓይኖች ኮሊንን ተመለከተቸው ።

“ እዚህ ስለመኖርህ ፍጹም አላወቅሁም ” አለች ትንፋሿ ቁርጥ ፣ ቁርጥ እያለ ። “ እኔ የመጣሁት . . . የመጣሁት . . . ” አለች።

በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ወደ ሚስ ሀበርድ ሮጠች ።

“እባክሽን ፣ እባክሽን ለፖሊስ አታመልክቺ ! እኔ ነኝ ! እነዚህን ዕቃዎች እስከዛሬ ስወስድ የነበርኩ እኔ ነኝ። ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም ። ለምን እንደሆነም ማሰብ አልችልም ። ለማሰብም አልፈልግም ። በቃ እንደዚሁ እንዲህ ያለ ሱስ ያዘኝ ። ” ከኮሊን አጠገብ እየተቻኮሉ ለች ተቅበጠበጠች። “አሁን ምንነቴን ለይተሃል... እንደገና ከ‘ኔ እንደ ማትነጋገር ገብቶኛል ። በጣም አደገኛ ሰው መሆኔ ገብቶኛል ...”

“ ተይ ’ባክሽ ! ቅንጣት እንኳ ” አለ ኮሊን ። ያ አስደሳች ድምጹ፣ የጋለ ስሜት የሚደመጥበትና የባልንጀርነትም ነው ። “ ትንሽ ግራ መጋባት ይታይብሻል በቃ ! ነገሮችን በሚገባ ካለማየት ብቻ ! የቆየ በሽታ ነገር የነበረብሽ ነው የሚመስለው ። በ‘ኔ የምትተማመኚ ከሆነ ሴሊያ እውነቴን ነው የምልሽ ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እኔ ከችግሩ አወጣሻለሁ ። ”

“ አ ፣ ኮሊን - እውነትህን ነው ? ”

ሴሊያ ሽሽግ በሌለው የፍቅር ስሜት ተመለከተችው ።

“ ከመጠን በላይ በሚያስፈራ አኳኋን ሳስብ ነበር ። ”

ልክ አጎቶች ለትናንሽ የዘመድ ልጆች በሚያደርጉት መንገድ እጅዋን ጨበጣት ።

“መልካም ! ከአሁን ወዲያ ግን ብዙም የሚያስጨንቅ ሀሳብ የለም ። ” ከተቀመጠበት ቶነስቶ በመቆም የሴሊያን እጅ በክንዱ ውስጥ በማሳለፍ ሚስ ሀበርድን አተኩሮ ተመለከታት ።

“ አሁን ስለዚያ ፖሊስን የመጥራት ጅላጅል ሀሳብ የሚደረግ ውይይት እንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ ። ምንም ዋጋ ያለው ሀብትን በተመለከተ የተካሄደ ሥርቆት የለም ። በሴሊያ የተወሰደው ዕቃ በሙሉ ይመለሳል ። ”

“ የእጅ አምባሩንና የፖውደር መያዣውን መመለስ አልችልም ! ከውስጥ ለውስጡ ቱቦ ውስጥ ጥያቸዋለሁ ። ነገር ግን እዳዲስ መግዛት እችላለሁ ” አለች ሴሊያ በፍርሃትና በጥርጣሬ ።

“ የልብ - ምት መለኪያውንስ ? ” አለ ፖይሮት ። “ የት ነው ያስቀመጥሽው ? ” ሲል ደግሞ ጠየቃት ።

የሴሊያ ፊት ቀላ ።

“ እኔ ምንም የልብ — ምት መለኪያ አልወሰድኩም ። ከማይ ረባ አሮጌ የልብ—ምት መለኪያ እኔ ምን አለኝ?” የፊቷ ቅላትጨመረ። “ ከኤልሳቤጥ ወረቀት ላይ ቀለም የደፋሁትም እኔ አይደለሁም ። እኔ ፍጹም — እንደዚያ ዓይነት የምቀኝነት ሥራ ሠርቼም አላውቅ ።”

“ ነገር ግን እኮ የወይዘሪት ሆብሐውስን ሻርፕ ቆራርጠሽና ቀዳደሽ ትተሻል ። ”

ሴሊያ ተቁነጠነጠች ።

“ ያ የተለየ ጉዳይ ነው ። ማለቴ—ቫሌሪ ዋጋም አልሰጠችውም።”

“ የጀርባ ሻንጣውስ ? ”

“ የለም ! እርሱን እኔ አልቆረጥኩትም ። ”

ፖይሮት ከሚስ ሀበርድ ትንሽ ማስታወሻ የገለበጠውን የዕቃ ዝርዝር አወጣ ።

“ እስኪ ንገሪኝ ? ” አለ። “ አሁን እውነቱ መሆን ይኖርበታል ። ከነዚህ ውስጥ አንቺ በሀላፊነት የምትጠየቂበትና የማትጠየቂበት የትኛው ነው ? ”

ሴሊያ ዝርዝሩን ከተመለከተች በኋላ ወዲያው መልስ ሰጠች ።

“ እኔ ስለ ጀርባ ሻንጣው ፣ ወይንም ስለ ኤሌክትሪክ አምፑሉ ፣ ወይንም ስለ ቦሪክ አሲዱ ወይንም የመታጠቢያ ጨው ምንም የማውቀው ነገር የለም ፣ ቀለበቱ ርግጥ ሥህተት ነው ። በጣም ውድ መሆኑን ካወቅኩኝ በኋላ መልሼዋለሁ ። ”

“ ገባኝ ። ”

“ ምክንያቱም እውሸተኛ ሰው ላለመሆን ነበር ። ብቻ እኔ — ”

“ ብቻ ምን ? ”

ከዐይኖቿ ጭንቀት ለዐመል ያህል ኩሏታል ።

“ አላውቅም — በእውነት አላውቅም ! ግራ ስለተጋባሁ ብቻ ነው ። ”

ኮሊን ትዕዛዝ በሚሰጥ ሰው አኳኋን አቋረጣት ።

“ በጥያቄ ባታስጨንቃት ምሥጋናዬ ከፍተኛ ነው ። ስለዚህ ነገር እንደገና እንደማይነሳ አረጋግጥልሃለሁ ። ከአሁን ጀምሮ ራሴን ስለ ’ርሷ በሀላፊነት አቀርባለሁ ። ”

“ አ ! ኮሊን ስለ እኔ ላሳየኸው ርህራሔ አመሰግናለሁ ። ”

“ ስለ ራስሽ ሴሊያ ብዙ ነገሮችን እንድትነግሪኝ እፈልጋለሁ ? ስለልጅነት ሕይወትሽ ለምሳሌ ፣ አባትሽና እናትሽ አብረው ሲኖሩ በፍቅር ነበር ? ”

“ የለም ! በጣም በሚያስፈራ ሁኔታ ነበር — ከቤት — ”

“ በትክክል ! እና — ”

ሚስ ሀበርድ አቋረጠች ። ሀላፊነት በሚሰማው ሰው አገላለጽ ፡

“ እንግዲህ ሁለታችሁም ፡ ለጊዜው ይበቃናል ። ሴሊያ እዚህ ድረስ በመምጣት እውነቱን በመግለጽሽ ደስተኛ ነኝ ። ብዙ ሀሳብ ፡ ጥርጣሬና ፍርሃት በመፍጠርሽ ሀፍረት እንዲሰማሽ ያስፈልጋል ።ለጊዜው የምናገረው ይኸው ነው ። ከኤሌሳቤጥ ጽሑፍ ላይ ሆነ ብለሽ ቀለም ስለአለማፍሰስሽ የተናገርሽውን ቃል ተቀብዬዋለሁ ። እንደዚያ ያሉ ነገሮች ትሠሪያለሽ ብዬ ፍጹም አላምንም። አሁን አንቺና ኮሊን መሔድ ትችላላችሁ ። ለዛሬው ምሽት ከሁለታችሁም የሚበቃኝን ያህል ተነጋግሬያለሁ ። ”

በሩ ከበስተጀርባቸው እንደተዘጋ ሚስ ሀበርድ በረጅሙ ተነፈሰች።

“ አሺ” አለች ። “ ስለዚህ ነገር ምን ታስባለህ ? ”

ከሔርኩሌ ፖይሮት ዐይኖች ላይ መፍነክነክ ይታይባቸዋል ።

“ እንደሚመስለኝ — አንድ የፍቅር ገቢር — በዘመናዊ ስልት ሲተወን ስንመለከት ነበርን ” አለ ።

“ ሌላ ዘመን ሌላ ባህል ” በሚል አንድ ጥቅስ ፖይሮት አጉተመ ተመ ። “ በኛ ዘመን በወጣትነታችን ፣ ወጣቶች ለልጃገረዶች ፣ በመ ንፈሳዊ ምጥቀትና ሀሳበ—አንክሮ አምላክን የመሻት ማንኛውም ፍልስፍና (ቴአቲብሲ) ላይ የተጻፉ መጽሐፎችን ማዋስ ወይንም በሚ ተርሊንክ ‘ የፍቅር ወፍ ’ ቲአትር ላይ መወያየት ነበር ። እነዚህ ሁሉ በአዕምሯዊ ስሜትና መንፈሣዊ ብቃት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ ። በአሁኑ ጊዜ ግን ከአካባቢ ራስን አስማምተው ለመንዝ የማይችሉ ፍጡራንና የበታችነትና የበላይነት ስሜቶች ናቸው ወንድና ሴት ወጣ ቶችን በአንድነት የሚያቆሯኛቸው ” አለ ።

“ ያው የማይረባ ነገር ብቻ ነው ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

ፖይሮት ግን አልተቀበለውም ።

“ የለም ፣ ሁሉም ነገር የማይረባ አይደለም ። መሠረታዊ ሀሳቦቹ የማይናቁ ናቸው ። ነገር ግን አንድ ሰው እንደ ኮሊን እውነተኛ ወጣት ቱመራማሪ ሲሆን ማየት የሚችለው የስሜት ልሽቀትና ትምክህትን በተጨማሪም የሀመምተኛውን ደስታ ቢስ የቤት ሕይወት ብቻ ነው ።”

“ የሴሊያ አባት የሞተው‘ኮ ገና የአራት ዓመታት ሕጻን ሳለች ነው ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ እና ከመልካሟ ግን ከደደቢ እናቷ ዘንድ የሚያስከፋ የህጻንነት ጊዜ ነው ያሳለፈችው ። ”

“ ለወጣቱ ማክናብ እንዲያ ብላ አለመናገሯ ብልሀነቷን የሚ ገልጽ ነው ። እንዲሰማው የምትፈልገውን ብቻ ነው የምትናገረው ። በጣም ፍቅር ይዟታል ። ”

“ ይህን ማጭበርበሪያ ታምንበታለህ መሴ ፖይሮት ? ”

“ የለም ! ሴሊያ ሲንድሬላ ውስብስብ ነገር አለባት ወይንም የም ትሠራውን ነገር ሳታውቀው ነው የምትሠራው ብዬ አላምንም ። እንደ ሚመስለኝ እነዚህን የማይረቡ ነገሮች ሥርቆት የተያያዘችው የየዋ ሁን ኮሊን ማክናብ ትኩረት ለማግኘት ስትል ነው ። በዚህም የሚያ ረካ ውጤት አግኝታበታለች ። ዓይነ አፋር ውብ ልጃገረድ ሆና ብት ቆይ ኖሮ ምናልባት ዘወር ብሎም አያያት ነበር ። በ‘ኔ አስተያዬት እን ዲት ልጃገረድ የምትፈልገውን ሰው ለማግኘት የማታደርገው ነገር አይኖራትም ። ”

“ እኔ ይህን ያህል የማሰብ ችሎታ ይኖራታል ብዬ አልገምትም ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

ፖይሮት መልስም አልሰጠም ። ተኩላተረ ። ሚስ ሀበርድ ግን ቀጠለች ።

“ ሁሉም ነገር ጉም መዝገን ነው ! በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ መሲ ፖይሮት እንዲህ ባሉ ነገሮች ውድ ጊዜህን በማባከኔ ። ብቻ መልካም አጨራረስ ያለው ነገር ሁሉ መልካም ነው ። ”

“ የለም ፣ የለም ” በማለት ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ። “ ገና ከመጨረሻው የተዳረስን አይመስለኝም ። ከምሥሉ ፊት ለፊት የተጋረጠውን የማይረባ ጋሬጣ ጠርገን አጽድተናል ። ነገር ግን ያልያልተብራሩ ነገሮች አሉ ። እኔ ደግሞ ከ‘ዚህ ሥፍራ አንዳች በጣም ችግር የሆነ — በእውነት ችግር የሆነ ጉዳይ አለ ብዬነው ‘ማስበው ።”

የሚስ ሀበርድ ፊት እንደገና ተለወጠ ።

“ እንዴ መሲ ፖይሮት ? በእውነት እንደዚያ ታስባለህ ? ”

“ የለም ፣ የ‘ኔ የራሴ ሀሳብ ነው . . . ወይዘሪት ፖትሪሺያ ሌንን ባነጋግራት በጣም እደሰት ነበር ። ያን ተሠርቆ የነበረውን ቀለበት ማየት እፈልጋለሁ ። ”

“ ለምን ? በሚገባ ትችላለህ መሲ ፖይሮት። ወደ ታች እወርድና እንድትመጣ አደርጋለሁ ። እኔም ስለ አንድ ጉዳይ ሊን ባትሰንን ማነጋገር ‘ፈልጋለሁ ። ”

ትንሽ የጥርጣሬ ገፅታ የሚታይባት ፖትሪሺያ ሌን ብዙም ሳት ቆይ ወዲያው መጣች ።

“ ሚስስ ሌን ! ስለረበሽኩሽ በጣም ይቅርታ . . . ”

“ ምንም አይደል ፣ ሥራ አልነበረብኝም ። ሚስ ሀበርድ ቀለ በቱን ለማየት መፈለግህን ነግራኛለች ። ”

ከጣቷ አውልቃ ቀለበቱን ሰጠችው ።

“ በእውነት ትልቅ አልማዝ ነው ፣ ነገር ግን አሠራሩ ጥንታዊ ነው ። የእናቱ የቃል ኪዳን ቀለበት ነበር ። ”

“ እናትሽ አሁንም በህይወት አሉ ? ”

“ የለችም ። ሁለቱም ወላጆቼ ሞተዋል ። ”

“ የሚያሳዝን ነው ! ”

“ አዎን ፣ ሁለቱም በጣም ጥሩ ሰዎች ነበሩ ። ነገር ግን እኔ መቅረብ የሚገባኝን ያህል አልቀረብኩኝም ። አንድ ሰው የሚሰማው መቼም ካለፈ በኋላ ነው ። እናቱ አንዲት ሣቂታ ፣ መልከ መልካም ጥሩ ጥሩ ልብሶችንና በጋራ መደሰትን የምትወድ ልጅ መውለድ ፈለገች ።በኋላ ግን አርኪዮሎጂ ለማጥናት በወሰንኩኝ ወቅት በጣም ተናደደች።”

“ ወትሮም እንደዚህ ቆራጥ ነበርሽ ? ”

“ ይመስለኛል ! የህይወትን ዘመን እጥረት ለተረዳ ሰው አንድ ጠቃሚ ነገር ሠርቶ ማለፉ አስፈላጊ ነው ። ”

ፖይሮት በሀሳብ ተወጥሮ አተኩሮ ይመለከታታል ።

እንደርሱ ግምት ፖትሪሺያ ሌን ወደ ሠላሣዎቹ ትሆናለች ። በግ ድየለሽነት ከተመረገው ሊፕስቲክ በስተቀር ምንም የውበት ቅባቶ ችን አልተጠቀመችም ። ቡና ብረት ቀለሙ ወጉሯ ከግንባሯ ተሰብስቦ ወደ ኋላ ተበጥሮ በባለሙያ ተሠርቷል ። እነዚያ አስደሳች ብሩህ ሰማ ያዊ ዐይኖች ከመነጽሩ ዘልቀው በአንክሮ ይመለከታሉ ።

“ ያንተ ያለህ ፈገግታ እንኳ የላትም” አለ ፖይሮት በስሜት ። “ ደግሞ ልብሶቿ ! ምንድነው የሚሉት ? ኋላ — ሽብሽብ — ቀርፋፈ ነው? ትክክል ነኝ ። እንደዚያ ነው በደንብ ነው የሚገልጸው ! ”

የተነገረው በሙሉ ሥህተት ነበር ። ፖትሪሺያ ለጆሮ ትንሽ አሰ ልቺ የሚመስል ፣ የዘመኑ ልጆች ልሳን አሰባበር ነበራት ። “ በጣም ብልህና ሥልጡን ልጅ ናት ” አለ ለራሱ ። “ የሚያሳዝነው ግን ይኸ ለዛዋ በየዓመቱ እየተለወጠ መሔዱ ነው ! በተለይ በርጅና—” አዕምሮው በትጽበት ከክብርት መስፍኒቱ ቬራ ሮዛኮፍ ትውስት ላይ ዐረፈ ። በእርጅና እንኳ ምን ዓይነት ብርቅ ግርማ ሞገስን መታ ደል ነው ! እነዚህ የዛሬዎቹ ወይዛዝርት ግን — ። ”

“ ምናልባት ስላረጀሁ ይሆናል ” አለ ፖይሮት ለራሱ ። “ ይህቺ እጅግ ጥሩ ልጅ እንኳ ለአንዱ እውነተኛ ኮከቡ ትሆን ይሆናል” አለ ። ይህን ሀሳቡን ግን ተጠራጠረው ።

ፖትሪሺያ በሚያሳዝን አኳኃን ፣ “ በቢስና በወይዘሪት ጆሀ ንስተን በደረሰባቸው ጉዳይ በጣም ነው ያዘንኩት ። ያን አረንጓዴ ቀለም መጠቀማቸው ሆነ ብለው ልክ ኒጌል የሠራው ለማስመሰል ነበር ። ነገር ግን እውነቴን ነው የምልህ መሴ ፖይሮት ኒጌል እንደ ዚያ ያለ ሥራ ፍጹም አይሠራም ” አለች ።

“ እንዲያ ነው ! ” በማለት ፖይሮት በመገረም ተመለከታት ። ፊቷ ቀልቷል ። ለመናገር የምትፈልግ ትመስላለች ።

“ ኒጌልን ለመረዳት ቀላል አይደለም ። ” አለች በየዋህነት መን ፈስ ። ቀጥላም “ ህጻን በነበረበት ወቅት ያሳለፈው አስከፊ ህይወት ነበር ” አለች ።

“ ያንተ ያለህ ደግሞ ሌላ ትረካ ። ”

“ አልተስማኝም ይቅርታ ! ”

“ ምንም አይደል ። ስትናገሪ የነበርሽው — ”

“ ስለ ኒጌል ነበር ። አስቸጋሪ የነበረ ስለመሆኑ ነው ። ማንኛውንም ዓይነት ሥልጣን የመጋፋትና የመቃወም ሁኔታ ይታ ይበታል ። በእውነት በጣም ጎበዝ ብልሀ አዕምሮ አለው ። ነገር ግን አልፎ አልፎ የማይጠበቅ እንግዳ ጸባይ ማሳየቱን አልከደም ። በቃ አለ አይደል ? ንቀት ማሳየት ይወዳል ። ስለሚስማው ነገር ለማ ብራራት ወይንም ስለ‘ራሱ ለማስረዳት ትዕቢቱ ያስቸግረዋል ። ከዚህ ሥፍራ ያለው ሰው ሁሉ ይህን ቀለም ያፈለስከው አንተ ነህ ቢለውም ፍጹም ብግር አይልም ። በቃ ‘ ከፈለጉ የራሳቸው ጉዳይ ነው ’ ብሎ ነው የሚተወው ። እንዲህ ዓይነቱ ጸባይ ደግሞ የጅልነት ነው ።”

“ አዎ በርግጥ ሰው ሊረዳው ያዳግታል ። ”

“ የሆነ ትምክህት ነገር ይመስለኛል ። ምክንያቱ ሁልጊዜም ቢሆን ስለማይረዱት ይመስለኛል ። ”

“ ለብዙ ዓመታት ታውቂው ነበር ? ”

“ የለም ፡ ለአንድ ዓመት ብቻ ነው የማውቀው ። ከሉቨር የገጠር መገናኛ በገብኝት ላይ ሆነን ነው የተገናኘነው ። ሀይለኛ ጉንፋን ይዞት ነበር ። በኋላ ግን የሳምባ ምች ሆኖ ተገኘ ። ሳሲታምመው ነበር ። ሁሉም ነገር በጣም የሚያበሳጨው ለ‘ራሱ ጤንነት ተገቢውን ጥንቃቄ የማያደርግ ሰው ነበር ። በአንዳንድ መንገዶች ነጻ ሰው ከመ ሆን ይልቅ እንደ ህጻን የሚንከባከበው ሰው ይፈልጋል ። ”

ፖይሮት በረጅሙ ተነፈሰ ። ሳያስበው ራሱን ስለ ፍቅር ጉዳይ ስልቹ ሆኖ አገኘው ። . . . በመጀመሪያ ላይ እንደሚያማምሩ ውብ ውሻ ዐይኖች ስትቁለጨለጭ የነበረችዋ ሴሊያ ነበረች ። አሁን ደግሞ ይህችን የተቀደሰችዋን ማርያም የመሰለች ፖትሪሺያን ተመለከተ ። አምን! ፍቅር መኖር አለበት ! ወጣቶች በጥንድ መሆን ተገቢያቸው ነው ። ነገር ግን ፖይሮት ያ ጊዜ አልፎበታል ። ተነስቶ ቆመ ።

“ ይህን ቀለበትሽን ከኔ ዘንድ እንዲቆይ ትፈቅጂልኛለሽ ወይ ዘሪት ? ነገ ካሰምንም መዘግየት እመልሰዋለሁ ። ”

“ ከፈለከው ትችላለህ ” አለች የመገረም አኳኋን የሚታይባት ፖትሪሺያ ።

“ በጣም ጥሩ ልጅ ነሽ ። አንድ ነገር ላሳስብሽ እወዳለሁ ” ‘ባክሽን እመቤት ለራስሽ ጥንቃቄ ይኑርሽ ” አለ ።

“ ጥንቃቄ ? በምንድነው የምጠነቀቀው ? ”

“ ባውቀው ደስ ባለኝ ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ። አሁንም አሁንም በጣም ሀሳብ ያስጨነቀው ይመስላል ።

— 6 —

በተከታዩ ቀን ሀበርድ በሣር በቅጠሉ ሁሉ መናደድና መጨስ ጀመረች ። የነቃችው ትንሽ ቀለል ብሏት ነበር ። በቅርቡ በተፈጁሙት ነገሮች ከመዋከብ ሀሳብ ትንሽ አገግማለች ። ጅላጅሏ ልጃገረድ ፡ በዚያ ጅላጅል ስልት የምትዘብነዋ (ለሚስ ሀበርድ የአፍታ እንኳ ትዕ ግሥት በማይሰጣት) ወይዘሪት ናት ለዚህ ሁሉ ነገር በሀላፊነት ትጠየቅ የነበረችዋ ። ከአሁን ወዲያ ግንሥርዓት መስፈኑ አያቀርም ።

በዚህ የሚያረጋጋ ልበ ሙሉነት ለቁርስ በመውረድ ላይ እያ ለች ይህ አዲስ ሠላም የሚያናጋ ነገር ገጠማት ። ተማሪዎቹ ይህን ልዩ ማለዳ በየግላቸው ፡ እንደየራሳቸው መንገድ ለመሞከር መርጠ ዋል ።

ሚስተር ቻንድራ ላል በኤልሳቤጥ ጽሑፍ ላይ የተፈጸመውን ሸር ስለሰማ በጥርጣሬና በፍርሃት ከሌላው ጊዜ በተለየ መንገድ እየተቅ በጠበጠ ይናገር ነበር ። “ ይህ ጭቆና ነው ” አለ ። ለመስማት በሚያ ስቸግር ችኮላ ፡ “ የውጭ ዝርያዎች ላይ ሆነ ተብሎ የሚፈጸም ጭቆና ነው ። ንቀትና ኋላቀር እምነት ፡ የቀለም ልዩነት ነው ። ይኸው በግ ልጽ ፡ በተጨባጭ ይታያል ” አለ ።

“አሁን ሚስተር ቻንድራ ላል ” አለች ሚስ ሀበርድ ቅጭም ብላ። “ እንደዚያ ዓይነቱን ነገር ለመናገር ፍጹም አትችልም ። ማንም ለምን እንደተደረገና ማን እንዳደረገው የሚያውቅ የለም ” አለች ደግማ ።

“ እንዴ ግን ’ኮ ሚስ ሀበርድ ሴሊያ ወዳንቺ ዘንድ የመጣች መስሎኝ ነበር ” አለች ጄን ቶሚሊንሰን ። “ የ’ርሷ አጥጋቢና በቂ መስሎኝ ነበር ። ሁላችንም በጣም ልናስብላት ይገባናል ። ”

“ እንደዚህ ያለህ ወራዳ ሰው መሆን አለብሽ ጄን?”ስትል ጠየ ቅች ቫሌሪ ሆብሐውስ በንዴት ።

“ እንደዚህ መናገሩ ትክክል አይመስለኝም ። ”

“ አጋልጣለች ! ” አለ ኔጌል ስቅቅ እያለና እየተሰማው። ቀጥ ሎም “እንዲህ ያለ ወራዳ የሆነ ቃል ! ቃሉ ራሱ ወራዳ ነው ! ” አለ ።

“ ለምን እንደሆን አልገባኝም ። ይኼ ‘ ጥፋትህን በሕዝብ ፊት አጋልጥ ’ የሚለው የአክስፎርድ የእምነት ሀራጥቃ (አንጃ) የሚጠቀም በት ቃል ነው ። በተጨማሪ — ”

“ ስለእግዚአብሔር ! ታዳያ ይህን የአክስፎርድ የእምነት ሀራጥቃ በቁርስ ፈንታ ማኘክ አለብን ? ”

“ ምንድነው ይኼ ሁሉ እንዴ ? ሲሊያ ናት ይህን ሁሉ ነገር የም ትሠራርቅ ነው የምትደው ? ለዚያ ነው ከቁርስ ላይ ያሶተገኘች ? ”

“ እኔ ምንም አልገባኝም ! ” አለ ሚስተር አኪቦምቦ ።

ማንም ያብራራለት ሰው አልነበረም ። ሁሉም የራሱን ሀሳብ ለመሰንዘር ፍርሃትና ጥርጣሬ ይዞታል ።

“ ምስኪን ህፃን ! ” ሲል ሊን ባትሰን ቀጠለ ፣ “ የገንዘብ ችግር ወይንም የመሳሰለው ነገር ያዟት ይሆን ? ” አለ ።

“ እኔ ፍጹም አልተደነቅሁም ታውቃለህ ? ” አለች በቀስታ ሳሊ ። “ ሁልጊዜም ቢሆን እንዲህ መሳዩ ሀሳብ ነበረኝ . . . ” አለች ።

“ ሲሊያ ናት ከጽሑፍሽ ላይ ቀለም ያፈሰሰች ነው የምትሉኝ ? ስትል ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ቡተገረመና ባላመነ ሰው አኳኋን ጠየ ቀች ። “ በጣም የሚያስደንቅና ለማመን የሚያስቸግርም ነበር ። ”

“ ሲሊያ ከጽሑፍሽ ላይ ቀለም አላፈሰሰችም ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ እንዳው ይህን ንትርካችሁን ሁላችሁም ብታቆሙ እንዴት በታደልኩ ። ሁሉንም በጥሞና በኋላ ላስረዳችሁ ብዬ ነበር ነገር ግን — ”

“ ነገር ግን ጄን ከበሩ ውጭ ቆማ ከትላንትና ወዲያ ስታዳ ምጥ ነበር ” አለች ቫሌሪ ።

“ የለም ! አላዳመጥኩም ። ለመሔድ ስል ነው ። ”

“ በቃ እንግዲህ ቢስ ” አለ ኒጌል ። “ ቀለሙን ማን እንደደፋ በደንብ ታውቂያለሽ ። እኔ ግን ያ ሸረኛ ኒጌል ከዚያች ትንሽ የመድሐኒት ቢልቃጥ ነው ቀለሙን ያፈሰሰ የሚመስለኝ ። ”

“ እ’ሱ አይደለም ። ውሸቱን ለማስመሰል ነው ! እንዴት እን ደዚህ ደደብ ትሆናለህ ? ”

“ ጅግና ሆኜ ለአንቺ መመኩቱ ነበረ ፖትሪሽያ ። ማን ነበር ትላንት ቀለሜን የተበደረው ? አንቺ ነሽ ? ”

“ እኔ ሊገባኝ ፍጹም አልቻለም ! ” አለ ሚስተር አኪቦምቦ ።

“ አንተ ከጉዳዩ ለመግባት አትፈልግም እይደለም ? ” አለች ።

“ አንተን ብሆን በፍጹም አልሳተፍበትም ነበር ። ”

ሚስተር ቻንድራ ላል ተነስቶ ቆመ ።

“ ማኡ ፣ ማኡ ለምን ተቋቋመ ብላችሁ ነው የጠየቃችሁ ? ግብፅ ለምን የስዊዝ ቦይ ተቃውሞ ኖራት ነው ጥያቄው ? ”

“ ገደል ግቡ ! ” አለ ኒጌል በቁጣ መለየውን ከቡናው ስኒ ማስ ቀመጫ ላይ በመወርወር ። “ በመጀመሪያ የእክስፎርዱ የእምነት ሀራጥቃ ፣ አሁን ደግሞ ፖለቲካ ! ቁርሱን ላይ መሐይሜ ነው ! ”

ወንበሩን በንዴት ከሥፍራው በማሽቀንጠር ከፍሉን ለቆ ወጣ።

“ ብርድ ነው ። ኮትህን ልበስ ፣ ” በማለት ፖትሪሺያ ከኋላው እየተቻኮለች ተከተለችው ።

“ ቋ ፣ ቋ ፣ ቋ ” አለች ቫሌሪ ። “ ዶሮ ላባ ታወጣና ክንፎቿን ሳትዘገይ ትዘረጋዋለች ! ”

ፊረንሣይቷ ወይዘሪት ጂኔቪይቭ ከሌሎቹ በእኩል ያረጃ በፍጥነት በእንግሊዝኛ ቋንቋ መነጋገር የሚትችለዋ ተማሪ በሬኒ የሚንሾካሾክላትን ማብራሪያ በመስማት ላይ ነበረች ። አሁን በችኩላና በፍጥነት ፊረንሣይኛውን ታዘንበው ጀመር ። በዚሁ ቋንቋዋ እንዲህ ስትል አንባረቀች ።

“ እንዴ ! ተረጋገጠ ? ያቺ ትንሿ ሴትዮ ናት ያን የፓውደር መያዣ የሠረቀች ? ምላሌ ሆነች በለኛ ! ፖሊስም ተጠርቷል ። እንዲህ ላለች የማትረባ ልጅ እኔ አልከራከርም . . . ”

ኮሊን ማክናብ የሚናገረው ነገር እንዲያመጥለት ለጥቂት ጊዜ ጥረት ሲያደርግ ቆየ ። ነገር ግን ያ የነረነነ ቀርፋፋ ድምፅ የበለጠ በሚጨጨሁት ደምፆች ተዋጠ ። ያን የታላቅነትና የሸንጋይነት ሁኔታውን በሙተው ፣ ያን ትልቅ ጡጫውን ከጠረጴዛው ላይ አሳረፈው ። ሁሉም ፀጥ ረጭ አለ ። የማልማላቱ ጠርሙስ ተንከባሎ ከጠረጴዛው በመንከባለል ተሠበረ ።

“ እስኪ አፋችሁን ያዙ ! ሁላችሁም ! አንድ ጊዜ የምላችሁን ስሙኝ ? እንዲህ ያለ መሀይምነትና ድንቁርና ፣ ክፋት ፍፁም ሰምቼም

አላውቅ ! እንዳው ስለሳይኮሎጂ ጭላንጭል ሀሳብም እንኳ የላችሁም ! ልጂቷ መወገዝ የለባትም ! እውነቴን ነው የምላችሁ ። በክፍተኛ የስሜት ቀውስ ውስጥ ስላለች ርተቻለ ክፍተኛ ክብካቤ ሳይለያት ሕክ ምና ማግኘት አለባት ። — ካልሆነ ደግሞ ህይወቷን በሙሉ ባልተ ደላደለ ሁኔታ ታሳልፋለች ። ማስጠንቀቂያ ነው የምሰጣችሁ ። ክፍ ተኛ ክብካቤ — ቢቃ የሚያስፈልጋት ይኼ ብቻ ነው ። ”

“ ከሁሉ በፊት ግን ” አለች ጂን ፡ ጥርት ባለና ርካታ በሚታ ይበት አገላለጽ ፡ “ ምንም እንኳ በርህራሔው ላይ የምስማማበት ብሆንም እንዲያ ላለው ነገር ምህረት ማድረግ ይገባናል ? ለሥርቆት ማለቴ ነው ። ”

“ ሥርቆት ? ” አለ ኮሊን ። “ይህ ሥርቆት አይደለም ! ኮውኝ ወዲያ ! አሁንስ ሁላችሁም አስጠላችሁኝ ። ”

“ የምታስገርም ነገር ናት ኮሊን ! ” አለች ቫሌሪ ፈገግ ብላ ።

“ በሰው ልጅ ጭንቅላት የምትገረሚ ከሆንሽ አምን ። ”

“ በርግጥ የኔ የሆነ ምንም ነገር አልወሰደችም ” አለች ፡ ጂን ። “ ነገር ግን አይመስለኝም ” በማለት አስተያዬቷን ሰጠች ።

“ የለም ፡ ካንቺ ምንም ነገር አልወሰደችም ፡ ” አለ ኮሊን በቁጣ እየገረመማት ። “ እንደዚያ ማለት ምን ማለት መሆኑን ብትረጂ ምናልባት ይህንንም ያህል እንኳ አይስማሽም ነበር ” አለ ።

“ በእውነት አልገባኝም — ”

“ ምን ማለትሽ ነው ፈጠን በይ ጂን ?” አለ ሊንትሰን ። “ አሁን መነታረኩንና መጨቃጨቁን እንተወው ። እኔም አንቺም መዘጣየታችን ነው ። ”

ሁለቱም በእንድነት ወጡ ። “ሴሊያን የበለጠ ጥረት እንድታደ ርግ ንገሪያት ? ” አለ በቀስታ ድምፅ ።

“ እንዴ ቲቃወሞዬን ማሰማት ‘ፈልጋለሁ ” አለ ሚስተር ቻንድራ ላል ። “ ቦሪክ ፖውደር ለዓይኖቹ ለነዚህ በጥናት ብዛት ለሚ ጨናበሱት አስፈላጊ ነው ፡ ነገር ግን ተወሰደብኝ ” ።

“ አንተም ትዘገያለህ ሚስተር ቻንድራ ላል ” አለች ሚስ ሀበርድ ኮስተር ብላ ።

“ ፕሮፌሰሩ በሰዓቱ አይመጣም ” አለ ፊቱን የከበደው ቻን ድራ ላል ። ነገር ግን ወደ በሩ መጓዙን አላቋረጠም ። “ይገርማል ! ብዙ

የሚያመራዎ ጉዳዮችን ስጠይቀው ከመሬት ተነስቶ የሚቆጣና የሚናደድ ሰው ነው — ። ''

'' ስለዚህ የፓውደር መያዣ መወያየቱ ለምንም አይጠቅመን '' አለች ጄኔቬቭ ።

'' እንግዚህኛ መነጋገር አለብሽ ጄኔቬቭ — ወደ ፊረንሣይ ተመልሰሽ እንግሊዝኛ መናገር ብትፈልጊ ይቸግርሻል ። ደግሞ በዚህ ሣምንት ሙጨረሻ ልዩ ምግብ አዘሽ ነበር ፣ አልከፈልሽኝም ። ''

'' ይቅርታ ፣ የገንዘብ መያዥያዬን አውን አልያዝኩም ። ዛሬ ማታ — ፈጠን በል ሬኒ በጣም ረፍዶብናል ። ''

'' እባካችሁን '' አለ ሚስተር አኪቦምቦ በትህትና እየተሞለከተ ፣ '' ሊገባኝ አልቻለም '' በማለት ተመለከተችው ።

'' ና አኪቦምቦ '' አለች ሳሊ '' ሁሉንም ጉዳይ እኔ አስረዳ ሃለሁ ወደ ቲቋሙ እየሔድን '' እግረመንገዳችንን አለች ።

ለሚስ ሀበርድ ራሷን በመነቅነቅ እያረጋገጠችላት ግራ የተጋባውን አኪቦምቦን ይዛ ከክፍሉ ወጣች ።

'' በሞትኩት ! '' አለች ሀበርድ በረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ። '' እስኪ ለምን ብዬ ነው እንዲህ ካለ ሥራ ገብቼ አንጀቴ 'ሚያ ረው ? ''

አብሯት የቀረችዋ ቫሌሪ በወዳጅነት መልክ ፈገግ አለች ።

'' አታስቢ እንዬ ! '' አለች ። '' እንዲህ መሆኑን ወድጄዋለሁ ፤ ሁሉም ብጥብጡ ወጣ አይደል ? ''

'' በጣም ቲደንቂ ነበር ማለት እችላለሁ ። ''

'' ሴሊያ ሆና ቲገኝች አይደል ? ''

'' አዎን ፤ አላወቅሽም ነበር ? ''

ቫሌሪ በሀሳብ በተዋጠ ሰው አነጋገር ፣ '' እንዲያውም ፣ ግልጽ ነበር ፣ እንደዚያ ማሰብ ነበረብኝ '' አለች ።

'' እስካሁን ስታስቢ ነበርሽ ? ''

'' አንድ ሁለት ነገሮች አስገርመውኝ ነበር ። ያም ሆነ ይህ ከም ትፈልግበት ሥፍራ ኮሊንን አግኝታዋለች ። ''

'' አዎን ፤ ስህተት መሆኑን ከማሰብ 'ሚያግደኝ ነገር የለም ። ''

“ መቼም ጠመንጃ ያነገበ ሰው አትፈልጊ ! ” በማለት ቫሌሪ ከት ብላ ሣቀች ። “ ለካስ የሥርቆት ሱስ በሽታ ነው ሲጫወትብን የቆየው ? አታስቢ እንዴ ። ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ። ሴሊያ የፓው ደሩን መያዣ ለጂኔቬብ እንድትመልስላት አግባቢያት ። በስተቀር ከገበታ ላይ ሠላም ማግኘት አንችልም ! ”

ሚስ ሀበርድ በረጅሙ ተነፈሰች ።

“ ኒጌል የሲኒውን ማስቀመጫ ሰንጥቆታል ፣ የማርማላቱም ጠርሙስ ተሠብሯል ። ”

“ የተረገመ ማለዳ ነው ፣ አይደለም ? ” አለችና ቫሌሪ ወጥታ ሔደች ። ሚስ ሀበርድ ከአዳራሹ ድምጿ ይሰማል ።

“እንደምን አደርሽ ሴሊያ ? ሁሉም ነገር ጸድቷል ። ለሁሉም ነገር ይቅርታ ሊደረግ ነው — በተቀደሰች ሠዓ ጂን አማካኝነት ተቃልሏል ። ኮሊን ግን ባንቺ ስም እንደ አንበሳ ሲያገሳብን ነው የቆየው ” አለች ።

ሴሊያ ወደ ምግብ አዳራሹ መጣች ። ዓይኖቿ በልቅሶ ቀልተዋል ።

“ አ ፣ ሚስ ሀበርድ ! ”

“ በጣም ዘገየሽ ሴሊያ ። ቡናው ቀዝቅዟል ፣ በዚህ ላይ ብዙም የሚበላ ነገር አልተረፈም ። ”

“ ሌሉቹን ማየቱን አልፈለኩም ! ”

“ ገብቶኛል ። ነገር ግን በቅርቡ ወይንም ዘግይቶ መገናኘታችሁ አይቀር ። ”

“ አምን ፣ አውቃለሁ ። ነገር ግን ያሰብኩት — በዚህ ምሽት የቀለለ ይሆናል ብዬ ነው ። በርግጥ ከዚህ አልቆይም ። በሣምንቱ መጨረሻ እሔዳለሁ ። ”

ሚስ ሀበርድ ኮስተር አለች ።

“ ለዚያ የሚያደርሰን ነገር ያለ አይመስለኝም ። መቼም ትንሽ የማያስደስት ነገር መኖሩ የሚጠበቅ ነው ። ያም ቢሆን ምንም አይደል ። — በአጠቃላይ በጣም ርህሩህ ወጣቶች ናቸው ። በርግጥ የወሰድሽውን ዕቃ ተመን በተቻለሽ ፍጥነት መመለስ አለብሽ ! ”

ሴሊያ ንግግሯን አቋረጠቻት ።

“ አምን ፣ ይሽው ቼክ አለኝ ። ያንን ልነግርሽ ነው የፈለኩት ። ” ወደታች በማቅርቀር ተመለከተች ። ቼክና ኤንቬሎፕ ከእጅዋ ይዛለች ።

“ምናልባት ከወጣሁ ካላገኘሁሽ ብዬ ነው ። በጣም ማዘኔን የሚገልጽ ደብዳቤና ቼኩንም ለሒሳብሽ እንዲያመች በእንድነት ትቼልሽ ልሒድ ነበር ። ነገር ግን የብዕሬ ቀለም አልቋል ” አለች ።

“ ገርገሩን ማዘጋጀት አለብን ። ”

“በተቻለኝ ፣ አዘጋጅቻለሁ ። ነገር ግን አዲስ ዕቃ ገዝቼ መስጠት ወይንም ገንዘቡን መክፈል ፣ የቱ እንደሚሻል አላውቅም ።”

“ አስብበታለሁ ። አሁኑኑ መወሰኑ ትንሽ ይቸግራል ። ”

“ ቼኩን አሁኑኑ ብሰጥሽስ ? በጣም ይቀለኝ ነበር ። ”

ካለ ንም መግደርደር ፣ “እውነት ? እንዴ ! ላንቺ የሚቀልሽ እስከሆነና ምናለበት ? ” አለች ሚስ ሀበርድ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የተዘጋጀ ገንዘብ ከእጃቸው ስለማይኖር እንደዚያ ማድረጉ የተሻለ መሆኑን በማስታወስ ። በተጨማሪ ከሚስ ኒኮሊተስ እንዳትጣላ ጀኔቪይቭንም ያበራርዳታል ። (ብቻ ችግር መኖሩ አይቀርም ።)

“ ጥሩ ይሁን ” አለችና ከገርገሩ ላይ ዓይኖቿን ወረወረች ። “ አሁኑኑ ይህን ያህል ማለቱ ግን ይከብዳል — ”

ሴሊያ በትህትና ፣ “ እንዳው በማምት የመሰለሽን ያህል በቼክ ልከፈልሽና ከተረፈ እንድትመልሺልኝ ወይንም ካነሰ እንድጨምር ልሽ እናደርጋለን ” አለች ።

“ በጣም ጥሩ ” አለችና ሚስ ሀበርድ ለጊዜው ይሆናል ብላ የያ ትገ ተውን የገንዘብ ጣሪያ ስትነግራት ፣ ሴልያም ባለማቅማማት ወዲያው ቲስማማች ። ቼኩን ከፈተችው ።

“ እንዴ ብዕር የለኝም ና ! ” በማለት የተለያዩ ነገሮች ከተደረ ደሩበት መደርደሪያ ሐዲች ። “ ከዚያም ሥፍራ ከኒጌል አረንጓዴ ቀለም በስተቀር ሌላ የለም ። በቃ እጠቀምበታለሁ ። ኒጌል ግድ የለ ውም ። አንድ ቢልቃጥ ኩዊንክ እገዛለሁ ፣ ስወጣ አስታውሽኝ ። ”

ብዕሯን ሞልታ በመመለስ ኮ ቼኩን ላይ ፃፈች ።

ለሚስ ሀበርድ ፣ እየሠጠቻት ሠዓቷን ተመለከተችው ።

“ እዘገያለሁ ። ለቁርስ ባልቆይ ይሻላል ። ”

“ አሁን አንድ ነገር ብትቀምሺ ሳይሻል አይቀርም ሴሊያ ? ትንሽ ዳቦና ቅቤ እንኳ ቅመሽ እስቲ ? በባዶ አፍ መውጣት ጥሩ አይደለም ። ምነው ፣ ፆ ን ሆነሻል ? ”

ጀሮኒሞ ማሊያናዊው አሽከር ወደ ክፍሉ በመግባት በእጁ ምል ክት መልዕክት ማስተላለፍ ጀመረ ። ያ መጣጣ የጠጣ መሳይ ፊቱ የሚያሥቅ ገጽታ ነበረው ።

“ እመቤቱ መጥተዋል። ሊያነጋግሩሽ ይፈልጋሉ” አለ። በመጨ ረሻ ላይ በምልክት ፣ “ በጣም ነው የተናደዱት ” ሲል ነገራት ።

“ እመጣለሁ ” አለች ።

ሴሊያ ገና ዳቦውን ሶመጎራረስ ስትዘጋጅ ሚስ ሀበርድ ክፍሉን ጥላ ወጣች ።

ሚስ ኒኮላቲስ በቁጣ ከመካነ —እንሠግት በዎግብ ወቅት እንደ ሚያንራ ነብር ከክፍሏ ውስጥ ላይ ፣ ታች ትላለች ።

“ ይኸ የምሰማው ግንድነው ? ” ስትል አምቧረቀች ። “ፖሊስ ጠርተሻል ? ለ‘ኔ ምንም ሳታማክሪ ? ለመሆኑ ማን ነኝ ብለሽ ነው የምታስቢው ? አምላኬ ! እንዳው ማነኝ ብላ ታስብ ይሆን ? ”

“ የለም ፤ ከፖሊስ ዘንድ አልሔድም ። ”

“ ውሸታም ነሽ ። ”

“ በቃ ፤ በይ ሚስ ኒኮሊቲስ ! እኔን እንደዚያ ብለሽ መናገር አት ችይም ! ”

“ በቃ ፡ በቃ ቲይው ፣ የለም ! እኔ ነኝ ሥህተተኛዋ ፣ አንቺ አይ ደለሽም ። ይበለኝ ። አንቺ የምትሠሪው በሙሉ ትክክል ነው ። ተደ ፍሮ ከማያውቀው ሆስቴል ፖሊስ ትጠሪብኛለሽ ! ”

“ ለመጀመሪያ ጊዜ ማለት ነው ? ” አለች ሚስ ሀበርድ ሌሎች የከፉ አጋጣሚዎችን በማስታወስ ። “ ምን ላድርግ አንድ በማጭበር በር የሚኖር የሀንድ ተማሪና አምላክ የተጣላው በሀሰት ስም የሚጠ ቀም ኮሚኒስት ሰባኪ አሉ — እና — ”

“ እና ! ታዲያ የኔ ጥፋት ነው ? ንገሪኝ እስኪ ! በሀሰት መታወቂያ መጥተው እየዋሹኝ በግድያ ወንጀል ፖሊስን ለመርዳት ቢፈልጉ የኔ ጥፋት ነው? ደግሞ የተሰቃየሁ አንሶኝ መፍራትና መጠበብ? ... ሆ !”

“ እኔ ምንም እንደዚያ ዓይነት ሥራ አልሠራሁም ። ፖሊስ ብና መጣ የተሻለ መሆኑን ብቻ ነው የገለጽኩት — እንደዚህ ካለ ተማ ሪዎች ከሚበዙበት ሥፍራ ሊያርስ የሚችል ነገር ነው ። እውነቱ ግን ማንም ፣ ፖሊስ የጠራ ሰው የለም ። አንድ የታወቀና የተከበረ የግል ወንጀል ተከታታይ ሰው ባለፈው ምሽት አብሮኝ ራት እንዲ

በላ ጋብኜ ነበር ። ለተማሪዎቹ በሥነ - ወንጀል ላይ ትግ ሀርታዊ ንግግር አድርጎላቸው ነበር ። ''

'' ደግሞ ለተማሪዎቻችን ስለ ሥነ — ወንጀል ማውራቱ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ! ራሳቸው በሚገባ ያውቃሉ ። ለመሥረቅ ለማጥፋትና ሸር ለመሥራት የፈለጉትን ለማድረግ ይችላሉ ! ምንም ማድረግ አይቻልም - ምንም ! ''

'' እኔ ግን አንድ ነገር አድርጌያለሁ ። ''

'' አዎን ፣ ለዚህ ለባልንጀራሽ የበላነው ፣ የጠጣነውም አልቀረሽ ። ያ ደግሞ አለመተማመንን በመካከላችን ፈጥሯል ። ''

'' ፍጹም ! ይህን ሥፍራ የመምራት ሀላፊነት አለብኝ ። ነገሩ ሁሉ ግልጽ መሆኑን ልገልጽልሽ እወዳለሁ ። ከተማሪዎቹ አንዱ የደረሰው ጥፋት በሙሉ ሀላፊነቷን ሳትደብቅ ራሷን አጋልጣለች ።''

'' በስባሳ ድንክዬ ድመት ! '' አለች ኒኮሊተስ ። '' ወዲያ አባሪልኝ ወይኗን አያሳያኝ !''

'' በራሷ ፍላጐት ቢቱን ለቃ መውጣቷ ነው። በዚህ ላይ ለጠፋው ዕቃ በሙሉ ከፍላለች ። ''

'' ምን ያደርጋል ? ይህ ውብ ድንቅ የተማሪዎች ቤት በርሷ የቲነሳ መጥፎ ስም ሊወጣለት ነው ። ከእንግዲህ ማንም አይመጣም ። '' ሚስ ኒኮሊተስ ከሶፋው ተቀምጣ እምባዋን ማዝነቡን ቀጠለች ። '' ማንም ስለ'ኔ ስሜት ግድ ያለው የለም '' እያለች በታ ፈነና በተዘጋ ድምጽ ታላቅሳለች ። '' ይኼ የጥላቻ ነ ፃ ። እኔ ተዘግቼ ወደ ሳን ቲወርውሬ ! ነገስ የምሞት ቢሆን ማን ግድ ይኖረዋል ? ''

ይህን ጥያቄ መመለሱ ተገቢ አለመሆኑን በማወቅ ሚስ ሀበርድ ክፍሉን ለቃ ወጣች ።

'' ሁሉን ቻይ አምላክ እስኪ ትዕግሥቱን ይስጠኛ ! '' አለች ሚስ ሀበርድ ማሪያን ለማነጋገር ወደ ወጥ ቤት ስትሔድ ።

ማርያ ፊቷን አጨፍግጋ ትንፍሽ ማለትም አልፈለገች ። ' ፖሊስ ' የሚለው ቃል ሳይነገር ከአየር ላይ እየተንሣፈፈ ነው ።

'' እኔ ነኝ የምከሠሰው ። እኔና ጄሮኒሞ — ምስኪኖች ! ከባዕድ ሀገር ድሮስ ቢሆን ምን ፍትህ ይጠበቃል ? አሁን የተሣሣተ ሩዝ ስለላኩ ሪሶቱውን ማዘጋጀት አልችልም ። በምትኩ ስፓጌቲ አበስላለሁ ። ''

'' ትላንትና ማታ ስፓጌቲ ነበር የበላነው ። ''

“ ምንም አይደል ! ከሀገሬ በየቀኑ ስፓጌቲ ነው የምንበላው ። ፓስታ ፖ ንጊዜም ቢሆን ጥሩ ነው ። ”

“ እምን ፣ ግን እሁን ያለሽው እንግሊዝ አገር ነው ። ”

“ በጣም ጥሩ ወጥ አዘጋጀለሁ ። የእንግሊዝ ወጥ ። አትወጂውም — ግን አልጫ — አልጫ አደርገዋለሁ ። ውሃውን በዛ አድርጊ ሽንኩርቱን በዘይት ከማቁላላት ይልቅ ‘ቀቅለውና — ፈንክትክት ካሉ ቅልጥሞች ቀይ ያልበዛበት ሥጋ እጨምርበታለሁ ። ”

ማርያ በሚያስፈራ አኳኋን ስትናገር ስለነበር ሚስ ሀበርድ ስለ ግድያ ወንጀል የፖ ትስማት መስሎ ተሰማት ።

“ በይ የፈለግሽውን ሥሪ ” አለቻትና በቁጣ ወጥ - ቤቱን ለቃ ወጣች ።

በዚያው ምሽት አሥራ ሁለት ሠዓት ላይ ሚስ ሀበርድ ደግሞ ሁኔታው እንደድሮዋ ሆኖ ተሰማት ። ከ’ራት በፊት እንዲያነጋግሯት ለተማሪዎች በመላ ከክፍላቸው ማስታወሻ አስቀመጠችላቸው ። ጥሪው በአብዛኛው ተቀባይነት እንዳለው ካወቀች በኋላ ሴሊያ ጉዳዩን እርሷ እንድትጨርስላት መጠየቋን ገለጸችላቸው ። እንደርሷ አስተሳሰብ ሁሉም ተስማማ ተውበታል ። ጀኔቬይቭ እንኳ ለፓውደር መያዣዋ በተ ተመነው ማለፊያ ዋጋ በጣም በመደሰት ፣ ከምቀኝነትና መጥፎ ስሜት ነፃ በሆነ ልበ ሙሉነት ሀሳቧን ገለጸች ። “ ይህ ቀውስ የአዕምሮ ችግር ውጤት መሆኑ ግልፅ ነው ። ይህቺ ሴሊያ በጣም ሀብታም ነች ፣ ሥርቆት አያስፈልጋትም ። ከራሷ ግን መረበሽ ይኖርባታል ። ሚስተር ማክናብ እዚያ ላይ ፍጹም አልተሳሳተም ” አለች ።

የ’ራት ደወል ሲደወል ሊን ባትሰን ወደታች በመውረድ ላይ የነበረችዋን ሚስ ሀበርድ ወደ ጎን ጎተት አደረጋት ።

“ ሴሊያን ከአዳራሹ ‘ጠብቃታለሁ ፡ አምጫት ። ሁሉም ነገር ሠላም መሆኑን ታየዋለች ። ”

“ በጣም ጥሩ ነው ሊን ። ”

“ አመሰግናለሁ እንዬ ። ”

ሾርባ በመቅረብ ላይ እያለ የሊን ድምጽ ሲተም ከአዳራሹ ይሰማል ።

“ ነይ ከዚህ ሴሊያ ከዚህ ያሉት በሙሉ ጓደኞቻችን ናቸው ። ”

በዚያ በሚተም ድምፁ ኒጌል የሾርባ ማህኑን እየተመለከተ ፣

“ መልካም ሥራ ተሠርቷል ! ” አለ ። አፉን ዘግቶ ሴሊያን እጁን በማወዛወዝ ተቀበላት ። የሌን ረጅም ከንዶች ከሴሊያ ትከሻ ላይ አረፉ ።

በተለያዩ ርዕሶች ላይ ውይይቱ ከጣሪያ በላይ ይሰማል ። ሴሊያን ከዚያም ከዚህም ጥያቄ ሲያጣድፋት ቆየ ።

በስተኋላ ላይ በድንገት ሳይታሰብ ያ ሁሉ ቀና መንፈሥ በእንድ ጊዜ ጸጥ ረጭ ባለ አጠራጣሪ ሁኔታ ተተካ ። በዚያ ወቅት ነበር ያን በንዴት የፋመ ፊቱን ወደ ሴሊያ በመመለስ ሚስተር አኪቦ ቦ ከጠ ረጴዛው በማስገግ ፣

“ ያልገባኝን ሁሉ አሁን በሚገባ አስረድተውኛል ።ዕቃዎችን በመሥረቅ በጣም ጎበዝ ነሽ ። ለረጅም ጊዜ ማንም ሊያውቅብሽ አልቻለውም ነበር ። በጣም ጎበዝ ነሽ ! ” አላት ።

በዚህ ላይ እንዳሉ ሳሊ ፊንች ከትንፋሿ እየተናነቀች፣ “ አኪቦ ምቦ ምንው ዎን አደረኩህ ? ” በማለት እጇን አፍና ከአዳራሹ ወጣች ። ከዚያ በኋላ አዳራሹ ከዳር እስከ ዳር በሣቅ ተሞላ ።

ኮሊን ማክናብ ዘግይቶ ተመለሰ ። ከወትሮው ይልቅ ከመናገር የተቆጠበ ይመስላል ። የምግቡ ሠዓት ለማብቃት እንደተዳረሰ ሌሎቹ ሳይጨርሱ ከመቀመጫው በሀዘን ተውጦ በመቆም በማጉረምረም ድምፅ ፣

“ ውጭ ከሰዉ ቀጠሮ ስላለኝ መውጣቴ ነኝ ። በመጀመሪያ ለሁ ላችሁም እንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ ። እኔና ሴሊያ ጥናቴን እንደ ጨረስኩኝ በሚቀጥለው ዓመት ልንጋባ ወስነናል ” አለ ።

በዚያ ዓይነ - አፋርነት መካከል የ‘እንኳን ደስ ያለህ !’ ውካታና ጥሪው፣ ጭብጨባው ከጓደኞቹ በመሠንዘር ላይ እያለ በመጨረሻ ላይ በልበ ሙሉነት እየተጎማለለ ወጣ ። በሌላው በኩል ደግሞ ሴሊያ በጣም ተፅናንታና ተረጋግታ ትታያለች ።

“ በቃ ! አንድ ይህና ሰው ወደ ምዕራብ ” አለ ሊን በትሰን ።

“ በጣም ተደስቻለሁ ሴሊያ ” አለች ፖትሪሺያ ። “ በጣም ደስተኛ እንደምትሆኝ ርግጠኛ ነኝ ” አለች በድጋሚ ።

“ አሁን የአበባው ሥፍራ ጽዱ ነው ” አለ ኒጌል ። “ ነገ ጥቂት ቺያንቴ አምጥቼ ለጤናሽ ጽዋችንን እናነሳለን ። ለምንድነው የኛ ይቱ ጂን ፊቷ የተለዋወጠው ? ምነው ጋብቻን ትጠያለሽ እንዴ ጂን ? ”

“ በፍጹም ኒጌል ! ”

“ ከነፃ ፍቅር ይልቅ የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ ፣ አይመስልሽም ? ለልጅቹ በጣም የተሻለ ነው ። ፓስፖርታቸው ላይ ሲታይ ደግሞ የበለጠ ያስደስታል ። ”

“ እናትየዋ ግን በጣም ወጣት መሆን የለባትም ” አለች ጂኔቬይቭ ። “ በፊዚዮሎጂ ክፍልም እንደዚያ ነው የሚናገሩት ። ”

“ እውነት ነው ምትይው ? ” አለ ኒጌል ። “ ሴሊያ ለአቅመ ሔዋን አላደረሰችም ነው የምትይ ? ነፃና አውሮፓዊት የሀያ አንድ ዓመት ኮረዳ ናት ። ”

“ የሚያስከፋኩ ነግግር አይደለም ” አለ ሚስተር ቻንድራላል ።

“ የለም ! የለም ! ሚስተር ቻንድራ ላል ” አለች ፖትሪሺያ “ በቃ አለ አይደል ውስጠ ወይራ ነገር ነው ። ሌላ እንኳ አይደለም ። ”

“ አልገባኝም ! ” አለ አኪቦምቦ ። “ አንድ ነገር ሌላ ትርጉም ከሌለው ለምን ይነገራል ? ”

ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን በድንገት ድምጿን ትንሽ ከፍ በማድረግ ፣

“ አንዳንድ ጊዜ ምንም ትርጉም የማይሰጡ ነገሮች ይነገሩና ነገር ግን ብዙ ትርጉሞችን ይሰጣሉ ። የናንተን የአሜሪካዊያንን ጥቅስ ማለቴ አይደለም ። እኔ የማወራው ስለአንድ ሌላ ነገር ነው ። ” ዘወር ብላ ጠረጴዛውን ተመለከተች ። “ ትላንት ስለሆነው ነገር ማለቴ ነው ” አለች ።

ቫሌሪ ትንሽ ቆጣ ብላ ፣

“ ምንድነው ቢስ ? ”

“ እባክሽን ” አለች ሴሊያ ። “ እንደማስበው በእውነት ነው ‘ ምልሽ ነገ ሁሉም ነገር ይስተካከላል ። እውነቴን ነው የምልሽ ። ከወረቀቶችሽ ላይ የፈሰሰው ቀለምና ያ የጀርባ ሻንጣው የማይረባ ሥራ ማለቴ ነው ። ባለቤቱ አንቺ ነሽ - ያደረግሽውም ካለ — ግድየለም ይስተካከላል ። ”

ስትናገር ከልቧ ነበር ፣ ፊቷ ቀልቷል ። አንድ ሁለት ሰዎች ይመለከቷታል ።

ቫሌሪ ትንሽ ሣቅ በማለት ፣

“ ከዚያ በኋላ ደስተኛ ኑሮ እንኖራለን ” አለች ።

ሁሉም ከተቀመጡበት በመነሳት ወደ ጋራ አዳራሹ ሔዱ ። ሲሊያ ቡናዋን እንዳትጠጣ የረበሻት ምንም ነገር አልነበረም ። ሬዲዮው ተከፍቶ ጥቂት ተማሪዎች ቀጠሮአቸውን መጠበቅ ወይንም መሥራት ጀመሩ ። በመጨረሻ ላይ የቁጥር 24 እና ቁጥር 26 ሒኮሪ ጎዳና ነዋሪዎች ወደ መኝታቸው ሔዱ ።

ከአልጋዋ ካሉት አንሶላዎች መካከል ገብታ ለመጋደም በሙሀጣት ላይ እያለች የሚያደክም ቀን መሆኑንም ያስታወሰች ሚስ ሀበርድ ነበረች ።

“ ለአምላክ ምስጋና ይድረሰው ” አለች ለ’ራሷ ። “ አሁን ሁሉም ነገር አበቃ ። ”

— 7 —

ሚስስ ሊመን ሁልጊዜ ቀርቶ አልፋ አልፋ እንኳ ከሥራ ዘግ ይታ አታውቅም ። ደመና ፡ ሀይለኛ መውጅ ፡ ሀይለኛ ጉንፋን ፡ የት ራንስፖርት እጥረት - ከነዚህ ውስጥ ማናቸውም ችግሮች ቢሆኑ እንኳ ይህችን ታታሪ ሴት ከሥራ አስቀርተዋት አያውቁም ። ነገር ግን ዛሬ ጠዋት ሚስስ ሊመን ልክ እቅጩን በአራት ሰዓት ላይ ከመ ድረስ ይልቅ አምስት ደቂቃዎች ያህል አሳልፋ ትንፋሿን መሰብሰብ እንኳ አቅቷት ነው የደረሰች ። በትህትና ይቅርታ ጠየቀች ።

“ በጣም አዝናለሁ መሴ ፖይሮት — እውነቴን ነወ በጣም ነው ማዝነው ። ልክ እህቴ ስትደውል እኔ ከቢት ለመውጣት በመዘጋጀት ላይ ነበርኩኝ ። ”

“ አሁን እንደሚመስሸኝ ሙሉ በሙሉ ሠላም ናት፡አይደለችም ?”

“ግልጽ ለማድረግ ፡ የለም አይደለችም ! ” አለች። ፖይሮት በጥር ጣሬ ዓይን ተመለከታት ። ቀጥላም “በርግጥ በጣም አዝናለች ! ከተማ ሪዎቹ አንዱ ራሷን በራሷ ገድላለች ! ” አሉችው ።

ፖይሮት አፍጥጦ ተመለከታት ። አንድ ነገር ለራሱ አጉተመተመ።

“ ምንድነው ያልከኝ መሴ ፖይሮት ? ”

“ የተማሪዋ ስም ማን ነበር ? ”

“ ሴሊያ አውስቲን የምትባል ልጅ ናት ። ”

“ እንዴት ? ”

“ ሞርፊያ ወስዳ ነው የሚሉት ። ”

“ ድንገተኛ አደጋ ይሆን ? ”

“ የለም ፡ ማስታወሻ የተወች ይመስለኛል ! ”

ፖይሮት ዝቅ ባለ ድምፅ ፡ “ እኔ እንኳ የጠበቅሁት ይህን አል ነበረም ፡ ይህን አልነበረም . . . ግን እውነት ሆነ ፡ አንድ ነገር እንደ ሚፈጸም አስቀድሜ አውቄ ነበር ” አለ ።

ሚስስ ሊመንን ቀና ብሎ ተመለከታት ። ርህስና ማስታወሻ ዋን ለመመልከት ነበር ። በረጅሙ በመተንፈስ ራሱን ነቀነቀ ።

“ የለም ፣ አንቺ የዛሬውን ደብዳቤ ከፋይል አያይዢው ! የምትችይውን መልሺ ። እኔ ግን ወደ ሔኮሪ ጎዳና መሔዴ ነኝ ። ”

ጀሮኒሞ ከሁለት ምሽቶች በፊት የክብር እንግዳ የነበረው ፖይሮት መሆኑን ከተገነዘበ በኋላ በጥድፊያና በአድርባይነት ሹክሹክታ ወሬውን ያዘንበው ጀመር ።

“ እንዴ ጌታዬ እርሶ ነዎት ። እኛ ችግር ውስጥ - ታላቅ ችግር ውስጥ ወድቀናል። ትንሿ እመቤት ዛሬ ጠዋት አልጋዋ ላይ ሞታ ተገኘች ። በመጀመሪያ ዶክተሩ መጣ ። ራሱን ነቀነቀ ። አሁን ደግሞ የፖሊስ ኢንስፔክተሩ መጥተዋል ። ከላይኛው ደርብ ከእመቤቴና ከክብርት እመቤቴ ናቸው ። ለምን ራሷን መግደል ፈለገች? ምስኪን! እስኪ ትላንት ምሽት ሁሉም ተደስቶ ትጭፍሩ ከተደረገ በኋላ! ”

“ ትጭፍት ? ”

“ አዎ ፣ አዎ ። ከሚስተር ኮሊን — ያውቁታል ጌታዬ - አንድ ረጅም ጃዊሳ ዘወትር ትምባሆ በፒፓ የሚያጤሰው ? ”

“ አውቀዋለሁ ። ”

ጀሮኒሞ የጋራ አዳራሹን በመከፈት በእንዳች ሚስጥር ጠባቂ ባለሟል አኳኋን ፖይሮት ወደ ውስጥ እንዲገባ አደረገ ።

“ እዚህ ይቆዩ ፣ እሺ ? ወዲያውኑ ፖሊሱ እንደወጣ ለእመቤቴ ከዚህ መሆንዎን እገልጻለሁ ። እንደዚያ ይሻላል ፣ እሺ ? ”

ፖይሮት በሀሳቡ ተስማማ ፣ ጀሮኒሞ ሰቆ ወጣ። ለብቻው ሆኖ ያ ምኞትና ረፍትን የማያውቀው ሰው እያንዳንዷን የተማሪዎች ዕቃ በጥንቃቄ ማጠናናት ቀጠለ ። ያገኘው ውጤት ብዙም ጠቃሚነት የሌለው፣ አንዳንድ ፍንጮችንም የማያጣ ነበር ። ተማሪዎቹ በአብዛኛው የግል ዕቃዎቻቸውንና ወረቀቶቻቸውን የሚያስቀምጡት ከመኝታ ቤቶቻቸው ነው ።

ከላይ ሚስ ሀበርድ ከኢንስፔክተር ሻርፕ ፊት ለፊት በመቀመጥ በትህትና የሚያቀርብላትን ጥያቄ በመቀበል ላይ ነበረች ። ከገጽታው ርጋታና ቁም ነገረኛነት ይነበባል ።

“ በርግጥ የሚያሳዝን ነገር ነው የሚሆንብሽ ፣ አውቃለሁ ” አለና፣ “ግን ዶክተር ኮልስ እንዳስረዳሽ ሁሉ የሆነውን ነገር በሚገባ ለማወቅ የሚካሔዱ የማስረጃ መሰብሰብና ጥያቄዎች ይኖራሉ ። ይህች ልጅ በቅርቡ በጣም ብስጭት ላይ ነበረች አይደለም ያልሽኝ ?”

“ አዎን ። ”

“ ፍቅር ነው ? ”

“ በትክክል እንደዚያ አይመስለኝም ” አለችና ሚስ ሀበርድ አመነታታች ።

“ብትነግሪኝ ጥሩ ነው ? ታውቂያለሽ ” አለ ኢንስፔክተር ቫርፕ ። ነገሩን ለማወጣጣት ገፋፋት ። “ እንዳልኩት ፣ ሁሉንም ነገር መረዳት አለብን ። በርግጥ ምክንያት አለ ወይንስ ይኖራል ብላ አስባ ነበር ሕይወቷን ለማጥፋት ? እንደው ርጉዝ ነች የሚል ፍንጭም አልሰማሽ ? ”

“ ፍጹም ! እንደዚያ ዓይነት ነገር አይመስለኝም ። ኢንስፔክተር ቫርፕ እኔ ለመናገር ያመነታታሁት ልጅቱ አንድ የማይረባ ነገር በመሥራቷና ይህን በይፋ ማወጣቱ አስፈላጊ ስላልመሰለኝ ነበር ። ”

ኢንስፔክተር ቫርፕን አሳለው ።

“ ይህና ሥልጣን አለን ። ወንጀል መርማሪው ሰው ደግሞ የበለጠ የሥራ ልምድ ያለው ነው ። ይህን ሁሉ ማወቅ ይኖርብናል ። ”

“ አዎን በሚገባ ! ጅልነቱ የኔ ነው ። እውነቱ ባለፉት ረዘም ያሉ ጊዜያት አንዳንድ ነገሮች ማለት እስከዚህም ጠቃሚ ያልሆኑ ዕቃዎች በመጥፋት ላይ ነበሩ ። ”

“አንዳንድ ጌጣጌጦች ማለትም ጥሩ ጥሩ ልብሶች ፣ ናይሎን ስቶኪንጎች እና የመሳሰሉትን ፣ ገንዘብም ጭምር ? ”

“ እኔ እስከማውቀው ድረስ እንኳ ገንዘብ የለም ። ”

“ እና ለጠፉት ዕቃዎች ሐላፊነቱ የልጅቷ ነበር ? ”

“ አዎን ። ”

“ እጅ ከፍንጅ ይዘሻት ነበር ? ”

“ በትክክል እንኳ እንደዚያ አይደለም ። ከትናንት ወዲያ እ . . . አንድ የቅርብ ወዳጄ ራት ለመብላት መጥቶ ነበር ። መሲ ፖይሮት — ስሙን እወቁ — አትወቁ እኔ የማውቀው ነገር የለም ። ”

ኢንስፔክተር ቫርፕ ከማስታወሻው ተመለከተ ። ዓይኖቹ በስፋት ተከፈቱ ። አዎን ስሙን ያውቀዋል ።

“ መሲ ሔርኩሌ ፖይሮት ? ” አለ ። “ በእውነት ? አዎን በጣም ጥሩ ነው ። ”

“ኒ’ሪት በኋላ ትንሽ ትፖሀርታዊ ንግግር እንዳደረገልን የሥርቆቱ መሬ ተነሳ ። ከዚያ በኋላ በሁሉም ፊት ፖሊስ እንድጠራ ነገረኝ ። ”

“ እንደዚያ አለ ? እንደዚያ አለ ? ”

“ ከዚያ በኋላ ሴሊያ ከመኝታ ቤቴ ድረስ በመጣት ራሷን አጋለጠች ። በጣም ተበሳጭታና አዝና ነበር ።”

“ በሕግ በኩል የተደረገ ነገር አለ ? ”

“ የለም ! ስለተሰረቁት ዕቃዎች ዋጋቸውን ለመክፈል ተስማምታ ነበር ። ሁሉም ሰው በሰላም ተቀብሏታል ! ”

“የገንዘብ ችግር ነበረባት ? ”

“ የለም ! ከቅድስት ካታሪን ሆስፒታል በመድሐኒት አከፋፋይነት በቂ ደመወዝ ታገኛለች ። በዚህ ላይ የራሷ የሆነ ጥቂት ገንዘብም ነበራት ። እንደዚያ ይመስለኛል ። ከአብዛኞቹ ተማሪዎቻችን የተሻለች ነበረች ። ”

“ስለዚህ ለመሥረቅ የሚገፋፋት ምንም ምክንያት የለማ? —ነገር ግን ደግሞ ሠረቀች ! ” አለ ኢንስፔክተሩ አቀርቅሮ እየጻፈ ።

“እኔ ግን የሥርቆት ሱስ በሽታ (ክሊፕቶማንያ) ይመስለኛል ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

“ያ ነው እንግዲህ ማለት የሚቻለው። መናገር የፈለግሁት በእቅሙ ምንም ዕቃዎችን የማይወስድ ሰው ግን ወስዶ ሲገኝ ይኼው ነው !”

“ ነገሩ በትክክል ገብቶህ እንደሆነ እኔ እንጃ ። ገባህ ? አንድ ወጣት ልጅ ነበር ። ”

“ ታልኪዳኑን አፈረሠባት ? ”

“ የለም ። እንዲያውም በተቃራኒው ነው ። እውነቱን ለመናገር ስለ’ርሷ በጣም በመቆርቆር ነበር የሚናገረው ። ትናንት ማታ እንዲያውም ከሪት በኋላ እንደሚጋቡ በይፋ አስታውቆ ነበር ። ”

የኢንስፔክተር ሻርፕ ቅንድቦች አሻቅበው ከግንባሩ ግን የመገረም ገጽታ ይታይበታል ።

“ ከዚያ በኋላ ከአልጋ በሚ ውጣት ሞርፊያ ወሰደች ? ያ ደግሞ የበለጠ የሚያስገርም ጉዳይ ነው ። አይደለም ? ”

“ እምን ነው ። ሊገባኝ ግን አይችልም ። ”

የሚስ ሀበርድ ፊት በጥርጣሬ መናወዝና ሀዘን ይታይበታል ።

“ ግን ደግሞኮ መረጃዎቹ ግልጽ ናቸው ” አለና ሻርፕ ከመካ ከላቸው ከጠረጴዛው ላይ የምትታየውን ትንሽ ብጣሽ ወረቀት በመመ ልከት ራሱን ነቀነቀ ።

ውድ ሚስ ሀበርድ (ይላል) ፣ በእውነት አዝናለሁ ይህ ማድረግ ከምችለው ነገር አንዱና የቲሻለው ነው ።

“ አልተፈረመም ። ነገር ግን የርሷ የእጅ ጽሑፍ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለሽም ? ”

“ የለኝም ። ”

ሚስ ሀበርድ ስትናገር ርግጠኛ ሆና ካለመሆኑም በላይ የተቀደ ደችዋን ደብዳቤ ስትመለከት ፊቷን አጨማ ዘበር ። ለምን አንዳች ስህተት ነገር እንዳለው ሆኖ በጣም ተሰማት — ?

“ ካለጥርጥር የራሷ የሆነ አንድ የጣት አሻራ አለበት ” አለ ኢንስፔክተሩ ። “ ሞርፊያው የቅድስት ካታሪን ሆስፒታል መለየ የተ ለጠፈበት ትንሽ ቢልቃጥ ነበር ። በዚህ ላይ ከቅድስት ካታሪን የመድ ሐኒት አከፋፋይነት ሥራ እንደምትሠራ ነግረሽኛል ። ምናልባት በቀ ላሉ ለማግኘት የተቻላት የሞርሐኒቱ ማስቀመጫ ቁም ሣጥን በቅርብ ስለሆነ ይሆናል ። ካለጥርጥር ትላንት ራሷን ለመግደል አስባ ከቤት የመጣች መሆን አለበት ። ”

“ አላምንም ! የማይመስል ነገር ነው ። ትላንት ማታ በጣም ደስተኛ ነበረች ። ”

“ እንግዲያውስ ከአልጋዋ ስትወጣ ሀሳቧ ተቀይሮ እንደሆነስ ? ምናልባት አንቺ ከምታውቂው በላይ ሁኔታ በሕይወቷ ደርሶባት ይሆ ናል ። ያ ይወጣብኛል የሚል ፍራቻ ይኖርባታል ። ለመሆኑ የዚህ ጠጣት ፣ ስም ማን ነበር ? የነበራቸውስ ፍቅር ከፍተኛ ነው ? ”

“ ኮሊን ማክናብ ይባላል ። ለድሀረ ምረቃው ከቅድስት ካተሪን በማጥናት ላይ ነው ። ”

“ ዶክተር ነው ? ከቅድስት ካታሪን ? ”

“ ሴሊያ ከ‘ርሱ በጣም ፍቅር ይዟት ነበር ። እንዲያውም ከርሱ ይልቅ ማለት እችላለሁ ። ”

“ ምናልባት ምክንያቱ እንደዚያ ሊሆን ይችላል ። ስለ‘ርሱ ብዙም አትጨነቅ ይሆናል ፣ ወይንም መናገር የማይገባትን ነገር አልነ ገረችው ይሆናል ። አዎ ፣ ወጣት ነበረች ፣ አልነበረችም ? ”

“ አዎን ፤ ሀያ ሦስት ሆኗታል ። ”

“ በዚያ ዕድሜ ፍጹም ካለመሆናቸውም በላይ ፍቅርን አክብ ደው ነው የሚያዩት ። አዎን ፣ እንደዚያ ነው ። ያሳዝናል ! ”

ከመቀመጫው ተነስቶ ቆመ ። “ ምናልባት እውነተኛው ነገር ይወጣል ብዬ እፈራለሁ ። ነገር ግን በምንችለው መንገድ ሚስጥራችንን መደበቅ አለብን ። በጣም እመሰግናለሁ ሚስ ሀበርድ ። አሁን የም ፈልገውን መረጃ በሙሉ አግኝቻለሁ ። እናቷ የሞተችው ከሁለት ዓመ ታት በፊት ነው ። የምታውቂው ዘመዷ ከዮርክሻየር የምትገኝ አክ ስቷ ብቻ ናት—ከ‘ርሷ በቲቻለን ግንኙነት ለመፍጠር እንሞክራለን ።”

ያን የተቀደደ ትንሽ ወረቀት ከሴሊያ ደብዳቤ በእንድነት አነሳው ።

“ አንድ ስለዚህ ነገር የተሣሣተ ሁኔታ ይኖራል ” አለች ሚስ ሀበርድ በድንገት ።

“ ሥህተት ? እንዴት ? ”

“ አላውቅም — ነገር ግን ማወቅ አለብኝ ። ምስኪን . . . ”

“ የ‘ርሷ ጽሑፍ ስለመሆኑ ርግጠኛ ነሽ ? ”

“ አዎን ? ‘ሚያጠራጥረኝ ‘ርሱ አይደለም ። ” አለችና ሚስ ሀበ ርድ እጅዋን ከዓይኗ ላይ አደረገች ው ።

“ ዛሬ ጠዋት በፍርሃት ተጀጅዬ ነበር ” አለች በትህትና ።

“ አዎ ! ላንቺ በጣም የፈተና ወቅት መሆኑ ይገባኛል ” አለ ኢንስፔክተሩ በሀዘን ስሜት ። “ ለጊዜው ብዙ የምናስቸግርሽ መስሎ አይታየኝም ሚስ ሀበርድ ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ በሩን ሲከፍት ወዲያውኑ ከበሩ ላይ ተለጥፎ በማዳመጥ ላይ የነበረውን ጀሮኒሞን አገኘው ።

“ ታዲያስ ! ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ሳይከፋ ። “ ከበር ላይ ሆነህ ታዳምጣለህ ? ”

“ የለም ፣ የለም ፣ ” አለ ጥፋተኛ መደረጉ የተሰማው ጀሮኒሞ ። “ የለም አላዳመጥኩም - ፍጹም ፣ ፍጹም ! መልእክት ይገፎ መምጣቴ ነው ። ”

“ ገባኝ ! የምን መልእክት ? ”

ጀሮኒሞ በቁጣ ፣

“ ከታችኛዋ ወለል አንድ ትልቅ ሰው እመቤት ሀበርድን ለማ ነጋገር ‘ፈልጋለሁ ስላለኝ ብቻ ነው ። ”

“ ጥሩ ነው የኔ ልጅ ሂደና ንገራት ። ”

ጀሮኒሞን አልፎ በመተላለፊያው በመውረድ ከጣሊያኑ ጦጽ ሐፍ ውስጥ እንዲት ገጽ በማውጣት በ'ግርጣቱ ጹካው እንዳይሰማ በት ሔዶ ተመለሰ ። ባለትንሽ ጠጣ ፊቱ ሰው እውነቱን መናገርና አለ መናገሩን ማረጋገጥም ይችል ይሆናል ።

ጀሮኒም የሚናገረውን ለመስማት በጊዜው ደረሰ ።

" ለ'ራት እንድ ምሽት የመጡት ሰው ፡ እኒያ ዒም ያላቸው ሰው ፡ እርሶን ለማነጋገር ከታች ይጠብቅዎታል ። "

" ዎን ? " አለች ሚስ ሀበርድ ። " አመሰግናለሁ ጀሮኒሞ ! ከእንድ ፡ ሁለት ደቂቃ በኋላ እመጣለሁ ። "

" ዒም ያላቸወ ሰው እ ? " አለ ሻርፕ ለራሱ ፊገግ ብሎ ። " ማን መሆኑን እወቂያለሁ አለ ። "

ወደታች በመውረድ ወደ ጋራ — አዳራሹ ገባ ።

" ታዲያስ መሴ ፖይሮት " አለው ። " ከተገናኘን ብዙ ጊዜ ሆነን ። "

ፖይሮት ከ'ላት ምድጃው አጠገብ ካለው የመጽሐፍ መደርደ ሪያ በእምብርክኩ ከነበረበት ለወይን በማይታወስ ፍጥነት ተነሳ ።

" ታዲያስ ? " አለ ። " ግን ካለጥርጥር - አዎን ኢንስፔክተር ሻርፕ መሆን አለበት አይደለም ? ነገር ግን አስቀድመህ በዚህ ክፍል አል ነበርክም ? "

" ከተዛወርኩኝ ሁለት ዓመታት ሆነውኛል ። ስለዚያ ከክራ ይስ ሒል ስለነበረው ጉዳይ ታስታውሳለህ ? "

" እንዴ ! በሚገባ ፤ አሁን ብዙ ጊዜ ሆኖታል ። እንተ አሁንም ቢሆን ገና ወጣት ነህ ኢንስፔክተር —"

" እያረጀሁ ነኝ እንጂ ፤ እያረጀሁ ። "

" — እኔ ግን አርጅቻለሁ ። አበቃ ! " ሲል ፖይሮት በረጅሙ ተነፈሰ ።

" አሁንም ቢሆን ገና ወጣት ነህ መሴ ፖይሮት ። በአንዳንድ ነገሮች ላይ በጣም ቀልጣፋና ትጉህ ነህ ። እንደዚያ እንበል ? "

" እንደዚያ ስትል ምን ማለትህ ነው ? "

" ማለቴ ፤ በዚያ ምሽት ለተማሪዎቹ ለምን በሥነ - ወንጀል ላይ ትምህርታዊ ንግግር ለማድረግ እንደመጣህ ለማወቅ 'ፈልጋለሁ ነው?"

ፖይሮት ፈገግታ አሳየ ።

“ ነገር ግን በጣም ቀላል ምክንያት አለው ። ሚስ ሀበርድ በጣም የማከብራት ጸሐፊዬ ማለት የወይዘሪት ሊመን እህት ናት ። እና ‘ርሷ በጠየቀችኝ ጊዜ — ”

“ ከዚህ በጊዜ እየተካሔደ የነበረውን ጉዳይ እንድታጠናላት በጠየቀችህ ጊዜ መጣህ ። እንደዚያ ነው ፣ አይደለም ? ”

“ ትክክል ! ”

“ ግን ለምን ? ያንን ነው ማወቅ የፈለኩት ። አንተን ከዚህ የሚያገባህ ምን ጉዳይ ይኖራል ? ”

“ የሚስበኝን ነገር ማለትህ ነው ? ”

“ አዎን ! እንደዚያ ማለቴ ነው ። ከዚህ ይህንንም ያንንም የምትመዝ አንዲት ደደብ ልጅ ነበረች ። ሁልጊዜም ዕቃ ይጠፋል ። ላንተ በጣም የማይረባ ጉዳይ አይሆንም መሴ ፖይሮት ? ”

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

“ እንደዚያ ቀላል አይደለም ። ”

“ ለምን ? ሞት ላይ ነው ክብደቱ ? ”

ፖይሮት ከወንበሩ ላይ ተቀመጠ ። በእጁ ከጉልበቱ ላይ የነበረውን አቧራ ጠራረገ ።

“ ባውቀው ደስ ባለኝ ” አለ ፖይሮት ።

ሻርፕ ተከሳተረ ።

“ አይገባኝም ” አለ ።

“ የለም ፣ ሊገባኝ አይችልም ። የተወሰዱትን ነገሮች — ” ራሱን ነቀነቀ ። “ ስሚት የማይሰጡ ምንም ዓይነት ጥለቶች — አይፈጥሩት - በቃ አንድ ተከታታይ የእግር አሻራ ተመሣሣይ ባልሆኑ እግሮች የተሠራ እንደማለት ነው ። አለ አይደለም ? ‘የደደብ ልጅ’ አሻራ እንደ ፖትሉት ዓይነት ነው ። እንግዲህ ከሴሊያ አውስቲን ጥለቶች የተመሳሰሉ ሌሎች ነገሮች ተደርገዋል ማለት ነው — ነገር ግን እይሳኩም ። ትርጉም የለሾች ናቸው ፣ በተለይ ምንም ፍቺና ትርጉም የሌላቸው ናቸው ። በርግጥ ቀናተኝነትንም የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችም አሉ ። ሴሊያ ደግሞ ቀናተኛ አልነበረችም ። ”

“ የሥርቆት ሱስ ህመም (ክሊፕቶማኒያ) ነበረባት ? ”

“ በጣም እጠራጠራለሁ ! ”

“ ታዲያ ዝም ብሎ ተራ ሥርቆት ነዋ ? ”

“ አንተ በ”ትለው ”መንገድ አይደለም ። እነዚህን ጥቃትን ዕቃ ”ች ማጨሰጉ የአንድ ወጣት ልብ ለመሳብ የተደረጉ ናቸው እላለሁ ።”

“ ኮሊን ማክናብ ? ”

“ አዎን ። ከሚገባው በላይ የኮሊን ማክናብ ፍቅር ይዟት ነበር ። ኮሊን ግን ትኩረት አልሰጣትም ። በጣም ውብ መልካም ሥነ ምግባር ያላት ጨዋ ወጣት ሆኖ ከመታየት ይልቅ ራሷን እንደወጣት ወንጀ ለኛ አስመስላ ማቅረቡን ወደደች ። ውጤታማ ሆነ ። ኮሊን ማክናብ በታላቅ መንገድ ወደቀላት ። ”

“ ያበቃለት ጅላጅል መሆን አለበት ማለት ነው ። ”

“ በፍጹም ! የለም ፣ ብልህ ሳይኮሎጂስት ነው ። ”

“ እንዴ !” ኢንስፔክተር ሻርፕ በረጂሙ ተነፈሰ ። “ ከእነዚህ አንዱ ፣ ገባኝ ። ” ከፊቱ ትንሽ ፈገግታ ይታይበታል ። “ በጣም ጎበዝ ብልህ ልጅ ናት ። ”

“ የሚያስደንቅ ነው ። ”

ፖይሮት እንደተገረመ ሰው ሁሉ ፣ “ በጣም የሚያስደንቅ ነው ” ሲል ቃሉን ደገመው ።

ኢንስፔክተር ሻርፕ ጠንቃቃነት ይነበብበታል ።

“ እንደዚያ ስትል መሴ ፖይሮት ? ”

“ ማለቴ በጣም ተደንቂበታለሁ — አሁንም እየደነቅኝ ነው ፣ ይህ ነገር በሆነ ሰው የተመከረችው ይሆን ? ”

“ ለምን ምክንያት ? ”

“ እንዴት ማወቅ ይቻለኛል ? ቸርነት ? ከመጋረጃ ጀርባ ሸር ? ለማወቅ ያዳግታል ! ”

“ ማን እንደሚሆን ሀሳቡን ማን ይሆን የሰጣት ? ”

“ እንጃ — እንጃ — ምንም ነገር የለም — ”

“ ያው ነው ” አለ ሻርፕ በሀሳብ እየናወዘ ። “ ለማወቅ አልተ ቻለኝም ። ይህን የሥርቆት ሱስ (ክሊፕቶማኒያ) የምታካሔድ ከሆነና ውጤትም ካገኘች በት ለምን ብላ ታዲያ ራሷን ትገድላለች ? ” አለ ።

“ መልሱ ራሷን አልገደለችም ነው ! ”

ሁለቱም ሰዎች ርስ - በርሳቸው ተያዩ ።

ፖይሮት አጉተመተመ ።

‘‘ ራሷ ስለማድረጓ ርግጠኛ ነህ ? ’’

‘‘ እንደንጹህ ወሀ የጠራ ማስረጃ መሴ ፖይሮት ። በስተቀር ሌላ ማሰብ አይቻልም —’’

በሩ ሲከፈት ሚስ ሀበርድ ገባች ። ፊቷ ቀልቷል ። ሀሳቧ የተሳካላት ትመስላለች ። አገጯ ግን በእልህ ተለጥሟል ።

‘‘ አግኝቸዋለሁ ’’ አለች በተሳካለት ሰው መንፈስ ። ‘‘ እን ደዎ ን እደርክ መሴ ፖይሮት ? አግኝቸዋለሁ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። በደንግት ነው ከጭንቅላቴ የገባው ። ይህ የራስን በራስ የመግደሉን ደብዳቤ ማለቴ ነው ። ሴሊያ በዎ ንም ዓይነት ልትጽፈ ው አትችልም !’’

‘‘ ለዎ ን አትችልም ሚስ ሀበርድ ? ’’

‘‘ ምክንያቱም የተጻፈው በተራ ጥቁር ሰማያዊ ቀለም ነው ። ሴሊያ ግን ብዕሯን የሞላቸው አረንጓዴ ቀለም ነው ። ከዚያ በተቀ መጠው ቀለም ’’ ሚስ ሀበርድ ከመጽሐፍ መደርደሪያው ጠቆመ ችና ፣ ‘‘ ትላንትና ጠዋት በቁርስ ሠዓት ’’ አለች ።

ኢንስፔክተር ሻርፕ ፣ አለ አይደል ትንሽ ለየት ያለው ኢንስፔክ ተር ሻርፕ ከሚስ ሀበርድ ንግግር በኋላ ሳይታሰብ ከክፍሉ ወጥቶ እንደገና ተመለሰ ።

‘‘ ትክክል ! ’’ አለ ። ‘‘ ሁሉንም አረጋግጫለሁ ።ከልጅቱ መኝታ ክፍል የነበረ ው ብዕር ከአልጋዋ አጠገብ የነበረው ፣ ከውስጡ ያለው አረንጓዴ ቀለም ነ ው ። ያረንጓዴ ቀለም — ’’ ።

ሚስ ሀበርድ ባዶ ሊሆን የተዳረሰውን የቀለም ቢልቃጥ አነሳች ።

ከዚያ በኋላ ከቁርስ ጠረጴዛ የነበረውን ገቢር በትክክል ፣ በቀ ጥታ ፣ በግልጽ ገለጸችላቸው ።

‘‘ ርግጠኛ ነኝ ’’ አለች ስትጨርስ ፣ ‘‘ ያ ቁራጭ ወረቀት የተ ቀደደ ው ትላንት ለ‘ኔ ስትጽፍ ከነበረው ደብዳቤ ላይ ነው — እኔም አልከፈትኩት ። ’’

‘‘ ምን አደረገችው ታዲያ ? ልታስታ ውሺ ትችያለሽ ? ’’

ሚስ ሀበርድ ራሷን ነቀነቀች ።

‘‘ ከዚህ ብቻዋን ጥያት የቤቱን ሥራ ለመቆጣጠር ሔድኩኝ ። በቃ ከዚህ አንድ ሥፍራ ጥላው ጨርሶም ረስታዋለች ። ’’

“ እና አንድ የሆነ ሰው አገኘው . . . ከፈተው . . . አንድ ሰው ” ሲል ንግግሯን አቋረጣት ።

“ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ተገንዝበሽዋል ፣ ? ስለዚህ ቁራጭ መረቀት ምንም አልተደሰትኩም ነበር ። ከክፍሏ ውስጥ የተቆለለ ትምህርታዊ ንግግሮች (ሌክቸር) የተጻፉባቸው መረቀቶች በብዛት አሉ — ከ‘ነዚህ በአንዱ ላይ ራስን በ‘ራስ ስለ መግደሉ መጻፏ የቀለለ ነው ። ይህ ማለት እንግዲህ አንድ የሆነ ሰው ላ‘ንቺ የተጻፈውን ደብዳቤ የመክፈቻ ወረፍተ ነገር ተመልክቶታል በራስ ማለት ነው — ይህን አንድ የተለየ ነገር ለመግለጽ የተጻፈውን ደብዳቤ አይቶታል ። ራስን ስለ መግደል የተጻፈውን — ”

ትንሽ ፀጥ ካለ በኋላ ዝቅ ባለ ድምጽ ፣

“ ይህ ማለት እንግዲህ - ”

“ ‘ራስን በ‘ራስ መግደል ” ሲል ሔርኩሌ ፖይሮት ጨረሰው ።

— 8 —

ምንም እንኳ ይህ በአሥራ አንድ ሠዓት ላይ የሚቀርብ መክሰሥ መቀበሉ ያን የቀኑን ከፍተኛ የሆድ ድግሥ ፣ ራት የሚሉትን የማያግድ ቢሆንም ፖይሮት ግን ስለለመደው የሚከለክለው ነገር አልነበረም ።

ያ ባለሙያ ጆርጅ በዚህ አጋጣሚ ትላልቅ ስኒዎችን በማውጣት ማለፊያ ጣዕም ያለው የሕንድ ሻይ በጀበና ፣ ትኩስ በጣም በቅቤ የራሱ ክብ ኬኮች ፣ ዳቦ ፣ ማርማላት አራት ማዕዘን ዘቢብ ኬኮችን አዘጋጅቷል ።

ይህ ሁሉ ድግስ በኩራት ወደ ኋላው በመለጠጥ ሦስተኛውን ስኒ ሻይ በመጠጣት ላይ ለነበረው ለኢንስፔክተር ሻርፕ ተብሎ የተዘጋጀ ነበር ።

“ እንደዚህ በጥድፊያ ስለመምጣቴ መቼም ይቅርታህን እትን ፍጊኝም መሴ ፖይሮት፣ ተማሪዎች እስከሚመለሱ ድረስ የአንድ ሠዓት ጊዜ አለኝ ። ሁሉንም መጠየቅና ማነጋገር እፈልጋለሁ ። በግልጽ ተስፋ ያለው ነገር መስሎ አይታየኝም። ባለፈው ምሽት አግኝተሃቸው ስለነበረ ምናልባት ጠቃሚ የሆነ ፍንጭ በተለይ ከውጭ ዜጎቹ ማን ላይ ጥርጣሬው እንደሚጎላ ያገኘኸው ነገር ካለ ብታካፍለኝ ለምስጋና ዩ ወሰን የለውም ? ”

“ ይህን ያህል ለውጪ ዜጎች ያለኝ ችግር ከፍተኛ ይመስል ሃል ? ወዳጄ ! ከመካከላቸው አንድም ቤልጅጋዊ የለም ! ”

“ ቤልጅጋዊ የለም ! ምን ማለት እንደፈለክ ገብቶኛል ። ማለት የፈለከው አንተ ቤልጅጋዊ እንደሆንክ ሁሉ ሌሎች ዜጐች ለአንተ ሊሆኑ እንደሚችሉት ለ’ኔም ባዕድ ናቸው ። ያ እውነት አይደለም ። ነው ? ማለት የፈለኩት ከ‘ኔ ይልቅ ስለአህጉራዊያኑ የተሻለ አንተ ታውቃለህ — ምንም እንኳ ስለ ሕንዶቹና ምዕራብ አፍሪካዊያኑ ብዙም ባታውቅ ማለቴ ነው። ”

“ የተሻለ ርዳታ በጉዳዩ ላይ ማግኘት የምችለው ከሚስ ሀበርድ ይሆናል ። ከ’ዚያ ሥፍራ ከ‘ነዚህ ተማሪዎች በመግባባት ለጥቂት

ወራት ኖራለች ። ከዚ'ም በላይ ስለሰው ልጅ ባህርይ ያላት እመ ለካከት በጣም የበሰለ ነው ። ''

'' አዎን ! በጣም የበሰለች ሰው ናት ። በጣም ነው የተማመንኩ ባት ። ባለቤቷንም ላነጋግራት 'ፈልጋለሁ ። ዛሬም ከቤት ስላላገኘ ኋት ነው ። አብዛኛዎቹ ተመሳሳይ ሥፍራዎች የ'ርሷ ሲሆኑ ጥቂት የተማሪ ከበቦችም ታካሂዳለች ። ይህንንም ያህል ተወዳጅነት ያላት አይመስለኝም ። ''

ፖይሮት ለአንድ ለሁለት ደቂቃዎች ምንም አልተናገረው ። ቀጠል በማድረግም ፣

'' ከቅድስት ካታሪን ነበርክ ? '' ሲል ጠየቀው ።

'' አዎን ፣ ቺፍ ሩርማሲስቱ ብዙም ሊረዳኝ አልቻለ ውም ። በልጅቱ ሞት ከ መጠን በላይ ሀዘንና ብስጭት ደርሶበታል ። ''

'' ለመሆኑ ስለ ልጅቷ ምን ይላል ? ''

''ከ'ዚያ ሥፍራ ከዓመት በላይ ሠርታለች ። በዚህ ላይ በሁሉም ሰው ትፈቀራለች ። እንደ'ርሱ አገላለጽ ከሆነ ግን ዝምተኛ ፣ ሥራዋን በቅንነትና በጥንቃቄ የምታካሔድ ነበረች'' ካለ በኋላ ትንሽ ቆይቶ፣ '' ሞርፊያውም የወጣው ከዚሁ መሆኑን አረጋግጫለሁ '' ሲል አሜ ወተው ።

'' ከ'ዚያ ነው ? ይገርማል — በጣም የሚያጠያይቅ ጉዳይ ይመ ስላል ። ''

'' ሞርፊያ ታርታሬት ነበር ። ከመድሐኒት ማከፋፈያው የመርዝ ማስቀመጫ ቁም ሣጥን ነበር ። ከላይኛው መደርደሪያ - ብዙ ጊዜ ከማይጠቀሙባቸው መደርደሪያ ነበር ። የ ሞርፌ እንክብሎች በአ ጠቃላይ ለጠቅላላ አገልግሎት የሚውሉ ናቸው ። ሞርፌን ሀይድሮ ክሎራይድ ከታርታሬት ይልቅ በአብዛኛው ዘወትር ጥቅም ላይ የሚ ውል ይመስላል ። ከሌሎች ላይ እንደምናየው ሁሉ በመድሐኒቶችም ረገድ የዘመኑ ፈሊጥ ብጤ ይኖራል ። ከዶክተሮቹም ዘንድ እን ዳው ተራ ግትልትልነት ይታያል ። ይህን እንኳ 'ርሱ አላወራኝም ። የ'ኔ ሀሳብና አስተያየት ነው ። ከቁም ሣጥኑ ከላይኛው መደርደሪያ በአንድ ወቅት በጣም የታወቁና ደግሞ ለዓመታት ስማቸው እንኳ ተጠርቶ ወይንም በፍጹም ታዘው የማያውቁ መድሐኒቶች አሉ።''

'' ስለዚህ የአንዲት አቧራ የወረሳት ቢልቃጥ መጥፋት እስከዚ ህም ዓይንን የሚስብ ሊሆን አይችልም ነው ። አይደለም ? ''

“ ትክክል! አልፎ አልፎ ያው ንብረት ቆጠራ ይደረጋል ። ማንም ሰው ቢሆን ሞርፊን ታርታሬት የሚል ነገር ለረጅም ጊዜ አዳምጦ አያውቅ ። ለሆነ ጉዳይ እስካልተፈለገ የቢልቃጡ መጥፋት ፍጹም ሊታወቅ አይችልም ። ወይንም ንብረት ቆጠራ ካልተደረገ በስተቀር። ሦስቱም መድሐኒት አካፋፋዮች የመርዙ ቁምጣጥንና የአደገኛ መድሐኒቶች ቁምጣጥኖች ቁልፎች አሉዋቸው ። ቁምጣጥኖቹ በተፈለጉ ጊዜ ይከፈታሉ ። ዘወትር ሥራ በሚበዛበት ወቅት አንድ ሰው ወደ ነዚህ ቁምጣጥኖች መመላለስ ይኖርበታል ። ቁም ጣጥኑም ተከፍቶ እስከ ሥራ መጨረሻ እንደዚያው ይቆያል ። ”

“ ከሲሊያ በስተቀር ሊከፍተው የሚችል ሌላ ሰው ይኖራል ?”

“ ሁለቱ መድሐኒት አከፋፋይ ሴቶችም አሉ ። ቢሆንም ከሒኮ ሪ ጎዳና ዎንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ። አንዷ ከሥፍራው አራት ዓመታት ቆይታለች ። ሌላይቱ የመጣችው ከአንድ ሁለት ሣምንታት በፊት ነው ። ከዲቮን ሆስፒታል ነበረች ። ጥሩ ሪኮርድ ነው ያላት ። ከ‘ዚያ ሌላ የሚገኙት ከቅድስት ካታሪን ለዓመታት የቆዩት ነባር ፋርማሲስቶች ናቸው ። እንግዲህ ወደ ቁምጣጥኑ እጃቸውን ለመሰደድ መብትና ችሎታ ሀላፊነትም ያላቸው እነዚህ ናቸው ። ሌላዋ ወለል የምታጸዳዳዋ አሮጊት ናት ። ከማለዳው ከሦስት እስከ አራት ስትን ከላወስ ስለምትቆይ ሴቶቹ ልጆች ከተመላላሾቹ ሕመማን ማስተና ገጃ ወይንም ከመድሐኒት ማከፋፈያው ሲሠሩ አንዲት ብልቃጥ ማጮለግ ትችላለች ። ነገር ግን በሆስፒታሉ ውስጥ ለብዙ ዓመታት ስለ ሠራች ያም ቢሆን የሚደረግ አይሆንም ። የላቦራቷሩ ሠራተኛ ብዙ ቢልቃጦችን ስለሚያሠራባቸው ከፈለገ አንዱን የሚከለክለው አይኖርም ። ነገር ግን እነዚህ አስተያዬቶች በመላ ሊሆኑ የሚችሉ አይደሉም ። ”

“ ታዲያ ከውጭ ወደ መድሐኒት ማከፋፈያው የሚገቡ ሰዎች አሉ ? ”

“ በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ ብዙ ሰዎች አሉ ። ለምሳሌ በመድሐኒት ማከፋፈያው አድርገው ወደ ቺፍ ፋርማሲስቱ ጽሕፈት ቤት የሚሔዱት ፣ ወይንም ከጅምላ መድሐኒት ሻጭ መደብሮች የሚመጡ ባለጉዳዮችም ወደ መድሐኒት አምራች መምሪያዎች የሚጓዙት በዚያው ነው ። አልፎ አልፎም አንዳንድ የመድሐኒት አከፋፋዮች ወዳጆችና ዘመዶችም ሊጠይቋቸው ይመጣሉ — ይህ እንኳ ሊሆን ይችላል ቢባል እንጂ የተለመደ አይደለም ። ”

“ የአሁኑ የተሻለ ነው ። ማነው ታዲያ በቅርቡ ሴሊያ አሙስቲንን ለመጠየቅ የመጣ ? ”

ሻርፕ ማስታወሻውን ተመለከተ ።

“ እንዲት ፖትሪሺያ ሌን የምትባል ወይዘሪት ያለፈውን ሣምንት ማክሰኞ መጥታ ነበር ። ሴሊያ ከመድሐኒት ማከፋፈያው የሥራ ሠዓት በኋላ ከፊልም ቤት መጥታ እንድታገኛት ፊልጋ ነበር ። ”

“ ፖትሪሺያ ሌን ” አለ ፖይሮት በሀሳብ ተውጦ ።

“ የቆየችውም ለሦስት ደቂቃዎች ብቻ ሲሆን ወደ መርዙ ቁም ሣጥንም አልቀረበች ። የቆመችውም ከተመላላሽ ሀሙማኖች መኝ ገሪያ መስኰት ሆና ሲሆን ሴሊያንና እንዲት ሌላ ልጅ ስታነጋግር ነበረች ። እንዲት ጥቁር ወይዘሪትም ስትመጣ ማየታቸውን አስታውሰዋል አ— ከሁለት ሣምንታት በፊት ነው የሚሉት ። ወይዘሪቷ እኳኋኗ ትንሽ ከበድ ያለ ነገር ነበር እንደሚናገሩት ። ሥራውንም በጣም እንደምታፈቅረው በመግለጽ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማስታወሻዎችም ወስዳ ነበር።የእንግሊዝኛ ቋንቋዋ በጣም የተጣራ ነው ።”

“ኤልሳቤጥ ጆሀንሰተን ልትሆንም ትችላለች ? ለሥራው ያላትን ዝንባሌ ገልጻለች ። አልነበረም ? ”

“ ተሠዓት በኋላው የክሊኒክ በጎ አድራጎት ክፍለ ጊዜ ነበር ። በእንደዚህ መሳይ ነገሮች አደረጃጀት በጣም ነበር የተደሰተችው ። በተጨማሪ ስለተቅማጥና የቆዳ ኢንፌክሽን የመሣሰሉት በሽታዎች በተሰጡት መድሐኒቶች ላይ የነበራትን አድናቆት ገልፃም ነበር ። ”

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

“ ሌላስ ? ”

“ ሌላ ማንም የታወቀ ሰው የለም ። ”

“ ዶክተሮች ወደ ማከፋፈያው ይመጣሉ ? ”

ሻርፕ ፈገግ አለ ።

“ ሀ·ልጊዜ ይመጣሉ ። ለሥራ ጉዳይና እንደዚሁም ይመጣሉ ። አንዳንድ ጊዜ ስለአንድ የተሰየ ቀመር ለመጠየቅ ሲመጡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከመድሐኒት መከፋፈያው ያለውንም ለማወቅ ይመጣሉ ።”

“ ከመድሐኒት ማከፋፈያው ያለውን ለማወቅ ?”

“ አዎን ፣ እንደዚያ ብዬ አስብኩኝ ። አንዳንዴ ምክር ይጠይቃሉ — ማለት ለአንዳንድ ዝግጅቶች በተለይ የሀመምተኛውን ቆዳ

የሚያልጡ ለሚመስሉትና ከእንሽርሽራት ስለሚታረኑት ለማወቅ ፣ አንዳንዶቹ ሀኪሞች ደግሞ ሶመጫወት—አለ አይደለም ለ'ረፍትያህል ብቅ ይላሉ ። ብዙዎቹ ወጣቶችም ቬጂኒንና አስፕሪን ለመውሰድ የዞረ ድፖር (አዳሪ ስካር) ሲኖርባቸው ይንጋጋሉ — በዚያው ለነገሩ ያህል ከወይዛዝርቱ ካንዷ ላይ አንድ ሁለት የፍቅር ቃላትን ጣል ለማ ድረግም ያህል ሊመጡ ይችላሉ ብዬም አስባለሁ ። የሰው ልጅ ባህ ርይ ያ ው የሰው ልጅ ባህርይ ነው ። ታያለህ እንዴት እንደሆነ ? ም ንም ቲስፋ የለ ው ። ''

ፖይሮት ፣ '' በትክክል የማስታወስ በሆነ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ የሒኮሪ ጎዳና ቲማሪዎች ከቅድስት ካታሪን ግንኙነት አላ ቸው ። ቀይ ጸጉር ያለው ልጅና በት—በትማን —አለ ። ''

'' ሌዎናርድ ባትሰን ትክክል ነው ። ኮሊን ማክናብም ለድሀረ ምረቃ የሚያጠናው ከዚሁ ነው ። በተጨማሪም ከፊዚዩ — ቱራፒ መምሪያ የፖትሠራ ጂን ቶሚልሰን የተባለች ልጅ አለች ። ''

'' እነዚህ ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ ከመድሐኒት ማከፋፈያው ይገባሉ ? ''

'' አዎን ፣ ከዚህ ሌላ ምን ያስፈልጋል ። ማንም ቢሆን መቼ እንደመጡና እንደ ነበሩ የሚያስታውስ አይኖርም ። ሁልጊዜ ያዩዋ ቸዋል ። በዓይን ያውቋቸዋል ። ጂን ቶሚልሰን በነገራችን ላይ ኪቆ ዩት መድሐኒት አከፋፋዮች የአንዱ ወዳጅ ናት — ''

'' ቀላል አይደለም '' አለ ፖይሮት ።

'' ቀላል አይደለም እላለሁ እኔም ! አየህ ማንም ከዚያ የሚሠራ ሁሉ ከመርዙ ቁምሣጥን ለመመልከት ይችላል ። በዚያም አጋጣሚ ይህን ያህል አደገኛ መርዝ እስኪ ስለምን ያስፈልጋል ? ወይንም ሌላ ተመሣሣይ ጥያቄ ፣ በዛሬው ጊዜ የሚጠቀምባቸው ማን ይሆን ? ሲሉ ይሠነዘራሉ ። ማንም ቢሆን ይህንን መላልሶ ማሰብና ማስታ ወስም ይችላል ። ''

ሻርፕ ትንሽ ከቆየ በኋላ ፣

''የእኛ ይሆናል መላ —ምት ሴሊያ አውስቲን አንድ የሆነ ሰው ሞርፊያ ሰጥቷት ከዚያ በኋላ የሞርፊያውን ቢልቃጥ በማስቀመጥ የተቀዳደደውን ደብዳቤ ከክፍሏ ራሷን በ'ራሷ የገደለች ለማስመ ሰል አስቀምጠው ነው ። ግን ለምን መሴ ፖይሮት ? ለምን ? ''

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ። ሻርፕ ቀጠለ ፣

“ ዛሬ ጠዋት አንድ የሆነ ሰው ስለ ሥርቆት ሱስ በሽታ (ክሊ ፕቶማንያ) ሴሊያ አውስቲን ሊኖርባት ይችላል ሲል እንደገለጸ ጠቅሰህልኝ ነበር ። ”

ፖይሮት ትንሽ እየከበደው ቀጠለ ።

“ ያ የኔ ተራ ግምት ነው ። ይሀን ብልህነት አስባው ከሆነ አጠራጣሪ መስሎ ነበር የታየኝ ። ”

“ ታዲያ ማነው ? ”

“ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከተማሪዎቹ ሦስቱ እንደዚህ ዐይነት አስተሳሰብ ነበራቸው ። ሊዎናርድ ባትሰን ምናልባት ለዚህ የሚሆን እውቀት ሳይኖረው አይቀርም ። ኮሊን ራሳቸውን መቆጣጠር ስለተሳናቸው ሰዎች ያለውን አስተሳሰብ ያውቃል ። ምናልባት እንደዚያ ያለ ተመሣሣይ ነገር ለሴሊያ በመጠቃቀስ ወይንም በመቀላለድ ሊያስተምራት ሞክሮ ይሆናል ። ነገር ግን በእውነት እንዲህ ያለው ጉዳይ ላይ ከወር ወደ ወር ሲል እንዴት ለመረዳት እንዳዳገተው ሊገባኝ አይችልም ? ምናልባት የራስ ወዳድነት ግፊት ከሌለው በስተቀር ፣ ወይንም ራሱ ነው ተብሎ ከተገመተው ሌላ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ፣ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ? (እንዲያ ዓይነቱ ነገር አንድ ሰው ሁልጊዜም ሊያስበው የሚገባው ጉዳይ ነው) ኒጌል ቻፕማን በጣም ተንኰለኛና ለእመሉ ደግሞ ቀንዐተኛ የሆነ አዕምሮ አለው ። ለራሱ ጥሩ ጨዋታ መስሎ ነው የሚታየው ። እንዳው የሕሊናውን ወቀሳ የማይፈራ ነገር መስሎ ነው የሚታየኝ ። አለ አይደል ? በእድሜ የበሰለ አስቸጋሪ ሀጻን ነገር ። ሦስተኛው ሰው ከሀሳቤ ያለችው ወጣት ሴት ቫሌሪ ሆብሐውስ ትባላለች ። በርግጥ ጭንቅላት ያላት ፣ በትምህርቷና በአመለካከቷ ዘመናዊ የሆነችና የኮሊንን ሁኔታ ለመገመትና ለመዳኘት የሚያስችላትን ያህል ስለ ሳይኮሎጂ ያነበበችም ሳትሆን አትቀርም ። ሴሊያን የምትወዳት ከሆነም ኮሊንን ማቃቄሉ ሕጋዊ ጨዋታ ይመስላታል ። ”

“ ሎዎናርድ በትሰን ፣ ኒጌል ቻፕማንን ፣ ቫሌሪ ሆብሐውስ ” አለ ሻርፕ ስሞቹን እየፃፈ ። “ ለዚህ ጉርሻ እግዜር ይስጥልኝ ። በም ጠይቃቸው ወቅት አልረሳም ። ሕንዶቹስ ? ከመካከላቸው አንዱ የህክምና ተማሪ ነው ? ”

“ የ‘ርሱ አዕምሮው በእጠቃላይ በፖለቲካ ሕማመ - ፍርሃ ትና በጥንቃቄ ብርገጋ የተወጠረ ነው ። ይሀን የሥርቆት - ሱስ በሽታ ሀሳብ ለሴሊያ አውስቲን ለመሠንዘር የሚችልና እንዲህ መሳዩንም ምክር የምትቀበለው መስሎ አይታየኝም ። ”

‘‘ ይህ ብቻ ነው ልትሰጠኝ የምትችለው ርዳታ መሲ ፖይሮት ?’’ ሲል ሻርፕ ከመቀመጫው በመነሳት ማስታወሻ ደብተሩን እየከ ዳደነ እያለ ጠየቀ ።

‘‘ ምንም ነገር ! ለምን ብዬ ? ’’

‘‘ በራሴው ወሰን እውቀት የምችለውን አደርጋለሁ ። ለ‘ኔ ያለኝ አንድ የተግባር መንገድ ብቻ ነው ። ’’

‘‘ ያ መንገድ ? ’’

ፖይሮት በረጅሙ ተነፈሰ ።

‘‘ ውይይት ነው ወዳጄ ። ውይይት እንደገና ደግሞ ውይይት ! እስከዛሬ ያየኋቸው ነፍሰ — ገዳዮች ብዙ ማውራት ይወዳሉ ። በ‘ኔ የተሰባሰበ ረጋ ብሎ የሚናገር ሰው ወንጀል በአብዛኛው ሁኔታ የማይ ሠራ ነው — ካደረገው በቀለለ ሀይለኛና በትክክል ግልጽ በሆነ መን ገድ ነው ። ነገር ግን የኛ ብልህ ነፍስ ገዳይ አንድ ቀን ወይንም በሆነ ጊዜ አስከፊው እጣ ፈንታ እንዲታያለት የሜሪውን ውል የት ላይ ነው ቋጠሮው በሚል መልክ ያስቀምጠዋል ። ወዳጄ ! እስኪ እነዚህን ሰዎች እነጋግራቸው ። በቀላል መስቀለኛ ጥያቄ ራስህን አትወስን ! አመለካ ከታቸውን ደግፍ ! አበረታታቸው ። ርዳታቸውን ጠይቅ ፣ ‘ሚጠረጥ ሩትን ሁሉ ለማወቅ ጥረት አድርግ — ነገር ግን ስለፈጣሪ ! ስለ ሙያህ ማስተማሬ እንዳልሆነ እወቅልኝ ። ችሎታዎችህን አስቀድሜ እውቃ ቸዋለሁ ። ’’

ሻርፕ በ‘ርጋታ ፈገግ አለ ።

‘‘ አዎን ’’ አለ ። ‘‘ ዘወትር መልካምና — በቅንነት ላይ የተመ ሠረተ ታላቅ ርዳታ ሳገኝ ነበርኩኝ ’’ አለ ።

ሁለቱ ሰዎች ወትሮው በመካከላቸው በቆየ ስሜት በፈገግታ ተያዩ ። ሻርፕ ከተቀመጠበት ተነስቶ ቆመ ።

‘‘ እያንዳንዳቸው ነፍሰ ገዳይ ሊሆኑ እንደሚችሉ አድርጌ ነው የተመለከትኳቸው ’’ አለ ዝግ ብሎ ።

‘‘ እኔም እንደዚያው ነው የማስበው ’’ አለ ፖይሮት በሀሳብ ተውጦ ። ‘‘ ሊዎናርድ ባትሰን ለምሳሌ ቁጡነት አለበት ። ራሱንም መቆጣጠር አይችልም ። ቫሌሪ ሆብሐውስ ደግሞ ጭንቅላት ስላላት ማንኛውንም ነገር በብልህነት ማዘጋጀት ይሆንላታል ። ኒጌል ቻኘ ማን እኩያ የማይገኝለት የሕጻን ባህርይ ያለው ነው ። ያች ፈረንሣይቷ ወይዘሪት ደግሞ ጠቀም ያለ ገንዘብ ካገኘች ለመግደልም የማትመ

ለስ ናት ። ፖትሪሺያ ሌን የእማዊ ባህርይ የሚታይባት ናት ። የእማዊ ባህርይ ያላቸው ሴቶች ደግሞ ጨካኞች ናቸው ። አሜሪካዊቷ ወደ ዘሪት ሳሊ ፊንች በጣም ተጫዋችና ደስተኛ ልጅ ናት ። ነገር ግንአንድን ነገር አስመስላ መታመን ከፈለገች ከሌሎቹ የተሻለ ችሎታ አላት ። ጄን ቶሚልሰን ጣፋጭነትና መንፈሣዊነት የሰፈነባት ትመስላለች ። ነገር ግን የሰንበት ጸሎታቸውን በእውነተኛ የመንፈሥ ምሉዕነት የሚያቀርቡ ነፍሰ - ገዳዮችን እናውቃለን ። እና ይህች ሕንዳዊት ልጃ ገረድ ኤልሳቤጥ ጀሀንስተን ምናልባት ከሆስቴሉ ካለች በአጠቃላይ የተሻለ ሞንቅላት ይኖራታል ። ውስጣዊ ስሜታዊ ሕይወቷን ለጭን ንቅላቷ ያስገዛች ልጅ ናት ። አደገኛ ነው ። እንዲህ ነው ብለን ልን ናገርለት የማይቻለን ለመግደል የሚገፋፉ ምክንያቶች ያሉት አንድ ደስተኛ ወጣት አፍሪካዊም አለ ። ሳይኮሎጂስቱ ኮሊን ማክናብም አለ ። ሀኪም ሆይ ራስህን ታክማለህ ? የሚባሉ ብዙ ሳይኮሎጂስቶች ነው አንድ ሰው የሚያውቀው ? ''

'' በእግዚአብሔር ፖይሮት ። ራሴን ነው ያዞርከው ! ማንም መግደል 'ሚችል ሰው የለም ? ''

'' ምንጊዜም ቢሆን የሚገርመኝ ይኼው ነው '' አለሔር ኩሌ ፖይሮት ።



— 9 —

ኢንስፔክተር ሻርፕ በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ከተቀመጠበት ወንበር በጀርባው ተለጥጦ በመሀረም ግንባሩን አሻሸው። እንዲት ቁጡ አኩራፊና ከመናገር ይልቅ ዕንባ የሚቀድማት ፈረንሣዊት ወይዘሪት ካኔጋገረ በኃላ አድናቂ ተሣላቂ ምንም ለመግባባት የማይፈልግ ፈረ ንሣዊ ወጣት ፣ ቀርፋፋና ተጠራጣሪ የዳች ተወላጅ ወሬኛና ችኩል አምባንርተኛ ግብጻዊ በየተራቸው አነጋገረ ። በተጨማሪ በጣም ው ስን የሆኑ ቃላትን ከሁለት ወጣት የቱርክ ተወላጅ ተማሪዎች ተለ ዋወጠ ። በእውነት የሚናገረውን አያወቁትም ነበር ። ከወጣቱ ኢራ ቃዊም ተመሣሣይ ምልልስ ተደረገ ። ርግጠኛ ነው ከእነዚህ ማንም ምንም አላደረገ ። ምንም ሊያደርግ አይቻለውም ። በሴሊያ አውስ ቲን ሞት ረገድ ምንም ሊፈጥሩ አይችሉም ። በእንዳንድ ቃላት ብቻ ተራ በተራ አሰናብቷቸው አሁን ደግሞ ከሚስተር አኪቦምቦ ተመ ሣሣይ ሁኔታ ለመፈጸም በመዘጋጀት ላይ ነበር ።

ወጣቱ ምዕራብ አፍሪካዊ አረፋ የመሰሉ ጥርሶቹን እያሳየ ከት ልቅ ሰው ይልቅ የሕጻን በሚመስል ፈገግታ ተመለከተው ።

" ልረዳህ ፈልጋለሁ - አምን በተቻለ " አለ ። " ለኔ በጣም ጥሩ ልጅ ነበረች። ይህች የሞተችዋ ወይዘሪት። እንድ ጊዜ አንድ ሣጥን ኤደንቦሮ ሮክ ከዚያም በፊት በሕይወቱ ቀምሺ የማላውቀው ጣፋጭ ሰጥታኝ ነበር ። መገደሏ በጣም የሚያሳዝን ነው ። ምናልባት የደም ጉማ ይሆን ? ወይንም ምናልባት አባቶቿና አጎቶቿ ይሆኑ ስማቸውን የሚያጎድፍ ወሬ ሰምተው የገደሏት ? "

ኢንስፔክተር ሻርፕ እነዚህ በሩቅ የሚደረጉ ነገሮች እንዳል ሆኑ አረጋገጠለት ። ወጣቱ ሰው በሀዘን ራሱን ነቀነቀ ።

" ለምን እንዲህ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም " አለ ። " ከዚህ ያለ ማንኛውም ሰው ለምን እንደዚህ ሊያደርጋት እንደፈለገ ሊገ ባኝ አይችልም ። እስኪ ትንሽ ከጸጉሯና ከጥፍሯ ቁርጥራጮች ስጠኝ እባክህ ? " አለ ። በመቀጠልም ። " ጥንቃቄ በሆነ መንገድ ላገኘው እችል እንደሆነ እሞክራለሁ ። ሣይንሣዊም ፣ ዘመናዊም ሳይሆን እኔ ከመጣሁበት ሥፍራ በጣም የሚጠቀሙበት መንገድ ነው " አለ ።

“መልካም ፣ አመሰግናለሁ ሚስተር አኪቦምቦ ። ነገር ግን አስ ፈላጊ መስሎ አይታየኝም ። እኛ - አ - እንደዚያ ዓይነት ነገሮችን እዚህ ሥፍራ አንጠቀምም ። ”

“ የለም ጌታዬ! በደንብ ይገባኛል ። ዘመናዊ አሰ ያለም ። የአቶ ቶሚክ ዘመን ግንኙት አይደለም ። ከሀገራችሁ በአዲሶቹ ዘመናዊ ፖሊ ሶች ከጥቅም ላይ አይውልም ። ከጫካ በሚኖሩ ሽማግሌዎች ጥንታ ዊያን ሰዎች ብቻ ነው ። ሁሉም ዘመናዊ ሥልቶች የበለጡና ፍጹም ውጤታማ እንደሆኑም አውቃለሁ ። ” ሚስተር አኪቦምቦ በትህትና እጅ በመንሳት ተነሳ ። ኢንስፔክተር ቫርፕ ለራሱ አጉመተመተ ።

“ ከልቤ ውጤት እንደምናገኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ስማችንን ለመጠበቅ ብቻ ስንል ነው ። ”

ተከታዩ መጠይቁ ከኒጌል ቻፕማን ነበር ። እርሱም ቢሆን የጠ ያቂነቱን ሚና ከ‘ጁ አስገብቶት አረፈው ።

“ይህ ፍጹም የተለየ ጉዳይ ነው ፣ አይደለም?” አለ ። ራስን በራስ ማጥፋት ነው ስትሉ ከተሳሳተ ዛፍ ላይ ቅርፊት እየላጣችሁ መሆኑን አስቀድሜ አውቄዋለሁ ። አጥጋቢ ሆኖም ያገኘሁት ከ‘ኔ አረንጓዴ ቀለም የቀለም ብዕሯን ማጠጣቷ የጉዳዩ ሁሉ መሠረታዊ ምህዋር አድርጌ ባሰብኩት ጊዜ ነው ። ነፍስ - ገዳዩ ያላየው አንድ ነገር ማለት ነው ። ለዚህ ወንጀል የመገፋፋት መንስኤ መሆን ስለሚችሉት ጉዳ ዮች ትኩረት የሰጣችሁ ይመስለኛል ። አይደለም ? ”

“ ይህን ጥያቄ ስጠይቅ ነበር ሚስተር ቻፕማንን ” አለ ኮም ጨጭ ብሎ ኢንስፔክተር ቫርፕ ።

“እንዴ በሚገባ ፣ በሚገባ ” ኦለ ኒጌል በበላይነት ስሜት እጁን አያወዛወዘ ። “ ኦለ አይደለም አቋራጭ - መንገድ መነዛነዙን መቀ ጠል ኦለብን ። ስም — ኒጌል ቻኘማን ። ዕድሜ — ሀያ አምስት ። የትው ልድ ሥፍራ—ናጋሳኪ— በጣም የሚገርም ሥፍራ ነው የሚመስለው። አባባና እማማ በጊዜው ከዚያ ምን ሲያደርጉ እንደነበር ማሰብም አልችል ። እንደሚመስለኝ ዓለምን በመነብነት ላይ መሆን አለባ ቸው ። ያም ቢሆን በግዴታ ጃፓናዊ አያደርገኝም ይገባኛል ። በዘ መነ — መዲብና በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ከለንደን ዩኒቨርስቲ ዲፕ ሎማዬን አግኝለሁ ። ሌላ ለማወቅ የምትፈልገው ነገር ይኖር ይሆን?”

“ የቢት አድራሻህ የት ነው ሚስተር ቻፕማን ? ”

“ ምንም የቤት አድራሻ የለኝ ውድ ጌታዬ ! አባት አለኝ ነገር ግን ተጣልተናል ፣ የ‘ርሱ አድራሻ ከ‘ዚያ በኋላ የኔ አይደለም ። እና

ቁጥር 26 ሔኮሪ ጎዳናና ኮውትስ ባንክ ፣ የሊደንሆል ጎዳና ማቋረጫ ዎች በሙሉ ልገኝባቸው የምችልባቸው አድራሻዎቼ ናቸው ። አለ አይደለም በጉዞ ላይ ለተዋወቀ ሁ ባልንጀራው አንድ ሰ ው እንደገና የማያገኘው የሚሰጠው ዓይነት አድራሻ ነው ያለኝ ። ''

ኢንስፔክተር ቫርፕ ለዚህ ትምክህት ለወጠረው የኒጌል ዐይነ-አ ዐጣንት ም ንም መልስ አልሰጠም ። ' ኒጌለ-ቫን ' በፊትም አስ ቀድሞ ያውቃቸዋል ። በልቡም ይህ የኒጌል ዓይነ አውጣነት ከግድ ያው በተያያዘ ጉዳይ እጠየቃለሁ የሚል የቱፊጥሮ ቅብቅጥብጥነት ለመሸፈን መሆኑን ጠረጠረ ።

'' ሴሊያ አውስቲንን ምን ያህል ታውቃታለህ ? '' ሲል ጠየ ቀው ።

'' ያ እንኳ በርግጥ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው ። ሁልጊዜ ስለምንተያይ አውቃታለሁ ፣ እንግባባለን ። በመካከላችን ጥሩ ሁኔታ ነበረ ። ብቻ ይህንንም ያህል አላውቅትም ። በርግጥ ቅንጣት እንኳ ትኩረት ከ'ርሷ ላይ የለኝም ። ምናልባት እኔን ልትነቅፍ የምትችልበት አንዱ መን ገድ ይህ ብቻ ነው ። ''

'' ለአንድ ለሆነ ምክንያት የነቀፈችህ ጊዜ ነበር ? ''

'' አም፣ይህን የሚተነኳኩስ የአግብአ ስሜቴን አትወደውም ነበር። በርግጥ ለረጅም ጊዜ ተንኰል አ ውጠንጣኝና እንደ ኮሊን ማክናብ ወረበላ ወጣት አይደለሁም ። ያን ዓይነቱ ወረበላነት ሴቶችን ሶመ ሳብ ብቸኛው ስልት ነ ው ። ''

'' ሴሊያ አውስቲንን ለ መጨረሻ ጊዜ ያየሃት መቼ ነበር ? ''

'' ትላንት ማታ ራት ላይ፣ ሁላችንም እንኳን ደስ ያለሽ ስንላት ነበር፣ ታ ውቃለህ? ኮሊን ቲነስቶ ካገሣና ካቲመ መ በኋላ በመጨረሻ በዓይነ አፋርነትነና መጀጀል መቲጫጨቱን አበሰረ። ከዚያ ሁላች ንም አወጋጋንና አበቃ ። ''

'' ከ'ራት ላይ ነበር ወይንስ ከጋራ — አዳራሹ ? ''

'' የለም ከ'ራት ላይ ነበር ። ከዚያ በኋላ እኛ ወደ ጋራ - አዳራሹ ስንሔድ ኮሊን ደግሞ ወደ አንድ ሥፍራ ሔደ ። ''

'' የተቀራችሁት ከጋራ — አዳራሹ ቡና ስትጠጡ ነበራችሁ?''

'' ያን ፈላሽ ቡና ካልከው - አዎን '' አለ ኒጌል ።

'' ሴሊያ አውስቲን ቡና ጠጣች ? ''

“ አምን ይመስለኛል ። ግለቱ እኔ ቡና መጠጣት አለመጠጣቷን አላየሁም ። ነገር ግን የጠጣች መሆን አለባት ። ”

“ አንተ ራስህ ለነገሩ ያህል ቡና ቀድተህ አልሰጠህትም ?”

“ ምን ዓይነት ነገር ነው የምታወራው ! እንደዚያ እያልክ በዚያ ዘልቆ በሚገባ መንገድ ስትመለከተኝ ለሴሊያ ቡናውን ቀድቼ ያን ጊዜ ‘ ማይሰጥ መርዝ ሞልቼ ወይንም አንድ ሌላ ነገር አድርጌ መስጠቴን ታውቃለህ ማለት ነው ። ይህ ሩህ — ስት — ትውስት ይመስለኛል ። (ሔፕኖቲክ) ፣ ግን እውነቱን ለመነጋገር ሚስተር ሻርፕ ፍጹም ከአጠገቧም አልሔድኩኝም — ግልጽ ለማድረግ ቡና ስትጠጣም አል ተመለከትኳትም፣ አመንከኝም አላመንከኝ እውነቴን ነው ! ይህን አረጋ ግጥልሃለሁ ! ለሴሊያ እኔ ራሴ ምንም ስሜት ኖሮኝም አያውቅ ። ያ ከኮሊን ማከናብ ያደረጉትም ትጭጭት ምንም ዓይነት የነፍስ ወን ጀል በቀል ከአዕምሮዬ አልፈጠረብኝም ። ”

“ ምንም ዓይነት እንደምትለው ማማይ ነገር አስበ አልነበረም ሚስተር ቻፕማን ” አለ ሻርፕ ኮስተር ብሎ ። “ በጣም የተጣማት ኩኝ ካልሆነ በስተቀር ለዚህ የተለየ የፍቅር አቅጣጫ የለውም ። ነገር ግን አንድ ሰው ሴሊያ አውስቲንን ከዚህ በተለየ መንገድ ተመለከ ታት ለምን ? ”

“ ብቻ ለምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ኢንስፔክተር ።ነገሩ በጣም የተወሳሰበ ተንኮል የሚታይበት ነው ። ምክንያቱም ሴሊያ ምንም ተንኰል የሌለባት ልጅ ነበረች ። የምናገረው ነገር የሚገባህ ከሆነ ። አንድን ነገር ቶሎ ለመያዝ የማትቸኩል ፣ ትንሽ የምትሰለች ፣ ፍጹም ግሩም የሆነች የጠራች ናት ለማለት እችላለሁ ። ሳለዚህ ራሷን የምታጠፋ ልጅ አይደለችም ! ”

“ ለነዚያ ለጠፉ ጥቃቅን ነገሮች ሴሊያ አውስቲን በሀላፊነት በተጠየቀችበት ወቅት በጣም ተገርመህ ነበር ? ”

“ ወዳጄ ምነው በላባ መታኸኝ ! የማይመስል ነገር ብዬ ነው ያሰብኩት ። ”

“ እነዚያን ነገሮች ትሠራለች ብለህ ምናልባት አላሰብክ ይሆን?”

የኒጌል የመገረም አጸለካከት ፍጹም እውነተኛ ይመስላል ።

“ እኔ ትሠራለች ብዬ ልገምት ? ለምን ብዬ ? ”

“ እንዲያውም ጥያቄው እንደዚያ መሆን ይችላል ፣ አይችልም ? አንዳንድ ሰዎች የሚያሥቅ ባህርይ ነው ያላቸው ። ”

“ እምን በእውነት ፡ ነገር ‘ማያገባኝ ደያብ መሆን እችላለሁ ። ነገር ግን እየተካሔደ በነበረው የማያረባ ሥርቆት ምንም አልተደነ ቅሁበትም ። ”

“ እትቲልድ ? ”

“ የለም ቀልድም መስሎ የመታየት ሀሳብ ከአዕምሮዬ ተፈጥ ሮብኝም አያውቅ ። እውነቱን ነው ኢንስፔክተር ። ሥርቆቶቹ በመላ ሳይኮሎጂካዊ ነበሩ ። ”

“ ሲሊያ አውስቲን የሥርቆት ሱስ በሽተኛ (ክሊፕቶማኒያክ) ናት ብለህ ታምናለህ ? ”

“ እውነቱን ለመናገር ምንም ሌላ ትርጉም የለውም ኢንስፔ ክተር ። ”

“ምናልባት እኔ ‘ማውቀውን ያህል አንተ ስለ ሥርቆት ሱስ በሽታ (ክሊፕቶማኒያክስ) አታውቅም ማለት ነው ሚስተር ቻፕማን ። ”

“ ከዚህ የተሻለ ሌላ ሊሆን የሚችል ነገር ማሰብ አልችልም ።”

“ እንደው አንድ የሆነ ሰው ይህን መንገድ በመጠቀም ወይዘሪት አውስቲንን አነሳስቶ — እንደ መሣሪያ በመጠቀም ሚስተር ማክ ናብ በሷ ላይ ትኩረት እንዲኖረው ለማድረግ አይችልም ብለህ ታስ ባለህ ? ”

የኒጌል ዓይኖች በአድናቆት ቅናት አበሩ ።

“ ይህ እንኳ በእውነት ሊሆን የሚችል ነገር ነው ኢንስፔክተር ሻርፕ ” አለው ። ቀጥሎም “ ታውቃለህ ስለዚህ ነገር ሳስብ ፍጹም ትክክል ነው የሚመስለኝ። በርግጥ ኮሊን አሠሩን ገሠሩን የሚቀበል አንጀት ነው ያለው ። ከነግሣንግሱ መዋጥ ነው ። ” አለ ኒጌል የሰማ ው አስተያዬት አንጀቱን አርሶት ውስጡን እየተፍነከነከ ። ቀጥ ሎም ራሱን በሀዘን ነቀነቀ ።

“ ነገር ግን ሴሊያ እንዲያ ማድረግ አልነበረባትም ” አለ ። “ በጣም ኮስታራ ልጅ ነበረች ። በኮሊን ላይ ፍጹም ቀልዳበትም አታ ውቅ ። ስለርሱ የጅል ርህራሔ ነበራት ። ”

“ ከዚህ ቤት ሲካሔድ ስለቆዩት ነገሮች እንዲያው የራስህ የሆ ነም ሀሳብ አልነበረህም ሚስተር ቻፕማን?ለምሳሌ በወይዘሪት ጆህን ስተን ወረቀቶች ላይ ቀለም እንደማፍሰስ ስለመሳሰሉት ነገሮች ? ”

“ እኔን እንደዚያ አድርጓል ብለህ ካሰብህ ኢንስፔክተር ሻርፕ በጣም ሥህተት ይሆናል ። በርግጥ በአረንጓዴ ቀለም መሆኑ እኔን ሊያ

ሊጠረጥረኝ ይችላል ። ግን ምነው ብለህ ብትጠይቀኝ በታ ከፋት ነው አልሃለሁ ። ''

'' ምን ? ክፋት ? ''

'' ቀለሜን መጠቀም ። አንድ የሆነ ሰው ሆነ ብሎ ተለሜን ተጠ ቅሞበታል ። ከዚህ ብዙ ጠባብ አስተሳሰብ አለ ኢንስፔክተር ። ''

ኢንስፔክተሩ ኮስተር ብሎ ተመለከተው ።

'' የጠበበ አስተሳሰብ አለ ስትል በትክክል ምን ማለትህ ነው ?''

ነገር ግን ወዲያውኑ የኒጌለ ፊት ተለዋወጠ ፣ ስሜቱን በአንድ ጊዜ አፈነው ። ቁጣም ሀዘንም ወይንም ደስታ አይታዩበትም ።

''በእውነት ሌላ ነገር ማለቴ እንኳ አልነበረም ። አለ አይደ ለም፣ እንደዚህ ብዙ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ እንደዚህ ዓይነት ጠባብነት መከሰቱ የማይቀር ነው ። '' ከኢንስፔክተር ቫርፕ የስም ዝርዝር ተከታዩ ሰው ሊዎናርድ በትሰን ነው ። ሊን በትሰን ከኒጌል የበለጠ ተጨንቋል ። ምንም እንኳን አኳኋናቸው የተለያየ ቢሆንም ተጠራጣሪነትና ለጸብ የተዘጋጀ መሆኑ ይታይበታል ። ''

'' መልካም ! '' ሲል አንቧረቀ ። የመጀመሪያዎቹ የተለመዱት መጠይቆች እንዳለቁ ፣ '' ለሴሊያ ቡና ቀድቼ ሰጥቻታለሁ ። ታዲያ ምን ይሁን ? '' አለ ።

'' ከራት በኋላ ቡናዋን ነው የሰጠኋት — እንደዚያ ማለትህ ነው ሚስተር በትሰን ? ''

'' አዎን ። ስኒውን ከማሞቂያው ሞልቼ ከአጠገቧ አስቀመጥኩት። አመንክም አላመንክ ! ነገር ግን ሞርፊያው ከውስጡ አልነበረበትም ።''

'' ስትጠጣው አይተሃል ? ''

'' የለም ስትጠጣ እንኳ አላየኋትም ። ሁላችንም ወዲያ ወዲህ ስንል ነበርን ። ወዲያውኑ ከአንድ ሰው መከራከር ጀመርኩኝ ። ስት ጠጣ አላየኋትም ። በዚህ ላይ በአካባቢዋ ሌሎችም ሰዎች ነበሩ ።''

'' ገባኝ ! በርግጥ ማለት የፈለከው ማንም ሰው ከቡና ስኒዋ ሞርፊያ ሊጨምር ይችላል አይደለም ? ''

' ከአንድ ሰው ስኒ አንድ ነገር ለመጨመር ሞክር ! ሁሉም ሰው ያያሃል ። ''

'' እንዲያ እንኳ ማለት አንችልም '' አለ ቫርፕ ።

ሌን በንዴት አምቧረቀ ።

“ ለምን ስል ይህችን ልጅ የምመርዛት ይመስልሃል ? እኔ እን ዲህ የማደርግበት ምንም ምክንያት የለኝም ። ”

“የለም ! አንተ ልትመርዛት ፈልገህ ነበር ብዬ አልተናገርኩም ።”

“ መርዙን የወሰደች ራሷ ናት ! ራሷ መሆን አለባት ! ከዚህ የተለየ ነገር ሊኖር አይችልም ። ”

“ እንደዚያ ሊሆን ይችል ነበር ይኸ ራስን - በ‘ራስ የማጥፋቱ ማታለያ ደብዳቤ ባይኖር ኖሮ ። ”

“ እኔ ለማታለል ! እርሷ ናት የጻፈችው ፣ አይደለችም ? ”

“ በዚያ ግለጻ ከጻፈችው ደብዳቤ ነው ። ”

“ መልካም — ከጻፈችው ላይ ትንሽ ቀዳ ራሷን ስለማጥፋቷ ልትጠቀምበት ትችላለች ። ”

“ ተው ! ተው ! ሚስተር ባትሰን ። ራስን በራስ ለማጥፋት ደብ ዳቤ የምትጽፍ ከሆነ አንድ ደብዳቤ መጻፍ ትችላለህ ። ለሌላ ሰው የጻፍከውን ደብዳቤ ወስደህ በጥንቃቄ አንዲት የተለየች አንቀጽ ብቻ በመቅደድ እንዲህ ያለ ሥራ አትሠራም ። ”

“ ላደርገው እችላለሁ ። ሰዎች ሲባሉ ሁሉንም የማይጠበቁ ነገ ሮች ይሠራሉ ። ”

“ እንደዚያ ከሆነ የተቀረው ደብዳቤ የት ሔደ ? ”

“ እንዴት ማወቅ እችላለሁ ? ያ የአንተ እንጂ የኔ ሥራ አይደ ለም ። ”

“ አዎን ! ሥራዬ እያደረኩት ነኝ ። የምጠይቅህን ጥያቄዎች በሥነ - ሥርዓት እንድትመልስ ትጠየቃለህ ሚስተር በትሰን ። ”

“ መልካም ! ምንድነው ማወቅ የፈለከው ? እኔ ልጅቷን አልገ ደልኩም ፣ ለመግደልም ‘ሚያበቁኝ ምክንያቶች የሉኝም ። ”

“ ትወዳት ነበር ? ”

ሌን ቁጣውን በመቀነስ ፣ “ አዎን በጣም እወዳት ነበር ። ጥሩ ልጅ ነበረች ። ትንሽ ሞኛሞኝነት ቢኖርባትም ጥሩ ሰው ናት ” አለ ።

“ብዙ ሰው ለረጅም ጊዜ ሲቸገርበት የቆየውን የዕቃዎችን መጥ ፋት እኔ ነኝ ባለች ጊዜ አምነሃት ነበር ? ”

“ አዎን ፣ መቼም እኔ እስካለች ድረስ አምኛታለሁ ። ነገር ግን በጣም እንግዳ ጉዳይ ነው ። ”

“ እንደዚያ ማድረጓ ትክክል አልነበረም ብለህ አስበህ ነበር ? ”

“ እንደዚያ እንኳ አላሰብኩም ፣ የለም በእውነት ። ”

ያ አምባገርተኛ ጸባዩ እየበረደ ሔደ ። አሁን ራሱን መከላከሉን ትቶ በግልጽ ለሚያስጨንቀው ችግር አዕምሮውን አማረከ ።

“ እንዲህ የሥርቆት ሱስ በሽታ (ኪሊፕቶማኒያክ) ያላት ሰው ዓይነት አይደለችም የምለው ነገር ከገባህ ” ኦለ ። “ ሌላም አል ነበረች ። ”

“ ይህንን ለምን እንዳደረገችው ሊኖራት የሚችለውን ሌላ ምክ ንያት ማሰብ አትችልም ? ”

“ ሌላ ምክንያት ? ሌላ ምን ምክንያት ሊኖራት ይችላል ”

“ ምናልባት የሚስተር ኮሊን ማክናብንን ስሜት ለማነቃቃት ፈለጋ ይሆናል ። ”

“ ያ እንኳ ትንሽ ሊሆን የሚችል ነገር ነው ? ”
“ ግን እኮ ስሜት አሳድሮባታል ። ”

“ አዎን ! በርግጥ አሳድሮባታል ። ኮሊን ለማንኛውም ሳይኮሎ ጂካዊ ቀውስ ሙት የሆነ ጉጉ ነው ። ”

“እና ሴሊያ አውስቲን ያንን የምታውቅ ቢሆን . . . ”

ሌን ራሱን ነቀነቀ ።

“እዚህ ላይ ተሣሥተሃል ። እንደዚያ ዓይነቱን ነገር ለማሰብ የም ትችል አልነበረችም ። ማለቴ እንደው የዕቅድ እንኳ እውቀትም አልነበራት ። ”

“ አንተ ግን እውቀቱ አለህ ፣ የለህም ? ”

“ ምን ማለትህ ነው ? ”

“ ማለቴ ከቅን መንፈሥ በመነሳት እንደዚያ ዓይነት አስተያ የት ሰጥተሃት ሊሆን ይችላል ነው ። ”

ሌን ትንሽ ዛቅ አለ ።

“ እንደዚያ ዓይነት የማይረባ ነገር ይሠራል ብለህ ትገምታለህ ? እብድ ነህ ! ”

ኢንስፔክተሩ ጥያቄውን ለወጥ አደረገ ።

“ ለመሆኑ ከኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ወረቀቶች ላይ ቀለም ያፈሠ ችው ሴሊያ አ ዮስቲን ነች ብለህ ትገምታለህ ወይንስ ሌላ ሰው ? ”

“ ሌላ ሰው፣ ሴሊያ እንደዚያ አላደረኩም ስትል ተናግራለች ። እኔም አምኛታለሁ ። ሴሊያ ሌሎች ሰዎች እንደሚያደርጉት በቢስ ተናዳም አታውቅ ። ”

“ ታዲያ ማነው የተናደደባት ? ለምን ? ”

“ ታውቃለህ ሰዎችን ተንኮስ ታደርጋለች ።” አለና ሌን ለእን ድና ለሁለት ደቂቃዎች ሲያስብ ከቆየ በኃላ፣ “የማይረባ ነገር የሚናገር ሰው ሲያጋጥማት፣ በጠረጴዛው አሻግራ እየተመለከተች በዚያ ሁል ጊዜም በምትገልጽበት እኳኋን ፣ ‘ እውነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን እፈራለሁ ። በቆጠራ እንደሚታውቀው . . . ’ በቃ እንደዚህ የመሳ ሰሉ ነገሮችን ነበር የምትነጋገረው ። አዎን ! ግን ታውቃለህ — እንደ መጣላቸው የሚናገሩ ሰዎችን ያናድዳል — በተለይ ለምሣሌ ያህል እንደ ኒጌል ቻፕማን የመሳሰሉ ሰዎችን ። ”

“ አዎን ፣ ኒጌል ቻፕማን ። ”

“ በዚህም ላይ አረንጓዴ ቀለም ነው ። ”

“ አዎን ፣ እንግዲህ ሊሆን ይችላል እላለሁ ። እንዳው ክፉ የማይ ረባ ሰው ነው። ታውቃለህ በዚህ ላይ የዘር ጥላቻ ስሜትም በትንሹ አያ ጣውም ። ከመካከላችን ርሱ ብቻ ነው ይህን ዓይነት ስሜት ያለው ።”

“ ካለህ ትውስት በዚህ ትክክለኛውን የመናገርና የማረም ፀባ ይዋ ወይዘሪት ጆሀንሰተን ያበሳጨችውንና ያስቆጣችውን ልትነ ግረኝ ትችላለህ ? ”

“ መልካም ፣ ኮሊን ማክናብ ብዙውን ጊዜ እንደተከፋባት ነበር ። ጄንትቶሚልሰንንም ከአንድ ከሁለት ጊዜ በላይ ይዛ አሣፍራ ታለች ። ”

ሻርፕ ጥቂት ዋጋ ቢስ ጥያቄዎችን ጠይቆ ነበር ። ሌን በትስን ግን ምንም ተጨማሪ ጠቃሚ ሀሳብ አላከለበትም ። ሻርፕ ቀጥሎ ያነጋገራት ቫሌሪ ሁብሐውስን ነበር ።

ቫሌሪ ረጋ ያለች፣ አለባበሷን ያሳመረችና ጠንቃቃነት የሚታይ ባት ወይዘሪት ነበረች ። የርሷ ከወንዶቹ የተሻለ ነበር ። እንደተናገረ ችው ከሆነ ሴሊያን በጣም ትወዳታለች ። ሴሊያ በርግጥ በተለይ ለኮሊን ማክናብ የነበራት ልዩ የሀዘን ስሜት ዓይነት ሳይሆን ግልጽ ልብ ነበራት ።

“ የሥርቆት ሱስ በሽታ (ክለፕቶማኒያክ) ነበረባት ብለሽ ታስቢ ያለሽ መይዘሪት ሆብሐውስ ? ”

“ አዎን ይመስለኛል ። ስለ ጉዳዩ እንኳ በእውነት ነው የምለው ብዙም አላውቅም ። ”

“ ይህን እንድታደርግ የገፋፋት ሰው አለ ብለሽ የምታስቢው ሰው ይኖራል ? ”

ቫሌሪ ትከሻዋን ነቀነቀች ።

“ ያን ጉረኛ ኮሊን የሚሉትን ለመሳብ ብላ ማለትህ ነው ? ”

“ ነጥቡን ደርሰሽበታል ሚስስ ሆብሐውስ ። አዎን ፣ እንደ ዚያ ማለቱ ነው ። አንቺ ግን ይህን ሀሳብ ያቱረብሽላት መስሎ አይ ታየኝም ። አያደለም ? ”

ቫሌሪ የተገረመች ትመስላለች ።

“ ውድ ወንድሚ ! በጭራሽ በተለይ የምወደው የአንገት ላይ ሻርፕ ተቆራርጦ እያለ ያን ያህል የማይሰማኝ ሰው አይደለሁም ። ”

“ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ይመክራታል ብለሽ የምታስቢው ሰው ይኖር ይሆን ? ”

“ እኔ እንጃ ! በቃ አለ አይደለም ተፈጥሮዋ ይመስለኛል ። ”

“ ተፈጥሮዋ ስትይ ምን ማለትሽ ነው ? ”

“ አዎን ፣ ስለ ሳሊ ጫማ ወሬና ሀሜታው ሲደለቅ በመጀመሪያ የጠረጠርኳት ሴሊያን ነበር ። ሴሊያ በሳሊ ላይ ቅንዐት ነበራት ። ሳሊ ፊንችን ማለቱ ነው ። ከዚህ በጣም የሠለጠነችና ዓይንን የምትስብ ልጅ እርሷ ናት ። ኮሊን በጣም አተኩሮባት ነበር ። በዚያ የሳሊ ጫማ በጠፋበት ምሽት ምን ታድርግ? በአሮጌ ጥቁር ቀሚስና ጥቁር ጫማ ሔደች ። ሴሊያ ግን ወተት ሠርቃ እንደጨለጠች ድመት ትመ ለከታት ነበር ። ይታይህ ፣ ለእነዚህ ጥቃቅን የእጅ አምባሮችና የፓ ውደር መያዣዎች አልጠረጠርኳትም ነበር ። ”

“ ታዲያ ለነዚህ በሀላፊነት ‘ሚጠየቀው ማነው ብለሽ ታስቢ ያለሽ ? ”

ቫሌሪ ትከሻዋን ነቀነቀች ።

“ የለም አላውቅም! ከጽዳት ሠራተኞቹ አንዷ ናት ብዬ አስቤ ነበር ።

“ የተቆራረጠው የጀርባ ሻንጣስ ? ”

“ የተቆራረጠ የጀርባ ሻንጣ ነበር ? ረስቻለሁ ። ያ እንኳ ዋጋ የሌለው ነገር ነው ። ”

“ ከ’ዚህ ሥፍራ ረዘም ላለ ጊዜ ቆይተሻል አያይል ወይዘሪት ሆብሐውስ ? ”

“ አዎን ። እንዲያውም ከነባሮቹ የመጀመሪያዋ እኔ ሳልሆን አልቀርም እላለሁ ። ለሁለት ዓመታት ተኩል ተቀምጫለሁ ማለቱ ነው ። ”

“ ከማንም በላይ ስለዚህ ሆስቱል ታውቂያለሽ ማለት ነዋ ? ”

“ አዎን ! እንደዚያ ነው ። ”

“ ስለ ሲሊያ አውስቲን ሞት ያለሽ ሀሳብ ምንድነው ? ማለት ለዚህ ሁኔታ መሠረታዊ መንሥኤ ነው ብለሽ የምታስቢው ? ”

ቫሌሪ ራሷን ነቀነቀች ። ፊቷ አሁን ለወጥ ይታይበታል ። ተኩ ሳትራለች ።

“ የለም ” አለች ። “ በጣም የሚዘገንን ጉዳይ ነው ። ሲሊያ እንድ ትሞት የሚፈልግ ሰው ፊጽሞ አይታየኝም ። በጣም ጥሩ የሆነች ከፋት የሌላት ልጅ ናት ። በዚህ ላይ ደግሞ ቃል ኪዳኗን ፊጽማ ነበር ከ... ”

“ አዎን ። እና ? ” ሲል ኢንስፔክተሩ ጠየቀ ።

“ ምክንያቱ ያ ይሆን ፣ እኔ እንጃ ! ” አለች ቫሌሪ ዝግ ብላ ፣ “ ምናልባት ስለታጨችና ። ደስተኛ ልትሆን ስለሆነ ይሆን ? ነገሩ ግን እንደዚያ የሚል ሰው እብድ ብቻ መሆን አለበት ። ”

ቃሉን እንኳ ስትናገር ትንሽ ሰውነቷ ሲዘገንን ይታያል ። ኢንስፔክተር ሻርፕ በሀሳብ ተመስጦ ተመለከታት ።

“ “አዎን ! ” አለ ። “ “እብዶችንም መሠረዝ አንችልም ።” ቀጠሎም፣ “ለመሆኑ ከኤልሳቤጥ ጆንስተን ማስታወሻዎችና ጽሑፎች ላይ ስለተፊጸመው ጥፋት ምን ሀሳብ ይኖርሻል ? ” አላት ።

“ ምንም ። ያ የማይረባ ሥራ ነው ። ለደቂቃ እንኳ ሴሊያ እንዲያ ዓይነት ድርጊት ትፊጽማለች ብዬ አላስብም ። ”

“ ማን ነው ብለሽ ታስቢያለሽ ? ”

“ አዎን . . . ግን አጥጋቢ ምክንያት የለኝም ። ”

“ ነገር ግን ምክንያት የለሽ ሀሳብ ነው ? ”

“ አንዳች ጥርጣሬ ነገር የምትቀበል አይመስለኝም ። ትቀበላለህ ኢንስፔክተር ? ”

“ እንዲያውም ካልሽስ ጥርጣሬ መስማት ነው የምፈልገው ፣

በሚገባ እስማዋለው ። በሁለታችን መካከል ሚስጥር ሆኖ ይቀራል ።

“ እንግዲያውስ ተሳስቼም ሊሆን ይችላል ፣ የፖትሪሺያ ሌን ሥራ ሳይሆን አይቀርም የሚል ሀሳብ አለኝ ። ”

“ አስገራሚ ነው ! በጣም ነው ያስደንቅሽኝ ሚስስ ሆብሐውስ። ፖትሪሺያ ሊንን በፍጹም አላሰብኳትም ። በጣም ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያላት ረጋ ያለች ወጣት ወይዘሪት ትመስለኛለች ። ”

“ አድርጋዋለች እኮ አላልኩም ። እርሷ ሳትሆን አትቀርም የሚል ሀሳብ ነው ያለኝ ። ”

“ በተለይ ለምን ስትል ይመስልሻል ? ”

“ ፖትሪሺያ ብላክ ቢስን ትጠላታላች ። ብላክ ቢስ የፖትሪሺያን ፍቅረኛ ኒጌልን በተሳሳተ ቁጥር ታርመዋለች ። አለ አይደለም ፍሬ ቢስ ነገሮችን አንዳንዴ እንደሚለፈልፍ ሁሉ ሲናገር እንገዲያስ ተካክል ትነግረው ነበር ። ”

“ ከኒጌል ይልቅ ፖትሪሺያ ሌን ትሆናለች ብለሽ ታስቢያለሽ ?”

“ አዎን ፤ ኒጌል ይህንንም ያህል የሚጨንቅ አይመስለኝም ። የራሱን ቀለም የሚጠቀም መስሎ አይታየኝም ። በጣም ብልህ ነው ። ነገር ግን ፖትሪሺያ ውድ ፍቅረኛዋ ኒጌል የሚጠረጠርበትን ነገር ሳታስብና ሳትጠነቀቅ ትሠራዋለች ማለት ዘበት ነው ። ”

“ ወይንም በኒጌል ቻትማን ላይ ጥላቻ ያለበት አንድ ሰው የ‘ርሱ ድርጊት እንዲመስል አድርጎትም ይሆናል ። ”

“ ያም ደግሞ ሌላ አማራጭ ነው ። ”

“ ኒጌል ቻፕማንን የሚጠላው ማነው ? ”

“ አዎን ፤ እንዴ! ጄን ቶሚልሰን አንዷ ናት ። እርሱና ሊን በት ሰንም ብዙ ጊዜ ሲተነኳኮሱ ነበር ። ”

“ በሴሊያ ላይ እንዴት ሞርፊያ ሊጠቀሙባት እንደቻሉ የምት ሰጭኝ ሀሳብ አለ ይሆን ? ”

“አዎን ፣ ብዙ አስቢያለሁ ፣ አሰላስያለሁ። በርግጥ ቡናው ከሁሉም የቀለለ መንገድ ይመስለኛል ። ሁላችንም ከጋራ - አዳራሽ ነበርን ። የሴሊያ ቡና ከአጠገቧ ከአንዲት ትንሽ ጠረጴዛ ላይ ነበር ። ሁልጊዜ የምትጠጣው ቡናዋ ከቀዘቀዘ በኋላ ነው ። እንደሚመስለኝ አንዱ

ጨካኝ አንጀት ያለው ሰው እንዲት እንክብል ወይንም የሆነ ነገር ሰው ሳያየው አዘንግቶ ከሲኒዋ ጣል አድርጎ ይሆናል ። እንግዲህ የሞት ከሽረቱን ማለት ነው ። ማለቴ በቀላሉ ሰው ሲመለከተው በሚችል አጋጣሚ ነው ሊደረግ የቻለው ። ''

'' ሞርፊያው '' አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ፣ '' በእንክብል መልክ አልነበረም ። ''

'' ታዲያ እንዴት ነበር ፣ በዱቄት መልክ ነበር ? ''

'' አዎን ። ''

ሻሌሪ ፊቷ ጭፍግግ አለ ።

'' ያ ደግሞ የበለጠ አስቸጋሪ ነው ፣ አይሆንም ? ''

'' ከቡና ሌላ የምታስታውሽው ነገር አለ ? ''

'' እንዳንዴ ከመተኛቷ በፊት አንድ ብርጭቆ የፈላ ወተት ትጠጣለች ። በዚያ ምሽት ግን የጠጣች አይመስለኝም ። ''

'' ከጋራ አዳራሹ በ'ዚያ ምሽት ምን እንደተፈጸመ በትክክል ልታስረጂኝ ትችያለሽ ? ''

'' አዎን ፣ እንዳልኩህ ሁላችንም ቲቀምጠን ስናወራ ነበርን ። አንድ የሆነ ሰው ሬዲዮውን ከፈተው ። አብዛኛዎቹ ወንዶች ልጆች ወደ ውጭ ወጥተው ነበር ። ሴሊያ ገና ሳይረፍድ ነበር ወደ አልጋዋ የሔደችው ። ጄን ቶሚልሰንም እንደዚያው ። ሳሊና እኔ ግን ከዚያው ከተቀመጥንበት ሆነን አመሸን ። እኔ ጥቂት ደብዳቤዎችን ስጽፍ ሳሊ ግን ስታጠና ነበረች ። ወደ መኝታ ከሔዱት የመጨረሻዋ እኔ ነኝ ብዬ አስባለሁ ። ''

'' ከወትሮው የተለየ አልነበረም ምሽቱ ? ''

'' በምንም ዓይነት ኢንስፔክተር ። ''

'' አመሰግናለሁ ሚስስ ሆብሐውስ ። አሁን ሚስስ ሊንን ከኔ ዘንድ ትጠሪልኛለሽ ? ''

ፖትሪሺያ ሊን በጣም ሀሳብ የገባት ትመስላለች ፣ ነገር ግን ጭንቀት አይታይባትም ። ጥያቄና መልስ ምንም አዲስ የፈጠሩት ነገር ፣ ያመጡት ፍንጭ የለም ። ስለ ኤልሳቤጥ ጀሀንስተን ጽሑፍ ጉዳይ በተጠየቀችበት ጊዜ ፖትሪሺያ ሴሊያ ለመሆኗ የማያጠራጥር መሆኑን ገለጸች ።

“ ነገር ግን እኮ ሚስስ ሌን አጥብቃ ነበር አለማድረጓን የገለጸች ። ”

“ አዎን በርግጥ ” አለች ፖትሪሺያ ። “ እንደዚያ ብላ ነበር ። ምናልባት አፍራባት ይሆናል ። ነገር ግን ከሌሎቹ ነገሮች አንጻር የሚያጠራጥርም አይደል ። ያጠራጥራል ? ”

“ ይመስለኛል ” አለች ፖትሪሺያ ፊቷ በመቅላት ላይ እያለ ። ቀጥላም “ ነገር ግን የልጅቷን ጽሑፎች ያበላሸው ኒጌል መስሏችሁ ነበር ። በቀለሙ ምክንያት ነበር ። እንደዚያ ዓይነቱ ነገር ደግሞ ፍጹም ደደብነት ነው ። ማለቴ እንደዚያ ዓይነት ሥራ ቢሠራ ኒጌል በፍጹም የራሱን ቀለም አይጠቀምም ነበር ። ይህን ያህል ሞኝነት ሊይዘው አይችልም ። ብቻ ለማንኛውም አያደርገውም ። ”

“ አብዛኛውን ጊዜ ከወይዘሪት ጆንስተን አይስማሙም ። አይደለም ? ”

“ አዎን ! አንዳንዴ የሚያናድድ ባህርይ አላት ። ነገር ግን እስከዚህም ግድ የለውም ” ። ፖትሪሺያ ሊን በቅን መንፈስ ወደፊት አሰገገች ። “ አንድ ሁለት ነገሮች እንድትረዳልኝ ጥረት ለማድረግ ‘ሞከራለሁ ኢንስፔክተር ። ስለ ኒጌል ቻፕማን ማለቴ ነው ። ኒጌል ከሌላ ሰው ይልቅ የራሱ ጠላት ነው ። ይህን ዓይነት አስቸጋሪ ባህርይ እንዳለው መቀበል የሚገባኝ የመጀመሪያዋ ሰው እኔ ነኝ ። ሰዎች በ‘ርሱ ላይ የተሳሳቱ ሀሳብ እንዲኖራቸው ያደርጋል ። ይህ አላጋጭነቱና አሽሚጣጭነቱ በሰዎች ላይ የሚሠራው አስቂኝ ነገር በሙሉ ሰዎች እንዲጠሉት አድርጓቸዋል ። እውነቱን ለመናገር እርሱ ግን ከዚህ የተለየ ነው ። በጣም ዓይነ አፋርና ደስተኛ ካልሆኑት ሰዎች ፡ መውደድን እየፈለጉ ነገር ግን በመንፈሥ በሚፈጥሩት ቅራኔ የሚለትና የሚሠሩትን እንድ ሳይሆን የሚቀርባቸው ዓይነት ሰው ነው ። ”

“ ገባኝ ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። “ መጥፎ እጣ ፈንታ ነው ያላቸው ። ” “ አዎን ግን ምንም ማድረግ አይቻልም ታውቃለህ ። በጣም መጥፎ አስተዳደግ ነው ። ኒጌል አስከፊ የልጅነት ሕይወት ነው ያሳለፈው ። አባቱ ክፉ ጨካኝ ሰው ነበር ። በፍጹም የሚረዳው ሀሳቡን የሚካፈልለት አልነበረም ። እናቱንም በጣም ያስቃያት ነበር ። ከሞተች በኋላ ከፍተኛ ጸብ በመካከላቸው ተነስቶ ኒጌል ከቤት ወጣ ። አባቱ ምንም ገንዘብ ከለከለው ። ኒጌልም ምንም ርዳታ እንደማይፈልግ ገለጸለት ። ቢሰጠውም እንደማይቀበል በይፋ ተናገረ ። ትንሽ ገንዘብ በእናቱ ኑዛዜ መሠረት ደርሶት ነበር ። ነገር ግን እንደገና ለአባቱ መልሶ አልጻፈም ። ወደርሱም ጨርሶ አልተጠ

ጋም ። በርግጥ ነገሩ ያሳዝናል ። ነገር ግን የአባቱ ክፉ ሰው መሆን ም ንም የሚያጠራጥር አይደለም ። ያ ሁኔታ ኒጌልን መራርና አስቸ ጋሪ ቢያደርገውም አልደነቅም ። እናቱ ከሞተች ጀምሮ ማንም የሚያስ ብሰትና ከብካቤ የሚያደርግለት ሰው ኖሮትም አያውቅ ። ጤንነቱም ደህና አልነበረም ም ንም እንኳ በአዕምሮው ጎበዝ ቢሆንም ። በሕይ ወቱ በመላ እንዲህ ያሼበ ጊዜ ስላላለፈ እውነተኛ ደስታ ኖሮት ማን ነቱን አሳይቶ ፍጹም አያውቅም ። ''

ፖትሪሺያ ሌን አቆመች ። ለረጅም ጊዜ በማውራቷ ምክንያት ፊቷ ቀልቶ ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ሲል ነበር ። ኢንስፔክተር ሻርፕ በሀሳብ ተውጦ ተመለከታት ። አዎን ብዙ ፖትሪሺያ ሊኖችን አስ ቀድሞ ተመልክቷል ። ' ከሰውዬው ፍቅር ይዟታል ' ሲል አሰበ ለራሱ ። ' እንደአካሉ አድርጎ የሚያስብላት አይመስለኝም ። ነገር ግን በእናቱ ተከቶ ለማየት ይፈልጋል። ከብካቤ እንድትሰጠው። አባቱ የተረገመ አተካራኛ ሳይሆን አይቀርም።ነገር ግን እናትየዋ ደግሞ ልጅዋን በማቀማጠል የምታባልግ ጅል ብጤ ሴት ከመሆኗም በላይ በአባቱና በርሱ መካከል ለተፈጠረው መሻከርም ምክንያት ሳትሆን አትቀርም ። እንደዚህ መሣይ ብዙ ነገሮችን አይቻለሁ ። ' ኒጌል ቻፕማን በሴሊያ አውስቲን ላይ ቀልቡ አርፎ ይሆን? በሚል ብዙ አሰ ላሰለ ግን አልመሰለውም ። ሊሆን ግን ይችላል። ' ፖትሪሺያ ሊን ይህን ነገር መቼም አምርራ ነው የምትዋጋውና ምትቃወመው ። ' በሴሊያ ላይ ጉዳት እስከማድረስ ጥላቻ ይኖራታል ? ለመግደል ያበቃታል ? ፍጹም — አይሆንም — ለማንኛውም የሴሊያ በኮሊን ማክናብ በእ ጮኛነት መያዝ ለመግደል የሚገፋፋውን መንስኤ ዋጋ ቢስ ያደርገ ዋል ። ፖትሪሺያ ሌንን አሰናብቶ ጄን ቶሚልሰንን አስጠራ ።

— 10 —

ሚስስ ቶሚልሰን ኮስታራ መሳይ የሀያ ሰባት ዓመት ወጣት ሴት ስትሆን በጣም ያልጠቆረ ማለፊያ ጸጉር ያላት ሆና ስስ ከንፈርና ከብዙ ሴቶች ላይ የሚታይ ዓይነት ደምግባት ነበራት ። እንደዚያው እንደተኮሳተረች ።

" አቤት ኢንስፔክተር ፣ ምንልርዳህ ? "

" ስለዚህ አሳዛኝ ጉዳይ የምትረጂን ጉዳይ ቢኖር ብዬ ነው ሚስስ ቶሚሊሰን ?"

" በጣም ይዘገንናል ! ሰውነት ይዘገንናል " አለች ጄን " ሴሊያ ራሷን በራሷ አጠፋች ሲባል በጣም ከፍቶን ነበረ ። አሁን ግን ግድያ ይሆናል የሚል ወሬ እየተሰማ ነው . . . " ንግግሯን አቁማ ራሷን በሀዘን ነቀነቀች ።

" እምን ፤ ራሷን አለመመረዟን እውቀናል " አለ ሻርፕ "መርዙ ከየት እንደመጣ ታውቂያለሽ ? "

ጄን ራሷን ነቀነቀች ።

" ከቅድስት ካታሪን ሆስፒታል ከምትሠራበት ሥፍራ መምጣቱን ተረድቻለሁ ። ግን በእውነት እንደዚያ መሆኑ ራስን በራስ ማጥፋት ያስመስላል ?"

" ካለጥርጥር ለዚያ ተብሎ የታሰበ ነበር " አለ ኢንስፔክተሩ።

" ግን ከሴሊያ በስተቀር መርዙን ለማግኘት የሚቻለው ሌላ ማን አለ ? "

" ብዙ ሰዎች ይኖራሉ " አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። እንደዚያ ለማድረግ ቆራጥ ሀሳብ ካላቸው በጣም ቀላል ነው ። አንቺ እንኳ ራስሽ ሚስ ቶሚልሰንም ብትሆኚ " አላት ። " ለማድረግ ከፈለግሽና ራስሽን ማጥፋት ብትፈልጊ ትችያለሽ ። "

" በእውነት ነው የምትለው ኢንስፔክተር ሻርፕ ? " ድምጿ በቁጣ ታምቋል ።

" አዘውትረሽ መድሐኒት ማከፋፈያውን ትጎበኚ ነበር ሚስ ቶሚልሰን ? "

“ አምን ፣ ከዚያ የሔድኩት ሜልድሪድ ኬሪን ለማየት ነበር ። ነገር ግን የመርዙን ቁጣጥን መፈታተሹን በተፈጥሮዬም አልሜውም አላውቅ ። ”

“ ግን ይህን ልታደርጊ አትችይም ነበር ? ”

“ በርግጥ እንደዚያ ዓይነት ነገር ፍጹም ሠርቼም አላውቅ ! ”

“ እንግባባ ሚስ ቶሚልሰን ። ጓደኛሽ የመድሃኒት መያገጥ ምቹን በማሸግ ላይ ነበረች እንበል ። ሌላይቱ ወይዘሪት በተመላላሽ ሕመማኑ መስኩት በመሥራት ላይ ነች ። ከፊት ለፊት ካለው ክፍል አብዛኛውን ጊዜ ሁለት አከፋፋዮች ብቻ ይኖራሉ ። በቀላሉ ከቢልቃጠቹ መደርደሪያ ኋላ አልፈሽ ወደ ክፍሉ መሀል ሮጠሽ ማቋረጥ ትች ያለሽ ። ከቁምጣጥኑ አንዲት ቢልቃጥ በማጮለግ ከኪስሽ በመጨመር ሁለቱም አከፋፋዮች ምንም ስለዚህ ሳያልሙ እንኳ መውጣት ትችያለሽ ። ”

“ ኢንስፔክተር ሻርፕ የምትናገረውን ነገር በሙሉ እቃወማለሁ። ስም የሚያጠፋ ክስ ይመስላል ። ”

“ የለም ፣ ክስ እንኳ አይደለም ። ሚስ ቶሚልሰን ? እንደዚያ ያለ ጉዳይ አይደለም ። አልተግባባንም ። እንቺ ራስሽ እንዲያ ዓይነት ሥራ ለመፈጸም እንደምትችይ ነግረሽኝ ነበር ። እኔም እንዴት እንደ ሚቻል ላሳይሽ ስለፈለኩኝ ነው ። ለእንድ ደቂቃ እንኳ እንቺ አድርገ ሽዋል የሚል አስተያዬት አልሰነዘርኩም ። ከሁሉም ነገር በላይ ደግሞ ” አለ ሻርፕ ፣ “ ለምን እንደዚያ ታደርጊያለሽ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ ትክክል ! የለም እኔ የሴሊያ ጓደኛ መሆኔን የተረዳህ አልመሰለኝም ኢንስፔክተር ሻርፕ ? ”

“ ብዙ ሰዎች በጓደኞቻቸው ይመረዛሉ ። አንድ ራሳችንን ልን ጠይቀው የሚገባን የሆነ ጥያቄ አለ ። ማለቴ ፣ ጓደኛ ፣ እውነተኛ ጓደኛ ሳይሆን ሲቀር ? ” አለ ።

“በ‘ኔና በሴሊያ መካከል ምንም አለመግባባት የለም ። እንደዚያ ዓይነት ነገር ፍጹም አልነበረም ። በጣም ነው የምወዳት ። ”

“ ከዚህ ቤት ለተፈጸሙት ሥርቆቶች እርሷ ነበረች የሚል ጥርጣሬ ነበረሽ ? ”

“ በፍጹም አልነበረኝም ! በሕይወቴ እንደዚህ የሚያስገርም ነገር ገጥሞኝም አያውቅ ። ሁልጊዜም ቢሆን ሴሊያ ከዚህ የበለጡ የአስተሳሰብ መርሆች የነበሯት ነበረች ። እንዲህ ዓይነቱን ነገር ትሠራለች ብዬ ፍጹም አላለምኩም ። ”

“ ትክክል ! ” አለ ሻርፕ በጥንቃቄ አትኩሮ እየተመለከታት ፣ “ የሥርቆት ሱስ በሽታ (ክሊፕቶማኒያክ) ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን መርዳት ይችላሉ ። አይችሉም ? ”

የጄን ቶሚሊሰን ከናፍሮች የበለጠ ተጋጠሙ ። እንደገና ከፈተ ቻቸውና መናገር ጀመረች ።

“ ያን ዓይነት ሀሳብ እንኳ ማብራራትና ማመካኘት የምችል አይመስለኝም ። እኔ ጥንታዊ ሰው ነኝ ። በ‘ኔ እምነት እንኳ ሥር ቆት ነው ። ”

“ እንዳንቺ እምነት ሴሊያ ዕቃዎችን የምትሰርቀው እውነቱን ለመናገር ልትጠቀምባቸው ነው ? ”

“ በትክክል እንደዚያ ነው ። ”

“ በርግጥ ተራ እምነተቢስነት ይመስላል ? ”

“ እኔ እንደዚያ ለማለት አልችልም ! ”

“ አሀ ! ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ራሱን እየነቀነቀ ። “ መጥፎ ነገር ነው ። ”

“ አዎን ! ሁልጊዜም ቢሆን በአንድ ሰው የተናደድክ በሚመስልህ ወቅት የሚረብሽህ ጉዳይ ነው ። ”

“ ፖሊሶችን ለዚህ ጉዳይ መጥራቱ እንደገባኝ ትክክል ነበር ። ”

“ አዎን ! እንደዚያ ማድረጉ በኔ አስተያዬት ትክክለኛው መንገድ ይመስለኛል ። አዎን ታውቃለህ ? ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ሥራዎችን እንደሠሩ መቶው የለባቸውም ። ”

“ አንድ ሰው ሌባ ሆኖ ሳለ የሥርቆት ሱስ በሽታ እንዳለበት ማጥናቱን አይደለም የምትይኝ ? ”

“ አዎን ፣ እንደዚያ ማለቴ ነው ። እንደዚያ ነው ። ”

“ ሚስስ አውስቲን የሙሽራ ሻማዎቿን ሳታብራና ሁሉም ነገር በደስታ ከመፈጸም ይልቅ . . . ”

“ በርግጥ አንድ ሰው ኮሊን ማክናብ በሚሠራው ነገር መደነቅ አይኖርበት ፣ ” አለች ጄን ቶሚሊሰን በምቀኝነት አገላለፅ ። “ ኢአማኒ ፣ ፍጹም እምነተቢስ ፣ የሚያቃቂል ጋጠወጥ ወጣት ስለ መሆኑ ርግጠኛ ነኝ ። ለማንም ቢሆን መጥፎ ደፋር ነው ። በዚህ ላይ ደግሞ በ‘ኔ አስተያየት ኮሚኒስት ይመስለኛል ! ”

‘‘እህ ! ’’ አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። ‘‘ በጣም አስከፊ ነገር ! ’’ ሲል ራሱን ነቀነቀ ።

‘‘ ሲሊያን የደገፉት ምናልባት ስለግል ንብረት ትክክለኛ አስተሳሰብ ስለሌለው ይሆናል ። ምናልባት ሁሉም ሰው ለራሱ የፈለገውን ነገር መውሰድ ይኖርበታል ብሎ ያስብ ይሆናል ። ’’

‘‘ ብቻ በማንኛውም መንገድ ’’ አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ፥ ‘‘ ሚስስ አውስቲን ራሷን አጋልጣለች ። ’’

‘‘ እርሷ መሆኗ ከታወቀ በኋላ አምን ፥ ’’ አለች ጂን ኮስተር ብላ ።

‘‘ ማነው እርሷ መሆኗን ያወቀ ? ’’

‘‘ ያ ሚስተር—ማን ነበር ስሙ—ፖይሮትነው፣ከዚህ የመጣው።’’

‘‘ ግን ፥ ለምን እርሱ እንዳወቃት አድርገሽ አሰብሽ ሚስስ ቶሚልሰን ? እርሱ እንደዚህ ብሎ አልተናገረም ። እርሱ ፖሊስ እንዲጠራ ብቻ ነው ምክር የሰጠው ። ’’

‘‘እርሷ መሆኗን ማወቁን በእንድ መንገድ አሳይቷት ይሆናል ። ጨዋታው እንዳለቀ ስለተረዳች ራሷን ለማጋለጥ ሔደች ’’

‘‘ በኤልሳቤጥ ጆንስተን ጽሑፎች ላይ ስለፈሰሰው ቀለምስ ? ያንተናግራለች ? ’’

‘‘ እኔ በ‘ውነት ‘ማውቀው ነገር የለም ። ግን ይመስለኛል ። ’’

‘‘ ስህተት ቢሆንስ ? ’’ አለ ሻርፕ ። ‘‘ አለማድረጓን አጥብቃ ገልጻ ነበር ። ’’

‘‘ ምናልባት እንደዚያ ሊሆን ይችላል። እኔም እርሷ አትመስለኝም ። ’’

‘‘ የሚመስልሽ ኒጌል ቻፕማን መሆኑ ነዋ ? ’’

‘‘ የለም ፥ ኒጌልም እንደዚያ ይሰራል ብዬ አላስብም ። እኔ ከሁሉም ይልቅ ሚስተር አኪቦምቦ ይመስለኛል ። ’’

‘‘ በእውነት ? ለምን ያደርገዋል ብለሽ ትገምቻለሽ ? ’’

‘‘ ምቀኝነት ! እነዚህ ጥቁሮችና ክልሶች ‘ርስ — በርሳቸው ቅንአተኞችና ጨካኝ ደደቦች ይመስሉኛል ። ’’

‘‘ የሚገርም ነው ሚስስ ቶሚልሰን ። ሴሊያ አውስቲንን ለመ ጨረሻ ጊዜ ያየሻት መቼ ነበር ? ’’

‘‘ ዓርብ ከ‘ራት በኋላ ። ’’

“ መጀመሪያ ወደ መኝታዋ የሔደች እርሷ ናት ? እርሷ ወይንስ አንቺ ? ማንኛችሁ ናችሁ ? ”

“ እኔ ነኝ ። ”

“ የጋራ - አዳራሹን ከለቀቀሽ በኋላ ወደ መኝታ ቤቷ አልሔ ድሽም ወይንም አላገኘሻትም ? ”

“ የለም ። ”

“ ከቡናዋ ሞርፊያ የጨመረው ሰው ማን መስሎ ይታይሻል ? ነገሩ እንደዚያ የተፈጸመ ቢሆን ? ”

“ ምንም ሀሳብ የለኝ ። ”

“ይህን ሞርፊያ ከቤቱ ውስጥ ወይንም ከነዋሪዎቹ በአንደኛው መኝታ ቤት ቲቀምጠ አላየሽውም ? ”

“ የለም ፣ የለም እንደዚያ አይመስለኝም ። ”

“ እንደዚያ አታስቢም ? ምን ማለትሽ ነው እንደዚያ ስትይ ሚስስ ቶሚልሰን ?”

“ አለ አይደለም ? ነገሩ ገርሞኝ ነው ። አዎን በርግጥ ውርርድም ነበረ ታውቃለህ ? ”

“ የምን ውርርድ ? ”

“አዎ ፣ ሁለት ሦስት የሚሆኑት ወንዶች ልጆች ሲከራከሩ ነበር።”

“ ስለምን ነበር ከርክራቸው ? ”

“ ሰው ለመግደል ስለሚቻልበት መንገድ ፣ በተለይ ደግሞ ስለመመረዝ ነበረ ። ”

“ ከውይይቱ ተካፋዮች እነማን ነበሩ ? ”

“ ኮሊንና ኒጌል የጀመሩት ይመስሉኛል ። ከ‘ዚያ በኋላ ሊን በት ሰን ተጨመረ ። ፖትራሺያም ገባችበት — ”

“ እንዲያው በዚያ ወቅት በትክክል የተባለውን ማስታወስ ትች ያለሽ ? — ክርክሩ እንዴት እንደተካሔደ ? ”

ጄን ቶሚልሰን ለጥቂት ጊዜ አምስለሰለች ።

“ አዎን ፣ የተጀመረው ግድያን በመርዝ ስለማካሔድ ነበር ። በተለይ መርዙን ለመያዝ የነበረውን ችግር በተመለከቱና ነፍስ ገዳዩ

በእብዛኛው ሊገኝ የሚችለው በመርዝ ሽያጭ ወይንም የማግኘት አጋጣሚን በማጥናት እንደሆነና ኂጌል ይህ ሁሉ የግዴታ አስፈላጊ አለመሆኑን ሲናገር አስታውሳለሁ ። እርሱም ማንም ሰው መርዝ ለመያዝ የሚያስችለው ሦስት የተለያዩ መንገዶችንና እነዚህም መንገዶች በማንም ሊታወቁ ወይንም ሊታዩ እንደማይችሉ ሲገልጽ ነበር ። ሊን በትሰን በባርኔጣ ውስጥ ሊሆን ይችላል ሲል ኂጌል ግን አልተቀበለውም ነበር ። እንደያውም ለማረጋገጥ መዘጋጀቱን ገለጸለት ። ፖት ኂጌልን ደገፈች ። እርሷ እንደምትለው ሊን ወይንም ኮሊን በፈለጉት ጊዜ ራሳቸውን ለመግደል መርዝ መጠቀም እንደሚችሉና ይህንኑ ተመሣሣይ ድርጊት ለመፈጸም ሴሊያም እንደምትችል ነበር ። ኂጌል ግን እርሱ ማለት የፈለገው ከ'ዚህ ፍጹም የተለየ መሆኑን ነው። እርሱ እንደሚለው ሴሊያ ከመድሐኒት ማከፋፈያው አንድ ነገር ብት ወስድ ሊታይ ይችል እንደነበር ነው ። ማለት ከጥቂት ጊዜ በኋላ አይተ ውት ከሥፍራው አለመኖሩን እንደሚረዱ ነው ። ፖት ግን ይህንን አል ተቀበለችውም ። ከፈለገች ከውስጡ ያለውን መድሐኒት በመውሰድ ቢልቃጡን ወይንም ጠርሙሱን በሌላ አንድ ነገር መሙላት እንደምት ችል ስትናገር ነበር። ኮሊን በንግግሯ ከማቀ በኋላ በነዚህ ቀኖች እንዲህ የሚደረግ ከሆነ ከህሙማን ብዙ ተታውሞ ሊፈጠር እንደሚችል ገለጸ። በርግጥ ኂጌል የተለየ መድሐኒቱን ለማግኘት 'ሚያስችል ሁኔታን ወይንም አጋጣሚን መግለጹ አልነበረም ። እርሱ እንደሚለው እርሱ ራሱ ምንም ዓይነት የዶክተርነት ወይንም መድሐኒት አከፋፋይነት ሥራ ሳይኖረው በቀላሉ ሦስት የተለያዩ መርዞችን በሦስት የተለያዩ መንገዶች ማግኘት እንደሚችል ነው ። ሊን በትሰንም ፣ ' ጥሩ መንገዶች ሀን ምንምን ናቸው ? ' ሲለው ኂጌል ፣ ' አሁን ልነግርህ አልችልም ! ነገር ግን በሚከተሉት ሦስት ሣምንታት ውስጥ የሦስት መርዞችን ቢልቃጦች ላቀርብልህ ካለጥርጥር እወራረዳለሁ ' ' አለ ። ሊን ባትሰን ይህን ቃሉን ካልፈጸመ የአምስት ፓውንዶችን ኖት እንደሚከፍል ቃል ገባ ። ''

'' ታዲያስ ? '' አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ጂን ንግግሯን ስታቆም ።

'' ታዲያ ለጥቂት ጊዜ ምንም አልተፈጸመም ነበር ። አንድ ምሽት ግን ከጋራ አዳራሹ ኂጌል ' በሉ ልጆች ተመልከቱ — ቃሌን የማላፈርስ ሰው ነኝ ' በማለት ሦስት የተለያዩ ቢልቃጦችን ከጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ ። አንድ የሀዮሳይን እንክብል ቢልቃጥ ፣ አንድ የቲንክቸር ደጂታሊስና የሞርፊን ታርታሬት ጠርሙሶች ነበሩ ። ''

ኢንስፔክተሩ ኩምጨጭ ብሎ ፣ '' ሞርፊን ታርታሬት ። ከላዩ ላይ መለያ ነበረው ? '' አለ ።

“ አዎን ፡ የትድስት ካታሪን ሆስፒታል ነው ። ያንን ያስታወስኩት በተለምዶ ዓይኔ ስላረፈበት ነው ። ”

“ ሌሎቹስ ? ”

“ አላስተዋልኩም ። ከሆስፒታል መድሐኒት ግምጃ ቤቶች አይ መስሉኝም ። ”

“ ቀጥሎስ ምን ተፈጠረ ? ”

“ በርግጥ ብዙ ወሬና እሠጥ አገባ ነበር ። ሊን ባትሰንም ‘ በል እንግዲህ የግድያ ወንጀል ፈጽመሀም ከሆነ በአሞር ጊዜ ውስጥ ወደአንተ መመራቱ ‘ ማይቀር ነው ’ ሲለው ኒጌል ፣ ‘ ቅንጣት ያህል ። እኔ ተራ ሰው ነኝ ። እኔ ከየትኛውም ክሊኒክ ሆነ ሆስፒታል ምንም ግንኙነት የለኝም ። ማንም ሰው ለደቂቃ እንኳ እንደ ዚያ ዓይነት ነገር ማሰብ አይ ቻለውም ። ከመድሐኒት መሸጫም መደብር ጠረጴዛ አልገዛችውም ። “ አለ ። ኮሊን ማክናብ ፒፖውን በማውጣት ከጥርሱ ያዘ ። ‘ ካለ ዶክተር ትዕዛዝ እነዚህን ሦስት ነገሮች የሚሸጥልህ ቀማሚ አይኖርም ። ’ አለው ። ብቻ ለማንኛውም ጥቂት ከተከራከሩ በኋላ ሌን በመ ጨረሻ ላይ ከፍሎ ማግኘቱን ተናገረ ። ‘ አሁን የገንዘብ እጥረት ስላለብኝ ላደረገው አልችልም ። ነገር ግን ምንም ‘ ሚያጠራጥር ነገር የለውም ። ኒጌል የተናገረውን አረጋግጧል ’ አለና ፣ ‘ ታዲያ እኒህን ጥፋተኛ መሣሪያዎችን ምን አናድርጋቸው ? ” ሲል ኒጌል ሣቅ ብሎ ‘ ሌላ አደጋ ከመድረሱ በፊት ልናስወግዳቸ ይገባል ’ አለውና ከቢልቃጡ እንክ ብሎቹን እያወጡ ከሳቱ ከተቷቸው ። የሞርፊንተር ታሬቱንም ዱቄት እንደዚሁ ከሳቱ ላይ ደፉት ። ቲንከቸር ዲጀታሊሱን ከሽንት ቤት ከመ ታጠቢያው ቀዳዳ ደፉት ። ”

“ ጠርሙሶቹስ ? ”

“ ጠርሙሶቹን የት እንዳደረሳቸው አላውቅም . . . ምናልባት ከቆሻሻ ወረቀቶች ቅርጫት የተጣሉ ይመስለኛል ። ”

“ ነገር ግን መርዙ ራሱ እንዲጠፋ ተደርጓል ? ”

“ አዎን ! ስለዚያ ርግጠኛ ነኝ ። አይቻለሁ ። ”

“ ለመሆኑ — መቼ ነበር እንዲያ የሆነው ? ”

“ ከሁለት ሣምንታት በፊት ይመስለኛል ። ”

“ ገባኝ ! አመሰግናለሁ ሚስስ ቶሚልሰን ። ”

ጄን በግልጽ እንዲነገራት ፈልጋ ከዚያው ተነሰተች ።

“ ዋጋ የሚኖረው ይመስልሀል ? ”

“ ሊሆን ይችላል ። እንዲህ ነው ብሎ መናገሩ ይከብዳል ።”

ኢንስፔክተር ሻርፕ ለጥቂት ጊዜ ሲያሰላስል ቆይቶ ኒጌል ቻፕማን እንደገና እንዲጠራ ጠየቀ ።

“ አሁን ከሚስስ ጂን ቶሚልሰን አንድ አስገራሚ ነጥብ ስላገኘሁ ነው ” አለ ።

“ አሀ ! ውድ ጂን በማን ላይ ደግሞ የአፅሞሮ ጥላቻ ስትፈጥር ቆይታ ይሆን ? ከኔ ላይ ነው ? ”

“ ስለ መርዝ ስታወራ ነበር ፣ ካንተ ከሚስተር ቻፕማን በተያያዘ ጉዳይ ። ”

“ ስለመርዝና ስለእኔ ? ያንተ-ያለህ ! ምንብላ ? ”

“ ከጥቂት ሣምንታት በፊት ከሚስተር ባትሰን ጋር መርዝ እንዴት ሊታወቅ በማይቻል ዘዴዎች ሊገኝ እንደሚችል መወራረ ዳችሁን ትከዳለህ ? ”

“ እንዴ ስለዚያ ! ” ኒጌል በድንገት ገጽታው በአግርሞት ተመላ። “ አዎን ! በርግጥ ! የሚገርም ነው ! ስለዚያ ፍጹም አላሰብኩም ነበር ። ጂን ከሥፍራው መኖሯንም አላስታወስኩም ። ነገር ግን ይህን ያህል ጥቅም አለው ብለህ ታስባለህ ? ”

“ ያን ማወቅ እንችልም ። ነገር ግን አምነሃል ? ”

“ እንዴ ! አዎን በጉዳዩ ላይ ስንነጋገርበት ነበርን ። ኮሊንና ሊን ስለ ጉዳዩ ከፍተኛነት ሲነታረኩ ነበሩ ። እና እኔ ደግሞ በቀላሉ ማንም ሰው መርዝ ማግኘት እንደሚችል ተናገርኩኝ — እንዲያውም በሦስት የተለያዩ መንገዶች ማግኘት እንደሚቻል ከገለጹኩኝ በኋላ ይህን ቃሌን በተግባር በመፈጸም እንደማረጋግጥ ቃል ገባሁ ። ”

“ ማለት በኋላ ተግባራዊ ያደረግኸውን ሐይት ? ”

“ አዎን ፣ በኋላ ተግባራዊ ያደረግሁትን ሐይት ማለቴ ነው ኢንስፔክተር ። ”

“ እነዚህ ሦስት መንገዶች ምን ነበሩ ሚስተር ቻፕማን ? ”

ኒጌል ራሱን ወደ አንድ ጎን አዘነበለ ።

“ ይህን የምትጠይቀኝ የመጥፎ ምግባር ምሣሌ አድርገኸኝም አይደል ? ” አለውና “ ከዚህም በላይ ማስጠንቀቂያ ልትሰጠኝ ትችላለህ ! ” አለ ።

“ ገና ማስጠንቀቂ ያረጀ አልያረስንም ሚስተር ቻፕማን ። በር ግጥ ራስህን የመጥፎ ተግባር ዎ ሣሌ አንተው እንዳልከው ማድረግ የለብህም ። በርግጥ ጥያቄዎቼን መመለስ ካልፈለግህ ያለ ምንም ችግር መተው ትችላለህ ፣ ግዴታ የለብህም ። ”

“ ዎን ለመመለስ እንደማልፈልግ አላውቅም ። ” ኒጌል ለአንድ ለሁለት ደቂቃ ሲያስብ ቆየ ፣ ከከናፍሩ ትንሽ ፈገግታ ወዛ ብሎበታል ።

“ በርግጥ ! ” አለ ፣ “ የሠራሁት ሥራ ያለጥርጥር ሕጉን ‘ሚቃ ወም ነው ። ከፈለግህም ለዚህ ሥራዬ ልትወነጅለኝ ትችላለህ ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ጉዳይ የነፋስ ጥፋት ወንጀል በመሆኑ ከምስኪኗ ሴሊያ ሞት የተያያዘ ከሆነና ጥቅም ካለው መናገር ያለብኝ ይመስለኛል ። ”

“ ዋናው የበሰለው አመለካከትና መቀበልም የምፈልገው ይኸው ስለሆነ ነው ። ”

“ እሺ እንግዲያውስ እናገራለሁ ። ”

“ እነዚህ ሦስት መንገዶች ምን ነበሩ ? ”

“ መልካም ። ” አለና ኒጌል ከወንበሩ ተለጥጦ ተቀመጠ ። “ከጋዜጦችስ ሁልጊዜ የምናነበው ዶክተሮች ከመኪናዎቻቸው አደገኛ መድሐኒቶችን ስለመጣላቸው አይደለም ? ህዝቡ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይገባል ማለት ነው ። ”

“ አዎን ። ”

“ ጎሽ ! ከሀሳቤ የመጣልኝ አንደኛው ቀላል መንገድ ከከተማ ውጭ በመሔድ አንድ የጠቅላላ ሀኪምና ዶክተር መከታተልና ሁኔታው ሲፈቅድ መኪናውን ከፍቶ ከዶክተሩ ዕቃ መያዣ መመልከትና የፈለኩትን መውሰድ ነው ። አየህ ! ከገጠር አውራጃዎችና ወረዳዎች ዶክተሮች አብዛኛውን ጊዜ የመድሐኒት መያዣዎቻቸውን ወደ ቤት ውስጥ ይዘው አይገቡም ። ይህን የሚወስነው የሚጎበኘው ህመምተኛ ዓይነት ነው ። ”

“ እና ? ”

“ እና አበቃ ። ማለት ለመጀመሪያው መንገድ ማለቴ ነው ። አንድ ሦስት ዶክተሮችን ከመካከላቸው አንዱን ግደየለሽ እስከማገኝ መከታተል ነበር ። ከዚያ በኋላ ምንም አላስቸገረኝም ። መኪናዋ ከአንድ የገጠር ቤት ውጭ ብቻዋን ቆማ ነበር ። በሩን ከፈትኩኝ ከመ

ድሐኒት መያዣው ተመለከትኩ ። አንድ ሀዩሳይን ሀይድሮብሮማይድ ቢልቃጥ ወሰድኩኝ በቃ ። ”

“ እሺ ! ሁለተኛውስ መንገድ ? ”

“ ያ እንግዲህ ውድ ሴሊያን በመጎትጎትና ወጥሮ በመያዝ የሚ ሆን ነው ። ፍጹም ጥርጣሬ የሌላት ልጅ ናት ። እንደነገርኩህ በጣም ደደብ ልጅ ናት።እኔ ምን እንደማደርግበት ምንም ሀሳብ አልነበራትም። አለ አይደለም ስለ ዶክተሮች አንጀ ማራንጀ የመድሐኒት ትዕዛዝ እወ ራላትና ዶክተሮች እንደሚጽፉት አንድ ትዕዛዝ ለቲንክቸር—ዲጂታ ሊስ እንድትጽፍልኝ ጠየቅኋት ። ጥያቄዬን ያለአንዳች ጥርጣሬ ፈጸ መችው ። ከዚያ በኋላ ከአንድ የአድራሻ ማውጫ ካለንደን ራቅ ያለ አስተዳደር የአንድ ዶክተር ስም በመፈለግ ስሙን ወይንም ተመሣሣይ ፊርማ ማስቀመጥ ብቻ ነው ። ከዚያ በኋላ በጣም ሥራ ከሚያጣድፈው ከለንደን አንድ አካባቢ ካለ ኬሚስት ማለት ያን የዶክተር ፊርማ ለይቶ ለማየትም ሆነ ለማጥናት ጊዜ ከሌለው ሰው ዘንድ በመሔድ መድሐኒቱን ያለ ምንም ችግርና እክል አገኘሁት ። ዴጂታሊስ ብዙውን ጊዜ የሚታዘዘው በብዛት ለልብ ችግር ሲሆን ትዕዛዛዙን የጻፍኩትም ከሆቴል ማስታወሻ ወረቀት ላይ ነው ። ”

“ በጣም ድንቅ ነው ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ቅጭም ብሎ ።

“ ራሴን የመጥፎ ምግባር ምሣሌ እያደረግሁት ነኝ ! ከድም ጽህ እያረጋገጥኩት ነው ። ”

“ሦስተኛውስ መንገድ ? ”

ኒጌል ወዲያው በፍጥነት መልስ አልሰጠም ። ቆየት ብሎ ግን ፣ “ ተመልከት አንዴ ? ግን ወዴት እያመራሁ ነኝ ? ” አለ ።

“ ካልተቆለፈ መኪና መድሐኒቶችን መሥረቅ ሌብነት ነው ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። “ በመድሐኒት ትዕዛዝ ማጭበበርበር ደግሞ . . . ”

ኒጌል አቋረጠው ።

“ በትክክል ማጭበርበር እንኳ አይደለም ። ነው ? ማለቴ ገን ዘብ አላገኘሁበትም፣ ፊርማውም ቢሆን የማንም ዶክተር ቅጂ ፊርማ አይደለም ። ማለቴ አንድ የመድሐኒት ትዕዛዝ በመጻፍ ኤች አር ጀምስ ብዬ ብጽፍበት ማጭበርበር ነው ? ” ትንሽ የሽሙጥ ዓይነት ፈገግታ ፈገግ በማለት ቀጠለ ። “ ምን ማለቴ እንደሆን ገባህ ? አን ገቴን አሰቀላሁት አይደል ? ይህን ይዘህ ዋጋዬን ልታሰጠኝ ጀርባህን ብታዞርብኝ አበቃልኝ ። በሌላው በኩል . . .

“እሺ በሌላው በኩል ሚስተር ቻፕማን ?”

ኒጌል በችኮላ ስሜት ፥

“እኔ አራዊትን እንጂ ሰው መግደል አልወድም ። ሰው መግ ደል በጣም አደገኛ ነገር ነው ። ያች ትንሽ ሠይጣን ሴሊያ መግደል የለባትም ። ግልፅ አይደለም ፥ ለመረዳት ‘ ፈልጋለሁ ። ግልፅ ነው ? አይ መስለኝም ። ይህን ደካማና የማይረባ ባህርዩን እንድትረዳኝ ነው ።

“ ፖሊስ ብዙ ነጻነትና የተግባር ችሎታ አለው ሚስተር ቻፕ ማን ። አንዳንድ ነገሮችንና ሁኔታዎችን ልክ እንደልበ ሩህሩህ ሁሉ ሀላፊነትን ወደጎን አድርገን መመልከት ይኖርብናል ። በልጅቱ ሞት ምክንያት ችግሩን ለማቃለል የምታደርገውን ርዳታ ሁሉ በሙሉ ልብ እንደምቀበልህ አረጋግጣለሁ ። አሁን ወዳጄ መቀ ጠል ትችላለህ ፤ እስኪ ሦስተኛውን መንገድ ልወቀው ?”

“መልካም ፥ አለው ኒጌል፥ አሁን ገና ከመሠረታዊው ነጥብ እየደ ረስን ነው ። ከሁለቱ መንገዶች ይልቅ በጣም አደገኛ ነው ። ነገር ግን በአብዛኛው በጣም የሚያስቅ ነው ። እየሀ ! ሴሊያን ከመድሐኒት ማከፋፈያው በሣምንት ለአንድና ለሁለት ጊዜ እየሄድኩ ስጎበኛት ነበር ። በመሆኑም አካባቢውን በሚገባ አውቀዋለሁ . . .”

“እና ቢልቃጧን ከቁምሣጥን ውስጥ ማጮለግ ትችል ነበራ ?”

“የለም... የለም! ያን ያህል እንኳ የቀለለ አይሆንም ከ‘ኔ አመ ለካከት አንጻር ትክክል አይደለም ። እንደ አጋጣሚ እውነተኛ ነፍስ ማጥፋት ከሆነ - ማለቴ መርዙን ሰው ለመግደል የሠረቅሁት ቢሆን ምናልባት መታወስ ያለበት ነገር ከዚያ እንደነበርኩኝ ነው ። ለማ ንኛውም ከሴሊያ የመድሐኒት ማከፋፈያ ለስድስት ወራት ያህል አልሔ ድኩም ነበር ፥ ሴሊያ ከኋለኛው ክፍል በአምስት ከአሥራ አምስት እና ንተ‘ ረፍት ’ በምትሉት ጊዜ ለአንድ ስኒ ቡናና ብስኩት ስትል ትሔድ ነበር ። የተቀሩትም ወይዛዝርት ሁለቱ በአንድነት ይወጣሉ ። አንዲት ሌላ አዲስ ወይዘሪትም ነበረች ። በዓይንም አንተዋወቅም ። እና ያደረ ግሁት ነገር እንደዚህ ነበር ። ወደ መድሐኒት ማከፋፈያው ነጭ ደርቤ ከአንገቴ ልብ—ምት መለኪያ አድርጌ ሔድኩኝ ። አዲሲቱ ልጅ በርግጥ ብትኖርም ከተመላላሽ ህመማኑ ማስተናገጃ በተደራራቢ ሥራ ተጠምዳ ነበር ። እኔም ገባሁና ወደ መርዙ ቁምሣጥን ቀጠል ኩኝ ። አንዲት ጠርሙስ አወጣሁና በመለያያው በኩል አድርጌ በመ ዞር ለልጂቱ‘ አድሬናሊን ለምን ያህል ነው የምታቆዩት ?’ ስላት ነገረ ችኝና ራሴን በመነቅነቅ የዞረ ድምር እንዳለበት ሰው በመምሰል ። አንድ ሁለት ቪጋኒን እንዳላት ጠየቅኋት ። ወዲያው ዋጥኳቸውና እንደ ገና እየተወለጋጋድኩ ወጣሁ ።‘ርዕይ ቅንጣት ያህል እንኳ ጥርጣሬ አልነ

በራትም።ከመሥሪያ ቤቱ—ውጭ የመጣሁ ወጋንም የህክምና ተማሪ ስ ለመሆኔም አልተጠራጠረች ። በታ አለ አይደል? እንደሀጻን ልጅ ጨዋ ታ ማለት ነው ። ሴሊያ ከዚያ ሥፍራ መሆኔን በፍጹም አላወቀችም ።''

'' የልብ ምት መለኪያ ? '' አለ ኢንስፔክተሩ በጥርጣሬ ፣ ''ከየት ነው የልብ ምት መለኪያውን ያመጣኸው ? ''

ኒጌል በድንገት በፈገግታ ተዋጠ ።

''የሊን ባትሰን ነበር''አለው።''ቀጥሎም ሠረቅሁት'' በማለትመለሰ።

'' ከዚህ ቤት ? ''

'' አዎን ። ''

'' እንግዲያውስ የልብ — ምት ሥርቆቱን ያቃልልናል ። የሴ ሊያ ሥራ አይደለም ማለት ነው ። ''

'' የፈጣሪ ያለህ ! የመሥረቅ ሱስ በሽታ (ክሊፕ ቶማኒያክ) ያለ በት የልብ ምት መለኪያ ሲሰርቅ አይታየኝም ። ይታይሃል ?''

'' ከዚያ በኋላ ምን አደረግህበት ? ''

'' አስያዝኩት '' አለ ኒጌል ይቅርታ በሚጠይቅ ሰው አኳኋን ።

'' ባትሰንን ትንሽ የሚጎዳው ነገር አይደለም ታዲያ ? ''

''በጣም እንጂ ! ነገር ግን እነዚያ መንገዶቼን ሳልገልጽ ማድረግ የማልፈልገውን ማለቴ ነው ። ስለዚህ ጉዳይ አልናገርም ነበር ። ያም ሆኖ '' ካለ በኋላ ኒጌል ሳቀ። ቀጥሎም ፣'' አንድ ምሽት ፣ ብዙም ሳል ቆይ አውጥቼው ትልቅ ከበርቻቻ ድግስ አደረኩለት ። ''

'' ምንም ኃላፊነት የማይሰማህ ሰው ነህ ! '' አለው ኢንስፔ ክተር ሻርፕ ።

'' ፊትለፊት መሆን ነበረብኝ ? '' አለ ኒጌል ፈገግታው እየ ሰፋ ። ''እነዚህን የሞት ቅመሞች ከጠረጴዛው ለማስቀመጥ ማን እንደ ወሰዳቸው ማንም ሳያውቅ ልሠርቃቸው መዘጋጀቴን እየነገርኳቸው እያለሁ ? ''

'' ልትነግረኝ የፈለከው '' አለ ኢንስፔክተሩ ፣ '' በሦስት የተ ለያዩ መንገዶች ሦስት የተለያዩ መርዞች አንድ ሰው ለመመረዝ ማንም ሳያውቅና ሳያስተውልህ ለማግኘት መቻልህን ነው ። ''

ኔጌል ራሱን ነቀነቀ ።

CITY - HALL LIBRARY
of
ADDIS ABABA

“ እንደዚያ ነው ” አለ ። “ ሁኔታዎችን ከግምት ካስጋባን እን ደዚያ ነው ። ነገር ግን ሊቀበሉት የሚችሉት ጉዳይ አይደለም ። ዋና ው ነጥብ መርዞቹ በሙሉ ቢያንስ ከሁለት ሣምንታት ወይንም ከዚያ በፊት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ተደርገዋል ። ”

“ ያ እንኳ ያንተ ሀሳብ ነው ሚስተር ቻፕማን ። ነገር ግን ሊሆን አይችልም ። ” ኒጌል ግን አትኩሮና ተኮሳትሮ ተመለከተው ።

“ ምን ማለትህ ነው ? ”

“ እነዚህ ነገሮች በእጅህ የቆዩት ለምን ያህል ጊዜ ነው ? ” ኒጌል ሲያምሰለስል ቆየ ።

“ መልካም ! የሀዩሲኑ ቢልቃጥ ለአሥር ቀናት ይመስለኛል ። ሞርፊን ታርታሬቱን ለአራት ቀናት ያህል ፡ ቲንክቸር ዲጂታሊኑን ያገ ኘሁት በዚያው ቀን ከሰዓት በኋላ ላይ ነበር ። ”

“ ታዲያ እነዚህን ነገሮች የት ነበር ያስቀመጥካቸው ? ሀዩሲን ይድሮብሮ - ማይዱንና ሞረፊን ታርትሬቱን ማለቴ ነው ? ”

ቁምሣጥኑ መሣቢያ ውስጥ ከእግር ሹራቦቼ ኋላ ገፋ አድርጌ ነበር ያስቀመጥኩት ። ”

“ ከዚያ ማስቀመጥህን ያየ ሰው ነበር ? ”

“ የለም ። ማንም ፡ ያለማየቱን ርግጠኛ ነኝ ። ”

የሆነ ሆኖ ኢንስፔክተር ሻርፕ ከድምጹ እንደተገነዘበው ለዐመል ያህል ማመነታታት ነበረበት ። ነገር ግን ለጊዜው በነጥቡ ላይ ብዙም አልገፋበትም ።

“ ልታደርግ የነበረውን ነገር የገለጽክለት ሰው ነበር ? መንገዶ ችህንና ስለነዚህ ነገሮች ማለቴ ነው ? ”

“ የለም ! ፍፁም እንደዚያ እንኳ አልገለጽኩም ። ”

“ እንደዚያ ስትል ሚስተር ቻፕማን ? ”

“ አልገለጽኩም ማለቴ ነው ። እውነቱን ለመናገር ያህል ለፖች ልነግራት ነበር ። ነገር ግን እንደማትቀበለው አወቅሁኝ ። በጣም ጠንቃቃ ናት ስለዚህ አልነገርኳትም ። ”

“ ከዶክተሩ መኪና ውስጥ መድሐኒቱን ስለመሥረቅህ ወይንም ስለትዕዛዝ ወረቀቱ ወይንም ከሆስፒታል ሞርፊያ ስለ መውሰድህ አልነገርካትም ነበር ? ”

“ በርግጥ በኋላ ላይ ስለ ዴጂታሊኑ ፣ መድሐኒት ማዘገየ ጽፌ አንድ ጠርሙስ ከኬሚስቱ ዘንድ ስለማግኘቴና ከሆስፒታሉ እንደ ዶክ ተር ሆኜ ማጭበርበሬን አጫውቻታለሁ ። ፖት ተገርማ ነበር ብዬ ለመና ገር ግን ይቅርታ‘ጠይቃለሁ ።ነገር ግን ከመኪናው ውስጥ ስላደረግሁት ሥርቆት አልነገርኳትም ። እንደልማዴ ትጨሳለች ብዬ ፈራሁ ። ”

“ ይህንን ውድድር ከፈጸምክ በኋላ መድሐኒቱን እንደምታጠፋ ገልጸህላት ነበር ? ”

“ አዎን ! በጣም ስለተጨነቀች በነገሩ ተናደደች። መልሼ ካመጣ ሁበት እንዳስቀምጥ ወይንም እንዳች ነገር እንዳደርግ ትጎተጉተኝ ጀመር ። ”

“ አንተስ እንደዚያ አልተሰማህም ነበር ? ”

“ ያንተ ያለህ ! የለም እንደዚያ ቢሆን አስቸጋሪ ይሆን ነበር ። ምንም ማለቂያ የሌለው ችግር ውስጥ ያስገባኝ ነበር ። በቃ ሦስታች ንም መድሐኒቱን ከ‘ሳት ላይ ጣልነው ! ከመታጠቢያ ጉድጓድ ከተ ትነው ! እንደዚያ አደረግነው ። ምንም ጉዳት አልተሠራበትም ። ”

“ አንተ እንደዚያ ትላለህ ሚስተር ቻፕማን ። ነገር ግን ጉዳት ሊሠራበትም ይችል ነበር ። ”

“ እንዴት ተደርጎ ! እንደነገርኩህ መድሐኒቱ ከ‘ሳት ላይ እስከተ ወረወረ እንዴት ሆኖ ? ”

“ እንዲያው እንደዚህ ይሆናል ብለህ አስበህ ነበር ሚስተር ቻፕ ማን ? አንድ ሰው ከደበቅሁበት አይቶኝ ይሆናል ! ወይንም ምናልባት አግኝቷቸውም ይሆናል ! ወይንም አንድ የሆነ ሰው ሞርፊያውን አጋ ብቶ ቢልቃጡን በሌላ ነገር ሞልቶት ሊሆን ይችላል ብለህ ? ”

“ ያንተ ያለህ ! የለም ። ” ኒጌል ትኩር ብሎ ተመለከተው ። “እን ደዚያ ያለ ነገር ፍጹም አላሰብኩም ! አላምንበትምም ! ”

“ ነገር ግን ሊሆን የሚችል ነው ሚስተር ቻፕማን ። ”

“ እንዴ ? ማንማ ማወቅ የሚችል ሰው አልነበረማ ! ”

“ እኔ ግን ማለት የምችለው ” አለ ኮስተር ብሎ ኢንስፔክተሩ፣ “ እንዲህ ካለ ሥፍራ ፣ አንተ ይሆናል ሊሆን ይችላል ብለህ ከምታ ስ በው የበለጠ ነገር ይታወቃል ብዬ ነው ” አለው ።

“ ጥልቅ ብዬነቱን ማለትህ ነው ? ”

“ አምን ። ”

“ እዚያ ላይስ ትክክል ልትሆን ትችላለህ ። ”

“ ከተማሪዎቹ መካከል በማናቸውም ጊዜ ያለ ምንም ችግር ከመኝታ ቤትህ የሚገቡት የትኞቹ ናቸው ? ”

“ መልካም ፣ ሊን ባትሰን ብዙ ጊዜ ይመላለሳል ። ብዙዎቹም ወን ዶች ወጣገባ ያበዙበታል ። ልጃገረዶች እንኳ አይደሉም ። ልጃገረዶቹ በኛ በኩል ወዳሉት የመኝታ ቤቶች መምጣት አይኖርባቸውም ። ሥነ ምግባርና ንጹ ሕይወት ማለቴ ነው ። ”

“ አይኖርባቸውም ነው ። ሊያደርጉት ግን የሚችሉ ይመስለኛል፣ አይደለም ? ”

“ ማንም ቢሆን ይችላል ” አለ ኒጌል ። “ ቀኑ ላይ ፣ ከሰዓት በኋላ ስምላሉ ማንም ሰው አይኖርም ። ”

“ ወይዘሪት ሌን ከክፍልህ መጥታ ታውቃለች ? ”

“ ሌላ ነገር ማለትህ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ ኢንስፔ ክተር ። ፖት አልፎ አልፎ ከመኝታ ቤቴ የጠጋገንችውን የግር ሹራ ቦች ይዛ ትመጣለች ። በቃ ከዚያ በላይ የሆነ ምንም ነገር የለም ። ”

ወደፊት በመለጠጥ ኢንስፔክተር ሻርፕ ፡

“ አንድ መገንዘብ የሚኖርብህ ጉዳይ ሚስተር ቻፕማን? ከዚያ ከጠርሙስ በቀላሉ መርዙን በመውሰድ ሌላ ነገር ሊተካበት የሚ ቻለው ሰው አንተራስህ ብቻ መሆንህን አይሆንም ? ” ሲል ጠየቀው ።

ኒጌል ትኩር ብሎ ተመለከተው ። ፊቱ በቅጽበት ጭው አለ ። ጭን ቀትና ጥበት አጠሉበት ።

“ አዎን ” አለ ። “ ያንን ከአንድ ደቂቃ ተኩል በፊት አስቢው ነበር ። አንተ ያልከውንም ነገር መፈጸም ይቻለኝ ነበር ። ነገር ግን ኢን ስፔክተር ፣ በዚያች ልጅ ላይ እንዲህ ያለ ቅጣት ለመፈጸም የሚያበቃኝ ምክንያት በዚህች ምድር ላይ በፍጹም አይኖረኝም ። ስለዚህ እላደ ረኩትም ። አሁንም ቢሆን - በሚገባ እንደ ተገነዘብኩት ያገኘከው የኔን ማስረጃነት ብቻ ነው ። ”

— 11 —

የውርርዱ ታሪክና የመርዙ ጥቅም ላይ እንዳይውል መደረግ በሊን ባትሰንና በኮሊን ማክናብ ተረጋገጠ ። ሌሎቹ ከሐዱ በኋላ ሻርፕና ኮሊን ማክናብ ቀሩ ።

" ለመርዳት ከምችለው በላይ ልጎዳህ አልፈልግም ሚስተር ማክናብ " አለው ። " የእጮኛህ በትጭጭታችሁ ምሽት መመረዝ ላንተ ምን ያህል እንደሆነ መገንዘብ እችላለሁ ። "

" ስለዚህ ማንሳቱ አስፈላጊ አይደለም " አለ ኮሊን ማክናብ ምንም የፊት ለውጥ ሳያሳይ። " በኔ ስሜት ብዙም መጨነቅ የለብህም ። ይጠቅመኛል ብለህ የምታስበውን ጥያቄ ብቻ ጠይቀኝ ። "

" የሴሊያ አውስቲን ባህርይ ሳይኮሎጂካዊ መነሻ አለው የሚለው ያንተ አስተሳሰብ ነበር ? "

" ለዚያ ምንም አጠራጣሪነት የለውም " አለ ኮሊን ማክናብ " ከፊለግህ ወደ ጉዳዩ ጽንሰ ሀሳብ እንድገባ . . . "

" የለም ! የለም ! " አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ በችኮላ ። " እኔ የሳይኮሎጂ ተማሪ ስለሆንክ ሀሳብህን በፍጹም ልብ በመቀበል ነው ። "

" የህጻንነት ጊዜዋ በተለይ አስከፊ ነበር ። አንዳች ስሜታዊ እቀባ መሥርቶባታል . . . "

" ሊሆን ይችላል ! ይሆናልም " አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ፤ ሌላ መጥፎ ዕጣ ፈንታ የወረሰውን የሕጻንነት ታሪክ ለመስማት ባለመፈለግ ።

" ከልጂቷ ጋር ለጥቂት ጊዜ በፍቅር ቆይታችኋል ? "

" ያን እንኳ መናገር የምችል አይመስለኝም " አለ ኮሊን ጉዳዩን በጥንቃቄ እያምሰለሰለ ። " እነዚህ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ ሳታስበው እየተገለጹልህ ሲሔዱ ያስደንቁህ ይሆናል ከመዛኝ — ህሊናችን ምንም የሚያጠራጥር ነገር አይፈጥሩብንም ። እዎን ፣ አፍ

ቅሬያት ነበር ። ነገር ግን እውነቱ አልተገለጸልኝም ነበር ። በወጣትነት ማግባቱ ዓላማዬ ባይሆንም ከነቃው አዕምሮው ውስጥ ከፍተኛ ሙግት እንደነበረ የሚያጠራጥር አይደለም ። ''

'' አዎን ፣ ትክክል ! ሴሊያ አውስቲን ከአንተ ጋር ባደረገችው ቃልኪዳን ደስተኛ ነበረች ? ማለቴ ምንም የራሷ የሆነ አጠራጣሪ ጉዳይ አልገለጸችልህም ? ግራ ያጋቧትን ነገሮች ? እንዲያው ምንም ላንተ መንገር የሚገባት ነገሮች አልነበሩም ? ''

'' ሥትሠሩ ስለነበረው ነገር ሁሉ በግልጽ ተናግራ ነበር ። ከአዕምሮዋ ቀርቶ የሚያስጨንቃት ምንም ነገር የለም ። ''

'' መቼ ልትጋቡ ነበር ያቀዳችሁት ? ''

'' ለረጂም ጊዜ ለመቆየት እንኳ አልነበረም ። ለጊዜው ግን ሚስት ለማግኘትና ትዳር ለመመሥረት ከምችልበት ሁኔታ ላይ አይደለሁም ። ''

'' ሴሊያ ከዚህ ሥፍራ ጠላቶች ነበሯት ? የማይወዳትና ጥላቻ ያሳደረባት ሰው አለ ብለህ ትገምታለህ ? ''

'' ይህን ለማመን ይቸግረኛል ። እንደዚያ ባለው ጉዳይ ላይ ብዙ አስቤበታለሁ ኢንስፔክተር ። እዚህ ያለው ሰው ሴሊያን የሚያፈቅራት ነው ። ይህን ፍጻሜዋን ያመጣው የግል ጉዳይ እንዳልሆነ ለራሴ ይሰማኛል ። ''

'' የግል ጉዳይ ስትል ምን ማለትህ ነው ? ''

'' ለጊዜው ግልጽ ማድረግ አልፈልግም ። አለ አያደል ? ግልጽ ያለ ሀሳብ እንኳ አይደለም ። ለራሴውም ቢሆን ማለቴ ነው ። ''

እንደዚያ አስከተናገረ ኢንስፔክተሩ አያስቸግረውም ።

ሁለቱ ቃለ ሠጠያቁ የተደረገላቸው የመጨረሻዎቹ ተማሪዎች ሳሊ ፊንችና ኤልሳቤጥ ጆሀንሰተን ናቸው ። ኢንስፔክተሩ ሳሊ ፊንችን በመጀመሪያ አነጋገራት ።

ሳሊ ዓይንን የምትስብ፣ ብትን ቀይ ጸጉር ያላት፣ ብሩህና ብልህ ዓይኖችን የታደለች ወይዘሪት ነበረች ። ከተለመደው ጥያቄና መልሶች በኋላ ሳሊ ፊንች የንግግሩን ሚና ራሷ ወሰደችው ።

'' ምን ማድረግ እንደፈለኩኝ ታውቃለህ ኢንስፔክተር ? የማስበውን ልነግርህ ፈልጌ ነበር ። እኔ በግል ማለቴ ነው ። ከዚህ ቤት አንዳች የተሳሳተ በጣም የተሳሳተ ነገር አለ ። ርግጠኛ ነኝ ! ''

'' ሴሊያ አውስቲን ስለተመረዘች ማለትሽ ነው ? ''

“ የለም!ከ‘ዚያ በፊት ነው የምልህ ። ለጥቂት ጊዜ እኔንም ሊሰ ማኝ ነበር ። ከዚህ ሥፍራ እየተካሔዱ ያሉትን ነገሮች አልወያይኳቸ ውም ። ያን የተቆራረጠ የጀርባ ሻንጣ አልወደድኩትም ። የቫሌሬ ሻርፕ መቆራረጡን አልወደድኩትም ። የብላክ ቢስ ጽሑፎች ላይ ተለም መፍሰሱን አልወደድኩትም ። ከዚህ ሥፍራ መሔድና በፍጥነት መውጣት ፈልጌ ነበር ። ያንን ለማድረግ አሁንም ወደኋላ አልሶም ። ወዲያው አንተ ከሸኘኸን በኋላ አደርገዋለሁ ። ”

“ አንድ ነገር መፍራትሽን ነው የምትነግሪኝ ወይዘሪት ፊንች?”

ሳሊ ራሷን ነቀነቀች ።

“ አምን ፡ ፈርቻለሁ ። አንድ ነገር ወይንም አንድ ምሕረት የለሽ ሰው ከዚህ ሥፍራ ያለ ይመሥለኛል ። አጠቃላይ ሥፍራው አይደለም — እንዴት አድርጌ ላስቀምጠው ያሆን ? ሌላ ነገር እንኳ አይደለም ። የሶም ፡ የለም ኢንስፔክተር ፡ ኮሚኒስቶችን ማለቴ አይ ደለም ። ቃላቶቹ ከከንፈርህ ሊወጡ ሲሞክሩ ተረድቼዋለሁ ። ኮሚ ኒስቶችን ማለቴ አይደለም ። ወንጀለኛ እንኳ እደሆን ይሆናል ምና ልባት ። እኔ እንጃ! ርግጠኛነት ይሰማኛል። ያቺ አስፈሪ አሮጊት ሴትዮ በሚገባ ስለነገሩ ታውቃለች ። ”

“ የምን አሮጊት ሴት ? ሚስ ሀበርድን ማለትሽ አይመስለኝም ። ነው ? ”

“ የለሙ! የለም! እንዬ ሀበርድ አይደለችም ። እርሷ ተወዳጅ ሴት ናት ። አሮጊቷ ኒኮሊተስንን ማለቴ ነው ፡ ያቺን አሮጊት ተኩላ! ”

“ በጣም ፡ ሚገርም ፡ ው ወይዘሪት ፊንች ! የበለጠ ልታብራራ ልኝ ትችያለሽ ? ስለ ሚስ ኒኮሊተስ ማለቴ ነው ። ”

ሳሊ ራሷን ነቀነቀች ።

“ የለም ! መግለጽ የማልችለው ያልኩት ያን ነው ። ልነግርህ የምችለው ነገር ቢኖር ሁልጊዜም በአጠገቧ ባለፍኩኝ ቁጥር ሰውነቴ መዘግነኑንና በፍርሀት መራዱን ብቻ ነው ። አንዳች እንግዳ ነገር ከዚህ ሥፍራ እየተካሔደ ነው ኢንስፔክተር ። ”

“ ትንሽ የበለጠ ግልጽ ብታደርጊው ፈልግ ነበር ። ”

“ እንዲያው ዝም ብዬ የምታኸር ነገር አድርገኸኝ ይሆናል ። መልካም! ምናልባት እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎች ሰዎችም እንደዚያው ተሰምቷቸው ይሆናል ። አኪምቦቦ ያውቃል ። እርሱም በጣም ፍር ሃት አለበት ። ብላክ ቢስም እንደምታውቅ ርግጠኛ ነኝ ። ነገር ግን

አታወጣውም ። ደግሞ ኢንስፔክተር ሴሊያም ስለዚሁ ጉዳይ አንድ ነገር ታውቅ እንደነበር ይሰማኛል ። ''

'' ስለምንድነው አንድ ነገር የምታውቀው ? ''

'' በቃ እንደዚያ ነው ። አንዳንድ የተናገረቻቸው ነገሮች እኮ ነበሩ ። በዚያ በመጨረሻው ቀን ሁሉንም ነገር ግልጽ ለማ ድረግ በራሷ በኩል ስላሉት ነገሮች ስታጋልጥ ሌሎችም ግልጽ መሆን የሚገባቸው ነገሮች እንዳሉ ትንሽ ጠቀስ አድርጌ ነበር ። እንደማ መስለኝ ስለ አንድ ሰው የምታውቀው አንድ ነገር ነበራት ። የተገደ ለችውም በዚህ ምክንያት ይመስለኛል ።

'' ነገር ግን እንደዚያ የከበደ ነገር ሲሆን . . . '' ሳሊ አቋረ ጠችው ።

'' ምን ያህል ከባድ መሆኑን እንደማታውቅ ገልጫለሁ ። በጣም ተጫዋች አይደለችም ታውቃለህ ። ዝምተኛ ናት ። አንድ ሚስጥር ላይ ደርሳለች ። ነገር ግን በሚገባ አላወቀችውም ። ዝም ብላ ይዛ መቆየቱ አደገኛ ሆነባት ። ለማንኛውም ያ ምንም ይሁን ምን የኔ አመለካከት ነው ። ''

'' ገባኝ ። አመሰግናለሁ . . . ሴሊያ አውስቲንን ያየሽበት የመ ጨረሻው ጊዜ ከጋራ - አዳራሹ ክ'ራት በኋላ ባለፈው ምሽት አል ነበረም ? ትክክለኛ ነኝ ? ''

'' ትክክል ነው ! አምን ከ'ዚያም በኋላ ያየኋት ይመስለኛል ።''

'' ከዚያ በኋላ ያየሻት የት ነበር ? ከመኝታ ቤቷ ? ''

'' የለም ። እኔ ወደ መኝታዬ በመሔድ ላይ እያለሁ ማለት ከጋራ ክፍሉ በመውጣት ላይ እያለሁ በፊት ለፊቱ በር ስትወጣ ነበር ። ''

'' ከፊት ለፊቱ በር ስትወጣ ? ከቤቱ ማለትሽ ነው ? ''

'' አምን ። ''

'' ያ ደግሞ የሚያስደንቅ ነው ። ማንም ይህን የተናገረ ሰው አል ነበረም ። ''

'' የሚያውቁት አልመሰለኝም ። በትክክል ይህና እደሩ በማ ለት ወደ መኝታዋ ስትሔድ ነበረች ። እኔ ባላያት ኑሮ ወደ መኝ ታዋ እንደሔደች አድርጌ እወስደው ነበር ። ''

'' በትክክል ወደ ላይ ሔዳ አንዳንድ ነገሮችን ደራርባ ከቤት ወጣች ? ትክክል ነው ? ''

ሳሊ ራሷን ነቀነቀች ።

“እንደሚመስለኝ የሆነ አንድ ሰው ለመገናኘት ነበር የወጣችው።”

“ገባኝ ! አንድ ሰው ከውጭ ወይንም ከተማሪዎቹ አንዱ ሊሆን ይችላል ።”

“እኔ እንኳ ከተማሪዎቹ አንዱ ሊሆን ይችላል የሚለውን እጠራጠራለሁ። አየህ ከአንዱ ጋር በግል መነጋገር ብትፈልግ ከቤት ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ ለመነጋገር አመቺ አይደለም ። እንግዲህ አንድ የሆነ ሰው ከቤት ወጥታ ውጭ እንድታገኘው ሀሳብ አቅርቦላት ይሆናላ ?”

“መቼ እንደተመለሰች አውቀሻል ?”

“የለም ! ፍጹም !”

“ጂሮኒሞ ወንዱ ሠራተኛ ያውቅ ይሆን ?”

“እርሱ ሊያውቅ ይችል የነበረው ከአምስት ሰዓት በኋላ ብት ወጣ ነበር፤ በዚያ ጊዜ ነው በሩን በመወርወሪያው ቀርቅሮ ሰንሰለቱን የሚመልሰው ። እስከዚያ ድረስ ማንም ሰው በራሱ ቁልፍ እየከፈተ መግባት ይችላል ።”

“ከቤቱ ስትወጣ ያየሻት በትክክል በስንት ሰዓት ላይ እንደነበር ታስታውሻለሽ ?”

“አራት ሰዓት አካባቢ ይሆናል ። ምናልባት ከአራት ትንሽ አንድ አሥር ደቂቃ ያህል ያለፈ ይመስለኛል ፣ ከዚያ የሚበልጥም አይመስለኝ ።”

“ገባኝ ፣ አመሰግናለሁ ወይዘሪት ፊንች ።”

ከሁሉም በመጨረሻ ኢንስፔክተሩ ያነጋገራት ኤልሳቤጥ ጆሀንስተንን ነበር ። በልጅቷ ብቃት በጣም ተደሰተ ። ጥያቄዎቹን በመላ በብልሀነት በጥራት በመመለስና በሥነ ሥርዓት ጊዜ እየሰጠችው ስትነጋግረው ቆየች ።

“ሴሊያ አውስቲን ” አለ ፣ “ያንቺን ጽሑፍ አለማበላሸቷን ፍጹም አጥብቃ ተቃውማለች ወይዘሪት ጆሀንስተን ። ታምኛታለሽ ?”

“ሴሊያ እንደዚያ ሠርታለች ብዬ ፍጹም አላምንም ! የለም !”

“ማን እንደሠራው አታውቂም ?”

“ግልጽ ያለው መልስ ኂጌል ቻፕማን ነው ። ነገር ግን ትንሽ ይህንንም ለማመን ያስቸግረኛል ። ኂጌል በጣም ብልህ ነው ። የራሱን ቀለም የሚጠቀም አይመስለኝም ።”

“ኂጌል ካልሆነ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል ?”

“ ያ በጣም የሚያስቸግር ይሆናል ። እንደሚመስለኝ ግን ማን መሆኑን ሲሊያ ታውቃለች — ወይንም ትጠራጠራለች ። ”

“ እንደዚህ ብላ ነግራሽ ነበር ? ”

“ ይህንንም ያህል ግልፅ አልነበረም ። ነገር ግን በዚያ በሞተችበት ቀን ምሽት ከ‘ራት በፊት ወደ መኝታ ክፍሌ መጥታ ነበር ። ልትነግረኝ የመጣችውም ምንም እንኳ ለተሠረቁት አንዳንድ ዕቃዎች ሀላፊ ሆና ብትቀርብም በፍጹም ጽሑፎቹን አለማበላሸቷን ነበር ። እኔም ይህንኑ እንደማምን ገለጽኩለት ። ነገር ግን ማን ሊሆን እንደሚችል ታውቅ እንደሆነ ጠየቅኋት ። ”

“ ታዲያ ምን አለችሽ ? ”

“ እርሷ ያለችኝ ” አለችና ኤልሳቤጥ ለጥቂት ጊዜ ጸጥ አለች ። የምትናገረውን ነገር ትክክለኛነት የምታረጋግጥ ትመስላለች — እርሷ ‘ ርግጠኛ መሆን እንኳ በእውነት አልችልም ፡ ምክንያቱ ለምን እንደሆነ አላውቅም . . . ሥህተት ወይንም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ። ርግጠኛ ነኝ ማንም ሆነ ማን በጣም ነው የሚያዝነው ። ራሱን እስከ ማጋለጥም ይደርሳል ። ’ አለችና ሲሊያ ቀጠለች ‘አንዳንድ የማይገቡኝ ነገሮች አሉ ፡ ፖሊሱ እንደመጣበት ቀን ፡ እንደ ኤሌክትሪክ አምፑ ሎቹ ’ አለችኝ ። ”

ሻርፕ አቋረጣት ። ”

“ እነዚህ ፖሊስና የኤሌክትሪክ አምፑሎች የምትያቸው ምን ድና ቸው ? ”

“ አላውቅም ! ሲሊያ ያለችው ‘ እኔ አልወሰድኳቸውም ’ ነው ። ቀጥላም የተናገረችው ‘ ከፓስፖርቱ የተዛመደ ነገር ከሆነ ይደንቀኛል ። እንደዚያ ይሆን ? ’ ነበር ። እኔም ፡ የምን ፓስፖርት ነው የምታወሪው ? ብዬ ስጠይቃት ‘ አንድ ሰው ፓስፖርት ያጭበረበረ ያለ ይመስለኛል ’ አለችኝ ። ”

ኢንስፔክተሩ ለአንድ ሁለት ደቂቃዎች ጸጥ ብሎ ቆየ ።

አሁን አንድ ጥለት ከአዕምሮው እየተቀረጸ ነው ። ፖስፖርት ...

“ ሌላስ ምን ነገር ነገረችሽ ? ” አለ ።

“ ሌላ እንኳ አልነገረችኝም ። ነገር ግን ‘ ነገ ደግሞ በበለጠ አውቃለሁ ’ ብላኝ ነበር ። ”

“ እንደዚያ አለች ? ስለዚህ ጉዳይ ነገ በይበልጥ አጣራለሁ ። በጣም ከፍተኛ ቁም ነገር ያለው አነጋገር ነው ሚስስ ጆሀንስተን ። ”

“ አምን ። ”

ኢንስፔክተሩ እንደገና እያሰላሰለ ጸጥ ብሎ ቆየ ።

ስለ ፓስፖርት አንድ ነገር — ከፖሊስ የተደረገ ጉብኝት . . . ወደ ሒኮሪ ጎዳና ከመምጣቱ በፊት ፋያሎቹን በመላ በሚገባ ተመ ልክቷቸዋል ። የውጭ ዜጋ ተማሪዎችን በሚያስተናግዱ ሆቴሎች ላይ ዓይን ተጥሎባቸዋል ። 26 ሒኮሪ ጎዳና እንኳ ጥሩ ሪኮርድ ነበረው። ነጥቦቹ በጣም ጠቃሚና ብዙም ሀሳብ የማይሰጡ ነበሩ። በእንዲት ሴት ገንዘብ የሚኖር በኢፊልድ ፖሊስ የሚፈለግ የምዕራብ አፍሪካ ተማሪም ነበረ ። ይህ ተማሪ ከሒኮሪ ጎዳና ለጥቂት ቀናት ቆይቶ ከዚያ ወደ ሌላ ሥፍራ ሔደ ። በመካከሉም ተይዞ ከሀገር እንዲወጣ ተደርጓል ። በካም ብሪጅ የአንድ ሀላፊ ሚስት በመገደሉ “ ፖሊሱን ለመርዳት ” ይህንኑ አውሮፓዊ - እስያዊ ለመፈለግ ከሆስቴሎቹና መኝታ ቤቶች የተለመደ ማጣራት ሲደረግ ነበር ። ይኸውም ቢሆን ወንጀሉን የፈጸመው አንድ ወጣት ለሆል ፖሊስ በገዛ ፈቃዱ እጁን ከሰጠ በኋላ ችግሩ ተቃሏል ። ሌላው አንድ የህቡዕ አመጽ በራሪ ወረቀት ሥርጭት ያደረገ ተማሪ ጉዳይ ነው ። እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ከጥቂት ጊዜ በፊት የተካሔዱ ስለነበሩ በምንም ዓይነት ከሴሊያ አውስቲን ሞት የተዛመዱ አልነ በሩም ።

በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ የኤልሳቤጥ ጆሀንስተንን ብልሀ አርቆ ተመልካች ዓይኖች ለመመልከት ቀና ሲል እርሷም እየተመለከ ተችው ነበረች ።

እንደመልስ ሁሉ፡ “ እስኪ ንገሪኝ ወይዘሪት ጆሀንስተን? እንዲ ያው ስለዚህ ሥፍራ አንዳች የተጣላተ ዐይነት — የተቀረጸብሽ ሀሳብ አለ ? ”

የመገረም ገጽታ ይታይባታል ።

“ በምን መንገድ ነው ስሕተቱ ? ”

“ እንዲህ ነው ብዬ መናገር እንኳ አልችልም ! ወይዘሪት ሳሊ ፊንች ስለነገረችኝ ስለአንድ ነገር እያሰብኩኝ ነኝ ። ”

“ አቤት ! ሳሊ ፊንች ? ”

የድምጿን ቃና መጨበጥ አልተቻለውም ። ጉጉት አሳደረበትና ቀጠለ ።

“ ወይዘሪት ፊንች አሽሚጣጭ ብትሆንም ተግባራዊ አመለ ካከት አላት ። ከዚህ ሥፍራ አንዳች ግራ የሚያጋባ ነገር መኖሩን

አጥብቃ ገለጸ ነበር — ምንም እንኳ እንዲህ ነው ብላ እቅጩን ባት ናገረውም ። ''

ኤልሳቤጥ ኮስተር ብላ ፣

'' ያ የርሷ አሜሪካዊ አስተዳደግ ያለዘበው የአስተሳሰብ ስልቷ ነው ። ሁሉም ያውና ቸው ። እነዚህ አሜሪካኖች ሲባሉ ቅብጥብ ጠች፣ አሳቢዎች ፣ ተጠራጣሪዎች ናቸው ። እያንዳንዷን የማትረባ ነገር ሁሉ ቦታ ይሰጧታል ! እስኪ ራሳቸውን በእስማት አዚም ፣ በሥለላ የአ ዕምሮ ፍርሃት ሀማም ፣ በኮሚዩኒዝም ቅዠት እያሽበሩ እንደሚያ ጃጅሉ ተመልከታቸው ። ሳሊ ፊንች ደግሞ የተለየች ናት ። ''

የኢንስፔክተሩ የማወቅ ፍላጎት ጨመረ ። ኤልሳቤጥ ሳሊ ፊንችን ትጠላታለች ። ለምን ? ምክንያቱ ሳሊ አሜሪካዊት ስለሆነች ነበር ? ወይንም ኤልሳቤጥ አሜሪካኖችን የምትጠላው ሳሊ ፊንች አሜሪካን ስለሆነችና ይህችን ባለ ቀይ ጸጉር አሜሪካዊት የምትስብ ውብ ወይ ዘሪት የምትጠላበት አንድ የሆነ ምክንያት ኖሯት ይሆን ? ምናልባት የግሷ ተራ የሴቶች ቅንዓት ሊሆን ይችል ይሆናል ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት ከደረሰበት አንድ ነጥብ ላይ አመለካከቱን ለማንተራስ ወሰነ ። በትህትናም ፣

''እንደዚህ ባለው አካባቢ እንደምታይው ሁሉ ወይዘሪት ጆሀን ስተን የአስተሳሰብ ችሎታ በጣም ሊራራቅ ይችላል ።እንዳንድ ሰዎች ለሁሉም ነገር ማስረጃዎችን እንፈልጋለን ። ነገር ግን ከፍተኛ የአስ ተሳሰብ ችሎታ ያለው ሰው ሲያጋጥመን ደግሞ — ''

አሁንም ለትንሽ ጊዜ ጸጥ አለ ። አነጋገሩ እንኳ ካብ ካብ ለማድረግ ነበር ። ለዚህ መልስ ይኖራት ይሆን ?

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ንግግሯን ቀጠለች ።

'' የምትለው ነገር ይገባኛል ኢንስፔክተር ። አንተው እንዳል ከው ከዚህ ሥፍራ ያለው ምሁራዊ ደረጃ ከፍተኛ አይደለም ። ኒጌል ቻፕማን በርግጥ የፍጥነት ችሎታ አለው ። ነገር ግን አዕምሮአዊ እው ቀቱ የጠለቀ አይደለም ። ሊዎናርድ ባትሰን የጥረት ፣ የጉልበት ሰው ነው ። ቫሌሪ ሆብሐውስ ጥሩ ጭንቅላት አላት ። አመለካከቷ ግን የሸቀጥ ነው ። በማንኛውም የሚጠቅም ነገር ላይ ጭንቅላቷን ለመ ጠቀም በጣም ትሰንፋለች ። ስለዚህ ከሁሉም ያልሆነ የሠለጠ፣ አዕ ምሮ ያስፈልግሃል ። ''

'' አዎን ! እንዳቺ ያለ ውድ ወይዘሪት ጆሀንስተን ። ''

አስተያየቱን ካለተ'ውሞ ተቀበለችው ። በዚሁ አጋጣሚ በአግ ርሞት ከዘመናዊ አስደሳች ባህርይዋ ጀርባ የራሱን ስውታዎች በማ ነጋገሥ በኩል ከፍተኛ ትምክህት ያላት ወጣት ሴት መሆኗን ተገ ነዘበ ።

" ወያዘራት ጆሀንስተን በ'ውነት ነው የምልሽ ከባልንጀሮችሽ ተማሪዎች ላይ ካለሽ አመለካከት የ'ኔም ተመሣሣይ ነው አላለሁ ። ቻፕማን ብልህ ቢሆንም ሀጻንነት ያታይበታል ። ቫሌሪ ሆብሐውስ ሞንቅላት አላት ነገር ግን ቢሕይወት ውስጥ ደስታን የጠገበች ትመ ስላለች ። አንቺ ያው ራስሽ እንደተናገርሽው ሁሉ የሠለጠነ አዕምሮ ነው ያለሽ ። ለ'ዚህ ነው ለተናገርሽው ሁሉ ዋጋ የምሰጠው — ለዚህ በከፍተኛ ደረጃ ብቸኛ ለሆነ የሠለጠነ አዕምሮ አስተያዬቶች አለኝ ማለቴ ነው ። "

ለጥቂት ጊዜ ከሚገባው በላይ ያጋነነ መስሎች ፈርቶ ነበር ። ነገር ግን ምንም የሚያስፈራው ነገር አያኖርም ።

" ስለዚህ ሥፍራ የሚነገር ምንም ሥህተት ሊኖር አይችልም ኢንስፔክተር ። የሳሊ ፊንችን ወሬ ትኩረት አትስጠው ። ይህ ሠላ ማዊ የሆነ ም ንም ችግር የሉለበት ሆስቴል ነው ። ከዚህ ሥፍራ ምንም ዓይነት የዓመጽ ሥራ ከንውን ማግኘት እንደማትችል አረጋግጣለሁ ።"

ኢንስፔክተር ሻርፕ ትንሽ የመገረም ሁኔታ ይታይበታል ።

" እኔ ስለ ዓመጽ ሥራ ከንውን አልነበረም ሳስብ የነበር ኩት ። "

" ገበቶኛል — " አለች ትንሽ በመደነቅ ሠልክ ። " ሴሊያ ስለ ፖስፖርት የተናገረችውን በማያያዝ ነበር ። ነገር ግን ጉዳዩን በማጤንና ሚስረጃዎቹን ከማምት በማስገባት የሴሊያ ሞት ለ'ኔ እንደ ሚመስለኝ የግል ጉዳይ የምለው ዓይነት — ምናልባትም የወሲብ ውስብስብ ችግር ሳይሆን አይቀርም ። ይህ ጉዳይ እኔ ሆስቴል ከም ለው ሆስቴል ወይንም ከዚህ በመካሔድ ላይ ካለ ፣ ማንኛውም ነገር የተያያዘ አለመሆኑን አረጋግጣለሁ ። ምንም እኔ የማውቀው ርግጠኛ ነገር የለም ። ከ'ዚህ አንዳች ነገር ቢኖር ለማወቅ እችል ነበር ። የማስ ተዋል ችሎታዬ በጣም ከፍተኛ ነው ። "

" ገባኝ ፣ በጣም አመሰግናለሁ ወይዘሪት ጆሀንስተን ። በጣም ቅንና ተባባሪ ሰው ነሽ ። "

ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ወጣች ። የኢንስፔክተር ሻርፕ ዐይኖች ከበሩ ላይ ተሰትረዋል ። አሥር አለቃ ኮብ ከሀሳቡ እስኪነቃ ደጋግሞ ሁለት ጊዜ መናገር ነበረበት ።

“ ምን ? ”

“ ይበቃል ጌታዬ ። ”

“ አዎን ሌላ ምን ይኖረናል ? ትንሽ ውብና ውድ ነገር ። ነገር ግን ኮብ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ። ነገ ከ‘ዚህ ሥፍራ የፍ ቲሻ ትዕዛዝ ይዤ እመጣለሁ ። አሁን እየተጨዋወትን እንወጣለን። እነርሱም ሁሉም ነገር ያለቀለት ይመስላቸዋል ። ነገር ግን ከ‘ዚህ ሥፍራ አንዳች ነገር እየተካሔደ ነው ። ነገ የማልገለብጠው ድንጋይ አይኖርም — አየህ የማታውቀውን ነገር ስትፈልግ እንዲህ ቀላል አይም ሰልህ ፣ ፍዳ ነው ምታየው ። ነገር ግን ፍንጭ የሚሰጠኝ ነገር የማግኘት እድል ይኖረኛል ። አሁን የወጣችዋ ልጅ በጣም ጉጉት የምታሳድር ናት ። የናፖሊዎን እኔ ያዊነት (ተከለሰውነት) ያላት ናት ። አንድ የም ታውቀው ነገር እንዳለ እጥብቄ እጠራጠራለሁ ። ”

— 12 —

ክፍል አንድ

ሔርኩሌ ፖይሮት ከሥራ ላይ ነው ። የመልስ ደብዳቤ በማጸፍ ላይ ነው ። ዐረፍተ ነገሩን በቃል እያጸፉት ሳይጨርሰው አቋረጠ ። ወይዘሪት ሊመን በጥያቄ መልክ ቀና ብላ ተመለከተችው ።

“ አቢት መሴ ፖይሮት ? ”

“ አዕምሮዬ ይጋልባል ! ” አለ እጁን በማወዛወዝ ፖይሮት ። “ ደግሞ ይህ ደብዳቤ እስከዚህም አስፈላጊ አይመስለኝም ። እባክሽ አንድ ጊዜ እህትሽን በስልክ አገናኚኝ ? ”

“ እሺ መሴ ፖይሮት ። ”

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፖይሮት ክፍሉን አቋርጦ በመሔድ ከጸሐፊው እጅ መነጋገሪያውን ተቀበለ ።

“ ሀሎ ! ” አለ ።

“ አቢት መሴ ፖይሮት ነህ ? ”

ሚስ ሀበርድ ትንፋሿን ለማውጣት የተቸገረች ትመስላለች ።

“ መቼም እንዳልረበሽኩሽ እተማመናለሁ ሚስ ሀበርድ ? ”

“ ረብሻውን አሁን አልፈዋለሁ ” አለች ሚስ ሀበርድ ።

“ ፍርሃትና ድንጋጤ ነበረብሽ ማለት ነዋ ? ” አለ ፖይሮት በቅን መንፈስ ።

“ አዎ ! ደህና ገልጸኸዋል መሴ ፖይሮት ። የነበረው ሁኔታ በት ክክል እንደዚያ ነበር ። ኢንስፔክተር ሻርፕ ለተማሪዎች በሙሉ ቃለ መጠይቁን ትላንት አቅርቦ ጨርሷል ። ዛሬ ደግሞ የፍተሻ ትዕዛዝ ይዞ ተመልሷል ። ሚስ ኒኮሊተስ የፍራቻ ጭንቀት ይዟት ከእጁ ላይ እየተንዘፈዘፈች ነው ። ”

ፖይሮት በጉዳዩ በጣም አዘነ ።

ሞኖሎግ ፣ “ እንዴት ቅንጡ ጥያቄ ልጠይቅሽ ፈልጌ ነበር ? የጠራትን ዕቃዎች ዝርዝር ልከሽልኝ ነበር — ሌሎችም በመካሔድ ላይ ያሉትን እንግዳ ነገሮች ። ልጠይቅሽ የፈለኩት ፣ እነዚህን ዝርዝሮች ስትጽፊ በትደም ተከተላቸው ነበር ? ”

“ ማለት የፈለክው ? ”

“ ማለት የፈለኩት የዕቃዎቹ ዝርዝር የተጻፈው በትክክል የመጥፋት ቅደም ተከተላቸውን ተከትሎ ነው ? ነው ” ።

“ የለም ! አልነበረም ። አዝናለሁ — እንዳስታወስኳቸው ነው ያስቀመጥኳቸው ። ያሳሳትኩህ ነገር ካለ በጣም አዝናለሁ ። ”

“ አስቀድሚ መጠየቅ ነበረብኝ ” አለ ፖይሮት ። “ ነገር ግን በዚያን ወቅት እስከዚህም ዋጋ ያለው መስሎ አልታየኝም ነበር ። ዝርዝሩ አሁንም ይኸው ከ‘ጄ ይገኛል ። አንድ የታሸት ጫማ ፣ የጅ አምባር ፣ የአልማዝ ቀለበት ፣ የፓውደር መያዣ ፣ ሊፕስቲክ ፣ የልብ-ምት መለኪያና ወዘተ ... ። ነገር ግን በጠፋበት ቅደም ተከተል አይደለም ነው የታ ትይኝ ? ”

“ አይደለም ። ”

“ አሁን ልታስታውሽው ትችያለሽ ፣ ወይስ በጣም ይቸግርሻል ? ትክክለኛው ቅደም ተከተል እንዴት ነው ? ”

“ አሁን ለማስታወስ እችል እንደሆን ርግጠኛ አይደለሁም መሴ ፖይሮት ። ጥቂት ጊዜ እንደሆነ ታውቃለህ ፣ ለማስታወስ መሞከር ይኖርብኛል ። ያኔ ከእህቴ ከተነጋገርኩኝ በኋላ ከአንተ ዘንድ እንደታ መጣ አውቄ ነበር ። ከዚያ ዝርዝር አወጣሁ ፣ ያስቀመጥኳቸው ግን እቃዎቹን እንዳስታወስኳቸው ቅደም ተከተል መሆን አለበት እላለሁ ። ማለቴ የታሸቱ ጫማ በጣም ልዩ ስለነበረ ፣ ቀጥሎ ደግሞ የ‘ጅ አምባሩና የፓውደር መያዣው ፣ የሲጋራ መለኮሻውና የአልማዝ ቀለበቱ ሁሉም በጣም ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸው ነገሮች በመሆናቸው የእውነተኛ ሴባ ሥራዎች አድርገን አየናቸው ። ሌሎቹን ትኩረት የማይሰጣቸውን ነገሮች በማስታወስ ጨምሬ ጻፍኳቸው ። እነዚህ ደግሞ የቦሪክአሲድ ፣ የኤሌክትሪክ አምፑሎችና የጀርባ ሻንጣዎች ነበሩ ። ዕቃዎቹ እንኳ ቁም ነገር ያላቸውም አልነበሩም ። በኋላ ላይ ከሀሳቤ ስለሙጡ የጻፍኳቸው ናቸው ። ”

“ ገባኝ ” አለ ፖይሮት ። “ አምን ገባኝ . . . አሁን ልጠይቅሽ የምወደው እመቤት አረፍ ብለሽ ጊዜው ሲኖርሽ . . . ”

‘‘ ሚስ ኔኮሊተስን ከመኝታዋ አስተኝቼ አዕምሮዋን የሚያረጋጋላት ነገር ከሰጠኋት በኋላ ጀርኒሞና ማርያን አበረታትቼ ሳበቃ ትንሽ ጊዜ ይኖረኛል ። ታዲያ ላደረግልህ የምትፈልገው ነገር ምንድነው ? ’’

‘‘ ተቀምጠሽ የተለያዩት ነገሮች የተፈጸሙባቸውን አጋጣሚዎች በመከተል ቅደም ተከተላቸውን እንድትጽፊልኝ ነው ። ’’

‘‘ ይቻላል መሴ ፖይሮት ። የጀርባ ሻንጣው የመጀመሪያ መሆኑን አምናለሁ ፣ የኤሌክትሪክ እግሮቹ — ከሌሎቹ ጉዳዮች በሙ ንም የተያያዘ መስለው አይታዩኝም - ቀጥሎ የጎጅ አግባሩና የጋውዴሩ መያዣ፣ የለም - የምሽት ጫማው ። እምን ለጊዜው ከ‘ዚያ ቆመህ እኔ ሀሳቤን ሳወጣ ሳወርድ መጠበቅ የለብህም ! በምችለው አትም በቅደም ተከተላቸው ለመጻፍ እሞክራለሁ ። ’’

‘‘ አመሰግናለሁ እመቤት ። ባለውለተኛዬ ነሽ ። ’’

ፖይሮት መነጋገሪያውን ከሥፍራው አስቀመጠ ።

‘‘ ከራሴ ተጣልቻለሁ ’’ አላት ለወይዘሪት ሊመን ። ቀጥሎም ‘‘ ከሥርዓትና ከቅደም ተከተል ተለያይቻለሁ ። ከመጀመሪያው ይህን ማረጋገጥ ነበረብኝ ። እነዚህ ሥርቆቶች የተካሔዱበትን ትክክለኛ ቅደም ተከተል ማወቅ ነበረብኝ ’’ አላት ።

‘‘ ያሳዝናል ! ያሳዝናል ’’ አለች ሳታስበው ወይዘሪት ሊመን ። ‘‘ ለመሆኑ እነዚህን ደብዳቤዎች አሁን ለመጨረስ አስበሃል መሴ ፖይሮት ? ’’

ፖይሮት አሁንም እንደገና ትዕግሥት በማጣት ለጊዜው ገለል እንድትልለት ጠየቃት ።

ክፍል ሁለት

የፍተሻ ትዕዛዙን በመያዝ ቅዳሜ ጠዋት ከሔኮሪ ጎዳና ከተ መለሰ በኋላ ኢንስፔክተር ሻርፕ ከሚስ ኒኮሊተስ መነጋገር እንደሚ ፈልግ ገለጸ ። ሚስ ኒኮሊተስ ከሚስ ሀበርድ ዘንድ ዘወትር ቅዳሜ ሒሳብ ለማወራረድ ትጣጣለች ። ማድረግ የፈለገውን አስታወቀ ።

ሚስ ኒኮሊተስ ጠንካራ ተቃውሞ አቀረበች ።

" ይህ እኮ ስድብ ፣ ስም ማጥፋት ነው ! ተማሪዎቹ ለቀው ይወ ጣሉ ። ከዚያ በኋላ አበቃልኝ ፣ ከሰርኩ . . . "

" የለም እመቤት ። ሁሉም ይገባቸዋል ። ርግጠኛ ነኝ ። ከዚ ያም በላይ የነፍስ ጥራት ወንጀል ነው ። "

" የነፍስ ጥፋት ወንጀል አይደለም — ራስን በራስ ማጥፋት እንጂ ። "

" ርግጠኛ ነኝ ፣ አንድ ጊዜ ካስረዳኋቸው በኋላ ማናቸውም አይቃወሙም . . . " ስትል ሚስ ሀበርድ አረጋጋቻት ።

"ርግጠኛ ነኝ፣" አለች፣"ሀሉም ሰው ይገባዋል። ከእንትና በስተ ቀር ማለቴ ነው። ፣" አለች በሀሳብ ተወጣ እንዳለች፣" እ... ምናልባት ከሚስተር አህመድ አሊና ከሚስተር ቻንድራ ላል በስተቀር ። "

" አቤቱ ፣ " አለች ሚስ ኒኮሊተስ ። "ለነ'ሱ ማነው ግድ ያለው?"

" አመሰግናለሁ እመቤት ፣ " አለ ኢንስፔክተር ። " እንግዲ ያውስ ከ'ዚሁ ከእንግዳ ቤትሽ እጀምራለሁ ። "

ወዲያውኑ አፍታም ሳትቆይ ሚስ ኒኮሊተስ ተቃውሞዋን በማ ሰማት አምቧረቀች ።

" ከሌላ ከፈለክበት ሥፍራ ፈትሽ ! " ነገር ግን እዚህ አይቻ ልም ! እቃወማለሁ ! " አለች ።

" አዝናለሁ ! ሚስ ኒኮሊተስ ፣ ነገር ግን ቤቱን ከላይ እስከ ታች መፈተሽ አለብኝ ። "

“ ያ ትክክል ነው ። ነገር ግን እዚህ ክፍል ውስጥ መሆን የለ በትም ። እኔ በቤቱ ውስጥ ከሕግ በላይ ነኝ ። ”

“ ማንም ከሕግ በላይ ሰው የለም ! ወደ ጎን እንድትሆኚልኝ ለመጠየቅ እገደዳለሁ ! ”

“ ይህ መጠን ያጣ ጭካኔ ነው ! ” አለችና ሚስ ኒኮሊተስ በቁጣ ፈገገች ። “ ሥልጣንህን ለማሳየት የምትፈልግ ሕገ ወጥ ሰው ነህ ! ለባለሥልጣኖች አመለክታለሁ ። ለተጠሪ እንደራሲዬም አመለክታለሁ ። ለጋዜጠኞች በሙሉ እጽፋለሁ ። ”

“ ለፈለግሽው አመልክቺ እመበት ! ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ፣ “ ብቻ ይህንን ክፍል መፈተሽ አለብኝ ! ”

በቀጥታ ከጽሕፈት ቤቱ ጀመረ ። አንድ ትልቅ የጣፋጭ ኬኮችና ብስኩቶች ካርቱን ፣ ብዙ ቁልል ወረቀቶችና በጣም የተሠበጣጠሩ ዕቃዎች ተመለከተ ። በቅደም ተከተል ፍለጋውን ከወደ ጥግ ከቆመው ቁም ሣጥን ቀጠለ ።

“ ቁም ሣጥኑ ተቆልፏል ። ቁልፉን ለማግኘት እችላለሁ ? ”

“ በፍጹም ! ” ስትል ሚስ ኒኮሊተስ መለሰች ። “ ፍጹም ፣ ፍጹም ፣ ፍጹም ቁልፎቹን አታገኝም ! አውሬ ፣ አሣማ ፖሊስ ! ፖሊስ ፣ይሽው ተፋሁብህ ። ተፋሁ ! ተፋሁ ! ተፋሁ ! ”

“ ቁልፉን ብትሰጪኝ የተሻለ ነው ፣ ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ “ ካልሆነ በቀላሉ በሩን እከፍተዋለሁ ። ”

“ ቁልፉን አልሠጥህም ! ቁልፉን ከማግኘትህ በፊት ከላዬ ልብሴን ሁሉ መቅደድና መግፈፍ አለብህ!ያ ደግሞ . . . ያ ደግሞ ስም ማጥፋት ይሆናል ! ”

“ ኮብ ! እባክህ ሞሮ አቀብለኝ ፣ ” አለ ኢንስፔክተሩ ወደ የራሱን ውሳኔ በመከተል ።

ሚስ ኒኮሊተስ በንዴት እየጮኸች ታለቅሣለች ። ኢንስፔክተር ሻርፕ ፆንም ዋጋ አልሰጣትም ። ሞረዱ ጠጣ ። ሁለት ስንጥቅ ብቻ ! ከዚያ በኋላ የቁም ሣጥኑ በር ተከፈተ ። ወደፊት ሲወድቅ ብዙ የተደበቁ የብራንዲ ጠርሙሶች ከቁም ሣጥኑ ይንዷዱ ጀመር ።

“ አውሬ ! አሣማ ! ዲያብሎስ ! ” ስትል ሚስ ኒኮሊተስ አምባረቀች በት ።

“ አመሰግናለሁ እመቤት ! ” አለ ኢንስፔክተሩ በትህትና ። ቁጥሎም ፣ “ከ‘ዚህ ጨርሰናል ” አለ ለባልደረባው ።

ሚስ ኒኮሌተስ የአዕምሮ ጭንቀት ይዟት እያለ ንበር ሚስ ሀበርድ በቅልጥፍና ጠርሙሶቹን ከሥፍራቸው የመለሰቻቸው ።

አንድ ልዩ ሚስጥር ፣ የሚስ ኒኮሊተስ የስሜት ሚስጥር አሁን ግልጽ ሆኗል ።

ክፍል ሦስት

ሚስ ሀበርድ ከክፍሏ ሆና ከግል የመድሐኒት ቁምሣጥን ውስጥ ጥቂት ማረጋጊያ ሙድሐኒት ስትቀዳ የፖይሮት የስልክ ጥሪ አንቃጨለ ። መነጋገሪያወን ካስቀመጠች በኋላ ወደ ሚስ ኒኮሊተስ ተመልሳ ሔደች ። ከራሷ ከግል ክፍሏ በተረከዟ ሶፋውን እየመታችና እያለቀሰች ሳለች ነበር ጥላት የወጣችው ።

" አሁን ይህን ጠጪ ፣ ከዚያ በኋላ ይሻልሻል " አለቻት ሀበርድ ።

" ጌስታፖ (የናዚ ደህንነት ፖሊስ) ! " አለች ሚስ ኒኮሊተስ ። በአሁን ጊዜ ጸጥ ብትልም ብስጭቱ እንዳለ ነው ።

" አንቺን ብሆን ምንም አልበሳጭም ነበር ፣ " አለች ሚስ ሀበ ርድ በትህትና ።

" ጌስታፖ ! " አለች ሚስ ኒኮሊተስ እንደገና ። " ጌስታፖ ! በቃ እንደዚያ ናቸው ! "

" ሥራቸውን መሥራት አለባቸው ። ይህንን ማወቅ ይኖርብ ሻል ፣ " አለች ሚስ ሀበርድ ።

" ታዲያ በግል ቁምጣዬ ገብቶ ማተራመሱ ነው ሥራቸው ? ያ እናንተ ማየት ሚገባችሁ አይደለም ... አልኳቸው ፣ ቆለፍኩት ። ቁልፉን ከሰውነቴ ውስጥ ደበቅኩት ። እንቺ ከዚህ በምስክርነት ባት ገኝ ልብሱን ካለአንዳች ሀፍረት ይቀዳድዱት ነበር ። "

" የለም ፣ እንደዚያ የሚያደርጉ አይመስለኝኝም ፣ " አለች ሚስ ሀበርድ ።

"ያ ያንቺ ሀሳብ ነው ! በምትኩ ሞረድ በማምጣት በሩን በሀይል ከፈቱት ። ለ'ዚህ በቢቱ ዕቃ ላይ ለደረሰው ጥፋት ከፋይዋ ማን እኔ ነኝ ። ገባሽ ? "

" አምን ፣ አየሽ ቁልፉን ለመስጠት ፈቃደኛ እስካልሆንሽ ... "

“ ቁልፉን ለምን እሰጣቸዋለሁ ? የራሴ ቁልፍ ነው ። የግል ቁልፌ ነው ። ይህ ደግሞ የግል ክፍሌ ነው ። አዎን የግል መኝታ ቤቴ ነው ። ስለዚህ ፖሊሶቹን ‘ውጡ ልኝ’ ! አልኩኝ። ነገር ግን አልወጡልኝም ።”

“ አዎን ፣ ግን ሚስ ኂሊተስ የነፍስ ግዳይ ወንጀል መፈጸሙን አትርሺ ። ከሰው ግድያ በኃላ አንድ ሰው በወትሮው ቀን የማያስደስቱ ነገሮችን ማሰወገድ አለበት ። ”

“ምንም የነፍስ ሣጥኑት የለም ብዝሽ !” አላት ሚስ ኂሊተስ ። ቀጥላም “ያቺድንክዩ ሴሊያ ራሷን በራሷ ነው ያጠፋች። የደደቢ ፍቅር ከፈጸመች በኃላ መርዝ ወሰደች ። ይህ ሁልጊዜም ቢሆን ሊፈጸም የሚችል ነገር ነው ። እነዚህ የዛሬዎቹ ወይዛዝርት ስለ ፍቅር ደደቦች ናቸው ። ልክ ፍቅር ችግር እንደሆነ ሁሉ ! ዓመት ፣ ሁለት ዓመት መከነፍ በቃ ያ ታላቅ ስሜት አበቃለት ! አንዱ ወንድ ከሌሎቹ ተመሣሣይ ነው ! እነዚህ ደደብ ልጃገረዶች ግን ይህን አያውቁም ። የእንቅልፍ እንክብሎችን ወይንም ሕዋስ የሚያነጣ መርዝ መውሰድ ወይንም ጋዝ ከፍቶ ራስን መግደል ነው ፣ አበቃ ! ” አለች ።

“ አዎን ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ አንድ ዙር በመሽከርከር ውይይቱ ከጀመረበት እንደተመለሰች ሁሉ ፣ “ አሁን ቅንጣትም ያህል አያሳስበኝም ፣ ” አለች ።

“ እንደዚያ ነው ሚሻልሽ ? እኔ ግን ወዳጄ ማሰብ አለብኝ ! ለ‘ኔ ከእንግዲህ ምንም ዋስትና አይኖረኝም ። ”

“ ዋስትና ? ” ሚስ ሀበርድ አተኩራ ትመለከታት ጀመር ።

“ ይህ እኮ የግል ቁምጣጥኔ ነው ፣ ” አለች ሚስ ኂሊተስ ። “ ማንም ከግል ቁምጣጥኔ ያለውን ነገር ሚያውቅ የለም ። እንዲያውም አልፈልግም ። አሁን ግን አውቀዋል ። በጣም ጭንቀት ተሰምቶኛል። አዎን የሆነ ነገር ሊያስቡ ይችላሉ... ብቻ የተለየ ምን ያስባሉ?”

“ እነ‘ሱ ስትይ ምን ማለትሽ ነው ? ”

ሚስ ኂሊተስ ያን ሠፊ ውብ ትከሻዋንች አንዘፈዘፈችውና እን ደገና በጸጥታ ተዋጠች ።

“ አይገባሽም ? ” አለቻት ። “ ይህ ሥራቸው ረፍትም አይሰ ጠኝ ። በጣም ነው ሚያስጨንቀኝ ። ”

“ ገልጸሽ ብትነግሪኝ ይሻልሻል ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ ምናልባት ልረዳሽ እሞክር ይሆናል ” አለች ደገመችና ።

“ ምስጋና ይግባው ከዚህ ባለመትኖቴ ። እነዚህ የበር ቁል ፎች በሙሉ ተመሳሳይ ናቸው ። እንዱ ቁልፍ ሌሎቹን በሙሉ መክ ፈት ይችላል ። እምላክ ይመስገነው ! እዚህ አልተኛም ። ”

ሚስ ሀበርድ ፣ “ ሚስ ኒኮሊተስ አንድ የምትፈሪው ነገር ካለ ብትነግሪኝ የተሻለ አይመስልሽም ? ” አለቻት ።

ሚስ ኒኮሊተስ ዓይኖቿን ወርወራ እንደገና መለሰቻቸው ።

“ እንቺው ራስሽ ተናግረሽዋል ፣ ” አለች ከአደጋው ለመሸሽ እንዳሰበች ሁሉ ። “ከዚህ ቤት የነፍስ ጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል ብለሽ ነበር ። ስለዚህ እንደተለመደው ሁሉ አንድ ሰው ሊጨነቅ ይገ ባዋል ። የሚቀጥለው ማን ይሆን ? ገዳዩ እንኳ ማን እንደሆነ ሚያ ውቅ ሰው የለም ። ምክንያቱም ፖሊሶቹ ደደቦች በመሆናቸው ነው ! ጉቦ ስለተቀበሉም ሊሆንይችላል ። ”

“ ይህ ሁሉ ዋጋ ቢስ ነገር ነው ታውቂያለሽ ? ” አለች ሚስ ሀበ ርድ ። “ ቀጥላም እስኪ ባክሽ ንገሪኝ ለእውነተኛ ጥርጣሬና ፍር ሃት ሚያበቃ ምክንያት አለሽ ? . . . ” ስትል ጠየቀቻት ።

ሚስ ኒኮሊተስ እንደገና መንጨርጨር ጀመረች ።

“ አሀ ! ለጥርጣሬዋና ለፍራቻዋ ምንም ምክንያት አይኖራትም ብለሽ ታስቢያለሽ ? ያው እንደተሉመይው በደንብ ታውቂዋለሽ ! አንቺ ማንም የማይስተካከልሽ አስገራሚ ፍጡር ነሽ ። ትደግሻለሽ ፣ ታዘጋ ጀለሽ ፣ በምግብ ላይ ገንዘቤን እንደውሃ ትደፊያለሽ ፣ ተማሪዎቹ እንዲ ወዱሽ የማታደርጊው የለ ! አሁን ደግሞ የግል ጉዳዬንም እንደፈለግሽ ማካሔድ ትፈልጊ ያለሽ ! የራሴን ጉዳይ ራሴ ነኝ የምጠብቀው ። ማንም እንዲያውቅልኝ አልፈልግም ። ትሰሚኛለሽ ? የለም ፣ አልፈል ግም ። ምንድነው ይኼ እሱ — የሚባለው ? ጥልቅ ብዬ ! ”

“ ተይ ‘ባክሽ ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ ቢመሰላቸት ።

“ ሰላይ ነሽ — ሁልጊዜም እንደዚያ ነው ሚሰማኝ ። ”

“ ምን ስሰልል አየሽኝ ? ”

“ ምንም ፣ ” አለች ኒኮሊሊተስ ። “ ከ‘ዚህ ምንም የሚሰለል ነገር የለም ። ምናልባት አለ ብለሽ ያሰብሽው ካለ ! ስለ‘ኔ አንዳች ውሸት ነገር ብሰማ ማን እንደዋሻቸው አውቃለሁ ልብአድርጊ ! ”

“ ሥራውን እንድለቅ ከፈለግሽ በግልጽ እንደዚያ ማለቱ የተ ሻለ ነው ! ” አለች ሚስ ሀበርድ በቁጣ ።

- HALL LIBRARY of

“ የለም መልቀቅ የለብሽም ፣ አግድሻለሁ ። በዚህ ጊዜ አይደለም ። በፖሊስ እጅ እያለሁ ፣ ይህን የነፋስ - ጥፋት ወንጀል ከእጃቹ ታቅፌ እያለሁ ፣ አይደለም ። እንደዚህ ሆኜ ጥለሽኝ እንድትሔጂ አልፈቅድልሽም ። ”

“ መልካም ፣ ጥሩ ነው ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ ከመጠን በላይ ተስፋ በመቁረጥ ። “ ነገር ግን በ‘ውነት ነው የምልሽ ምን እንደም ትፈልጊ ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ። አንዳንዴ ራስሽንም የም ታውቂ መስሎ አይታየኝም ። ከአልጋዩ አረፍ በይና እስኪ ጥቂት አሸልቢ — ”

— 13 —

ሔርኩሌ ፖይሮት ከቁጥር ሀያ ስድስት ሒኮሪ ጎዳና ላይ ከታክሲ ወረደ ።

ለብዙ ጊዜ እንደሚተዋወቅ ወዳጅ ሁሉ በትህትና በተቀበለው ጆሮኒሞ በሩ ተከፈተለት ። ከእዳራሹ የፖሊስ ሀላፊው ቆሞ ስለነበር ጆሮኒሞ ፖይሮትን ወደ ምግብ ቤቱ አስገብቶ በሩን ዘጋው ።

“ በጣም እደገኛ ነው ፣ ” አለ በሹክሹክታ የፖይሮትን ካፖርት ለማውለቅ እየረዳው ሳለ ። “ከዚህ ፖሊስ ተለይቶንም አያውቅ ! በቃ ጥያቄው፣እዚያ ውጡ፣ከዚህ ውረዱ፣ቁም ሣጥን ፍተሻው፣ መደርደሪያ አሰሣው ፣ የማርያ ወጥ — ቤት እንኳ ሳይቀር ምኑ ቀረ ! ማርያ በጣም ተናድዳ ነበር ። ፖሊሱን በልውስ መዳመጫ እናቱን እለዋለሁ ብላኝ እኔ ነኝ የከለከልኳት ። የለም ፖሊሶች በልውስ መዳመጫ መመታት የለባቸውም ፣ማርያ ይህንን ብታደርጊ የበለጠ ጥርጣሬ ላይ እንወድቃለን ብዬ አልኳት . . . ”

“ የተሻለ አስተሳሰብ ነው ያለህ ፣ ” አለ ፖይሮት በማበረታታት ። “ ለመሆኑ ሚስ ሀበርድ ረፍት ላይ ናት ? ”

“ ከእሳቸው ዘንድ ወደ ላይ ልውሰዶት ? ”

“ ትንሽ ታገስ ” አለ ፖይሮት ። ቀጥሎም “ ያን የኤሌክትሪክ አምፖሎች የጠፉበትን ቀን ታስታውሳለህ ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ እንዴታ ፣ አስታውሳለሁ ! ግን ብዙ ጊዜው ነው ። አንድ - ሁለት — ሶስት ወራት ያህል ይሆነዋል ። ”

“ በትክክል ቀኑን አታስታውስም ? ”

ጆሮኒሞ ማንሰላሰል ጀመረ ።

“ አላስታውስም ፣ ” አለ ። ቀጠል አድርጎም “ ፖሊስ በመጣበት ቀን ይመስለኛል። በየካቲት ውስጥ — ” አለ ።

“ ፖሊስ ? ደግሞ ፖሊስ ከዚህ ምን ሊሠራ ይመጣል ? ”

“ ሚስ ኒኮሊተስን ስለአንድ ከአፍሪካ የመጣ ነውረኛ ተማሪ ሊመጠየቅ ነበር ። ምንም ሥራ አይሠራም ነበር ። ወደ ሥራና ሠራ ተኛ በመሐድ ብሔራዊ ርዳታ ተሰጠው ። እንዲት ሴት አፈቀረ ። እሷም ለእሱ ስትል ከወንዶች ጋር ትሔዳለች ። በጣም አስጸያፊ ተማባር ነው ። ይህን ድርጊቱን ደግሞ ፖሊስ አልወደደውም ። ይህ ሁሉ እንደሚመስለኝ ሲደረግ የነበረው ከማንችስተር ወይንም ከፊ ልድ ነው ። ከዚያ ጠፍቶ ነበር ወደዚህ የመጣው ። ፖሊሶችም ተከ ታትለውት በመምጣት ሚስ ሀበርድን አነጋገሯት ። እሷም ‘ከዚህ ላቆየው አልፈለኩም ። ምክንያቱም አልወደድኩትም ። ስለዚህ አስወጣዋለሁ’ ብላ ነገረቻቸው ። ”

“ ገባኝ ፣ እየተከታተሉት ነበር ማለት ነው ። ”

“ ስኩዚይ ? ” አለ በጣሊያንኛ እንዳልገባው ለመግለጽ ።

“ ሊይዙት ጥረት ሲያደርጉ ነበሩ ? ”

“ አዎን ፣ አዎን ትክክል ነው ። አግኝተውት ከእሥር ቤት አስ ገቡት ። ምክንያቱም በወሲብ ገቢ ነበር ‘ሚኖረው በወሲብ ገቢ መኖር ደግሞ ትክክል አይደለም ። ይህ የተከበረ ቤት ነው ። እን ደዚያ ያለ ነገር ከ‘ዚህ መፈፀም አይቻልም ። ”

“ አፓ ፑሎቹ የጠፉበት ቀን ነበር ? ”

“ አዎን ። ለማብራት ስጫነው ድርግም ብሎ ቀረ ። ከጋራ አዳራሹ ሔድኩኝ ከ‘ዚያም እምፑል የለም ። ከመሳቢያዎቹ ተመለከት ኩኝ ። ትርፍ አምፑሎች መኖራቸውን አውቃለሁ ። እነዚያም አም ፑ ሎች ተወስደዋል ። ወደ ወጥ ቤት በመሔድ ማርያን ትርፍ አም ፑሎች የት ማግኘት እንደምችል ጠየቅኋት ። ነገር ግን ተቆጣችኝ ። ፖሊሶች መምጣታቸውን አልወደደችም ። የትርፍ አፓ ፑል ጉዳይ እሷን የሚያገባት አለመሆኑን ገለጸችልኝ ። ስለዚህ ሻማዎች አምጥቼ አበ ራሁ ። ”

ፖይሮት ጀሮኒሞን ተከትሎ ወደ ላይ ሚስ ሀበርድን ለማግኘት በመውጣት ላይ እያለ ይህን ታሪክ ከሀሳቡ አብላላው ።

ፖይሮት በሚስ ሀበርድ የጋለ አቀባበል ተደረገለት ። የደከማትና የታክታት ትመስላለች ። እንዲት ትንሽ ማስታወሻ አውጥታ ሰጠች ው።

“ የሚቻለኝን አድርጌያለሁ መሴ ፖይሮት ። እነዚህን ዕቃዎች በቅደም ተከተላቸው ለመጻፍ ሞክሬያለሁ ። ነገር ግን ፍጹም ትክክል ነኝ ብዬ አልነግርህም ። አየህ ብዙ ወራት እንደገና ወደ ኋላ ተመልሰህ ይህ መቼነበር? ያ መቼ ሆነ ማለቱ በጣም የሚከብድ ጉዳይነው ። ”

“ በጣም ባለውለተኛዬ ነሽ እመቤት ። ሚስ ኒኮሊተስ እንዴት ናት ? ”

“ማረጋጊያ መድሐኒት መሳይ ሰጥቻታለሁ ። አሁን እንቅልፍ እንደወሰዳት ተስፋ አደርጋለሁ ። በፍተሻው ትዕዛዝ ላይ በጣም ነበር የተበሳጭችው ። ከግል ክፍሏ ውስጥ ያለው ቁም ሣጥኗ እንዳይከፈት አጥብቃ ስትቃወም ነበረች ። ኢንስፔክተሩ ግን ሰብሮ ከፈተው ። ከውስጡ ብዙ የብራንዲ ጠርሙሶች እየተንዷዱ ወደቁ ። ”

“ እንዴ ! ” አለ ፖይሮት በመገረም ድምጽ ።

“ ብዙ ነገሮችን የሚያስረዳን መሰለኝ ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ ከሲንጋፖር ሳለሁ እንዳየሁት ሁሉ ፣ ይህን ያህል መጠጥ ለምን እንደነበረ እንኳ አለማሰቤን አላውቅም ። ይህ በርግጥ እንተን የሚጠቅምህ ጉዳይ እንኳ አይደለም ። ”

“ እኔን ሁሉም ነገር ይጠቅመኛል ፣ ” አለ ፖይሮት ።

እንደተቀመጠ ሚስ ሀበርድ የሰጠችውን ትንሽ ወረቀት ማጥናት ቀጠለ ።

“ አህ ! ” አለ ከአንድ ሁለት ደቂቃ በኋላ ። “ አዎን አሁን አስታወስኩት ። በትክክል ጌጣጌጦቹና የመሳሰሉት ከመጥፋታቸው በፊት ነበር የተፈጸመው ። ከአንድ ጥቁር ቲማሪ ገጥሞን ከነበረ ችግር የተያያዘ ሳይሆን አልቀረም ። ይህ ከመፈፀሙ ከአንድ ከሁለት ቀን በፊት ነበር የሐደው ። ከመሐዱ በፊት የቂም በቀል ሥራ ነው ብዬ ማሰቤን አስታውሳለሁ ። በርግጥ ትንሽ ችግር ተፈጥሮ ነበር ። ”

“ አህ ! ጀሮኒሞም እንደዚያ ዓይነት ነገር ጠቃቅሶልኝ ነበር ። ከዚህ ሥፍራ ፖሊስ ተጠርቶ ነበር ? ትክክል ነው ? ”

“ አዎን ። ከሼፍልድ ወይንም ቢርሚንግሀም ወይንም ከሆነ ሥፍራ መጠይቅ የነበረባቸው ይመስለኛል ። ከእውነቱ ይልቅ አሉ ባልታ ነበር ። አለ አይደል? አሥነዋሪ ገቢና የመሳሰሉት ነገሮች ከስ ከፍርድ ቤት የቀረበበት ይመስለኛል ። ብቻ ከዚህ ሥፍራ የቆየው ለሦስትና አራት ወራት ያህል ነበር ። ጸባዩን አልወደድኩትም ። እንዲያው አኳኋኑን ሳየው ማለቴ ነው ። ስለዚህ ክፍሉ እንደተያዘ ገለጽኩለት ። ሞሐይ እንደሚገባውም ነገርኩት ። ፖሊስ ሲመጣ ምንም አልተገረምኩም ። በርግጥ ፣ ወዴት እንደሔደ ልነግራቸው አልቀቻለኝም ። ያም ሆነ ይህ ራሳቸው አገኙት ። ”

“ የጀርባ — ሻንጣውን ያገኘሽው ከዚያ በኋላ ነበራ ? ”

“ አዎን ፣ ይመስለኛል ለማስታወስ ይከብደኛል ። እየሀ ሊን ባትሰን ለጉብኝት ለመውጣት ሲዘጋጅ ነበር ። የጀርባ — ሻንጣውን ቢወጣ ቢወርድ ሊያገኘው አልተቻለውም ። በጣም ሀይለኛ ጭቅጭቅ ተፈጠረ ። ብዙ ፍተሻ አካሔደ ። በመጨረሻ ላይ ከውሃ ማፍያው ኃላ ተሰነጣጥቆ ተደብቆ ጀሮኒሞ አገኘው ። እንግዳ የሆነ ነገር ነው ። ግራ የሚገባና ሞ ሠረተ ቢስ ነገር ነው መሴ ፖይሮት ። ”

“ ትክክል ፣ ” ሲል ፖይሮት ተስማማ ። “ ግራ ሚያጋባና መሠ ረተቢስ ነው ” አለና ለጥቂት ጊዜ በሀሳብ ተውጠ ቆየ ።

“ አዎን ፖሊሶች - ይህን አፍሪካዊ ተማሪ ሪመፈለግ በመጡ በት ቀን ይመስለኛል — ጥቂት የኤሌክትሪክ አምፑሎች መጥፋታቸ ውን ጀሮኒሞ የነገረኝ ። አዎን መሰለኝ . . . በ‘ዚያ ቀን ይሆን ?”

“ አዎን በትክክል እንኳ እንደዚያ ብዬ ማስታወስ አይቻለኝም ። አዎን ፣ አዎን ትክክል ትመስለኛለህ ። ከፖሊስ ኢንስፔክተሩ በአ ንድነት ከላይ ወርጄ ከጋራ - አዳራሹ አብረን ስንገባ ከሥፍራው ሻማዎች ሲበሩ መመልከቴን አስታውሳለሁ . . . ”

“ ከጋራ — አዳራሹ ማን ነበር ? ”

“እንዴ!አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ነበሩ። በዚያን ወቅት ሁሉም መጥ ተዋል ። ጊዜው ምሽት ነበር። ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ይጠጋል ። ጀሮ ኒሞን ስለአምፑሎቹ ጠየቅሁት። መወሰዳቸውን ነገረኝ። ለምን እንዳል ቲካቸው ጠየቅሁት ። ምንም አምፑሎች እንደሌሉን አስረዳኝ ። መሠረተቢስ የማይረባ ቀልድ ስለመሰለኝ የባሰ ተናደድኩኝ ። እንደ ሥርቆት ሳይሆን እንደቀልድ ተመለከትኩት ። የተገረፃ ኩት ከዕቃ ግምጃ በታች ን ብዙ አምፑሎችን ሊመጠባበቂያ ስለምናስቀምጥ ነበር ። በጊዜው እስከዚህም አላተኮርኩበትም መሴ ፖይሮት ። ”

“አፖፑሉቹና የጀርባ ሻንጣው...” አለ ፖይሮት በሀሳብ ተውጦ።

“ አሁንም ቢሆን ለ‘ኔ የሚታየኝ እንደዚያ ነው ፣ ” አለች ሚስ ሀበርድ ። ቀጥላም ፣ “ ማሰቴ እነዚህ ሁለት ነገሮች ከትንሿ ምስኪኗ ሴሊያ የማይረቡ ጥፋቶች የተያያዙ አይመስሉኝም ። ይህንን የጀርባ ሻንጣ አለመንካቷን በፍጹም ልብ መግለጿን ታስታውሳለህ” አለችው።

“ አዎን ፣ እውነት ነው ። ይህ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ቆይተው ነው ሥርቆቱን የጀመሩት ? ”

“ ውድ መሴ ፖይሮት ይህንን ሁሉ ማስታወሱ ምን ያህል ከባድ መሆኑን ማሰብ አትችልም ? እስኪ ልሞክር — በሚያዝያ ፣ የለም

በየካቲት — በየካቲት መጨረሻ ላይ ነበር ። አዎን ፣ አዎን ! ጂኤቭየ የ'ጅ አምባሯን ከዘያ አንድ ሣምንት አስቀደማ የጣለችው ይመስ ለኛል ። አዎን ... ሀያና ሀያ አ ስት መካከል ። መሆን አለበት ''

'' ከ'ዚያ በኃላ ሥርቆቶቹ ያለማቋረጥ ቀጠሉ ? ''

'' አዎን ። ''

'' ይህ የጀርባ ሻንጣ የሊን ባትሰን ነበር ? ''

'' አዎን ። ''

'' በዚህ የተነሳ ተበሳጭቶ ነበር ? ''

'' አዎን ግን ያንን መከተል የለብህም መሴ ፖይሮት ፣ '' አለች ሚስ ሀበርድ ትንሽ ፊገግ ብላ ። '' ሊን ባትሰን ታውቃለህ የተለየ ዓይነት ልጅ ነው ። ተግባቢ ፣ ቸር ፣ ችኩል ግን ከመሬት ተነስቶ የሚጨስ ተናዳጅ ጸባይ ያለው ሰው ነው ። ''

''ይህ የጀርባ ሻንጣእንዴት ያለ ነው፣ አሠራሩ ለየት ያለ ነገር ነውን''

'' የለም ተራ ነገር ነው ። ''

'' አንድ ከ'ርሱ የሚመሳሰል ሻንጣ ልታሳይኝ ትችያለሽ ? ''

''አዎን በሚገባ። ኮሊን የተመሳሰለ ሻንጣ ያለው ይመስለኛል። በጣም ተመሳሳይ ነው ። ኔጊልም — ሌንም ሌላ አንድ ገዝቷል ። አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ ሚገዟቸው ከጐዳናው መጨረሻ ላይ ነው ። ለተለያዩ የሠፈር ምሥረታ ወይንም የጉዞ መሣሪያዎችና ለባላገር ጎብኚዎች የሚ ሆኑ መሣሪያዎች የሚገኙበት ጥሩ መደብር ነው ። ቁምጣዎች ፣ የመ ኝታ ከረጢቶች ፣ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል ። በጣም ርካሽ ናቸው ። ከማንኛውም ትላልቅ ጐ ደብሮች በሚቀንስ ዋጋ ነው ሚሸጥባቸው ።''

'' አንዱን የጀርባ ሻንጣ ለመመልከት እችላለሁ እመቤት ? ''

ሚስ ሀበርድ ወደ ኮሊን ማከናብ ክፍል ይዛው ሔደች ። ኮሊን አልነበረም ። ሚስ ሀበርድ ግን ቁም ሣጥኑን ከፍታ የሚፈልገውን ሻንጣ ሰጠችው ።

'' ይኸውልህ መሴ ፖይሮት ። ይህ ከጠፋውና ተቆራርጦ ካገ ኘነው በጣም ተመሳሳይ ነው ። ''

'' ለመቁረጥ ከተፈለገ በጣም መገዝገዝ አለበት ፣'' አለ ፖይሮት በማጉሊያ የጀርባ ሻንጣውን በአግርሞት እየተመለከተ ። '' አንድ ሰው በተራ የጥልፍ መቀሶች በፍጹም ሊቆራርጠው አይችልም'' አላት።

“ የለም አንተ እንዳሰብከው አይደለም — ብቻ የሆነ ሀይል መጠቀም ይታይበታል ። ሀይልና ... ይገባሃል ? — ቅንዓት ! ”

“ ይገባኛል ፣ አምን ይገባኛል ። ጥሩ ስሚት አይደለም ። ሀሳቡ እንኳ ተገቢ አይመስለኝም ። ”

“ በጋላ ግን ያ የቫሌሪ የአንገት ሻርፕ በተገኘ ጊዜ ተቆራርጦ ሳየው የእብድ ሥራ ነው የመሰለኝ ። ”

“ አዎ ፡ ” አለ ፖይሮት ። ግን እዚያ ላይ የተሳሳትሽ ይመስለኛል እመቢት ። በዚህ ጉዳይ ውስጥ የእብደት ጉዳይ ሊኖር የሚችል አይመስለኝም ። ይህ ዓላማና ምክንያቱ ነው ። ሥልቱም ነው እንበል ? ”

“ አምን ስለነዚህ ጉዳዮች አንተ በበለጠ ታውቃለህ መሴ ፖይሮት ። ከ‘ኔ የበለጠ ” አለች ሚስ ሀበርድ ። “ እኔ ማለት ምችለው ብቻ ነገሩን አልወደድኩትም ነው ። እኔ እስከማውቀው ከዚህ ሥፍራ ብዙ ጥሩ ተማሪዎች እንዳሉ ሲሆን፣ ነገር ግን ጥፋተኞቹ ከ‘ነሱ ውስጥ ከሆኑ የማልፈልገውን ሆነው ስለማገኝ ሀዘኔ እጅግ ይከብድ ይሆናል ። ”

ፖይሮት ወደ መስኩቱ ቀረበ ። ከፊተውና ከዚያ ከጥንታዊ የፎቅ በረንዳ ላይ ወጣ ።

የክፍሉ ፊት ለፊት ከቢቱ ኋላ ነበር። ከበስተታች አንዲት ትንሽ ጠቆር ያለች የአትክልት ሥፍራ ትታያለች ።

“ ከፊት — ለፊቱ ይልቅ ከ‘ዚህ ሥፍራ የበለጠ ጸጥ - ረጭ ያለ ነው ፣ አይደለም ? ” አለ ።

“ አምን ። ነገር ግን ሒኮሪ ጎዳና በእውነት ድምጽ የሚበዛበት አይደለም ። በዚህ በኩል ሆነህ ድመቶቹን በመላ ማታ ታገኛቸ ዋለህ ። አለ አይደል እየጮሁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቆርቆሮዎቹን ከዳኖች ሲያንኳኩ ። ትሰማለህ ”

ፖይሮት አፉት የተጨፈለቁ የአመድ ማጠራቀሚያዎችንና የሆኑ የጓሮ ግሣንግሶችን ተመለከተ ።

“ የውሃ ማፍያው ቢት የት ነው ? ”

“ ያውና በሩ ፣ ከታች ከከሰል ቢቱ ቀጥሎ ። ”

“ ገባኝ ። ”

በሀሳብ እንደ ተዋጠ ወደታች ተመለከተ ።

“ ሌላስ በዚህ ትይዩ መኝታ ክፍል ያለው ሰው አለ ? ”

“ኒጌል ቻፕማንና ሌን ባትሰን ከዚህ በሚቀጥለው ክፍል ናቸው ።

“ ከነ‘ሱስ ወዲያ ? ”

“ ከዚያ የሚቀጥለው ቤት የልጃገረዶቹ ክፍል ነው ። በመጀ መሪያ ሴሊያ፣ከ‘ዚያ በኋላ ኤልሳቤጥ ጆሀንስተንና ፓትሪሺያ ሌን ። ቫሌሪና ጄን ቶሚልሰን ከፊት ለፊቱ ናቸው ። ”

ፖይሮት ራሱን እየነቀነቀ ወደ ክፍሉ ተመለሰ ።

“ ይህ ወጣት በጣም ንጹህ ነው ፣ ” ሲል አጉተመተመ ፣ ዙሪ ያውን በአድናቆት እየቃኘ ።

“ አዎን ። የኮሊን ክፍል ሁልጊዜም ቢሆን በጣም ንጹህ ነው ። አንዳንዶቹ ልጆች በጣም በሚያስከፋ ሁኔታ ነው የሚኖሩት ፣ ” አለች ሀበርድ።“ የሊን ባትሰንን ክፍል ማየት አለብህ ፣ ” አለች‘ው በርካታ ቀጥላም “ ጥሩ ልጅ ’ኮ ነው መሴ ፖይሮት ” አለች‘ው ።

“ እነዚህ የጀርባ ሻንጣዎች ከጎዳናው መጨረሻ ካለው መደ ብር ነው ይሸጣሉ ያልሽኝ ? ”

“ አዎን ። ”

“ የመደብሩ ስም ማን ይባላል ? ”

“ መሴ ፖይሮት እኔ እንጃ አላስታውስም ። ማብሎሪይ መሰ ለኝ ። ወይንም ኬልሶ ። የለም ፣ ስሞቹ እንደማይመሳሰሉ ይገባኛል ። ነገር ግን ከአዕምሮዬ ያለው እንደዚያ ዓይነት ነገር ነው ። በ‘ውነት ፣ በርግጥ ጥቂት ሰዎች አንድ ጊዜ ኬልሶ ሌሎች ደግሞ ማብሎሪይ ብለው ሲጠሩ ስለሰማሁ ነው ። በጣም የሚመሣሰሉ ስሞች ነበሩ። ”

“ አሀ ! ” አለ ፖይሮት ። “ እንደዚያ ያሉት - ምክንያቶች ናቸው ዘወትር የሚያስደንቁኝ ነገሮች ። ”

እንደገና ለአንድ ጊዜ በመስኮቱ አሾልቆ ተመለከተ ። የእት ክልቱን ሥፍራ ቃኘ ። ሚስ ሀበርድን ተሰናብቶ ከቤቱ ወጣ ።

ከማዕዘኑ እስኪደርስ ድረስ የሔኮሪን ጎዳና ተከትሎ በመ ሔድ ወደ ዋናው መንገድ ታጠፈ ። ሚስ ሀበርድ የሰጠችውን ገለጻ በመከተል መደብሩን ችግር ሳይገጥመው አገኘው ። መደብሩ በብዛት የሽርሽር ዘንቢሎችን ፣ የጀርባ ሻንጣዎችን ፣ መቀ - ፋሽኮዎችን ፣ የስፖርት ዕቃዎችን ፣ ቁምሳጥኖችን ፣ የመስክ ሽሚዞችን ፣ የፀሐይ

ቁሮችን ፣ ድንኳኖችን ፣ የዋና ልብሶችን ፣ የብስክሌት መብራቶችን ፣ ባትሪዎችን ሌሎችም የወጣትና የአካል ማጎልመሻ መጠቀሚያ ትጥቆችን ለናሙና አስቀምጧል ። ከመደብሩ በላይ የተለጠፈው ስም ማብሎሪይ ወይንም ኬልሶ ሳይሆን ሔክስ ነበር ። ከውጭ የተደረደሩትን እነዚህን ናሙናዎች በደንብ ካጠና በኃላ ፖይሮት ወደ ውስጥ በመግባት ለአንድ የሆነ የወንድም ልጅ የጀርባ ሻንጣ ለመግዛት እንደሚፈልግ ገለጸ ።

“ አየህ ‘ ጫካ ለማደር ’ ነው ገባህ ? ” አለ ፖይሮት በፈረንጳይኛና በእንግሊዝኛ ። “በ‘ግሩ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር የሚፈልገውን በሙሉ ከጀርባው ተሸክሞ ይጓዛል ። የቤት መኪናዎች ፣ የጭነት መኪናዎች አልፈው የሚሔዱት ሁሉ ነጻ ጉዞ ይሰጡታል ። ”

አጠር መጠን ያለውና ባለ ግራጫ ጸጉሩ ትህትት ባለመደብር በችኮላ ፣

“ አህ ፣ ገባኝ አገር እንወቅ ነው ፣ ” አለ ። “ ዛሬ ሁሉም እንደዚያ ማድረግ ጀምረዋል ። አውቶቡሶቹንና ባቡሮቹ ብዙ የጎንዘብ ኪሣራ ሣይደርስባቸውም አይቀር ። አገር እንወቅ በአብዛኛው የአውሮፓ ወጣት እየተደረገ ነው። እሺ እንግዲህ ‘ርሶ የፈለጉት የጀርባ ሻንጣ ነው ጌታዬ ? ተራ የጀርባ ሻንጣ ? ”

“ አዎን ። ብዙ ዓይነት ነው ያላችሁ ? ”

“ አዎን ለሴቶች የሚሆኑ በጣም ቀለል ያሉ አንድ ሁለት አሉን ። ይህ ግን እኛ የምንሸጠው አጠቃላይ ዕቃ ነው። በጣም ጠንካራ ሲሆን ብዙ የሚቆይ አደጋ ጆይና ርካሽ ነው ። ”

አንድ ጠንካራ የሸራ ሻንጣ አመጣ ። ፖይሮት ከኮሊን ክፍል ያየው ዓይነት ተመሣሣይ ነው ። ፖይሮት በደንብ ተመለከተው ። ጥቂት አስፈላጊ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ጠያየቀ ። ከዚያ በኃላ ሒሳቡን በመክፈል ፈጸመ ።

“ አዎን እነዚህን ዓይነት በብዛት ነው የምንሸጥ ፣ ” አለ ሰውዬው ዕቃውን ሲጠቀልል ።

“ከ‘ዚህ አካባቢ ብዙ ተማሪዎች ይኖራሉ ፣ አይደለም ? ”

“ አዎን ። ይህ ለብዙ ተማሪዎች አጎራባች ነው ። ”

“ከሒኮሪ ጎዳና አንድ ሆስቴል ያለ ይመስለኛል ። አይደለም ? ”

“ እንዴታ ! አዎን ። ከዚያ ላሉት ወጣት ወንዶች ብዙ ሽጪላ ችዋለሁ ። ለወጣት ሴቶቹም ጭምር ። ከመሔዳቸው በፊት ከዚህ

በመምጣት የፈለጉትን ሁሉ ያገኛሉ ። ዋጋዎቼ ከትላልቅ መደብሮች ይልቅ ይቀንሳሉ ። እኔም ይህንኑ እነግራቸዋለሁ ። ይኸውሎት ጌታ ዬ ፣ የወንድሞ ልጅ በአገልግሎቱ እንደሚደሰት ምንም ጥርጥር የለኝም ። ''

ፖይሮት አመስግኖት የዕቃውን ጥቅል ይዞ ወጣ ።

አንድ ሁለት ርምጃዎችን እንደተጓዘ ከኃላው ከትከሻው ላይ አንድ እጅ ሲያርፍ ተሰማው ።

ኢንስፔክተር ሻርፕ ነበር ።

'' ለማግኘት የፈለግኩትን ሰው ሳገኝ ፣ '' አለ ሻርፕ ።

'' የቤት ፍተሻህን የተወጣህ መሰለኝ አይደለም ? ''

'' ፍተሻውን ፈትሻለሁ ። ነገር ግን የሚገባኝን የተወጣሁ አይመስለኝም ። ከዚህ አካባቢ ጥሩ ሳንድዊችና ማለፊያ ስኒ ቡና የሚገኝበት ሥፍራ አለ ። ሥራ ከሌለብህ አብረኸኝ ብትመጣስ ? ላጫውትህ እፈልጋለሁ ። ''

የሳንድዊቹ ቡና ቤት ምንም ሰው አልነበረበትም ። ሁለቱ ሰዎች ጣሀኖቻቸውንና ስኒዎቻቸውን ይዘው ወደ አንዲት ከጥግ ከምትገኝ ጠረጴዛ ሔዱ ።

ከዚያ ሆኖ ሻርፕ ከተማሪዎቹ ያገኛቸውን መልሶች በሙሉ አጫወተው ።

'' ማስረጃ ያገኘንባት ሰው ወጣቱ ቻፕማን ብቻ ነው ! ብዙ ነገር ነው የተገለጸልን ። ሦስት የተለያዩ መርዞች ከ'ጁ ነበሩ ! ነገር ግን በሴሊያ አውስቲን ላይ ጥላቻ ኖለው ብሎ መገመት አይቻልም ። ወን ጀለኛ ቢሆን የሠራውን ሥራ በሙሉ ዘርዝሮ ሳይደብቅ ይናገራል ለማለት እጠራጠራለሁ ። ''

'' ሌሎች ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችንም ቢጠቀምም . . . ''

'' አዎን — ያን ሁሉ ከመሳቢያ ውስጥ መደበቁ ትክክል አይደለም ! ደደብ ፣ ወርንጭላ አህያ!'' አለ ። ኤልሳቤጥ ጀሀንስተን ስለሴሊያ የተናገረችውን በሙሉ አጫወተው ።

'' የተናገረችው እውነት ከሆነ ዋጋ ያለው ጉዳይ ነው ። ''

'' በጣም እንጂ ፣ '' ሲል ፖይሮት ተስማማ ።

ኢንስፔክተሩ የተናገረችውን ደገመለት ።

'' ነገ ስለዚህ ጉዳይ በበለጠ እረዳለሁ '' አለ ።

“እና — ያ ነገ ሚባል ነገር ለዚያች ምስኪን ልጅ በድጋሚ ሳያመጣላት ቀረ ። የቤት ፍተሻህ — ያስገኘው ውጤት ኦለ ? ”

“አንድ ሁለት ነገሮች ነበሩ — ምን ማለት እችላለሁ ? — ያልተጠበቀ ነገር ይሆናል ያናልባት ። ”

“ለምሳሌ ? ”

“ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን የኮሚኒስት ፓርቲው አባል ነች ። ፓርቲ ካርዷን አግኝተናል ። ”

“እሺ ፣” አለ ፖሮት በሀሳብ ተውጦ ። ቀጥሎም “የሚያስገርም ነው አለ ። ”

“አልጠበክውም ነበር ፡ አይደለም ? ” ኦለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። “ትላንትና እስከጠየቅኋት ድረስ እላውቅሁም ነበር ። ያቺ ልጅ ተከለ - ሰውነቷ ቀላል አይደለም ። ”

“ለፓርቲው ጠቃሚነት ያላት አባል ትመስለኛለች” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ። “ታይቶ ማይታወቅ አዕምሮ ያላት ወጣት ሴት ናት ። ”

“ለኔ ግን በጣም የተለየ ነገር ነበር ፣ ” አለ ኢኒስፔክተር ሻርፕ። “ምክንያቱ እነዚህን ዝንባሌዎቿን በግልጽ አሳይታ ስለማታውቅ ነው ። ድምጿን አጥፍታ ከሒኮሪ ጎዳና ቁጭ ብላልሃለች ! ነገር ግን ከሲሊያ አውስቲን ምንም የተያያዘ ነገር ያለው አይመስለኝም ። ማለቴ - ከአዕምሮ ብቻ የሚቆይ ነገር ነው ። ”

“ሌላስ ምን አገኘህ ? ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ ትከሻውን ሳብ ረገብ አደረገው ።

“ወይዘሪት ፖትሪሺያ ከመጣቢያዋ ውስጥ እጅግ በጣም በአረንጓዴ ቀለም የተበከለ መሀረብ ነበራት ። ”

የፖያሮት ቅንድቦች አሻቀቡ ።

“አረንጓዴ ቀለም ? ፖትሪሺያ ሌን ! ከኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ጽሑፎች ላይ ቀለሙን አፍስሳ በኋላ ከእጅዋ ላይ ጠረገችው ማለት ነው ? ግን በ‘ውነት . . . ”

“ውድ ፍቅረኛዋ ኒጌል እንዲጠረጠርባት አልፈለገችም ነበር ፣ ”ሲል ሻርፕ ወረፍተ — ነገሩን ጨረሰው ።

“እንደዚያም ማሰብ አያቻልም ። አንድ የሆነ ሰው መሀረቡን ከመጣቢያው ሊከተው ይችላል ። ”

“ ትክክል ! ”

“ ሌላስ ነገር ? ”

“ መልካም፣” ሲል ሻርፕ ለጥቂት ጊዜ ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ “ የሊዎናርድ ባትሰን አባት ከሎንግዊዝ ቫሌ ሆስፒታል የተመ ሰከረለት የአዕምሮ በሽተኛ ይመስለኛል ። ይህ ግን ምንም ዋጋ ያለው ጉዳይ አይሆንም ። ግን . . . ”

“ እም የሊን ባትሰን አባት እብድ ነው ። ምናልባት እንተ እንዳ ልከው ዋጋ ያለው ጉዳይ አይሆን ይሆናል ። ነገር ግን ከትውስታችን ማጎደር መቆየት ሚገባው ጉዳይ ነው ። ይህ ጭንቀት — ፍራቻ ሀመሙ ምን ዓይነት ልዩ መልክ እንዳለው ማወቁ በጣም የሚያ ጓጓ ነገር ሳይሆን አይቀርም ። ”

“ ባትሰን በጣም ግሩም ወጣት ነው ፣ ” አለ ሻርፕ። “ ነገር ግን ብስጭትና ንዴቱን ሊያበርዱት የማይቻል ነው ። ”

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ። ሳያስበው ድንግዝግዝ ባለሁኔታ ሲሊያ አውስቲንን አስታወሰ ። ‘ በርግጥ ፡ የጀርባ ሻንጣውን እኔ አልቆራ ረጥኩም ። ለማንኛውም እንዲያ ዓይነቱ ነገር የብስጭት መውጫ ነው’ ብላ ነበር ። “ ብስጭት መሆኑን እንዴት ልታውቀው ቻለች ? ሊን ባትሰን የጀርባ ሻንጣውን ሲገዘግዝ አይታው ይሆን ? ” ሻርፕ በፈ ገግታ ወደሚያወራው ጉዳይ ሀሳቡን መለሰ ።

“. . . ሚስተር አህመድ አሊም በጣም የመጠቁ ወሲባዊ መጣ ጥፎቹና ፖስት ካርዶቹ በፍተሻው ወቅት ለምን እንደዚያ እንደሆነ ይገልጻሉ ። ”

“ ብቻ ብዙ ተቃውሞዎችም ተፈጥረው ነበር አይደለም ? ”

“ነበሩ እንጂ ! ፈረንሣዊቷ ልጅ በተለይ ጭንቀት ነበረባት ። እንድ ሕንዳዊ ሚስተር ቻንድራ ላል የሚባል ደግሞ ዓለም አቀፍ ተቃውሞ አሰማለሁ ብሎ አስቸግሮን ነበር ። ከዕቃዎቹ መካከል የዓመጽ በራሪ ወረቀቶች ነበሩበት ። ያ የተለመደ ገሚስ ብስል ነገርም አልቀረ። አንዱ አፍሪካዊ ደግሞ የባህል ዕቃዎችና የአምልኮት መማጸኛዎች ይብቆ ነበር ። አዎን ፡ የፍተሻ ትዕዛዝ የሰውን ልጅ ልዩ ልዩ የባህርይ ገጽ ለማወቅም ይረዳል ። ስለ ሚስ ኒኮሊተስና ስለ ልዩ ቁምፃጥኗ ሰም ተሃል ? ”

“ አዎን ስለዚያ ሰምቻለሁ ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ ፣ቅ አለ ።

“ ያን ያህል ባዶ የብራንዲ ጠርሙሶችን አይቼም አላውቅ ! ነገር ግን በጣም ተናዳብን ነበር ! ”

ሣቀና ወዲያው ተኰሳተረ ።

“ ነገር ግን የፈለግነውን አላገኘንም፣” ነ ለ ። ቀጥሎም “ በትክክል ከተዘጋጁ ሕጋዊ ፓስፖርቶች በስተቀር ሌሎች የሉም አለው ።”

“እንደዚህ መሳይ ማጭበርበሪያ ፓስፖርቶችን ለማግኘት መጠበቅ አልነበረብህም ወዳጄ ! ከፓስፖርት በተያያዘ ጉዳይ ቁጥር 26 ሒኮሪ ጎዳናን በደፋ የመጎብኘት እድል አጋጥሞህ ነበር ? ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ማለቴ ነው ። ”

“ የለም ። በጠቀስከው ጊዜ ውስጥ ያጋጠሙንን አጋጣሚዎች ብቻ ልነግርህ ሞክራለሁ ። ”

በጥንቃቄ አንድ በአንድ ዘረዘረለት ።

ፖይሮት በተመስጠ አደመጠው ።

“ ያ ሁሉ ስሜት ሚሰጥም ጉዳይ አይደል ፣ ” አለ ።

ራሱን ነቀነቀ ።

“ ነገሮች ስሜት ሊሰጡ ሚችሉት ከመጀመራያቸው ስንጀምራቸው ብቻ ነው ። ”

“ ያን መጀመሪያው ምንድነው የምትለው ፖይሮት ? ”

“የጀርባ ሻንጣ ነው ወዳጄ ! ” አለ ፖይሮት በትህትና ። “ የጀርባ ሻንጣ ! ሁሉም ነገር የጀመረው በጀርባ ሻንጣው ነው ! ”

— 14 —

ክፍል አንድ

ሚስ ኒኮሊተስ ሁለቱንም ጀሮኒሞንና ብሰጩዋን ማርያን ስት ጨቀጭቅ ከነበረችበት ከታችኛው ወለል ደረጃዎቹን ወደ ላይ መወ ጣጣት ተያያዘች ።

"ውሸታሞች! ሌቦች!" አለች ሚስ ኒኮሊተስ ጎላ ባለ የድል አድራጊ ነት ድምጽ ። "ጣሊያኖች ሲባሉ ውሸታሞችና ሌቦች ናቸው!" አለች።

ደረጃውን በመውረድ ላይ የነበረችዋ ሚስ ሀበርድ ዓይኖቿ በን ዴት እየተንቀለቀሉ አካባቢውን ቃኘች ።

" ራት በማብሰል ላይ እያሉ እነሱን ማበሳጨት ተገቢ አይደ ለም ! " አለች ።

" ጉዳዬ ነው ? " አለች ሚስ ኒኮሊተስ ። " ለራት እኔ ከዚህ አልቆይም ። "

ከምላሷ ልታወጣው የነበረውን ሚስ ሀበርድ ጨቁና ያዘችው ። ራሷን ተቆጣጠረችው ።

" ጥሩ ነው ሚስ ኒኮሊተስ ። "

" እንደተለመደው ሰኞ እመጣለሁ " አለች ሚስ ኒኮሊተስ ።

"ባክሽን የቁምሣጥኔን በር የሚሠራልኝ ሰው ሰኞ ጠዋት ፈልገሽ እንድታቆይኝ ። የተሠራበት ደረሰኝ ወደ ፖሊስ ይሔዳል ። ይገ ባሻል ? ወደ ፖሊስ . . . "

ሚስ ሀበርድ ምታመነታታ ትመስላለች ።

" በተጨማሪ አዳዲስ የኤሌክትሪክ አምፑሎች ከጨለማ ጋ ላለፊያው ያስፈልጋሉ ። ባለ በዙ ሻማ መሆን አለባቸው ። መተላለፊ ያዎ ቹ በጣም የጨለሙ ናቸው ። "

“ ለቁጠባ ሲባል ከመተላለፊያዎቹ ባለ አነስተኛ ሻማ አፃፑ ሎችን አድርጉ ብለሽ አዘሽን ነበር ። ”

“ ያ ባለፈው ሣምንት ነበር ! ” ስትል አንቧረቀች ። “ አሁን ግን የተለየ ነው ።ይኸው ከትከሻዬ ይታየኛል . . . ማነው የሚከተለኝ ? ይገርመኛል ! ”

ሴትየዋ እየተወች ናት ወይስ የሚያስፈራራት ሰው አለ? ስትል ሚስ ሀበርግድ አሰበች ። ሚስ ኂኮሊተስ ወትሮም ሁሉንም ነገር የማታነን ባህርይ ስላላት በተናገረችው ነገር ላይ እምነት ማኖሩ በጣም ይከብዳል ።

ሚስ ሀበርድ በጥርጣሬ ፣ “ ብቻሽን ወደ ቤት ለመሔድ እን ደምትችይ ርግጠኛ ነሽ ? አብሬሽ ብመጣ ትፈቅጃለሽ ? ” አለቻት ።

“ ከዚህ ይልቅ እዚያ ሰላም ሆናለሁ ። እውነቴን ነው ምልሽ ! ”

“ ግን የፈራሽው ነገር ምንድነው ? ብትነግሪኝ ምናልባት ለመ ርዳት — ”

“ አንቺን ሚያገባሽ ነገር የለም ። ምንም ነገር አልነግርሽም ። ይህ በተከታታይ የምትጠይቂኝ ጥያቄ የጤና አይመስለኝም ። ”

“ አዝናለሁ ፡ — ”

“ተሰማሽ አይደል?” አለችና ሚስ ኂኮሊተስ ከበር መልስ ፈገግታ አሳየቻት ። “ ተበሳጭቼ ባለኩኝ ! አዎን ። ነገር ግን ብዙ ሚያሳስበኝ ነገር አለ ። አስታውሺ በጣም ነው የማምንሽና የምተማመንብሽ ። አንቺ ባትኖሪ የኔዋ ውድ ሀበርድ እስኪ ምን ይውጠኝ ነበር ? ፍጹም ማወቅ አልችልም ። ተመልከች እጄን ስስምልሽ ። መልካም ሣምንት ! ደህና ደሪ ! ”

ሚስ ሀበርድ በፊት ለፊቱ በር በመውጣት በሩን ከላይዋ ስት መልስ ተመለከተቻት ። ስሜቷን በእርካታ በማያርቅ “ መልካም ፀባይ !” ሚስ ሀበርድ እንደገና ወደ ወጥ - ቤቱ ወጣች ።

ሚስ ኂኮሊተስ በፊት ለፊቱ ደረጃዎች አድርጋ በዋናው በር በመ ውጣት ወደ ግራ ታጠፈች ። ሒኮሪ ጎዳና ሰፋ ያለ መንገድ ነው ። ብዙዎቹ ቤቶች ከእትክልት ሥፍራቸው ገባ ብለው ነው የተሠ ሩት ። ከመንገዱ መጨረሻ ትንሽ ደቂቃዎች ከቁጥር 26 በመጓዝ ወደ ለንደን አውቶቡሶች ሚያጓሩበት ትልቅ ጎዳና ይገባል ። ከመን

ገዱ መጨረሻ የትራፊክ መብራቶችንና መጠጥ ቤቶች ከማዕዘኑ ላይ ደግሞ ኩንስ ኤክሌስ ይታያሉ ። ሚስ ኢኮሊተስ ከጎዳናው መካከል ገባች ። እሁንም እሁንም ከትከሻዋ አቅጣጫ ትመለከታለች ። ከአ ጠገቧ ግን ምንም ሰው የለም ። ሒኮሪ ጎዳና ዛሬ ምሽት ጭር ፣ ጸጥ ረጭ ብሏል ። ወደ ኩይንስ ኤክሌስ ስትጠጋ ርምጃዋን አፋጠነች ። በችኩል አመለካከት ቃኘት አድርጋ ከትልቁ ቡና ቤት እንደ ጥፋ ተኛ ሁሉ ሹልክ ብላ ገባች ።

ያዘዘችውን ደብል ብራንዲ እየተጎነጨች ሳለች መንፈሷ ቀስ በቀስ እየተስተካከለ መጣ ። አስቀድማ ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደነ በረችዋ ፍርሃት ጭንቀት የነበረባት ሴት አይደለችም ። በፖሊሶቹ ላይ ያሳደረችው ጥላቻ ግን አልቀነሰም ። ዝቅ ባለ ስትንፋሷ ውስጥ ፣ ''ጌስታፖ ! አስከፍላቸዋለሁ ። አዎን መክፈል አለባቸው ! '' በማለት አጉረምርማ መጠጡን ጨለጠችው ። ሌላ አዘዘችና በቅርብ ስለሆኑት ነገሮች ማንሰላሰል ገባች ። መጥፎው እድል ፣ መጥፍው እጣ - ፈንታ በዚያ ልዩ ድብቅ ንብረቷ ላይ በዋልጌ ፖሊሶች የተፈጸመው የማጋለጥ ተግባር ብቻ ነው ። ከተቀሩትና ከተማሪዎቹ ጆሮ ይህ ወሬ አለመዳረሱ ብዙ ተስፋ የሚያሳድር ይሆናል ። ሚስ ሀበርድ አዎን ምናልባት ሚስጥር ጠባቂ ልትሆንም ላትሆንም ትችላለች ። ዛሬ ለመሆኑ የሚታመን ሰው ይኖራል ? እነዚህ ነገሮች ሁሌም በሰ ፈው ነው የሚነፍሱት ፣ ጆሮኒሞም እውቋል ። ምናልባት ለሚስቱ ነግ ሯት ይሆናል ። እሷም በተራዋ ለጽዳት ሠራተኛዋ ትነግርና ከዚያ በኋላ ዳር እስከ ዳር መዳረሱ የማይቀር ነው ። አንድ ድምፅ ከኋላዋ ሲናገር ከሀሳብ ሰመመኗ አባነናት ።

'' እንዴ ! ሚስ ኒክ ? ይህ የአንቺ ማዘውተሪያ ሥፍራ መሆኑን አላውቅም ነበር ! '' አለ አንድ ድምጽ በቁልምጫ ጠርቷት ።

''ወደ ኃላዋ ከመቅጽበት በመዞር የረፍት ትንፋሽ ተነፈሰች።''

''የማውቀው ሰው ነው እንዴ ?'' አለች። '' እኔ የመሰለኝ ግን. .''

'' ማን መሰልኩሽ ታዲያ ? ትልቁ አደገኛው ተኩላ ? ምንድ ነው ምትጠጪ ? አንድ ልጋብዝሽ ? ''

'' ብስጭት ብቻ ! '' አለች ሚስ ኒኮሊተስ ጀነን ብላ ። '' እነ ዚህ ፖሊሶች ቤቴን በመፈተሽ ላይ ነበሩ። እንዲያው ሁሉንም ሰው ነው የረባበሹት ። ምስኪን ልቤ ። ለልቤ በጣም ጥንቃቄ መውሰድ አለብኝ። ለመጠጥ ግድ የለኝም ። ግን በእውነት ልቤን ይደክመኛል። ትንሽ ብራንዲ አስቢ . . . ''

'' ብራንዲን ሚስተካከል መጠጥ የለም ። ይኸውልሽ ! ''

ሚስ ኒኮሊተስ ኩይንስ ኤክሌስን በአዲስ መንፈስና በደስታ ጥላ ወጣች ። አውቶቡስ ላለመውሰድ ወሰነች ። ግሩም ምሽት ነበረ ። አየሩም ይስማማታል ። ያለ ጥርጥር አየሩ በጣም ይስማማታል ። እግሮቿ ምንም አልከዷትም ። ግን ትንሽ ይወናከራሉ ። አንድ ብራንዲ ባትጨምርበት ምናልባት ብልህነት ይሆን ነበር ። ቢሆንም ነፋሻው አየር ጭንቅላቷን ማረጋጋቱ የማይቀር ነው ። ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ እሷ ያለች እመቤት ከክፍሏ ሆና ዘወትር ብትጠጣ ምን አለበት ? ምን ነውር አለው ? ሰክራ ታይታ አታውቅ ። ሥካር ? በፍጹም ሰክራ አታውቅም ። ለማንኛውም ከጠሉባት ፣ ከነዘነዟት መሐኟ መድረሻቸውን ትነግራቸዋለች ! ጥቂት ነገሮችንም ታውቃለች ፣ አይደለም እንዴ ? ምላሷን ማሾል ከፈለገች ! ሚስ ኒኮሊተስ ግራ ቀኝ ለጸብ እንደ ሚዘጋጅ ሰው በማስመሰል ከአንድ በሚያስፈራ አኳኋን ወደ ርሷ በመ ምጣት ላይ ከሚገኝ የፖስታ ሣጥን ምሰሶ ለመዳን አቅጣጫ ለመቀየር ተንገዳገደች ። ካለጥርጥር ከጭንቅላቷ ትንሽ እየዞረባት መሆንአለበት ። ምናልባት ለጥቂት ጊዜ ከዚህ ከግድ ግዳው ደገፍ ብትል ? ለአንድ ለሁ ለት ደቂቃ ዓይኖቿን ከደን ብታደርግ . . .

ፖሊስ ሀላፊው ቦት በኅዚያ ተክለሰውነቱ ከመንገዱ ላይ ራመድ ራመድ ሲል ፍርሃት የያዘው አንድ መኰንን አቆመው ።

“ ጌታዬ አንዲት ሴት ከዚህ ትታያለች ። በእውነት ነው የምለው በጣም የታመመች ወይንም አንድ ነገር የሆነች ትመስላለች ። ከአንድ የአፈር ቁልል ላይ ተጋድማለች ። ”

ፖሊስ ሀላፊው ቦት ወደዚያው አመራ ። ትንሽ ከተራመደ በኋላ ከአንድ የተንጋለለ ቅርጽ አጠገብ ደረሰ ። ጥርጣሬውን ጠንከር ያለው የብራንዲ ሽታ አረጋገጠለት ።

“ ሩቋን ስታለች ፣ ” አለ ። “ሠክራለች ። ደህና ! አታስብ ጌታዬ። እንዴት እንደምናደርግ እንመክራለን ። ”

ክፍል ሁለት

ሔርኩሌ ፖይሮት የእሁድ ቁርሱን ከበላ በኃላ ጺሙን ከቸኩሌት ስኒ-ቁርስ በጥንቃቄ በማጽዳት ወደ እንግዳ ክፍሉ አለፈ ።

ከጠረጴዛው ላይ በሥርዓት አራት የጀርባ ሻንጣዎች ዋጋቸው እንደተያያዘ ተደርድረዋል ። ለጀርጅ የተሰጠው ትዕዛዝ ውጤት ነው ። ፖይሮት በትላንትናው ቀን የገዛውን የጀርባ ሻንጣ ከጥቅልሉ በማ ውጣት ከሌሎቹ ጎን አስቀመጠው ። ውጤቱ የሚያስገርም ነበር ። ከሚስተር ሒክስ የገዛው ሻንጣ በማንኛውም መንገድ በጀርጅ ከተ ለያዩ ተቋማት ከተሸመቱት የሚተናነስ መስሎ አይታይም ። ነገር ግን በጣም ርካሽ ነበር ።

“ ይገርማል ! ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ።

ሻንጣዎቹን አተኩሮ ተመለከታቸው ።

አንድ በአንድ ፈታተሻቸው ፣ አጤናቸው ። ከውስጥና ከውጭ አገላብጦ ጠርዛቸው ተገናኝቶ የተሰፋበትን ፣ ኪሶቻቸውን ፣ ማንገ ቻዎቻቸውን ተመለከተ ። ተነስቶ ወደመታጠቢያው ክፍል ሔደና ትንሽ ግን በጣም ስል ቢላዎ ይዞ ተመለሰ ። ከሚስተር ሒክስ የገ ዛውን ሻንጣ የውስጡን ወደውጭ ገልብጦ ታቹን በቢላዎው ወጋው ። ከውስጥና ከታች ካለው መካከል አንድ የተጣጠፈ ነገር እንዲያውም ወረቀት የሚመስል ነበረበት ። ፖይሮት የተቆረጠውን ሻንጣ በከፍ ተኛ መገረም ተመለከተው ።

ከዚያ በኃላ ሌሉቹን ሻንጣዎች መወጋጋቱን ቀጠለ ።

በመጨረሻ ላይ ቲቀምጠ ያደረሰውን ጥፋት ምን ያህል መሆ ኑን ተመለከተ ።

ከ‘ዚያ ሳልኩን ወደ እ‘ሱ በማስጠጋት ትንሽ ዘግየት ብሎ ለኢ ንስፔክተር ሻርፕ ደወለለት ።

“ ስማኝ ወዳጄ ፣ ” አለው በፈረንሣይኛ ፣ “ ሁለት ነገሮችን ብቻ ማወቅ ፈልጋለሁ ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ ከት ብሎ ሣቀ ።

“ ስለፊረስ ጸባይ ሁለቱን ብናገር ፣

ከሁለቱ አንዱ የጀርባው መቆርቆር ፣ ” አለ ።

“ አልተሰማኝም ፣ ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት በመገረም ።

“ ምንም አይደል ። ምንም አይደል ። አንድ የማውቀውን ግጥም ነው ። ለማወቅ የፖትፈልጋቸው ሁለቱ ነገሮች ምንድናቸው ? ”

“ ትላንትና ባለፉት ሶስት ወራት ከሒኮሪ ጎዳና የሆነ የፖሊስ ክትትል እንደተደረገ ጠቃቅሰህልኝ ነበር ። ቀናቱንና ሰዓቱን ልት ነግረኝ ትፐላለህ ? ”

“ አዎን ቀላል ነው ። ከማኅደሮቹ እናገኘዋለን ። ትንሽ ጊዜ ስጠኝ እስከ መለከትልህ ። ”

ብዙም ሳይቆይ ኢንስፔክተሩ ወደ ስልኩ ተመለሰ ። “ የመጀ መሪያው ክትትልና ጥያቄ በአንድ የአመጽ ፕሮፓጋንዳ ሲያሰራጭ በነበረ ሕንዳዊ ተማሪ ላይ ታህሣሥ 18 - በ9.30 ከሰዓት በኃላ ላይ የተደገረ ነበር ። ”

“ በጣም ረጂም ጊዜ ነው ። ”

“ እንደገና ሞንታጉ ጀንስ የሚባል አውሮፓዊ - እስያዊ ከካ ምብሪጅ ከሚስ አላይስ ኮምቤ ግድያ በተያያዘ ጉዳይ ተፈልጎ ነበር ። ጊዜውም የካቲት 24 - በ11.30 ከሰዓት በኃላ ላይ ነበር ። እንደገና ዊሊያም ሮቢንስን የተባለ የምዕራብ አፍሪካ ዜጋ በሸፊልድ ፖሊሶች ተፈልጎ ነበር ። ጊዜውም መጋቢት 6 - በ15 ሰዓት ላይ ነበር ። ”

“ በጣም አመሰግናለሁ ። ”

“ ግን ከነዚህ ጉዳዮች አንዳቸውም እንኳ ቢሆኑ ግንኙነት አላ ቸው ብለህ ካሰብክ — ”

ፖይሮት እቋረጠው ።

“ የለም ምንም ግንኙነት የላቸውም ። የኔ ትኩረት በተፈጸሙ በት ቀንና ሰዓት ላይ ብቻ ነው ። ”

“ ምን ላይ ደርሰሃል ፖይሮት ? ”

“ የጀርባ ሻንጣዎችን ቆራርጪ በማየት ላይ ነኝ ወዳጄ ። በጣም የሚያስገርም ነው ። ”

በርጋታ መነጋገሪያውን ከሥፍራው አስቀመጠው ።

ትላንት ከሚስ ሀበርድ በተጨማሪ ያገኘውን የፅሁፎች ዝርዝር ማስታወሻ ከኪሱ አወጣ ።

የጆርባ ሻንጣ (ሊን ባትሰን)
የኤሌክትሪክ መብራት አምፑሎች
የጅ አምባር (የጄኔቭይቭ)
የአልማዝ ቀለበት (የፖትሪሺያ)
የፓውደር መያዣ (የጄኔቭይቭ)
የምሽት ጫማ (የሳሊ)
ሊፕስቲክ (የኤልሳቤጥ ጆሀንስተን)
የጆሮ ጉትቻዎች (የቫሌሪ)
የልብ — ምት መለኪያ (የሊን ባትሰን)
የመታጠቢያ ጨው (?)
የተቆራረጠ ሻርፕ (የቫሌሪ)
ሱሪ (የኮሊን)
የምግብ ማዘጋጃ መጽሐፍ (?)
ቦሪክ አሲድ (የቻንድራ ላል)
የባህል የኮሌታ ጌጥ (የሳሊ)
ከኤልሳቤጥ ጽሑፎች ላይ ቀለም መፍሰስ ።

(በተቻለኝ ማስታወስ የቻልኩት ይህንን ነው ። ፍጹም ትክክለኛ ነኝ ማለት አልቻልኩም ። ኤል ሀበርድ ።)

ፖያሮት ለብዙ ጊዜ ተመለከተው ።

በረጅሙ በመተንፈስ ለራሱ አጉተመተመ ።

“ አዎን . . . ያለማወላወል . . . ዋጋ የሌላቸውን ነገሮች ማስወገድ ተገቢ ነው . . . ”

ይህንን ማን ሊረዳው እንደሚችል ከአዕምሮው አንድ ሀሳብ ነበረው ። ቀኑ እሁድ ነው ። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ምናልባት ከቤት ሳይሆኑ አይቀሩም ።

የቁጥር 26 ጎዳናን የስልክ ቁጥር በመደወል ሚስስ ቫሌሪ ሆብሐውስን እንዲያቀርቡለት ጠየቀ ። አንዳች ወፍራም ድምጽ የት እንዳለች የሚያመነታታ መልስ ሰጠው ። ነገር ግን ሔዶ እንደሚያረጋግጥለት ነገረው ።

ዝቅ ያለ አንዳች ድምጽ በሹክሹክታ መለሰለት ።

“ ቫሌሪ ሆብሐውስ ነኝ ። ”

“ ሔርኩሌ ፖይሮት ነኝ ታስታውሽኛለሽ ። ”

“ በሚገባ ሙሴ ፖይሮት ። ምን ልታዘዝ ? ”

“ የሚቻል ከሆነ ለአሮር ሙያያት ፊልጌሽ ነበር ። ”

“ በሚገባ ! ”

“ ከዚያው ከሒኮሪ ጎዳና ልምጣ ? ”

“ አዎን እጠብቅሃለሁ ። ጀሮኒሞ ወደ መኝታ ቤቴ እንዲያ መጣህ እነግረዋለሁ ። እሁድ እለት ብዙም ለብቻ መገለል ከዚህ አይ ታይም ። ”

“ አመሰግናለሁ ወይዘሪት ሆብሐውስ ። ባለውለተኛዬ ነሽ ።”

ጀሮኒሞ ለፖይሮት በሩን በፈገግታ ከፈተለት ። ወደፊት በማስ ገባት በዚያ በተለመደ የወሬ አቀባይ የአነጋገር ስልቱ ፣

“ በቀስታ ወደ ወይዘሪት ቫሌሪ ይገቡዎት ሔዳለሁ ። እሽ . . . ሽ . . . ሽ . . . ” አለው ።

ጣቶቹን ከከናፍሩ ላይ አስቀምጦ ወደ ላይ ይዞት ወጣ ። ከአንድ ሒኮሪ ጎዳናን ፊት ለፊት ከሚያሳይ ማለፊያ ክፍል አስገባው ። እንደ መኝታ ቤት በሥርዓት የተያዘና መጠነኛ ምቾት ያለው ክፍል ነው ። ወደ መቀመጫነት የሚቀየረው ረጅሙ አጠር ያለው ምቹ አልጋ በአሮጌ ውብ የፐርሺያ ምንጣፍ ተሸፍኗል ፣ ከአንድ ሥፍራ ዓይንን የሚስብ ውብ ከማለፊያ እንጨት የተሠራ የንግሥት አኒ ባለ መሣቢያ የጽሕፈት ጠረጴዛ ተጀንኖ ተቀምጧል ። ፖይሮት የቁጥር 26 ሒኮሪ ጥንታዊ የዕቃ ቅርስ መሆኑን ተገነዘበ ።

ቫሌሪ ሆብሐውስ እንግዳዋን ለመቀበል እንደቆመች ትታያለች። በጣም የደከማት ይመስላል ሲል አሰበ ። ከዓይኗ ዙሪያ ጠቋቁር ቀለበቶች ነበሩ ።

“ በጣም ውብ ሥፍራ ነው ፣ ” አለ ፖይሮት የሰላምታዋን አጸፋ እየመለሰ እያለ ። “ ከብርና ሞገሥን ሚጨምር ሥፍራ ነው ። ልዩ ሁኔታ አለው” አለ እንደገና ።

ቫሌሪ ፈገግ አለች ።

“ከ’ዚህ ለረጂም ጊዜ ኖሬያለሁ ፣ ” አለች ። “ ሁለት ዓመታት ተኩል ። ምስት ሊሞላ ነው ። የተቻለኝ ያህል ለፋሁ ይኸው የ‘ራሴ የምለው ዕቃ አፍርቻለሁ ። ”

‘‘ ተማሪ አይደለሽም ። ተማሪ ነሽ ? ’’

‘‘ አይደለሁም ። የድርጅት የግዥ ወኪል ነኝ ። ሥራ አለኝ ። ’’

‘‘ከውበት ድርጅት ነበር ? ’’

‘‘ አዎን ። ለሳብሪና የግዥ ወኪል እኔ ነኝ ። የውበት ሳሎን ነው ። እኔም ከንግዱ ትንሽ ድርሻ አለኝ ። ከማስዋብ ሥራችን ጎንለጎን ሌላም የንግድ ሥራ እንሠራለን ። የተዛመዱ ነገሮችን ማለቴ ነው ። አን ዳንድ የፊረንጣይ ዘመን አመጣሽ ቁሣቁሦችን . . . ያ ነው የ‘ኔ የሥራ ድርሻ ።

‘‘ አብዛኛውን ጊዜ ወደ ፖሪስና ወደ አህጉሩ ትሔጃለሽ ? ’’

‘‘ አዎን በወር አንድ ጊዜ አንዳንዴም አከታትዬ እሄዳለሁ ።’’

‘‘ ይቅርታሽን ጠይቃለሁ ፣ ’’ አለ ፖይሮት ‘‘ እንግዳ ሁኔታ ካጣየሁም . . . ’’ አላት ።

‘‘ ምናለበት ? ’’ በአጭሩ አቋረጠችው ፣ ‘‘ በዚህ አሁን በምንገኝበት ሁኔታ ሁላችንም እንግዳ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ነን ማለት ይቻላል ። ትላንትና ብዙ ጥያቄዎችን ለኢንስፔክተር ሻርፕ ስመልስ ነበርኩኝ ። ትንሽ ከፍ ያለ ወንበር የምትፈልግ መሰለኝ መሲ ፖያሮት ከአጭር ባለመያገፊያ ወንበር ይልቅ ። ’’

‘‘ የሰውን ፍላጎት ለመረዳት ብዙም የሚያዳግትሽ አትመስይ ኝም እመቤት ፣ ’’ በማለት ፖይሮት በጥንቃቄና በሥነ ሥርዐት ከባለ ትልቁ መያገፊያ ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ቫሌሪ ከመቀመጫ — አልጋው ተቀመጠች ። ሲጋራ ጋበዘ ችው ። ለ‘ራሷም አንድ ለኩሰች ። አትኩሮ ተመለከታት ። ከደ ካማ ገጽታ ይልቅ ከማለፊያ ውበት የተሻለ የሚስብ ቅብጥብጥ ተከለ ሰውነት አላት ። ብልህና ውብ ወጣት ሴት ሲል አሰበ ። ይህ ቅብ ጥብጥነቷ በቅርቡ በሆነው ምርመራና ክትትል ወይንስ የባህሪዋ ሽልም ይሆን ? ለ‘ራት በተጋበዘበትም ቀን የዚህኑ ተመሳሳይ ሀሳብ ሲያስብ ነበር ።

‘‘ ኢንስፔክተር ሻርፕ ጥያቄ ሲያቀርብልሽ ነበረ ? ’’ ሲል ጠየቀ ።

‘‘ አዎን ። ’’

‘‘ የምታውቂውን ሁሉ ነግረሽዋል ? ’’

‘‘ ትክክል ። ’’

“ እውነተኛ መሆኑን እጠራጠራለሁ ፣ ” አለ ፖይሮት ።

በሽሙጥ ተመለከተችው ።

“ ለኢንስፔክተር ሻርፕ የሰጠሁትን መልስ እስካላወቅህ እንዴት አስተያዬት ለመስጠት ትችላለህ ? ” አለች ።

“ የለም የኔው የማይረቡ ሀሳቦቼ ናቸው ። ” ራሱን መታ መታ አደረገ ። ይህ ደግሞ ፖይሮት ግራውን ቀኝ ፡ ጥቁሩን ነጭ ብሎ እንደወትሮው ለማሳመን እንደሚሞክር ያስታውቅበታል ። ብቻ ቫሌሪ አልሣቀችም ። ቅጭም ብላ ተመለከተችው ። ስትናገር ግን አንዳች ኻኮላ ይታይባታል ።

“ ወደ ዋናው ነጥብ ብንሔድስ መሴ ፖይሮት ? ” ስትል ጠየቀች ። “ ወደ የት በማምራት ላይ መሆንህን መረዳት አልቻልኩም ።”

“ ካለጥርጥር እንጂ ወይዘሪት ሆብሐውስ ። ”

ከኪሱ ትንሽ እሽግ አወጣ ።

“ ከዚህ ምን እንዳኖርኩኝ መናገር ትችያለሽ ? ”

”እኔ ባለ አውሊያ አይደለሁም መሴ ፖይሮት ። በወረቀቶችና ጥቅልሎች አሾልቄ ማየት አልችል ። ”

“ከዚህ የያዝኩት፡” አለ ፖይሮት ፣ “ከወይዘሪት ፖትሪሺያ ሌን የተሠረቀውን የጣት ቀለበት ነው ።”

“ የፖትሪሺያ የጋብቻ ቀለበት ? ማለቴ የእናቷ የጋብቻ ቀለበት ነው ? አንተ ዘንድ ምን ሊሠራ ተቀመጠ ? ”

“ ለአንድ ለሁለት ቀን እንድታውሰኝ ጠይቂያት ነው ። ”

ቫሌሪ በመደነቅ ቅንድቦቿን አሻቀበች ።

“ በርግጥ ? ” አለች ።

“ በቀለበቱ በጣም ስለተገረምኩኝ ነበር ፡ ” አለ ፖይሮት ። “ በመጥፋቱና በመመለሱ በሌላም አንድ ምክንያት ስለተገረምኩኝ ነው ። ስለዚህ ወይዘሪት ሌን እንድታውሰኝ ጠየቅኋት ። አልተቃወመችኝም ወዲያው ተስማማች ። በቀጥታ ወደ አንድ ጌጣጌጥ ሠራተኛ ጓደኛዬ ዘንድ ወሰድኩት ። ”

“ እናስ ? ”

“ ከላዩ ላይ ስለነበረው አልማዝ ሪፖርት እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁት ። የምታስታውሽ ከሆነ ከላዩ ላይ አንድ ትልቅ የከበረ ደንጊያ

ነበረበት ። በትናንሽ የከበሩ ደንጋዮች ፈርጦች በሁለቱም ወገን ያጌጠ ነበር ። ታስታውሻለሽ እመቤት ? ''

'' ይመስለኛል ። ነገር ግን በትክክል እንኳ አላስታውስም ። ''

'' ግን እንቺ ነሽ የሰጠሻት ፣ እይዶለም ? ከሾርባ ሣህንሽ ነበር ።''

'' እንደዚያ ነበር የተመለሰው ! አምን አስታውሳለሁ ። ልውጠው ምንም አልቀረኝ ነበር '' አለችና ቫሌሪ ትንሽ ሣቅ አለች ።

'' እንዳልኩት ፣ ቀለበቱን ወዲ ጌጣ ጌጥ ሠራተኛ ጓደኛዬ ወስጄ ስለአልማዙ ያለውን አስተያዬት ጠየቅሁት ። መልሱ ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? ''

'' እንዴት ማወቅ ይቻለኛል ? ''

'' የሰጠኝ መልስ የከበረ ደንጊያ መሣዩ ነገር አልማዝ አለመሆኑን ነው ። ቲራ ዚርኮን ነበር ። ነጭ ዚርኮን ። ''

'' ይገርማል !'' አለች አትኩራ እየተመለከተችው።ድምጿ ትንሽ የሚያጠራጥር ነበረ ። ነገር ግን ቀጠለች ። '' ምትለኝ ዚርኮን ሆኖ ሳለ ፖትሪሺያ ግን አልማዝ ነው ብላ አሰበች ። ወይንስ . . . ''

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

'' የለም ፣ እንደዚያ ማለቴ አይደለም ። የጋብቻ ቀለበቱ ነበር ፣ ይገባኛል ። የፖትሪሽያ እናት ቀለበት ። ሚስስ ፖትሪሽያ ከይሀና ቢተሰብ የመጣች ወጣት እመቤት ናት ። ቢተሰቦቿ ይመስለኛል ካለጥርጥር ከዘመን አመጣሽ ቀረጡ በፊት ምቾትና ድሎት ባለበት ሕይወት ውስጥ ነበሩ ። በነዚህ ማህበረሰቦች አካባቢ እመቤት ገንዘብ ብዙውን ጊዜ የሚጠፋው በጋብቻ ቀለበቶች ላይ ነው ። የጋብቻ ቀለቡት በጣም ውብ ቀለበት መሆን አለበት ። የአልማዝ ቀለበት ወይንም ሌሎች የከበሩ ደንጊያዎች የያዙ ቀለበቶች መሆን አለባቸው ። ርግጠኛ ነኝ የወይዘሪት ሌን አባባዋ ለእማማዋ ሌላ ነገር ሣይሆን የሰጡዋቸው በጣም ውድ የሆነ ቀለበት ነበር ።

'' ይህን እንኳ '' አለች ቫሌሪ ፣ '' ካንተ ሀሳብ ላይ አልስማማ በት/ም ። የፖትሪሽያን አባት እንኳ እስከዚህም ታዋቂነት የሌላቸው የገጠር መሬት ከበርቴ ናቸው ። እንደዚያ ነው እርግጠኛ ነኝ ።''

'' ስለዚህ ፣'' አለ ፖይሮት ፣ ''ይህ የከበረ ደንጊያ በሌላ ደንጊያ የተተካ መስሎ ይታየኛል ። ''

'' እንደሚመስለኝ ፣ '' አለች ቫሌሪ በቀስታ ። '' ፖት ምናል ባት የከበረ ደንጊያውን ጥላው ይሆናል ። በአልማዝ መተካቱን ስለማትችልም በምትኩ ዚርኮን አድርጋበት ይሆናል ። ''

“ የሚያስኬድ አማራጭ ነው ፣ ” አለ ሔርኩሉ ፖይሮት ። ቀጥ ሉም ፣ “ ነገር ግን የሆነው ጉዳይ ይህ አይመስለኝም ፣ ” አለ ።

“ መልካም መሴ ፖይሮት ፣ መላ ት እስከሆነ ዎን ሆነ ብለህ ነው ታዲያ ምታስበው ? ”

“ እኔ ‘ ማስበው ፣ ” አለ ፖይሮት ፣ “ ቀለበቱ በእመቤት ሴሊያ መወሰዱንና ሆነ ተብሎ አልማዙ ከላዩ ላይ ተወስዶ ቀለበቱ ከመ መለሱ በፊት በዚርኮን (በጨረቃ አልማዝ) መተካቱን ነው ። ”

ቫሌሪ ቀጥ ብላ ተቀመጠች ።

“ “እንተ የምታስበው ሴሊያ አልማዙን ሠርቃዋለች ብለህ ነው?” ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

“ የለም ፣ ” አለ ። “ እኔ የሚመስለኝ አንቺ የሠረቅሽው መሆ ኑን ነው ” አላት ። ቫሌሪ ሆብሐውስ ትንፋሿን ዋጥ አደረገች ።

“ በእውነት ? ” ስትል ድፃ ጿን ከፍ በማድረግ አቋረጠች ። “ ይህ ለኔ ትንሽ ያለአግባብ መለጠፍ ይመስለኛል ። ይህን ለመናገር እስኪ ዎን ዓይነት ማስረጃ አለህ ? ”

“ አዎን ፣ ” ሲል ፖይሮት ንግግሯን አቋረጠው ። “ ማስረጃ አለኝ ። ቀለበቱ በሾርባ ማህን ተመልሷል ። እኔ ራሴ አንድ ምሽት አብሬያችሁ በልቻለሁ ። የዚያን ቀን ሾርባ እንዴት እንደሚቀርብ ተመልክቻለሁ ። ከሰፊ ጎድጓዳ ማህን ከጎን በኩል ከሚገኝ ጠረጴዛ ላይ ነበር ። ስለዚህ ማናቸውም ከሾርባ ማህናቸው ቀለበት ቢያገኙ የገባው ከዚያ ሥፍራ ሾርባውን በሚጨልፈው ሰው (ምናልባት በጀሮኒሞ) ወይንም በባለ ሾርባው ማህን ነበረ ማለት ነው ። ይህን ያደረግሽ አንቺ ነሽ ! ጀሮኒሞ አይመስለኝም ። እንደሚመስለኝ የቀለበቱን በዚያ መንገድ መመለስ ያዘጋጀሽው አንቺ ነሽ ። አንቺ ፣ ሒስ ማድረግ ቢፈቀድልኝ ቀልደኛ የተዋናይ ስሜት ያለሽ ይመስለ ኛል ። ቀለበቱን በማንሳት ! በማዳነቅ ! የስሜትሽን ሽሙጥ አረካሽው አይደለም እመ ቤት ? ይህን በመሥራት ግን ራስሽን አሳልፈሽ መስጠትሽን አል ተገነዘብሽም ። ”

“ አበቃ ? ” አለች ቫሌሪ በትዕቢትና ንቀት ።

“ የለም ፣ የለም በምንም ዓይነት አላበቃ ። አየሽ ሴሊያ በዚያ ምሽት ለተደረጉት ሥርቆቶች ራሷን በሀላፊነት ስታቀርብ እንዳንድ ጥቃቅን ነጥቦችን ተመልክቼ ነበር ። ለምሳሌ ስለዚህ ቀለበት ስትና ገር ፣ ዎን ያህል ዋጋ እንደነበረው አልተገነዘብኩም ነበር ። ወዲ ያው እንዳወቅሁኝ ለመመለስ ተዘጋጅሁ ። እንዴት አወቀች ማለስ

ቫሌሪ ? ቀለበቱ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ማን ነገራት ? እንደገና ስለ ተቆራረጠው ሻርፕ ትንሿ ሴሊያ ስትናገር ፥ ' ያ እንኳ የማይረባ ነገር ነው ። ቫሌሪ ዋጋም አልሠጠችው . . . ' ብላለች ። ይህን የመሰለ ውድና ውብ የሐር ሻርፕ ሲቆራረጥ እንዴት አይሰማሽም ነበር ? ከዚ ያና በዚያን ጊዜ ይህ ሁሉ የሥርቆት ዘመቻና ራሷን የሥርቆት ሱስ በሽተኛ (ክሊፕቶማኒያክ) አስመስሎ ማቅረቡ ፥ የኮሊንን ትኩረት መሳቡ ለሴሊያ በአንድ የሆነ ሰው እንደተነገራትና እንደተቀነባበረ ከአዕምሮዬ ሀሳብ ጸነስኩኝ ። ማለትም ከሴሊያ አውስቲን የተሻለ ጭንቅላት ባለው አንድ ሰው በተጨማሪም ደህና ተግባራዊ የሆነ የሳይኮሎጂ እውቀት ባለው ሰው መሆኑን ተረዳሁ ። ቀለበቱ በጣም ዋጋ ያለው መሆኑን ነግረሻታል ። ቲቀብለሻት አመላለሱን ደግሞ እንቺው አዘጋጀሽ ። በተመሳሳይ መንገድ ባንቺው ዕቅድ መሠረት ያንኑ ሻርፕ በስለት እንድትቆራርጠው አደረግሻት ። አይደለም ? ''

'' ይህ ሁሉ ባዶ ሀሳብ ነው፣'' አለች ቫሌሪ ። '' በጣም ከእውነት የራቀ ሀሳብ ነው ። ኢንስፔክተሩም ሴሊያን እነዚህን ቲንኩሎች እንድትሠራ ያደረግሻት አንቺነሽ ብሎኝ ነበር ። ''

'' ታዲያ ምን መለሽለት ? ''

'' ይህ የማይረባ አስተሳሰብ ነው ፥ አልኩት '' አለች ቫሌሪ ።

'' ለ'ኔስ ምንድነው መልስሽ ? ''

ቫሌሪ ለአንድ ለሁለት ደቂቃዎች ያህል በጥያቄ መልክ ቲመ ለከተችው ። ትንሽ ቆይታ ዣቅ አለችና ሲጋራዋን ኮስትራ ከኃላዋ ያለውን መከዳ ቲደግፋ ቲለጠጠች ።

'' ትክክል ነህ ። እኔ ነኝ የመከርኳት ። ''

'' ለምንድነው ብዬ ብጠይቅሽ ? ''

ቫሌሪ ትዕግሥቷ አልቆ ፥

'' አምን ፥ በተራ ጅላጅል የዋህ ባህርይ ምክንያት ነው ። በቅን መንፈስ የተደረገ ጣልቃ ገብነት ነው ። ሲሊያ ከዚያ እንደት ንሽ ጣዕረ - መንፈሥ ሥራ ፈታ ዘወር እንኳ ብሎ የማያያትን ኮሊን በፍቅር እየጣመነች አንጀቷን ስታንዘፈዝፍለት ነበር ። ይህ ሁሉ በጣም የሚያስጠላ ጉዳይ ነበር ። ኮሊን ከነዚህ በሀሳብ ራቅ አዳሪ ከሆኑት ወጣቶች አንዱ በሳይኮሎጂ ቲጠቅልሎ በትምክህትና ልሽቀት በውስጣዊ ስሜት አቀባዮች ወዘተ ታርቆ ፥ ታጭቆ እያለ ከርሱ ላይ

እንደዚህ ማቻኩሉ ማጃጃሉ ቀልድ መስሎ ታየኝ ። ብቻ ሴሊያን ደግሞ እንደዚህ አሳዛኝ ሆና ማየቱ በጣም አስጠላኝ ። ስለዚህ አስጠጋኃት አነጋገርኳት ፥ መከርኳት ። ምክሬን በተግባር እንድትተረጉመው ገፋፋኋት ። ትንሽ ጭንቀት ነበረባት ይመስለኛል ። ነገር ግን በዚሁ ወቅት የማድረጉ የመተወኑ ፍላጎቷ በጣም ከፍ እያለ መጣ ። በርግጥ ከዚያ በኋላ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ውድ ጌጥ በመጥፋቱ ሽብር ተፈጥሮ ፖሊስ ተጠርቶ ሁሉም ነገር አስከፊ አቅጣጫ መያዙ ሊመጣ ነው ። ስለዚህ ከትንሿ ያደብ ይህንን ቀለበት ተቀበልኳትና በሆነ መንገድ እንደመለስኩት ነገርኳት ። በዚሁ አጋጣሚ ጌጣጌጥና የሴቶች መዋቢያ ቅባቶችን እንዲሁም ዋጋ ያለው የራሴ ዕቃ ላይ እንድ አደጋ እንድታደርስ ማለትም ምንም ችግር የማያደርስባት ነገር ላይ የሆነ ጉዳት የሠረቀች በማስመሰል እንድትፈጽም ወተወትኳት ።''

ፖይሮት በረጂሙ ተነፈሰ ።

'' በትክክል እኔም ያሰብኩት እንደዚያ ነው ። ''

'' አሁን ግን ባላደረገው እወድ ነበር '' አለች ቫሌሪ በሀዘን ። ቀጥላም '' እውነቴን ነው የምለው ። ይህ በጣም ጭካኔ ነው ። ልክ እንደ ጀንቶሚልስን ። ግን ሆነ ተፈጸመ ! '' አለች ።

'' የለም አሁን '' አለ ፖይሮት '' ወደዚህ ስለ ፖትሪሺያ ቀለበት ወደ ጀመርነው ጉዳይ እንመለስ ። ሴሊያ ላንቺ ሰጠችሽ ። አንድ ሥፍራ አገኘሁት ብለሽ ለፖትሪሺያ እንድትመልሽላት ነበር ። ነገር ግን ለፖትሪሺያ ከመመለስሽ በፊት '' ትንሽ ጊዜ ጸጥ ብሎ '' ምን ተፈጸመ ! '' አለ ።

ከአንገቷ ያጣፋችውን ሻርፕ ቁጪት በጣቶቿ ስትገምድ ስትፈታ ስታፍተለትል ተመለከተ ። በበለጠ ለማጣት በሚያስገድድ አነጋገር ቀጠለ ።

'' በጣም ገንዘብ ችግሮሽ ነበር እ. . . አይደለም ? ''

ፊቷን ቀና አድርጋ ሳታየው ራሷን ቀና በማድረግ ብቻ ገለጸችለት ።

'' ያንን ግልጽ አደርጋለሁ ብያለሁ '' አለች በምሬት ። ''የኔ ችግር መሴ ፖይሮት ቁማር ነው ። አብሮኝ የተፈጠረ ነገር ስለሆነ ምንም ማድረግ አልችልም ። ከሚይፌየር ከሚገኝ አንድ ትንሽ ክለብ አባል ነኝ ። የት እንደሆነ ግን መናገር አልችልም ። በፖሊስ ቢከበብ ወይንም አንድ የሆነ ችግር ቢደርስ ሀላፊነቱን መውሰድና ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም ። በቃ አባል ብቻ መሆኔን ከገለጽኩኝ በቂ ነው ። ሩሌቲ (ድብልብል ኳስ በቀዳዳ በማስገባት ዕጣ)

ና ባካራት (የካርታ ቁማር) ሌሎችም ጨዋታዎች አሉ ። ብዙ ተበልቻለሁ ። የቀረኝ ይኼ የፖት ቀለበት ብቻ ነበር ። አንድ የዚርኮን ቀለበት (ጨረቃ አልማዝ) በሚሸጥበት የጌጣ ጌጥ መደብር በማለፍ ላይ ነበርኩኝ ። ለ'ራሴ እንዲህ ብዬ አሰብኩኝ ። ይህ አልማዝ በነጭ ዚርኮን ቢተካ ፖት ልዩነቱን ማወቅ አትችልም ! ብዬ አሰብኩ ። በዚህ ላይ አብሮህ የቆየ ቀለበት ካለህ አተኩረህ አትመለከተውም ። ከወትሮው አልማዙ ትንሽ ይብዘዝ ቢልብህም መኩላት አለበት ወይንም መጽዳት ይኖርበታል ብለህ ብቻ ነው የፓ ትተወው እንጅ አትጠራጠርም ። እንግዲህ በዚህ ሀሳብ ከተረጋጋሁ በኃላ አልማዙን በማንጣት ሸጥኩት ። በዚያው ከሾርባ ማህኔ አገኘሁት ብዬ ባስመሰልኩበት ቀን ከላዩ ላይ ዚርኮኑን ተካሁበት ። በርግጥ ወራዳ ተግባር ነው ፡ እቀበለዋለሁ ። ይኸው ነው ! አሁን በሙሉ ተረድተኸዋል ። እውነቱን ለመናገር ሴሊያ ለዚህ ጉዳይ ማ ወቀስ አትችልም ። ''

''የለም፡የለም፡ገብቶኛል፡'' አለ ፖይሮት ራሱን እየነቀነቀ። ''ነገር ግን ከ'ዚያ ላይ ነው እመበት ትልቅ ሥህተት የሠራሽው አለች ። ''

'' ተገንዝቤዋለሁ ፡ '' አለች ቫሌሪ ቅጭም ብላ ። ቀጥላም በመረረ ሀዘን ፡

'' ግን ምን ፋይዳ አለው ? ምን ጥቅም ስ ሊኖረው ? የፈለከውን አድርገኝ ። ለፖት ንገራት ። ለኢንስፔክተሩ ንገር ። ለዓለም ግለጸው! ግን ምን ውጤት ይኖረዋል ? ሴሊያን ማን እንደገደላት ለማግኘት እንዴት ሊረዳን ይችላል ? ''

ፖይሮት ተነስቶ ቆመ ።

'' አይታወቅም ፡ '' አለ ፡ '' የቱ እንደሚረዳንና የቱ እንደማይረዳን ማወቅ አይቻለንም ። አንድ ሰው አንድን ነገር ሊሸፍኑ ሚችሉ ነገሮችን ማጽዳት ይኖርበታል ። ሴሊያ ያደረገችውን ነገር እንድታደርግ ያነሳሳትን ሰው ማወቁ ለኔ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው ። አሁን ይህን አውቄአለሁ ። ስለቀለበቱ ግን ራስሽ ሚስስ ፖትሪሺያ ሌን ዘንድ ሔደሽ የሠራሽውን ሥራ ገልጸሽ በተለመደው መንገድ ይቅርታ እንድታደርግልሽ ጠይቂያት ። ''

ቫሌሪ ሀፍረት ዋጣት ።

'' በጣም ጥሩ ምክር ነው የሰጠኸኝ ፡ '' አለች ። '' እሽ ከፖት ዘንድ እሔድና ለዚህ ወራዳ ተግባሬ ዓይኔን በጨው አጥቤ ይቅርታ ጠይቃታለሁ ። ፖት በጣም ጥሩ ሰው ናት ። በሚቻለኝ ጊዜ አልማዙን እንደምተካው እገልጽላታለሁ ። ያንን አይደለም የፈለከው መሲ ፖይሮት ? ''

'' እኔ የፈለኩት ሳይሆን መደረግ ሚገባውም ይኼ ነው ። ''

በሩ ሳይታሰብ በድንገት ተከፈተ ። ሚስ ሀበርድ ገባች ። ትኩሩ አጥሯታል ። ፊቷን በማየት ቫሌሪ ፣

“ ፃ ን ሆነሻል እንዴ ? ም ን ተፈጠረ ? ” ስትል ጠየቀቻት ።
ሚስ ሀበርድ ከወንበሩ ተዘፈጠች ።

“ ሚስ ኒኮሊተስ ናት ተይኝ ! ”

“ ሚስ ኒክ ? ም ን ሆነች ? ”

“ ተይኝ ወዳጄ ። ሞታለች ! ”

“ ሞተች !? ” አለች ቫሌሪ በኻኮላ ። “ እንዴት ? መቼ ? ”

“ ከጎዳና ላይ ትላንት ማታ ያነሷት መስለኝ ። ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወስዷት ። እነርሱ ሚሉት ትንሽ — ”

“ ሠክራ ? እንደዚያ ነው ያሉት . . . ”

“ አዎን — ስትጠጣ ነበረች ። ብቻ — ሞተች — ”

“ ምስኪኗ አሮጊት ኒክ ። ” አለች ቫሌሪ ። ከችኩል ድምዳሜ ፍራቻና መንገታገት አለባት ።

“ ፖይሮት በርጋታ ።

“ ትወጃት ነበር እመቤት ? ”

“ ብቻ እንግዳ ነገር ነው ። በርግጥ ከፉ አሮጊት ልትሆን ትች ላለች ። ቢሆንም አዎን . . . በመጀመሪያ ከዚህ ስመጣ - ከሦስት ዓመታት በፊት ፣ እንዲህ እንደአሁን — በኋለኛው ጊዜ እንደሆነችው ቁጡና - ብስጩ አልነበረችም ። ጥሩ ወዳጅ ልትሆን ም ትችል ሰው ነበረች — ተጫዋች — ተግባቢ ። ካለፈው ዓመት ጀምራ ነው በጣም የተለወጠች ው ። ”

ቫሌሪ ሚስ ሀበርድን ተመለከተች ።

“ ሁልጊዜ አዘውትራ መጠጥ ስለም ትወስድ ይመስለኛል ። ብዙ ጠርሙሶችና ሌሎች ነገሮች ከክፍሏ አግኝተዋል ። አልነበረም ? ”

“ አዎን ፣ ” አለች ሀበርድ በማመንታታት ። ቀጥላም “ ራሷን ነው የም ትወቅሰው ። ብቻዋን ከቤት ስትሔድ ትላንት ማታ የለቀ ቅኋት እኔ ነኝ ። አንድ የፈራችው ነገር ነበራት ፣ ” ስትል አንቧረቀች ።

“ የፈራችው ? ” አሉ በድንገት ፖይሮትና ቫሌሪ ።

ሚስ ሀበርድ ራሷን በሀዘን ነቀነቀች ። ያን ጭምት ክብ ፊቷን ጭንቀት አጥልቶበታል ።

“ አዎን ። አንድ ነገር እንደሚከታተላት ስትናገር ነበር ። ምን እንደፈራች እንደትነግረኝ ጠይቂያት ነበር ፣ ግን አናናቀችኝ ። ምን ያህል አንድን ነገር ማጋነን ወይንም ማሳነስ እንደምትችል ጸባይዋን ማንም መረዳት አይችልም ። አሁን ግን በጣም ነው የተገረምኩት —”

ቫሌሪም ፣ “ እርሷ - ነበረች - ብለሽ አላሰብሽም - ” አለች ።

ከዓይኖቿ የፍርሃትና የጭንቀት ገጽታ ይታያል ። አልጨረሰችም አቋረጠችው ።

ፖይሮት ፣

“ የሞቷ ምክንያት ምንድነው ተባለ ለመሆኑ ? ” ሲል ጠየቀ ።

ሚስ ሀበርድ በሀዘን ፣ “ እነሱ — ምንም አላሉ ። እንግዲህ ምርመራ ይኖራል - ማክሰኞ ዕለት — ” አለች ።

HAILE SELASSIE I LIBRARY
OF
ADDIS ABABA

— 15 —

ከኒው ስኮትላንድ ያርድ ፀጥ ያለ ክፍል ውስጥ አራት ሰዎች በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል ።

ስብሰባውን ይመራ የነበረው የአደንዛዥ ዕጽ ክትትል ቡድን መሪ የሆነው ሱፐርኢንቴንደንት ዋይልዲንግ ነበር ። ከ'ርሱ ቀጥሎ ሃምሳ አለቃ ቤል የተባለ ሠርቶ የማይደክመው ቅን አሳቢ ፣ የአዳኝ ውሻ ችሎታን የታደለ የሚመስል ወጣት ተቀምጧል ። ከወንበሩ ተለጥሎ በጽሞናና በተጠንቀቅ የተቀመጠው ኢንስፔክተር ሻርፕ ነው። አራተኛው ሰው ሔርኩሌ ፖይሮት ነበር ። ከጠረጴዛው ላይ የጀርባ ሻንጣ ተቀምጧል ።

ሱፖርኢንቴንደንት ዋይልዲንግ በሀሳብ ሰጥሞ አገጩን በጣቶቹ መታ መታ በማድረግ ላይ ነው ።

" በጣም " ሚገርም ሀሳብ ነው መሴ ፖይሮት ፡ " አለ ጠን ቃቃና ተጠራጣሪ በሆነ አነጋገሩ ። " አምን በጣም የሚገርም ነው ፣ ነው ፡ " አለ በድጋሚ ።

" አምን እንዳልኩት ፣ ይህ እንግዲህ ዝም ብሎ ሀሳብ ነው ፣ " አለ ፖይሮት ። ዋይልዲንግ ራሱን ነቀነቀ ።

" አጠቃላዩን ሥፍራ ነድፈነዋል " አለ ። " በርግጥ ይህ በድ ብቅ ማስረጉ በአብዛኛው ጊዜ የሚካሔድ ነው ። በተለያየ መልኩ ማለቴ ነው ። እነዚህኑ ሕገወጦች አጸዳዳን ስንል እንደገና ደግሞ ከአ ንድ የሆነ ሥፍራ ጀምረው እናገኛቸዋለን ። ስለ 'ራሴ ክፍል ለመና ገር ባለፉት አንድ ዓመት ከመንፈቅ ለሆኑ ጊዜያት ብዙ ዕጽ ወደዚህ ሀገር ሲገባ ነበር ። በአብዛኛው ሔሮይን ነው ። አነስተኛ ያልሆነ ኮክ ዕጽም ጭ ር ነበር ። ከክፍለ - አህጉሩ ውስጥ በየሥፍራው የተለያዩ ማከፋፈያ ሥፍራዎች አሉ ። የፊረንሣይ ፖሊሶች እንዴት ወደ ፊረንሣይ እንደሚገባ ቢያውቁም ተመልሶ ግን እንዴት እንደ ሚወጣ ርግጠኞች አይደሉም ። "

" ምናልባት ፡ " አለ ፖይሮት " ችግሮቻችሁ በሦስት ከፍ ተኛ ርዕሶች ይከፈላሉ ብል ትክክለኛ እሆን ይሆን ? የማከፋፈል

ችግር ፡ ወደ ሀገር ውስጥ ደብቆ የማስገባት ችግር ፣ ይህን ንግድ የሚ ያካሒደው ትርፉን የሚያፍሰው ሰው ማንነት አለመታወቅ ችግር አይደሉም ? ''

''ከሞላ ጎደል ትክክል ነው ። ስለትናንሽ (ቸርቻሮ) አከፋ ፋዮችና እንዴት እንደሚከፋፈል ጥቂት እናውቃለን ። አንዳንድ የደረስንባቸውን አከፋፋዮች ምናልባት ወደ ትልቁ ዓሣ ሊመሩን ይችሉ ይሆናል በሚል ፈተሻ እያወቅን ትተናቸዋል ። በብዙ የተለያዩ መንገዶች ነው ፣ ሚከፋፈለው። በናይት ክለቦች ፡ በመጠጥ ቤቶች ፡ በመድሐኒት መደብሮች ፡ የሆነ የማይረባ ዶክተር በመጠቀም ወይንም በመሳሰለው ዘዴ ፡ በዘመናዊ ልብስ ሰፊዎች ፡ በፀጉር ሰሪዎች አማ ካኝነት ነው ። የሚቀባበሉት ደግሞ ከፊረሥ እሽቅድም ድም ሥፍራ፡ ከጥንታዊ ቅርሶች አሻሻጮች ዘንድ ፡ አንዳንዴም በሕዝብ ከተጨናነቁ መደብሮች ውስጥ ነው ። ነገር ግን ይህን ሁሉ መናገሩ አስፈላጊ አይ ደለም ። የጉዳዩ ይኼኛው ክፍል አይደለም ዋናው ቁም ነገር ። ይህን ሁሉ በተቻለን መከታተሉ አያዳግትተንም ። ይሽ ትልቁ ዓሣም ማን መሆኑን የሆነ ጥርጣሬ ያሳደርንበትም ሥፍራ አለ ። ቅንጣት ጥርጣሬ ሊያሳድሩ የማይችሉ አንድ ሁለት በጣም የተከበሩ ከበርቴ ጨዋ ሰዎች ናቸው ። በጣም ጠንቃቃዎች ናቸው ። ዕፀን በፍጹም በጣታቸውም አይ ነኩትም አያስቲላልፉትም ፡ ትናንሾቹ አከፋፋዮቻቸው እንኳ ማንነታ ቸውን አያውቋቸውም ። ነገር ግን አሁንም አሁንም በመደጋገም ከመካ ከላቸው አንዱን ቢያስተው ከእጃችን መወደቁ አይቀርም ። ''

'' እንደገመትኩት ሁሉ በብዛት ታውቃላችሁ ። እኔን ግን ጉጉት ያሳደረብኝ ሶስተኛው ነጥብ ወደ ሀገር ውስጥ እንዴት ተደብቀው እንደሚገቡ ማወቁ ነው ። ''

'' አዎን የኛይቱ ሀገር ደሴት ናት ። የተለመደው መንገድ ጥን ታዊ የሆነው የባህር መንገድ ነው ። በጭነት መርከብ ። ከባሩ ጠረፍ ከአንድ ሥፍራ ላይ ከትንሽ ቆር በስተደቡብ ሲመቻች በሞተር ጀልባ በፍሉ በኩል አድርጎ ጭልጥ ይላል ። ይህ ለጥቂት ጊዜ ከቀጠለ በኃላ በእንዲህ ዓይነት መልኩ በክትትላችን መሠረት ከባለጀልባው ላይ ጥርጣሬያችን ሲያርፍ የርሱ ነገር እዚያ ላይ ያበቃል ማለት ነው ። በቅርቡ ዕዕ አንድ ሁለት ጊዜ ከአየር መንገዶቹ በአንዱ መጥቶ ነበር ። ትልቅ የገንዘብ ሥጠታም ነበር ። ከነዚህ አስተናጋጆች ወይንም ከአውሮፕላን ሠራተኞች አንዱ ደጋግመው ፆንም ማያውቁ መሆና ቸውን ገልፀዋል ። በዚህ ላይ ደግሞ አስመጪ ነጋዴዎቹም አሉ ። አየህ ትልቅ ፒያኖ ወደ ሀገር የሚያሰመጡ የተከበሩ ሰዎች ፡ ወይንም የማይጠረጠሩ ሌሎች ! ለጥቂት ጊዜ ደህና ጨዋታ ተጫውተዋል ፡ ሆኖም መጨረሻቸውን እስክናይ ድረስ እንጠብቃለን ። ''

“እንደዚህ ያለ የተከለከለ ንግድ በሚካሔድበት ወቅት ከውጪ ማስገባቱ ከፍተኛ ችግር መሆኑን ትስማማበታለህ ? ”

“በሚገባ እንጂ ! ከዚህም በላይ ነው ። ለጥቂት ጊዜ ያህል በጣም አሳስቦን ነበር ። ለመቆጣጠር ከምንችለው ዕጽ በላይ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ነበር ። ”

“ ሌሎች ነገሮችስ ፣ ለምሳሌ እንደ ከበረ ድንጊያ ዓይነት ? ”

የሃምሳ አለቃ ቢል ፣ “በከፍተኛ መጠን እየተካሔደ ነው ጌታዬ ። በድብቅ አልማዞችና ሌሎች የከበሩ ድንጊያዎች ከደቡብ አፍሪካ አውስራትራሊያ ጥቂት ደግሞ ከሩቅ ምሥራቅ በመጉረፍ ላይ ናቸው። ያለማቋረጥ በየጊዜው ወደ ሀገር ውስጥ በመግባት ላይ ናቸው ። እንደኤት እንደሆነ ግን አናውቅም ። አንድ ቀን አንዲት ወጣት ሴት ፣ ተራ ቱሪስት (ሀገር ጎብኝ) በአጋጣሚ ትውውቅ ጥንድ ጫማዎችን በፋሉ አድርጋ ለማሳለፍ ትጠይቃለች ። አዳዲስ አይደሉም ። ቀረጥም አይከፈልባቸውም ። አንድ ሰው የረሳቸው ተራ ጫማዎች ናቸው የሚመስሉት ። ካለምንም ጥርጥር ተስማማች ። እንዳጋጣሚው ከሥፍራው ነበርን ። የጫማዎቹ ተረከዞች ሲከፈቱ ቀዳዳዎቹ በመላ ያልተቆራረረጡ አልማዞች ተሞልተዋል ” ሲል አጫወታቸው ።

ሱፐርኢንቴንደንት ዋይልዲንግም ፣

“ እስኪ መሴ ፖይሮት የትኛውን ነበር ማወቅ የፈለከው ? ዕዕ ወይንስ የከበረ ድንጊያ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ ማናቸውንም ። ማንኛውም በትንሹ ሊያዝ የሚችል ነገር ግን ብዙ ዋጋ ያለውን ማለቴ ነው ። በውሃው ፋል አድርጎ እንደገለጽኩት ሁሉ ከመነሻ — መድረሻ ጭነት የሚያጓጉዙ የመርከብ ማጓጓዣ አገልግሎት መንገድ ያለ ይመስለኛል ። በሕጋዊ መንገድ በገበያ የሚሸጡ ጌጣ ጌጦች ከተጣበቁባቸው ቀለበቶች ላይ የከበሩት ድንጊያዎች እየተላጡ ከእንግሊዝ እየወጡ በዎትካቸው በድብቅ ሌሎች ሕገ ወጥ ድንጊያዎችና ዕጾች ይገባሉ ። አዎን ይህ እነዚህን ነገሮች የተሟሰነ ገንዘብ እየተከፈለው የሚያጓጉዘው አካል ከማከፋፈል ተግባር ያልተያያዘ ነጻና ትንሽ ድርጅት ነው ። ”

“ ከዚያ ላይ እንኳ ትክክል ነህ ! ከአሥርና ከሀያ ሺህ ፓውንዶች ዋጋ የማይነተናነስ ሔሮይን በአንዲት በጣም አነስተኛ ሥፍራ ማጓጓዝ ይቻላል ። በተመጣጣይ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ውድ የከበሩ ድንጊያዎችም እንደዚሁ መጓጓዝ ይችላሉ ። ”

“ አያችሁ ፣ ” አለ ፖይሮት ፣ “ የአሥራጊ - ነጋዴዎቹ ድክመት የሰውልጅ ባህርይ ነው ። ከጥቂት ጊዜ በኃላ ወይንም ዘግይቶ

አንድ የአውሮፕላን አስተናጋጅ ፣ የሆነ ከመዝናኛ ጀልባ ያለ ባህር አፍቃሪ ፣ አዘወትራ ከዚህ ፈረንሣይ የምትመላለስ አንዲት ሴት ፣ አንድ ከመጠን በላይ ትርፍ ሚያጋብስ አስመጪ ነጋዴ ፣ ካለምንም መተዳደሪያ ደህና ኑሮ የሚኖር ሰው ማጠራጠር ይችላል ። ነገር ግን ይህ ነገር ምንም በማያውቅ የዋህ ሰው ወደ ሀገር ውስጥ ሚገባ ከሆነ ከዚህም በላይ በእያንዳንዱ ጊዜ በተለያዩ ሰዎች ከተጠቀሙ እያንዳንዱን የጭነት መርከብ የመከታተሉ ችግር ከመጠን በላይ ይባባሳል ። ”

ዋይልዲንግ ወደ ጀርባ ሻንጣው በጣቱ በማመልከት “ ያ ነው የእንተ ጥርጣሬ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ አዎን ለዛሬው ቀን ጥርጣሬ ያልተጋለጠ ሰው ማነው ? ተማሪ ነው ። ቆራጥ ፣ በጣም ታታሪ ተማሪ ። በጣም ገንዘብ ሚቸግረው ደሃ ፣ ከጀርባው ከሚሸከመው ነገር በስተቀር ሌላ ዕቃ የማይዝ ። በአውሮፖ ውስጥ በሀገር እንወቅ ጉዞ ሚዘዋወር ። በዚህ ላይአንድ ተማሪ ብቻ በተለይ ዕፀን የሚያመላልስ ከሆነ ሁልጊዜ እሷን ወይንም እ‘ሱን ለይቶ ማወቁ አያዳግታችሁም ። ዋናው ችግር ግን አስተላላፊዎቹ በጣም የዋሆች መሆናቸውና የቁጥራቸው መብዛት ነው ።”

ዋይልዲንግ አገጩን አሻሸ ።

“ እንዴት እንደሚዘጋጅ በትክክል ታውቃለህ መሴ ፖይሮት ?’ ሲል ጠየቀው ። ሔርኩሌ ፖይሮት ትከሻውን ነቀነቀ ።

“ ያ እንኳ የኔ ግምት ነው ። አብዛኛውን ነገር እንደተሳሳትኩ ምንም ጥርጥር የለው። ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ አሠራሩ እንደዚህ ይመስለኛል ። በመጀመሪያ የሻንጣዎች መደብሮች ከገበያ ተከፈቱ ። ሻንጣዎቹ ተራ ጊዜያዊ የሆኑ ናቸው ። ከሌሎቹ ሻንጣዎች የተመሳሰሉና ለተሠሩበት ምክንያት የሚሆኑ ናቸው ። ከሌሎቹ ሻንጣዎች የተመሳሰሉ ናቸው ። እንዲህ ስል ፍጹም ማለቴ አይደለም ። ከሥሩ ትንሽ ልዩነት አለው ። እንደምታዩት በቀላሉ ሊነሳ የሚችል ነው ። አወፋፈሩና አሠራሩ የከበሩ ደንጊያዎችን ወይንም የተፈጨ ዱቄት በማደራረብ መደበቅ እንዲችል ነው ። ካላያችሁት በስተቀር መጠራጠር አትችሉም ። ንጹህ ሔሮይን ወይንም ንጹህ ኮኬይን የሚይዘው በጣም ትንሽ ሥፍራ ነው ። ”

“ ትክክል ፡ ” አለ ዋይልዲንግ “ ታውቃለህ ፡ ” በጣቱ በችኮላ ለካው ፡ “ በዕፅ ከአምስት ወይንም ከስድስት ሺ ብር በላይ ምንም ሳትጠረጠር ማሳለፍ ትችላለህ ። ”

“ በትክክል ፡ ” አለ ሔርኩሉ ፖይሮት ። “ አበቃ ! ሻንጣ ዎቹ ቲሠርተው ለሽያጭ ከገበያ ላይ ቀረቡ ። ምናልባት በ‘ከአንድ መደብር በላይ ውስጥ ለሽያጭ ቀርበው ይሆናል ። ባለ መ ደብሩ የቲዋከበ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ። ምናልባት በጣም የሚያቲርፉ ግን ርካሽ መደብር ይሆናል ። ከሌሉቹ የሀገር እንወቅ የጉዞ ዕቃዎች ና መሣሪያ ዎች መደብሮች ሲወዳደር ብዙም ልዩነት እስከሌለው ድረስ ማለቴነው። በርግጥ ከበስተኃላው አንድ ድርጅት ይኖራል ። በጥንቃቄ የተያዘ የቲማሪዎች ስም ዝርዝር ከሕክምና ትምህርት በት ፡ ከለንደን ዩኒ ቨርስቲና ክሌሎችም ሥፍራዎች ይኖራል ። አንድ ራሱ ቲማሪ የሆነ ሰው ወይንም ነኝ የሚል ሰው ምናልባት ከሁሉም ፊት ስሙ ይኖ ራል ። ቲማሪዎች ወደ ውጭ ይሔዳሉ ። በመልስ ጉዞው ከሆነ ሥፍራ ላይ ቲመሳሳይ ሻንጣ ለውጥ ይደረጋል ። ቲማሪው ወደ እንግሊዝ ይመ ለሳል ። የቀረጥ ፍተሻው እስከዚህም ችግር አይኖረውም ። ቲማሪው ወይንም ቲማሪዋ ከሆስቴላቸው ይመለሳሉ ። ዕቃውን ያወጣዋል ። ባዶውን ሻንጣ ከቁም ሣጥን ወይንም ከከፍሉ አንድ ጥግ ላይ ይወረወ ራል ። ከ‘ዚህ ሥፍራ እንደገና የሻንጣ መቀያየር ይኖራል ። ካልሆነም ቲመሳሳዮ የሻንጣ ቂጥ በጥንቃቄ ይወጣና ሌላ ይገባለታል ። ”

“ከሒኮሪ ጎዳና የቲፈጸመው ችግር እንደዚያ ነው ብለህ ታስባለህ?” ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

“ አዎን እጠራጠራለሁ ” አለ ።

“ ግን እንዴት ልታስበው ቻልክ መሴ ፖይሮት ? ትክክለኛ እን ደሆንክ አድርገን ብናስብ ? ”

“ አንድ የጀርባ ሻንጣ የቲቆራረጠ ነበር ፡ ” አለ ፖይሮት ። “ ለምን ? ይህን ጥያቄ ሚመልስ በቂ ምክንት እስከማይገድ ድረስ አንድ ሰው ምክንያቱን ለማግኘት መሞከር አለበት ። ወደ ሒኮሪ ጎዳና ስለሚመጡት የጀርባ ሻንጣዎች አንዳች እንግዳና ግራ የሚያ ጋባ ጉዳይ አለ ። በጣም ርካሽ ናቸው ። ልዩ የሆኑ ድርጊቶችም ተከ ታትለው ቲፈጽመዋል ። ነገር ግን ለሥርቆቶቹ በሙሉ ሀላፊነቱን ወስዳ ራሷን ያጋለጠችው ልጅ የዚህ ሻንጣ መቆራረጥ በርሷ ያለመ ካሔዱን ምላ ቲገዝታ አስረዳች ። ሌሉቹን ነገሮች መውሰዷን ራሷን በማጋለጥ እስከተናገረች ድረስ እንዴት ይህንን ካደች ? ስለዚህ የ‘ዚህ ሻንጣ መቆራረጥ ሌላ ምክንያት ይኖረዋል ማለት ነው ። የጀ ርባ ሻንጣ መቀዳደድ ፡ ከጥቅም ውጭ ማድረግ እንደኔ ቀላል ጉዳይ አይደለም ። በጣም አድካሚ ሥራ ነው ። አንድ ሰው ላድርገው ቢል ይከብደዋል ። ያን አጠቃላይ ግ ት ባገኘሁበት ወቅት ነበር ፍንጭ ማግኘት የቻልኩት ። (አጠቃላይ ግ ት ብቻ ፡ በቃ ። ምክ

ንያቱም ከጥቂት ወራት በኋላ ሰዎች ሚኖራቸው ትውስት ሙሉ በሙሉ ትክክል አይሆንም) ነገር ግን በማጥ - የጀርባ ሻንጣው ከጥቅም ውጭ የሆነው አንድ የፖሊስ መኩንን የሆስቴሉን ሀላፊ ለማነጋገር በመጣበት ቀን ነበር ። ፖሊስ መኩንኑ የተጠራበት ምክንያት በሌላ ጉዳይ ነበር ። ነገር ግን ለእናንተ እንደዚህ አስቀምጠዋለሁ ። እንግ ግዲህ እንዳችሁ በዚህ የማስረግና የማጭበርበር ነገር የገባችሁ ሰዎች ትሆናላችሁ ። ወደ በቱ በነዚያ ምሽት ትሑዱና ፖሊስ ከላይኛው ፎቅ ከሚስ ሀበርድ በመነጋገር ላይ እንደሆነ ትሰማላችሁ ። ወዲያ ያውኑ ፖሊሶቹ ይህን ማስረግ ፡ ማጭበርበር የደረሱበት አድርጋችሁ ትገምታላችሁ ። ስለዚህ ሪመረቲሽና ጥያቄ ለማድረግ የመጡ ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ ። በዚያ ወቅት ከ ውጭ ዕቃ ይዞ የመጣ - ወይ ንም - በቅርቡ ዕቃው የተደረገበት የኮንትራባንዱ ሻንጣ አለ ብለን እንገምት ። አሁን እንግዲህ ፖሊሶች ግን እየተደረገ እንዳለ በመከ ታተል ላይ እስከሆኑ ከሒኮሪ ጎዳና የሚመጡት በፍጥነት የተማሪዎ ቹን የጀርባ ሻንጣዎቹ ለመመልከት ይሆናል ። ምናልባት ከቤቱ ውስጥ በፍጥነት የተማሪዎቹን የጀርባ ሻንጣዎች ሪመመልከትም ይሆ ናል ። ከቤት ውስጥ ስትወጡ የሚፈለገውን ሻንጣ ሳትይዙ ይሆናል የወጣችሁት እንበል ። እንደምታውቁት ሁሉ አንድ የሆነ ሰው ከውጭ የተባለውን ዕቃ እስከሚያይ ቤቱን በዓይነ ቁራኛ እንዲጠባበቅ በፖሊስ ተቀምጠ ይሆናል ። ይህን የጀርባ ሻንጣ ደብቆም ለማውጣት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ ልታደርጉ የዎ ትችሉት ነገር ሻንጣውን በመቆ ራረጥ ቁርጥራጩን ከውሣ ማሞቂያው ቤት ቆሻሻ ዕቃ መከመሪያ መደ በቅ ነው ። የሃሽሽ ዕጽ ወይንም የከበረ ደንጊያ ከበቱ ውስጥ ካለ ከመ ታጠቢያ ጨው ቀላቅሎ መደበቅ ይቻላል ። ጊዜያዊ ርዎ ጃ ማለት ነው። ነገር ግን ባዶ ሻንጣ እንኳ ቢሆን የሀሺሽ ዕጽ ከተሸሸገበት ምናልባት በጥበቅ ፍተሻ የሔሮይን ወይንም የኮኬይን ዕጽ ሊታወቅ ይችል ይሆ ናል ። ስለዚህ ሻንጣው ከሽጥቅም ውጭ መሆን ይገባዋል ። መቀዳደድ አለበት ። ይህ የሚቻል በመሆኑ ትስማማላችሁ ? ''

'' እንደተናገርኩት ሁሉ ይህ ሀሳብ ነው ፡ '' አለ ሱፐር ኢን ቴንደንት ዋይልዲንግ ።

'' እስካሁን እንደትልቅ ነገር ያልታየ አንድ ትንሽ አጋጣሚ ከሻንጣው ሊያያዝ የሚችል መስሎ ይታያል ። እንደ ጣሊያናዊው የቤት ሠራተኛ እንደ ጄሮኒሞ አባባል ከሆነ ፖሊሶች በተጠሩበት ቀን ከአዳራሹ የነበረው መብራት ጠፍቶ ነበር ። እዎ ቹሎችን በማዎጣት ለመተካት ሔደ ። የሚተኩትም እዎ ቹሎች ተሠርቀዋል ፡ የሉም ። ከአ ንድ ከሠዓት ቀን በፊት ግን ኪመሣቢያዎቹ እዎ ቹሎች መኖራቸውን ተመልክቶ ነበር ። ይህ ነገር አስቀድሞ የታሰበበት መስሎ ነው

የሚታየኝ ። ርግጠኛ ነኝ ብዬ መናገር እንኳ አልችልም — ተራ አጋጣሚ አድርጋችሁ ልትረዱትም ትችላላችሁ ። ማለት አንድ ይህንኑ የማጭበርበር ድብቅ ንግድ በማካሔዱ ሥራ እጁን የከተተ ማንኛውም ሰው ፊቱ ቢታይ በመብራቱ ማንነቱ ስለሚታወቅ ይህንን በመፍራት ለመሸሸግ ይፈልጋል ። ስለዚህ ከአዳራሹ መብራት አጋ ጥሉን በማንሳት በተጨማሪ መለወጫም እንዳይኖር አዳዲሶቹንም ይወ ስዳል ። ስለዚህ ከአዳራሹ ውስጥ ሻማ ተለኮሰ ። ይህ እንግዲህ የኔ የይሆናል ግምት ነው ።''

'' በጣም ብልህና ጠቃሚ ሀሳብ ነው ፣'' አለ ዋይልዲንግ ።

'' ሊሆን የሚችል ነው ጌታዬ ፣'' አለ የሃምሳ አለቃ ቤል ።

'' ባሰብኩት ቁጥር ተግባራዊነቱ ጎልቶ ነው ሚታየኝ'' አለ ።

'' ከሆነ ግን '' ሲል ቀጠለ ዋይልዲንግ ፣'' ከሔኮሪ ጎዳና በተጨማሪ በሌሎች አካባቢዎችም ሊኖር አይችልም ? '' አለ ።

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

'' አዎን ። ድርጅቱ ብዙና የተለያዩ የተማሪዎች ክለቦችንና የመሰሰሉትን ያቅፋል ። ''

'' ግንኙነታቸውን ማግኘት አለባችሁ ፣'' አለ ዋይልዲንግ ። ኢንስፔክተር ሻርፕ ለመጀመሪያ ጊዜ '' አዎን እንዲት ሴት አለች ጌታዬ ፣ ወይንም ነበረች ። እንዲት የተማሪዎችን ክለቦችና ድርጅቶች የምታካኒድ ሴት ናት ። ከሔኮሪ ጎዳና ያለች ሚስ ኒኮሊተ የተባለች ናት '' ሲል ተናገረ ።

ዋይልዲንግ ፖይሮትን መልከት አደረገው ።

'' አዎን ፣'' ኦለ ፖይሮት ። '' ሚስ ኒኮሊተስ መሆን ኦለባት ። ራሷም ባታካሔድባቸውም ቅሉ ከሁሉም ሥፍራ የገንዘብ ጥቅም አላት ። የ'ርሷ መንገድ የየሥፍራውን ሥራ ለመምራት እንከን የማይገኝበትና አስቀድሞም ቢሆን መልካም ሥነ ምግባር ያለው ጠንካራ ሰው በመፈለግ መጠቀም ነው ። የ'ኔ ጓደኛ ሚስ ሀበርድ እንዲህ ዓይነት ሴት ናት ። የገንዘቡ ድጋፍ የሚስ ኒኮሊተስ ነው - እ'ሷም ብትሆን እንዳው ለይስሙላ ያህል ነው ባለቤትነቷ ብዬ እጠራጠራለሁ ። ''

''እ - ሁ ፣'' አለ ዋይልዲንግ ። '' እንደሚመስለኝ ስለ ሚስ ኒኮ ሊተስ የበለጠ ማወቁ አስፈላጊ ነው ። ''

ሻርፕ ራሱን ነቀነቀ ።

“ እንከታተላታለን ፣ ” አለ ። “ መሠረታዊ ታሪኳንና ከየት እንደመጣች ለማወቅ ጥረት እናደርጋለን ። በጥንቃቄ መደረግ አለ በት ። ወፎቻችንን ቶሎ ማስበርገግ የለብንም ። የገንዘብ አቅም መሠ ረታዊ ታሪኳንም እናያለን ። ያቺ ሴት ተወዳዳሪ የማይገኝላት አደ ገኛ ሰው ናት ። ”

የቤት ፍተሻውን ትዕዛዝ ያዘው በሔዱበት ወቅት በሚስ ኒኮ ለተስ የገጠማቸውን ችግር አንድ በአንድ ዘረዘረላቸው ።

“ የብራንዲ ጠርሙሶች ! ምናልክ ? ” አለ ዋይልዲንግ ። “እና ጠጣች ? ጥሩ ፣ ያ ነገሩን ሁሉ ቀላል ያደርገዋል ።ምን ሆነች ? ጠፋች ?”

“ የለም ጌታዬ ። ሞታለች ! ”

“ ሞታለች ? ” ዋይልዲንግ ቅንድቦቹን አሻቀበ ። “ ሕግ ወጥ የሆነ ሥራ ከዚህ አካባቢ እየተካሔደ ነው ” አለ ።

“ እኛም እንደዚያ ነው ያሰብነው — አዎን ። ከሬሣ ምርመ ራው በኋላ እናረጋግጣለን ። እንደሚመስለኝ ትንሽ አዕምሮዋን ነካ ለድረግ ጅምሯት ነበር ። ለግድያ አልተደራደረች ይሆናል ። ”

“ ስለሴሊያ አውስቲን ጉዳይ ነው የምትለው ልጁቱ ፣ የምታ ቀው ነገር ነበራት ? ”

“ አዎን ትንሽ ታውቃለች ፣ ” አለ ፖይሮት ፣ “ ግን በትክክል ለማስቀመጥ ታውቅ የነበረውን ነገር አልነበረም የምታውቅ ! ”

“ አንድ ነገር እያወቀች ሳለ ወድየት የሚያመራ መሆኑን አታውቅም ነው ምትለው ? ”

“ አዎን ትክክል ! ብልህና አስተዋይ ልጅ አልነበረችም ። የሆነ ጣልቃገብነት ለማመን ምትችል አልነበረችም ። ነገር ግን አንድ ነገር በማየት ፣ ወይንም በመስማት ምንም ሳትጠረጥር ስለ ጉዳዩ ጠቃቅሳ ይሆናል ያስገድለኛል ብላ አላሰበች ይሆናል ። ”

“ ምን እንዳየች ወይንም እንደሰማች መገመት አትችልም መሴ ፖይሮት ? ”

“ ግምት ብቻ ነው ፣ ” አለ ፖይሮት ። “ ከዚህ የተለየ ነገር ማድ ረድ አልችልም ። በርግጥ ስለ ፖስፖርት የተጠቀሰ ነገር አለ ። ከዚያ ቤት የሀሰት ፓስፖርት ይዞ በአህጉሩ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በውሸት ስም ሚመላለስ ሰው አለ ? የነገሩ መታወቅ ለዚያ ሰው ከፍተኛ አደጋ ማድረስ ይችላል ? አንድ የሆነ ሰው ሻንጣውን ይዞ ወይንም

ምናልባት የማስመሰያውን የሻንጣ ሥር ሲያነሳው እርሷ ግን ምን እንደሚሠራ ሳታውቀው ድንገት ተመልከታው ይሆን ? ምናልባት የመ ብራት አገ ፑሎቹን ያነሳውን ሰው ተመልከታው ይሆን ? ደግሞ ለጉ ዳዩ ምንም ግፑ ት ሳትሰጥ ለሰውዬው ወይንም ለሴትየዋ ጠቃቅሳላት ፣ ይሆን ? ያንተ ያለህ ! እኔ እንጃ ! '' አለ ሔርኩሌ ፖይሮት በቁጣና በንዴት ። ''ግፑ ት ! ግፑ ት ! ግፑ ት ! አንድ ሰው የበለጠ ማወቅ ይገባዋል ። ሁልጊዜ አንድ ሰው የበለጠ ማወቅ ይገባዋል ! ''

'' መልካም ፣ '' አለ ሻርፕ ፣ '' እንግዲህ በሚስ ኒኮሊተስ መሠ ረታዊ የሕይወት ታሪክ እንጀምራለን ። አንድ ነገር ማግኘት እንችል ይሆናል ። ''

'' ከመንገዳቸው ያስወገዷት ምናልባት ታወራለች ብለው ፈር ተው ይሆን ? ብታወራስ ኖሮ ? ''

'' በሚስጥር ለሆነ ጊዜ ስትጠጣ ነበረች . . . እንዲያ ማለት ደግሞ ከጭንቅላቷ ወጥቶ ነበር ማለት ነው '' አለ ሻርፕ ። ''ምናልባት መቋቋም አቅቷት ያለውን አስታውካው ይሆናል ። ከዚያ ላይ መረጃ ማግኘት ዘበት ነው ። ''

'' ይህን የማጭበርበር ሥራ የምትመራ እኅሷ አይደለችም ። እኅሷ ናት ? '' ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

'' እንደዚያ አያመስለኝም ፣ አይደለችም ። ' ርሳ በግልጽ ናት ገባህ ። ምን እየተካሔደ እንዳለ ታውቃለች ነገር ግን ከበስተጀርባ ያለች ዋናዋ መሪና አቀናባሪ እኅሷ ናት ማለቱን አልችልም ። የለም አይደለችም ። ''

'' ከበስተጀርባ ስላለው ሰው የምታውቀው ነገር አለ ? ''

'' አምን መገመት እችላለሁ — ተሳስቼም ይሆናል ። አምን — ተሳስቼም ይሆናል ! ''

16

ክፍል አንድ

‘‘ከሒኮሪ ጎዳና ዳካሪ፣’’አለ ኒጌል ፣‘‘አይጧ ሰዓቱን ቲሽከርካሪ ፣ ፖሊሱ ሲላት ክፍ ፣ ክፍ ፣ መጨረሻ ማን ይሆን የሚያቸንፍ ? ’’ ሲል ደመደመው ።

ትንሽ ቆይቶ እንዲህ ሲል ቀጠለ ።

‘‘ መናገር ወይንም አለመናገር ? ያ ነው ጥያቄው ! ’’

ለራሱ ትኩስ ሻይውን ቀድቶ ከቁርስ ጠረጴዛው ላይ ተቀመጠ ።

‘‘ ምን መናገር ? ’’ አለ ሊን ባትሰን ።

‘‘ ማንኛውንም እንድ ሰው ሚያውቀውን ፣ ’’ አለ ኒጌል በመጀ ነን እጁን እያወዛወዘ ።

ጀን ቶሚልሰን አስተያየቱን ባለመቀበል ፣

‘‘ በርግጥ አዎን ! ጥቅም ያለው ማንኛውም መረጃ ካለን አዎን በርግጥ ለፖሊስ መናገር ይኖርብናል ። ያ ብቻ ነው ትክክለኛው ’’ አለች ።

‘‘ በኔ በኩል በነዚህ ፖሊሶች አልስማማም ፣ ’’ አለ ሬን አስተ ያየቱን ከውይይቱ በተሳታፊነት ሲሰጥ ።

‘‘ ምን መናገር ? ’’ ሲል ሊዎናርድ ባትሰን በድጋሚ ጠየቀ ።

‘‘ የምናውቃቸውን ነገሮች ነዋ ! ’’ አለ ኒጌል ። ስለ ‘ርስበ‘ርሳ ችን የምናውቀውን ማለቱ ነው ’’ ሲል ጨመረበት ። ዓይኖቹ በምቀ ኝነት ግለው ከጠረጴዛው አርፈዋል ።

‘‘ ከሁሉም በላይ ደግሞ ፣ ’’ አለ እየተፍነከነከ ፣ ‘‘ ስለ‘ርስ - በ‘ርሳችን ብዙ ነገሮችን እናውቃለን ፣ አናውቅም ? ማለቴ እንድ ሰው አብሮ እስከኖረ ፣ በአንድ በት እስከሆነ ብዙ ያውቃል ። ’’

“ ግን ማነው ቁም ነገር ያለውንና የሌለውን ነገር መመስን ሚቻለው ? በፍጹም የፖሊስ ሥራ ያልሆኑ ብዙ ጉዳዮች አሉ ፣ ”አለ ሚስተር አህመድ ዓሊ ። ሲናገር በስሜትና ኢንስፔክተሩ ስለ ፖስት - ካርዶች የተናገረው ነገር እየታወሰው ነበር ።

“ ከመኝታህ አንድ የተለየ የሚያስገርም ነገር ማግኘታቸውን ሰምቻለሁ ፣ ” አለ ኒጌል ወደ አኪቦሎ ቦ ፊቱን መልሶ ።

ጥቁር በመሆኑ የደም ፍላቱ መልታህቱን ሲያቀላው ባይታይም ሚስተር አኪቦሎ የዓይን ቆቦቹ አንጀቱ ድብን ሲል በርግብግቢት ነዘሩ ።

“ በሀገሬ በጣም የሚሠራበት ላዕላይ - አምልኮት ነው ፣ ” አለ ። “ አያቱ ነው ከ‘ዚህ ያሥጣኋቸውን ነገሮች የሰጠኝ ። ስለ መልካም ተግባርና አክብሮት በማለት ነው ያቆየሁት ። እኔ ራሴ ዘመናዊና ሣይንሳዊ ነሆኑ ነገሮች የማምን ነኝ ። በአስማትና ምትሃት አላምንም። ነገር ግን ከቋንቋ ችግር የተነሳ ለፖሊሶቹ ለማስረዳት አልተቻለኝም።”

“ ውድ ጄን እንኳ የ‘ራሷ ሚስጥሮች እንዳሏዋት ይሰማኛል ፣ ” አለ ኒጌል ወደ ወይዘሪት ቶሚልስን ፊቱን በመመለስ ።

ጄን በንዴት መሰደብ እንደሌለባት ገለጸች ።

“ ይህን ሥፍራ ትቼ ወደ ወ.ሴ.ክ.ማ. መሔድ አለብኝ ፣ ” አለች

“ ቲይ ባክሽ ጄን ፣ ” አለ ኒጌል ። “ አንድ ተጨማሪ እድል ስጭን ። ”

“ አ ፣ በቃህ ኒጌል ! ” አለች ቫሌሪ በጭንቀት ። “ ፖሊሶች እንዲህ ባለ ሁኔታ መግባት ያለባቸው ይመስለኛል ። ”

ኮሊን ማከናብ ጉሮሮውን በሚገባ አረጣጠበው ።

“ በ‘ኔ አስተያዬት ፣ ” አለ በዳኝነት አገላለጽ ፣ “ ይህ የአሁኑ ሁኔታ ለ‘ኛ ግልጽ መሆን አለበት ። የሚስ ኒክ ሞት መንስኤ በትክክል ምን እንደነበር ማወቅ የለብንም ? ”

“ ከሬሣ ምርመራው መረዳት እንችላለን ፣ ” አለች ቫሌሪ ትዕግሥቷ ማለቁ እያስታወቀባት ።

“ እጠራጠራለሁ ” አለ ኮሊን ። “ ምርመራውን ሊሰርዙት ይችላሉ ። ”

“ ልቧ ይመስለኛል ፣ አልነበረም ? ” አለች ፖትሪሺያ ። “ ከመንገድ ላይ ወድቃ ነው የተገኘችው ” አለች እንደገና ።

“ ሠክራና መራመድ እንኳ አትቷት ነበረ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሲወ ስዷት ” አለ ሊን ባትሰን ።

“ ትጠጣለች ማለት ነው ፣ ” አለች ጂን ። “ ይገርማችኋል ሁልጊዜ እንደዚያ ብዬ አስብ ነበር ። ፖሊሶቹ ቤቱን ሲፈትሹ ከግል ክፍሏ ባዶ የብራንዲ ጠርሙስ ቁምሣጥኑን ሞልቶ ተገኘ ። እኔም አመንኩኝ ” ስትል አከለችበት ።

“ የኛይቱ ጂን ምንም እንደማያመልጥሽ ርግጠኛ ነኝ ፣ ” አለ ኒጌል በማረጋገጥ ።

“ ግን አንዳንዴ ለምን እንግዳ ባህርይ እንደምታሳይ ይህ ሊገ ልጸው አይችልም ፣ ” አለች ፖትሪሺያ ።

ኮሊን ጉሮሮውን እንደገና አረጣጠበ ።

“ እንዴ ! ሆ . . . ” አለ ። “ ቅዳሜ ማታ እኔ ወደ ቤት በመመለስ ላይ እያለሁ ርሷ ወደ ኩይንስ ኔክሌስ ስትጓዝ ነበር ። ”

“ከዛያ ነው ካፍ ጠሚ ድረስ የጠጣችው ፣ ” አለ ኒጌል ።

“ በመጠጥ ምክንያት ነው የሞተች በለኛ ? ” አለች ጂን ።

ሊን ባትሰን ራሱን ነቀነቀ ።

“ የአንጐል — አዕምረት ደም - ፍሰት ? አይመስለኝም ። ”

“ በእግዚአብሔር ! ተገድላለች ብለህ አታስብም ። አይደለም ?” አለች ጂን ።

“ ካለጥርጥር ! ” አለች ሳሊ ፊንች ። “ ምንም አያስደንቀኝም ።”

“ እባካችሁ ... ” አለ ሚስ አኪቦምቦ ። “ አንድ የሆነ ሰው ነው የገደላት ተባለ ? ትክክል ነው ? ”

ከአጠገቡ ያሉትን በሙሉ አንድ በአንድ ተመለከታቸው ።

“ እንደዚህ ዓይነቱን ነገር ለማጠናከር ምንም ማስረጃ ገና አላ ገኘንም ፣ ” አለ ኮሊን ።

“ ግን ማን ሊገድላት ይፈልጋል?” ስትል ጂኔቪይቭ ጠየቀች ። “ ብዙ ገንዘብ ምትተወው ነበረ ? ሀብታም ብትሆን የሚቻል ይመስ ለኝ ነበር ። ”

“ የምታሳብድ ሴት ናት የኔ ውድ ፣ ” አለ ኒጌል ። “ ሁሉም ሊገድላት የሚፈልግ እንደነበር ርግጠኛ ነኝ ። እኔማ ሁልጊዜ እመኝ ላት ነበር ፣ ”በማለት በደስታ እየተፍነከነከ ማርማላቱን አወጣ ።

ክፍል ሁለት

“ እባክሽ ወደዘራት ሳሊ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ እችላለሁ ? ከቁርስ በኋላ ስለተባለው ነገር ነው ። ብዙ ሳስብ ነበርኩኝ ። ”

“ እሺ ግን አንተን ብሆን ኖሮ ብዙ አስብ ነበር ፣ አኪምቦምቦ ፣” አለች ሳሊ ። እንደገና “ ጤናማ አይደለም . . . ” ስትል ተናገረች ።

ሳሊና አኪምቦምቦ ከሪጂንት ፓርክ ወጭ ተቀምጠው ምሳ ቸውን በመመገብ ላይ ናቸው ። ሞቃቱ ጊዜ መምጣቱን እያስመሰከረ ስለሆነ ሬስቶራንቱ በሰፊው ተከፍቷል ።

“ ዛሬ ማለዳውን ፡ ” አለ አኪምቦምቦ በሀዘን ፡ “ በመላ በጣም ተረብሼ ነበር ። የአስተማሪዬን ጥያቄ ለመመለስ አልተቻለኝም ። በ‘ኔ አልተደሰተም ። እ‘ሱ እንደሚለው ሁሉንም ነገር ከመድሐኒት እየቀዳሁ የማቀርበው አንጂ እኔ ከ‘ራሴ የማፈልቀው ነገር አይኖርም ። ነገር ግን እዚህ የመጣሁት ከመጽሐፍት ብዙ እውቀት ለማግኘት ነው። እንደሱማትም እኔ ከምጽፈው ይልቅ ከመጽሐፍት ያለው ሀሳብ የተሻለ ነው ። ምክንያቱም የእንግሊዝኛ ቋንቋዬ ጥሩ አይደለም ። ከዚህ በተጨማሪ ዛሬ ጠዋት ከሐኮሪ ጎዳና ካለው ችግርና ከተፈጠረው ነገር በስተቀር ምንም ማሰብ አልተቻለኝም ። ”

“በ‘ዚህ ረገድ እንኳ ትክክል ነህ ፡ ” አለች ሳሊ ። “ ዛሬ ፍጹም እኔም መማርም አልቻልኩኝ ። ”

“ እ’ኮ ስለዚያ አልነበረም አንዳንድ ነገሮችን እንድትነግሪኝ የጠየቅሁሽ ። በጣም እያሰብኩኝ ነበርኩ ። ”

“ እስኪ ምን እያሰብክ እንደነበርክ ማወቅ እፈልጋለሁ ። ”

“ ጥሩ ይህ ቦር - አ - ሲክ ነው ። ”

“ ቦር - አ - ሲክ ? እንዴ ቦሪሲክ ! አዎን ። ታዲያ ምን ሆነ ? ”

“ እኔ እንጃ በደንብ ልረዳ አልቻልኩም ። አሲድ ነው ይሉታል ? ድኝ - አሲድ (ሶልፊዮሪክ አሲድ) መሣይ ነገር ነው ? ”

“ የለም እንደ ድኝ - አሲድ አይደለም ፡ ” አለች ሳሊ ።

“ ለቤተሙከራት የሚሆን መከረት ብቻ አይደለም ? ”

“ ከቤተ - ሙክረት ምንም ዓይነት ሙክረት አድርገውበት የሚ ያውቁ አይመስለኝም ። ምንም ጉዳት የማያደርስ ፍዝ ነገር ነው ። ”

“ ማለት ከዓይንም ውስጥ ቢገባ ? ”

“ ትክክል ። እንዲያውም ጥቅሙ እንደዚያ ነው ”

“ እንግዲያውስ የምፈልገውን ነገር ተረድቻለሁ ። ሚስተር ቻን ድራ ላል ነጭ ዱቄት ያለበት ነጭ ቢልቃጥ አለው ። ዱቄቱን ከሞቀ ውሃ አድርጎ ዓይኑን ይታጠብበታል ። ሁልጊዜ የሚያኖረው ከመታ ጠቢያው ነው ። አንድ ቀን ከዚያ ሲያጣው በጣም ተናደደ ። ያ ይሆን ቦ-ር-አሲ-ክ ? ”

“ ይህ ሁሉ ስለ ቦርአሲክ ነው ? ”

“ ብዙ እነግርሻለሁ ። አሁን ግን ኡይደለም ። የበለጠ አስብበታለሁ ። ”

“ የማያገባህ ነገር ውስጥ ሁሉ ጥልቅ አትበል ። የሚቀጥለው የአንተ አስከፊ እድል እንዲሆን አልፈልግም አኪቦምቦ ። ”

ክፍል ሦስት

“ ቫሌሪ ትንሽ ምክር ልትሰጪኝ ትችያለሽ ? ”

“እንዴት ልሰጥሽ እችላለሁ ጂን ፣ ምንም እንኳ ሰዎች ለምን ምክር እንደሚፈልጉ ባላውቅም ። አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጣቸውንም አይቀበሉም ። ”

“ ይህ እንኳ የሕሊና ጉዳይ ነው ” አለች ጂን ።

“ስለዚህ በመጨረሻ ላይ አማካሪ ሲጠፉ መጠየቅ ‘ሚገባኝ ሰውነኝ ! በቃሽ ! ምንም መናገር አልችልም ተይኝ ! ። ”

“ እባክሽ ቫሌሪ እንደዚያ ዓይነት ነገር አትናገሪ ! ”

“እውነተኛ ነገር ነው ” አለች ቫሌሪ ። ይህን እየተናገረች የያዘችውን ሲጋራ ተረኮሰችው ። “ከፖሊሶች ዕቃዎችን ርመደበቅ አስገባለሁ፣ ከውበት ሳሎኑ ለሚመጡት መልክ - ጥፋ ሴቶች በጣም የሚያላሽቁ ወሬዎችን እናገራለሁ ፣ ገንዘብ በሚቸግረኝ ጊዜ ለሥራ ጉዳይ ስንዝ ሳልከፍል በማጭበርበር እጓዛለሁ ። ግን እባክሽ እስኪ ንገሪኝ ከዚህ ሁሉ ስለ ከፋው ጉዳይ ? ”

“ኒጌል ከፋርስ ላይ ስለተናገረው ጉዳይ ነው ። አንድ ሰው ስለሌላው የሆነ ሚስጥር ቢያወቅ ይህን በየቦታው መናገር ያለበት ይመስልሻል ?’

“ ምን ዓይነት ደደብ ጥያቄ ነው ! እንደዚያ ዓይነት ነገር በአጠቃላይ መልኩ ማስቀመጥ አትችይም ! ምንድነው እስኪ መነገርና አለመነገር የሚኖርበት ? ”

“ ስለ ፓስፖርት ነው ! ”

“ ፓስፖርት ? ” ቫሌሪ በጣም ተገረመች ። “ስለማን ፓስፖርት ?”

“ስለኒጌል ፓስፖርት ነው ። የሐሰት ፓስፖርት እኮ ነው ያለው ። ”

“ ኒጌል ? ” የቫሌሪ ድምጽ መጠራጠሯን ያመለክታል ። “ ማመን አልችልም ። ፍጹም የሚሆን አይመስለኝም ። ”

“ ሆኗል እንጂ ። ታውቂያለሽ ቫሌሪ ፣ አንዳንድ ጥርጣሬዎች ያሉ ይመስለኛል ። ፖሊስ ሲሊያ ስለ ፓስፖርት የሆነ ነገር ተናግራለች ሲል የሰማሁ መሰለኝ ። ”

“ ምናልባት ያንን ስላወቀችበት ገድሏት ይሆን ? ”

“ ተውኔት መሰል ነገር ነው ” አለች ቫሌሪ ። “ እውነቱን ለመ ናገር የነገርሽኝ አንድ ቃል እንኳ አላምንም ። ይህን ስለ ፓስፖርት የሚተርከውን ነገር በውነት እኖ ነሽበታል ? ”

“ አምን አይቸዋለሁ ። ”

“ እንዴት አየሽው ? ”

“ ፍጹም ያልታሰበ አጋጣሚ ነበር ” አለች ጂን ። “ የራሴን የወረቀት ሻንጣ ከአንድ ሁለት ሣምንት በፊት ለሆነ ጉዳይ ስመለከት በሥህተት የኒዬልን ሻንጣ ተመለከትኩኝ ። ሁለቱም ከጋራ አዳራሹ ከመደርደሪያው ላይ ነበሩ ። ”

ቫሌሪ ተንከተከተች ።

“ ሌላ ብይ ባክሽ ፣ ” አለቻት ። “ ምን እየሠራሽ ነበርሽ ? በቃ ዘለሽ ጥልቅ እ ? ”

“ የለም ፣ በ‘ርግጥ እንደዚያ እንኳን አላደረኩም ! ” አለች ጂን በንዴት ድምጽ ። “ አንድ በሕይወቴ ውስጥ ያላደረግሁት ነገር ቢኖር የሰዎችን የግል ሰነዶች ማየት ነበር ። እንደዚያ ዓይነትም ሰው አይደ ለሁም ። እንዳው ራሴን ስቼ ነበር መሰለኝ ፣ እና ብቻ ከፍቼ . . . በቃ ወረቀቶች መመራረጥ ጀመርኩኝ . . . ”

“ ስሚኝ እስኪ ጂን ፣ እንደዚያ ያለ ችግር ሊያጋጥምሽ አይችልም ። የኒዬል የወረቀት ሻንጣ ካንቺ በጣም ይተልቃል ። በዚህ ላይ የተለየ ቀለም ነው ያለው ። ነገሮችን ካመንሽ ያን ዓይነት ሰው መሆንሽንም መቀበል ይኖርብሻል ። እሺ መልካም ! የኒዬልን ሰነዶች እንዳጋጣሚ ለማየት እድል አገኘሽና አየሻቸው ? ”

ጂን ከተቀመጠችበት በቁጣ ተስፈንጥራ ተነሳች ።

“ በርግጥ ቫሌሪ በጣም የሚያስከፋሽ ከሆነ . . . የማትቀበ ይው ከሆነና . . . ደስ ካላለሽ . . . እሺ . . . ”

“ቀጥይ ! ቀጥይ ልጅት ! ” አለች ቫሌሪ ። “ ቀጥይ ! ነገሩን ለማወቅ አሁን በጣም ጓጉቻለሁ ፣ አውሪልኝ እባክሽ ፣ ለማወቅ እፈልጋለሁ ።”

“ደህና ይሽውልሽ ፣ ይህ ፓስፖርት ...” አለች ጂን ፣ “ከሥር ነበር ። ከላዩ ላይ የሆነ ስም አለበት ። ስታንፎርድ ነው ? ስታንሊ ? በቃ እንደ ዚያ ዓይነት ስም ነው ። ብቻ በሀሳቤ ‘ኒዬል የሌላ ሰው ፓስፖርት ይዟል ማለት እንግዳ ነገር ነው ’ በማለት ተገረምኩኝ ። ፎቶግራ ፉን ከፍቼ ስመለከተው የኒዬል ነው ! አይታይሽም ታዲያ በሁለት ስም እንደሚኖር ? ለፖሊስ ማመልከት የ‘ኔ ሀላፊነት ይመስልሻል ? ”

ቫሌሪ ከት ብላ ሣቀች ።

“ አዝናለሁ ጄን ! ” አለቻት ። “ እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ምክንያት በጣም ቀላል ነው ። ፖት አስረድታኛለች ። ኒጌል የገንዘብና የአንድ ሌላ ችግር አጋጥሞት ስለ ነበር ስሙን ቀየረው ። ብቻ በህጋዊ መንገድና በሥነ ሥርዓት ያደረገው ነገር ነው ። የመጀመሪያው ስሙ ስታንፊልድ ወይንም ስታንሊ ፣ በቃ ፣ እንደዚያ ያለ ስም ይመስለኛል ። ”

“ እንዴ ! ” በማለት ጄን ቆጣ ብላ ተመለከተቻት ።

“ ካላመንሽኝ ፖትን ጠይቂያት ” አለች ቫሌሪ ።

“ የለም ፡ አንቺ እንዳልሽው ከሆነ ስህተት የሠራሁ መሆን አለብኝ ። ”

“ በይ እንግዲህ ጊዜ መልካሙን ይግጠሞ ሽ ቫሌሪ ። ”

“ ብቻ ከኒጌል አንገት ላይ ቢላዎሽን ማጋደም ፈልገሽ ነበር ! አልነበረም ? በፖሊስ ልታስይዥው ? ”

ጄን ከመቀመጫዋ ተነሳች ።

“ ልታምኚኝ አትችይም ቫሌሪ ፡ በቃ ተይው ፡ ” አለች ! “ ዋናው ነገር እኔ የምፈልገው ሥራዬን መሥራት ብቻ ነው ወዳጄ ። ”

ከፍሉን ለቃ ወጣች ።

“ ገደል ግቢ ! ” አለች ቫሌሪ ።

በሩ ተንኳኳ ። ሳሊ ገባች ።

“ጉዳዩ ምንድነው ቫሌሪ ? ምነው ከንፈርሽን አንዘረበብሽው ? ”

“ ያቺ አምላክ የተጣላት ጄን አናዳኝ ነው ። አደገኛ ሰው ናት ! ይህችን ምስኪን ሴሊያን የደፋቻት ጄን ለመሆኗ ትንሽም ጥርጣሬ የለኝ ! ጄን ከወንጀል ሳጥኑ ከፍርድ ቤት ገብታ ባያት የሚሰማኝን ደስታ ልገልጽልሽ አልችልም ። ”

“ እኔም አንዳንቺው ነኝ ” አለች ሳሊ ። “ ነገር ግን እንደዚያ የሚሆን አይመስለኝም ። ጄን ማንንም ለመግደል የሚያስችል ቆራጥነት ያላት አይመስለኝም ። ”

“ ስለ ሚስ ኒክስ ምን ታስቢያለሽ ? ”

“ ምን እንደማስብ እንኳ አላውቅም ፡ ይገርምሻል ። ነገር ግን ሁሉንም ነገር በቅርቡ የምንረዳ ይመስለኛል ። ”

“እርሷንም ቢሆን እንደዚሁ ደፍተዋት ነው፡አትጠራጠሪ!”አለች ቫሌሪ

“እስኪ ለምን ብለው ? እንዲያው ከዚህ ሥፍራ ምን እየተካ ሔደ ይሆን? ” አለች ሳሊ ።

“ ባውቅ ኖሮ ደስ ባለኝ ። ግን እንዴት ሳሊ ዘወትር ሰዎችን ተጠራጥሮ ይዘለቃል ? ” አለች ።

“ምን ማለትሽ ነው ቫል ሰዎችን ተጠራጥሮ ይዘለቃል ስትይ?”

“እገሌ ነው ፣እገሌ ነው በማለት ማሰላሰልና ማሰብ ማለቴ ነው። አለ አይደል ‘አንተ ትሆን?’ ማለት ነገር ። አንድ ስሜት አለኝ ሳሊ። ከዚህ ሥፍራ የሆነ እብድ ያለ ይመስለኛል ። እውነተኛ እብድ ሰው ። ክፉ ጨካኝ ሰው ፣ ማለቴ ነው ። እኝህ ሰዎች’ኮ ዱባ አይደሉም ! እየ ተቀረደዱ የሚጣሉ ነገሮች . . . ”

“ እንደዚያ ማሰቡ የተሻለ ነው ” አለች ሳሊ ሰውነቷ እየተዘ ገነነ ።

“ ተይኝ ! ብቻ የሆነ ሰው ወደ አስከፊ አዘቅት እያመራ ነው ። በጣም ይሰቀጥጣል ። ”

ክፍል አራት

“ ኂጌል እንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ ። ”

“ ጥሩ ፣ ምን ነበር ፖት? ” ኂጌል በብስጭትና ተስፋ በመቁረጥ ከመሣቢያዎቹ ያተራምሳል ። “ እንዴ! ጽሑፎቼን በሙሉ የት አገባኋቸው ? እዚህ የከተትኳቸው መስሎኝ ነበር ። ”

“ እንደዚያ አትበል! ሁሉንም ነገር የትም ወርውረኽው ነበር። እኔ ነኝ አስተካክዬ ያስቀመጥኩልህ ። ”

“ ምንድነው የምትይኝ ወረቀቶቼን መፈለግ የለብኝም ? ”

“ ኂጌል ፣ የምልህን በመጀመሪያ መስማት አለብህ ! ”

“ እሺ ፖት ተስፋ አትቁረጭ ፣ አትናደጅ ! ምንድነው ?”

“ አንድ ለአንተ መናገር ‘ሚገባኝ ነገር አለ ። ”

“ ስለግድያ ወንጀል አይመስለኝም? ወይስ ነው?” አለ ኂጌል በተለመደ አገላለጹ ።

“ የለም፣ በእውነት እንደዚያ እንኳ አይደለም ። ”

“ መልካም ። ከዚህ ያነሰ ታዲያ ምን ዓይነት ሐጢአት ሊሆን ነው ? ”

“ አንድ ቀን ነበር ያየሁት ።በዚያ የ‘ግር ሹራብህን ሰፋፍቼ ከክፍልህ በማምጣት ከመሳቢያህ ውስጥ በአስቀመጥኩበት ቀን . . . ”

“ እናስ ? ”

“ አንድ የሞርፊያ ቢልቃጥ ከ‘ዚያ ሥፍራ ነበር ። ከሆስፒታል አገኘሁት ብለህ የነገርከኝን ማለቴ ነው ። ”

“ እና ስለዚህ መጨነቅ ጀመርሽ ! ”

“ ግን‘ኮ ኂጌል ያስቀመጥከው ከመሣቢያው ውስጥ ከ‘ግር ሹራቦችህ መካከል ማንም ሊያገኘው ከሚችልበት ሥፍራ ነበር ። ”

“ ማንም ለምን ብሎ ? ካንቺ በስተቀር ከግር ሹራቦቼ አካባቢ የሚደርስ ሰው ፈጽሞ የለም! ሊኖርም አይችልም ! ”

‘‘ ጥሩ ! እንደዚያ የትም ወርውሮ መተው ጥሩ ሥራ አይመስለ ኝም። በዚህ ላይ ደግሞ ውርርድህን ከጨረስክ በኋላ እንደዎ ታስወግ ደው ነግረኸኝ ነበር ። ምንም ርዎጃ አልወሰድክም ፣ ግን ከዚያው ተቀምጠ ቆየ ። ’’

‘‘በርግጥ አላነሳሁትም ። ገና ሦስተኛውንም አላገኘሁም ነበር ።’’

‘‘ መልካም ፣ በጣም ሥህተት መስሎ ታየኝ ። ስለዚህ ቢልቃጡን ከመሣቢያው ወስጀ መርዙን ካወጣሁት በኋላ በተራ የሶዳ ባይካር ቦኔት መልሼ ሞላሁት ። ሁለቱም በትክክል ይመሳሰላሉ ። ’’

ኒጌል ጽሑፎቹን ለመፈላለግ መፈባበሹን እቋረጠ ።

‘‘ መሀሪው አምላክ ! እውነትሽን ነው የምታወሪው ? ለሊንና ለኮ ሊን ‘መድሐኒቱ ሞርፊን ሶልፌት ነው ወይንም ታርታሬት ወይንም የሆነ ነገር’ እያልኩ ስምል ስገዘት በቃ ተራ የሶዳ ባይካርቦኔት ነበራ ! ይህን ሁሉ ጊዜ ? ’’

‘‘ አዎን አየሀ . . . ’’

ኒጌል አቋረጣት ። ቅንድቦቹን ሰበሰበ ። በበለጠም ተኮሳተረ ።

‘‘እንዲያ መሆኑ ውርርዱን በፍጹም አላፋረሰውም ታውቂያለሽ? ርግጠ ኛ አልነበርኩማ። እንዲህ ይሆናል የሚል ምንም ሀሳብ አልነበረኝም።’’

‘‘ ግን እኮ ኒጌል ከዚያ ሥፍራ ማስቀመጡ በጣም አደገኛ ነበር ። ’’

‘‘ ያንት ያለህ ! ፖት ሁልጊዜ እንደዚህ መጨነቅ ይኖርብ ሻል ማለት ነው ? ለመሆኑ ምን አደረግሽው ? ’’

‘‘ ከሶዳባይካርቦኔት ጠርሙስ አድርጌ ከመሀረብ መሣቢያዬ አስቀመጥኩት ። ’’

ኒጌል በመገረም ተመለከታት ።

‘‘ በ‘ውነት ፖት ለምትሠሪው ሥራ ሁሉ ምክንያት ያስፈልገዋል! ለመሆኑ እንደዚህ ያደረግሽው ለምን ነበር ? ’’

‘‘ ከዚያ ቢቀመጥ የተሻለ ስለ መሰለኝ ነው ። ’’

‘‘ የኔ ወለላ ፣ ሞርፊያው ከቁም ሣጥኑ ተቆለፈም አልተቆለፈ ፣ ከእኔ የእግር ሹራቤ ላይ ሆነ ካንቺ መሀረቦች መካከል የሚያመ ጣው ችግር አልነረበም ። ’’

‘‘እንዴ ለምን አያመጣም ? እኔ ለራሴ ለብቻዬ ክፍል ሲኖረኝ አንተ ግን ብቻህን አይደለህም ። ’’

‘‘ ለምን ሞርፊያውን ይሠርቀዋል ብለሽ አላሰብሽም ነበር ሊን፣ ወይንስ ፖሊሶች ያጮልጓታል ብለሽ ነው ? ’’

‘‘ የለም ፣ ከዚያ በፊት ነው የጠፋው ። ’’

‘‘ ስትይ . . . ? ’’ በማለት ኒጌል በንዴት ፊቱ ተለዋውጦ ጠየቃት ። ‘‘ ግልጽ እናድርገው ። አንድ ሶዳባይክ የሚል መለያ ያለበት ቢልቃጥ ሞርፊን ሶልፌት የያዘ አለ ። ይህ ቢልቃጥ ከሆነ አንድ ሥፍራ ላይ ተቀምጧል ። በማናቸውም ጊዜ አንድ የሆነ ሰው ከሆነ ሥፍራ ላይ ቢታመም አንድ የሻይ ማንኪያ ሊያፍስለት ይችላል ። አይችልም ? መሀሪው አምላክ ! ፖት ! በቃ አደረግሽው ማለት እኮ ነው ! በነገሩ በጣም ከተጨነቅሽበት መድሐኒቱን ለምን የትም ሥፍራ ወረወርሽው ታዲያ ? እስኪ ንገሪኝ ? ’’

‘‘ ምክንያቱም ፣ ውድ ነው ብዬ ስላሰብኩኝ ከመጣል ይልቅ ወደ ሆስፒታል ቢመለስ የተሻለ ይሆናል ብዬ ነው ። ውርርድህን እንዳሸነፍክ ለሴሊያ ሰጥቻት ወደ ሆስፒታል ልመልሰው አስቤ ነበር ። ’’

‘‘ ለኦርሷ አለመስጠትሽን አውንስ ቢሆን ርግጠኛ ነሽ ? ’’

‘‘የለም፣በእውነት አይደለም።ማለት የፈለከው እኔ መድሐኒቱን ሰጥቻት ራሷን ገደለች ነው ። ስለዚህ በእጠቃላይ የአንቺ ጥፋት ነው አይደል ?’’

‘‘ እስኪ ረጋ በይ ! ሊመሆኑ መቼ ነው የጠፋው ? ’’

‘‘ በትክክል እንኳ አላስታውስም ። ሴሊያ ከመሞቷ አንድ ቀን አስቀድሜ ከሥፍራው ፈልጌው ነበር ። ነገር ግን ማግኘት አልቻልኩም ። ምናልባት ከአንድ ሌላ ሥፍራ አስቀምጨው ይሆናል ብዬ አሰብኩኝ ። ’’

‘‘ ከመሞቷ አንድ ቀን አስቀድሞ ነበር የጠፋው ? ’’

‘‘ ይመስለኛል ’’ አለች ፖትሪሺያ ፊቷ በድንጋጤ ነጥቶ ። በርግጥ ‘‘ በጣም ደደብ ነኝ ! ’’

‘‘ ይህ እንኳ ትህትናና ጨዋነት ነው ! ’’ አለ ኒጌል ። ‘‘ ለመሆኑ የጨቀየ ጭንቅላትና አዙሮ የሚያይ ሕሊና ለምን ያህል ጊዜ ይሆን አብረው መጓዝ የሚችሉት ? ይገርማል ! ’’

‘‘ ኒጌል ! ለፖሊስ መናገር ያለብኝ ይመስልሃል ? ’’

“ አምን ፣ ገደል ግቢ ! ” አለ ኂጌል በቁጣ ። “ አምን ፣ እንደዚያ ይመስለኛል ! ግን የኔው ጥፋት ነው ። ”

“ የለም ፣ የኔ ወለላ ኂጌል ፣ እኔ ነኝ ጥፋተኛዋ ። እኔ ራሴ ... ” ’

“ በመጀመሪያ ይህን የተረገመ መድሐኒት የሠረቅሁት እኔ ነኝ ” አለ ኂጌል ፡ “ በወቅቱ ውርርዱ የሁሉንም ቀልብ ሚስብ ነገር ሆኖ ነበር ። አሁን ግን ከየሥፍራው የሆነ ያልሆነ ተቃውሞ እየሰማሁ ነኝ ። ’

“ አዝናለሁ ! በወሰድከት ወቅት ለ ... ”

“ ለደህና ነገር ነበር ። አውቃለሁ ! አስቢ እስኪ ፖት ፣ መርዙ ጠፋ የሚለውን ጉዳይ ማመን አልችልም ። የት እንዳስቀመጥሽው ረስተሽዋል ። እንዳንዴም ዕቃዎችም አሳስተሽ ካልሆነ ቦታ ታስ ቀምጫለሽ ። ”

“ አምን ግን — ”

አመነታታች ፣ ከአሻቀበው ቅንድቧ ጥርጣሬ ይነበብበታል ።

ኂጌል በችኮላ ከነበረበት ሥፍራ ተንቀሳቀሰ ።

“ በይ ወደ መኝታ ቤትሽ እንሒድና በደንብ እንፈልግ ?” አላት ።

ክፍል አምስት

“ ኒጌል ! እነዚህ የውስጥ ልብሶቼ ናቸው ። ”

“ በ‘ውነት ! ፖት እንዲህ እያስፈራራሽ ልትጫወችቢኝ አት ችያም ! ቢልቃጡን የደበቅሽው ከፖንቶችሽ ነበር ፣ እንደዚያ አይደ ለም ? ”

“ አዎን ፡ ግን እኔ ርግጠኛ መሆኔን . . . ”

“ ከሁሉም ሥፍራ ሳንፈልግ ርግጠኞች መሆን አንችልም ። እኔ እንኳ አንድ በአንድ ቤቱን ለመፈተሽ ቆርጨ ነው የመጣሁት ።”

ከበሩ ላይ በግድየለሽነት ሲንኳኳ ይሰማል ። ወዲያው ሳሊ ፊንች ገባች። ዓይኖቿ በእግርሞት በሰፊው ተከፈቱ ፣ አፈጠጠች። ፖት በእጅዋ ሙሉ የኒጌልን የግር ሹራብ ይዛ ከአልጋዋ ላይ ተቀምጣለች ። ኒጌል የጠረጴዛውን መሣቢያ አውጥቶ በአንዳች ነገር ፍርሃትና ጥርጣሬ እንደገባው ድንክ ውሻ ሁሉ ከተከመረው ዳንቴልና ሻሽ ይመለካከ ታል ። ከላዩ ላይ ግን የተበታተኑ የሴት ፖንቶች ፣ የጡት መያዣዎች፣ የ‘ግር ሹራቦችና ሌሎችም የሴቶች የበዓላት ልብሶች አሉበት ።

“ ስለእግዚአብሔር ከ‘ዚህ ሥፍራ ምን እየተካሔደ ነው ያለው ? ”

“ ባይካርቦኔት እየፈለግን ነው ” አለ ኒጌል በአጭሩ ።

“ ባይካርቦኔት ? ለምን ? ”

“ አሞኛል ” አለ ኒጌል ፈገግ ብሎ ። “ አንድ ሥፍራ ላይ አሞ ኛል ከ‘ርሱ በስተቀር የህመም ስሜቴን የሚቀንስልኝ ምንም ነገር የለም ” አላት ።

“ ብቻ አንድ ሥፍራ ትንሽ ማግኘት እንደምችል ርግጠኛ ነኝ ። ”

“ አይሆነኝም ሳሊ ። የፖት ብቻ ነው የሚስማማኝ ። ይህን ልዩ የሆነ ቁርጥማቴን ሊያስታግስልኝ የሚችል ብቸኛ መድሐኒት ይኼ ልዩ መለያ ያለው ባይካርቦኔት ነው ። ”

“ እብድ ነህ ! ” አለች ሳሊ ። “ ምንድነው ፖት የሚለው ? ”

ፖትሪሺያ ራሷን በብስጭት ነቀነቀች ።

“ ሶዳ ባያኪን አይተሻል ሳሊ ? ” ስትል ጠየቀቻት ። “ከቢል ታጡ ትንሽ የቀረ ነበር ። ”

“ የለም አላየሁም ። ” አለችና ሳሊ በጥርጣሬ ተመለከተቻቸው ። ግንባሯን ኮሰተረችው ። “ እስኪ ለማስታወስ ልሞክር ። የሆነ ሰው ከዚህ ሥፍራ ነበር ? የለም ፣ አላስታውስም — ፖት ቴምብር ይኖርሽ ይሆን ? ደብዳቤ ለመላክ ፈልጌ ነበር ፣ ነገር ግን የለኝም ። ”

“ ከዛያ ሥፍራ ከመጣቢያው አለልሽ ። ”

ሳሊ ትንሿን የጽሕፈት - ጠረጴዛ መጣቢያ ተመለከተች ። ከውስጥ የቴምብር ስብስብ አወጣች ፣ አንዱን ቆረጠችና ከደብዳቤው ለጥፋ ከእጅዋ ያዘችው ። ከተጠቀመችበት በኋላ የቴምብሩን ስብስብ ከመጣቢያው መለሰችው ። ከደስኩ ላይ የሀ ለት ተኩል ሣንቲሞች ዝርዝር አስቀመጠች ።

“ አመሰግናለሁ ፣ ይህንንም ደብዳቤሽን በአንድነት ልላከው ? ’

“ አዎን ፣ ግንተይው ይሁን ፣ ትንሽ የሚቆይ መስሎ ይታየኛል ።”

ሳሊ ራሷን በመነቅነቅ ክፍሉን ለቃ ወጣች ።

ፖት የያዘችውን የ‘ግር ሹራቦች በመጣል ጣቶቿን ፍርክርክ ስርታ በብስጭትና በሀዘን ገፅታ ተቀመጠች ።

“ ኒጌል ? ”

“ አቤት ! ” ኒጌል ከልብስ ቁምሣጥኑ ካሉት ኮቶች ኪሶች በመ ፈታተሽ ላይ ነበር ።

“ አንዳች ለመናገር የምፈልገው ነገር ነበረኝ ። ”

“ ያንተ ያለህ ! ፖት ምን ነገር ልታመጪ ይሆን ደግሞ ? ”

“ የለም ! ትናያዳለህ ብዬ ፈርቼ ነው ። ”

“ባለፈው ተናድጄ ወጥቶልኛል። አሁን ግን ያለብኝ ፍርሃት ነው። ሴሊያ የነ መረዘችው እኔ በሠረቅሁት መድሐኒት ከሆነ ለዓመታት ከእሥር ቤት እቆያለሁ ብዬ እፈራለሁ። ባልሰቀልም እንኳ ያ አይቀርልኝም።”

“ከዚያ በፍጹም የተያያዘ አይደለም ። ስለ አባትህ ነው ።”

“ ለምን ! ” አለና ኒጌል የሽሙጥ መደነቅ ከፊቱ አሳየ ።

“ በጣም መታመማቸውን ታውቃለህ ? አታውቅም ? ”

“ የፈለገውን ያህልም ቢታመም ግድ የለኝ ! ”

“ በሬዲዮ ትላንት ማታ ስለተነገረ ነበር ። ‘ ሰር እርተስ ስታንሊ የታወቁት የቅመማ ሊቅ በአስከፊ ሁኔታ ተኝተው በመታመም ላይ ናቸው ’ ይላል ። ኒጌል የሚሞቱ ከሆነ መታረቅ ይኖርብሃል ። ”

“ እየተሰቃየ ነው ! እሺ እታረቃለሁ ! ”

“ ግን የሚሞቱ ከሆነ . . . ”

“ ያው ጤነኛም ሆኖ እንደነበረው ፣ ሲሞትም ጨካኝ አውሬ እንደሆነ ነው ! ”

“ እንደዚያ መሆን የለብህም ኒጌል ። እንዲህ መመረርና ርህራሔ የሌለህ ሰው መሆን ያለብህ አይመስለኝም ። ”

“ ስሚ ፖት — አንድ ጊዜ ነግሬሻለሁ ። እናቴን ገድሎብኛል ።”

“አዎን ፣ ብለህኝ ነበር ፣ እናትህንም እንደምትወዳቸው አውቃለሁ። ነገር ግን ኒጌል ፣ አንዳንዴ ከተገቢው በላይ ታጋንናለህ ። ብዙዎቹ ባሎች ብዙውን ጊዜ በጣም ጨካኝና ምንም ስሜት የሌላቸው ናቸው ። ይህንን ሚስቶቻቸው ከመቃወማቸውም በላይ ሀዘነተኞችም ናቸው ። ነገር ግን እናትህን አባትህ ገደሏቸው ብሎ መናገሩ ከመጠን ያለፈ ብልግና ከመሆኑም በላይ መሠረተቢስ ወሬ ነው ! ”

“ ስለዚህ ብዙ የምታውቂ ይመስለኛል ። አይደለም ? ”

“ አባትህ ከመሞታቸው በፊት አለመታረቅህ ይቆጭሃል ። ስለዚያ ነው . . . ” አለች ። ትንሽ ዝም ብላ ራሷን ካጠናከረች በኋላም ፣

“ ለዚህ ብዬ ነው — ለአባትህ ጽፌ ልነግራቸው . . . ”

“ ጽፈሽለታል ? ያንን ደብዳቤ ነው ሳሊ ልትልከው የነበረው ?” ወደ ጽሕፈት ጠረጴዛው ተቻኮለ ። “ ገባኝ ፤ አወቅኩልሽ ! ” አለ ።

አድራሻ ተጽፎበት ቴምብር የተለጠፈበትን ደብዳቤ አነሳው ። በተቻኮሉና የሚንቀጠቀጡ ጣቶቹ ወዲያው ቀዳድዶ በታተነውና ከወረቀት ቅርጫቱ ከተተው ።

“ በቃ ! ያ ነው ! እንደዚያ ዓይነቱን ነገር ሁለተኛ አትሞክሪ ! ”

“ በውነት ነው የምልህ ኒጌል ፣ ፍጹም ሀጻን ነህ ! ደብዳቤውን መቅደድ ትችላለህ ። ነገር ግን ሌላ ደብዳቤ ከመጻፍ ልትከለከለኝ አትችልም ! ደግሞ እጽፋለሁ ! ታያለህ ! ”

“ በሽታሽ ረመዳን የማይችል የስሜት ሰው ነሽ ! እንዳው አባቴ እናቴን ገድሏታል ብዬ ስነግርሽ ትንሽም አይሰማሽ ? ምንም ያልተ ሸፋፈነ እውነተኛና ግልጽ ነገር ነው የነገርኩሽ።እናቴ ከመጠን በላይ መድሐኒት ተሰጥቷት ነው የሞተች ። በምርመራ ወቅት በሥህተት ነው የወሰደችው ብለው መለሱ። ነገር ግን ሥህተት አልነበረም ። በአ ባቴ ሆነ ተብሎ የተሰጣት ነበር ። ሌላ ሴት ለማግባት ስለፈለገ ነበር። እናቴ ግን የፍቺ . . .

“ በጣም አዝናለሁ ኒጌል . . . ፍጹም እንዲህ ይሆናል ብዬ አላለምኩም . . . ”

“ መልካም ፣ አሁን በሚገባ ተረድተሽዋል . . . የተከበረውንና የታወቀውን አርተር ስታንሊ ከምርምሮቹና ከጸረ - ባክቴሪያዎቹ ጋር ሰሙ እንደ ሰማይ ሥትር ረጅም አረንጓዴ ዛፍ ወጥቶ የነበረው ሰው ግን ያቺ ፍቅረኛውን አላገባትም ። ሽተት አለች ። ነገ በኔ ብላ አሰበች ። ”

“ ውድ ኒጌል ፣ እንዴት የሚያስፈራ ነገር ነው ! በጣም ነው ያዘንኩት . . . ” አለች ።

“ ጥሩ ነው ። ሁለተኛ ስለዚህ ጉዳይ አናነሳም ። በይ አሁን ይህን የተረገመ ባይካርቦኔት ፍለጋችንን እንቀጥል ። አሁን እስኪ በት ከክል ምን እንዳደረግሽበት ለማስታወስ ሞክሪ ? ራስሽን ከእጅችሽ ደፍተሽ እስቢ ፖት . . . ”

ክፍል ሰድስት

ጀኔቬየቭ ከጋራ አዳራሹ ፊቷ ተለዋውጦ ገባች ። አንድ ላይ የነ በሩትን ተማሪዎች ዝቅ ባለና በማስቀጥጥ ደምጽ አነጋገረቻቸው ።

“ አሁን ርግጠኛ ነኝ ! ሴሊያን ማን እንደገደላት በሚገባ አውቄአለሁ ! ” አለች ።

“ ማን ነበር ጀኔቬየቭ ? ” አላት ሬን ። ቀጥሎም “ ምን ማስረጃ ኖሮሽ ነው ይህን እንድትናገሪ ያበቃሽ ? ” አላት ።

ጀኔቬየቭ በጥንቃቄ የጋራ አዳራሹ በር መዘጋቱን ተመለከ ተች ። ድምጿንም ቀነሰችው ።

“ ኒጌል ቻፕማን ነው ! ”

“ ኒጌል ቻፕማን ? ማን ለምን ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ ስሙ እስኪ ! አሁን በመተላለፊያው አድርጌ ወደ ታች ደረ ጃውን ለመውረድ ስመጣ ከፖትሪሺያ ክፍል ድምጽ ሰማሁኝ ። ቀረብ ብዬ ሳደምጥ የሚናገረውም ሰው ኒጌል ነበር ። ”

“ ኒጌል ? ከፖትሪሺያ ክፍል ? ” ጂን ባላመነ ሰው አነጋገር ጠየቀች ። ግን ጀኔቬየቭ ወሬዋን ቀጠለች ።

“ አባቱ እናቱን እንደገደሉ ነበር የሚያወራት። ሌላም ነገር . . . ከዚያም ስሙን እንደ ቀየረ አንዳንድ ነገሮች ጠቀቀሰ ። ይህ ደግሞ ግልጽ ጉዳይ ነው ! አይደለም ? አባቱ ነፍሰ ገዳይ ከሆኑ ልጁ ደግሞ የዚህ መጥፎ ባህርይ የደም - ውርስ አለው ማለት ነው። ”

“ሊሆን ይችላል ! ” አለ ሚስተር ቻንድራ ላል የተናገረችውን በደስታ በማጠናከር ፣ ቀጥሎም “ ያለጥርጥር ሊሆን ይችላል ። በጣም ጠብ ወዳድ ነው ። ኒጌል አመለካከቱ ያልተስተካከለና ራሱን መቆ ጣጠር ማይችል ሰው ነው ። ትስማማላችሁ ? ” በማለት ወደ አኪ ቦምቦ በመዞር ሲመለከት እሱም በመደነቅ ያን ጥቁር ብሩሽ መሳይ ጸጉር ራሱን በመነቅነቅ በደስታ ተውጦ ነጭ ጥርሱን ፈለቀቀ ።

“ ሁልጊዜም ቢሆን ይህ ስሜት በጣም ነው የሚሰማኝ ” አለች ጄን ። ቀጥላም “ኒጌል ምንም የርህራሔና የአርቆ ማሰብ ስሜት የለ ውም . . . በቃ! የላሸቀ ፣ የሸቀ ባህርይ ነው ያለው ” አለች ።

“ ወሲባዊ ግድያ ነው ” አለ ሚስተር አህመድ አሊ ። “ እንደ ሚመስለኝ ይቺን ልጅ አብሯት ያተኛና ነው የሚገድላት ፣ ምክን ያቱም ጥሩና የተከበረች ልጅ ስለሆነች ጋብቻ ለመፈጸም ወደ ፊት ትጠብቃለች በማለት ይሆናል ..”

“ በስባሳ ! ” አለ ሊዎናርድ ባትሰን ድምጹን ከፍ አድርጎ ።

“ ምንድነው ያልከው ? ”

“ በስባሳ ! ነው ያልኩት ” ሲል ሊን አንቧረቀ ።

CITY - ከተማ
OF
ADDIS ABABA

17

ክፍል አንድ

ከፖሊስ ጣቢያው ተቀምጦ ኒጌል የኢንስፔክተር ሻርፕን ባለ ግርማ ዓይኖች በመቅበጥበጥ እየተመለከተ ነው ። ግራ በተጋባ ሁኔታ ቆም ፣ ረገጥ በማድረግ ንግግሩን ወደ ማገባያዱ ተታርቧል ።

"የነገርከን ጉዳይ በጣም አሳሳቢ መሆኑን ተገንዝበሃል ሚስተር ቻፕማን ? እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው ። "

" በርግጥ ተገንዝቤዋለሁ ። አስቸኳይ ጉዳይ ባይሆን እስከዚህ ድረስ መጥቼ ፍጹም አልናገርም ነበር ። "

" እንዳልከን ወይዘሪት ሌን ይህን ሞርፊን የያዘውን የባይ ካር ቦኔት ቢልታጥ መቼ እንዳየችው በትክክል አታስታውስም ነበር ? "

"እርሷም ራሷ በጣም ግራ ተጋብታለች ። የበለጠ ለማሰብ በሞከረች ቁጥር የበለጠ ርግጠኛ አለመሆኗ ይሰማታል ። አንተ ነህ ግራ ያጋባሽኝ ነው የምትለው ። ወደ እናንተ ስመጣም በጸጥታ ለማስታወስ በመሞከር ላይ ነበረች ። "

" አሁኑኑ ወደ ሒኮሪ ጎዳና ብንሔድ መልካም ነው ። "

ኢንስፔክተሩ እየተናገረ እያለ ከጠረጴዛው ያለው ስልክ አንቃጨለ ። የኒጌልን ቃል በመቀበል ላይ የነበረው የፖሊስ ሀላፊ እጁን በመዘርጋት ስልኩን አነሳ ።

" ወይዘሪት ሌን ናት ፡ " አለ ወዲያው ድምጽ እንደሰማ ። "ሚስተር ቻፕ ማንን ማነጋገር ትፈልጋለች ። "

ኒጌል ከጠረጴዛው አግድም በመንጠራራት መነጋገሪያውን ተቀበለው ።

" ፖት ? ኒጌል ነኝ ! "

የልጂቱ ድምጽ ትንፋሽ እያጠረውና ቃላት በቃላት ላይ እየተነባበረ ስትናገር ይሰማል ። " ኒጌል ! ያገኘሁት ይመስለኛል ! ማለቴ አሁን ማን እንደወሰደው አውቄ ያለሁ . . . ታውቃለህ . . . ከመሀረቤ መሳቢያ ነው የተወሰደው ፣ ማለቴ . . . ታውቃለህ ፣ አንድ ሰው ብቻ ነው . . . "

ድምጹ ተቋረጠ ።

" ፖት ? ሀሎ ! ትሰሚኛለሽ ? ማን ነበር ? "

" አሁን ልነግርህ አልችልም ። በኋላ ትመጣ የለ ? "

መነጋገሪያው ለፖሊስ ሀላፊውና ለኢንስፔክተሩ በጣም ቅርብ ስለሆነ ጥርት ብሎ ይሰማል ። ለኒጌል የመጠይቅ አስተያዬት ኢንስፔክተሩ ራሱን በመነቅነቅ መልስ ሰጠ ።

" ንገራት አሁኑኑ እንደርሳለን ! " አለ ።

" አሁኑኑ መምጣታችን ነው ፣ " አለ ኒጌል ። " በዚህች ደቂቃ ውስጥ መንገድ ላይ ነን ። "

" መሀሪው አምላክ ! እዚሁ ከክፍሌ ውስጥ ነኝ ። "

" እስከዚያው ፖት . . . "

ወደ ሒኮሪ ጎዳና ሲደረግ በነበረው አጭር ጉዞ ላይ ቃል እንኳ የተነፈሰ አልነበረም ። ሻርፕ ይህ መጨረሻው ይሆን እያለ በማንሰላሰል ላይ ነበር ። ፖትሪሺያ ሌን ልትሰጥ የምትችለው ማስረጃ ይኖር ይሆን ወይንስ የራሷ ግምት ? በግልጽ ለርሷ ከፍተኛ ቁም ነገር መስሎ የታያት አንድ ነገር አስታውሳ ይሆናል ። ከአዳራሹ ሆና እንደደወለችና የምትናገረውን ነገር ሚያዳምጥባት ሰው መኖሩን አሰበ ። በዚህን የምሽት ወቅት ብዙ ሰዎች ይተላለፉበት ይሆናል ።

ኒጌል የቁጥር 26 ሒኮሪ ጎዳናን በር በራሱ ቁልፍ ከፍቶት ወደ ውስጥ ዘልቀው ገቡ ። በጋራ - አዳራሹ የተከፈተ በር አሾልቆ ሻርፕ የሌዎናርድ ባትሰንን ያልተበጠረ ራስ ከመጽሐፍ አቀርቅሮ ተመለከተው ።

ኒጌል ወደ ላይ ይዟቸው ወጥቶ ከመተላለፊያው ሲደርስ ወደ ፖት ክፍል ቀጠለ ። በዝቅተኛ ድምጽ በማንኳኳት ወደ ውስጥ ከፍቶ ገባ ።

" ታዲያስ ፖት ? መጣን — "

ንግግሩን በመካከል አቋረጠው ። ሳግ አፈነው ። ያለ ምንም እንቅስቃሴ ተደፖሞ ቆመ ። ከትከሻው ሻርፕ መታየት የሚቻለውን ነገር ለማየት ችሏል ።

ፖትሪሺያ ሌን ከወለሉ ተደፍታለች ።

ኢንስፔክተሩ ኒጌልን በርጋታ ወደ ጎን አደረገው ። ወደፊት በመሔድ ከልጅቱ ከርቻችት ያለ ሰውነት አጠገብ ተንበረከከ ። ራሷንም ቀና አደ ረገው ፣ ትርታዋን አዳመጠ በጥንቃቄ ራሷን ከመጀመሪያ ሥፍራውላይ አኖረው ። በጎግሩ ተነስቶ ቆመ ። ፊቱን ሀዘን ውጦታል ፣ ደምኗል ።

“ የለችም ? ” አለ ኒጌል ድፃ ጹ ከወትሮው ይልቅ ተቀይሮ “ የለችም ! የለችም ! የለችም ! ”

“ አዎን፣ ሚስተር ቻፕማን ሞታለች!” አለ ድፃ ዉን ከፍ አድርጎ።

“የለም ! የለም ... ፖት አትሞትም ! ውድና የዋኋ ፖት ! እን ዴት ብለሽ ? ”

“ በ’ዚህ ነው ! ”

ለማጥቃት በጣም ቀላል ነበር። በአካባቢው በተገኘ ሙሣሪያ ነው የተገ ደለች ው። ወረቀቶቹ እንዳይበታተኑ ከበስተላይ የተደረገው መጫኛ እብ ነበረድ ነው ። እንዲያመች ከሱፍ የጎግር ሹራብ ውስጥ ተከቷል ።

“ ከኋላ ጭንቅላቷን ነው የመታት ። ቃንም አፍታ የማያቆይ መሣሪያ ነው ። የምነግርህ አንድ ነገር ቢኖር ሚስተር ቻፕማን ም ን እንደደረሰባት እንኳ ራሷም የምታውቀው አይመስለኝም ። ”

ኒጌል በሀዘን ተጨብጦ ከአልጋው ተቀመጠ ።

“ ከጎግር ሹራቦቹ አንዱ ነበር . . . ልትጠጋግነው አስባ ነበር ... አቤቱ አምላኬ ልትሰፋፋልኝ ነበር . . . ”

ማልቀሱን ቀጠለ ። ሲያለቅስ እንደ ሕጻን ልጅ ነበር ። እንባ ውን እንደዝናብ ነበር የሚዘራው ። ራሱንም ጨርሶ አያውቀውም ነበር ።

ሻርፕ የሁኔታዎችን ቅደምተከተል በማያያዝ ላይ ነበር ።

“ አንድ በደንብ የምታውቀው ሰው ነበር ። አንድ የሆነ ሰው እብነበረዱን ከጎግር ሹራቡ ውስጥ ከቶት ነው ! ። ታየዋለህ የወረ ቀት መጫኛውን እብነበረድ ሚስተር ቻፕማን ? ”

እብነበረዱን ለማሳየት የግር ሹራቡን ገፈፈው ።

ኒጌል አሁንም እያለቀሰ ተመለከተው ።

“ ፖት ሁልጊዜ ከዴስኳ የምታስቀምጠው እብነበረድ ነው።”

ከእጆቹ ላይ ፊቱን ቀበረው ።

“ፖት ... ወየው ፖት ! ካላንቺ ብቻየን ም ን ማድረግ እችላለሁ!”

ያን ያልተበጠረ ጸጉሩን ወደ ኋላ በመንነስነስ ቀጥ ብሎ ቁጭ አለ ።

“ አዎን ማንም ይሁን ማን ይህን ሥራ የሠራውን ሰው እገድ ለዋለሁ ! እገድለዋለሁ ! ይህን ነፍሰ-ገዳይ አውሬ አልምረውም ! ”

“ አይዞህ ረጋ በል ሚስቲር ቻፕማን ። አዎን ፣ አዎን ፖን ያህል እንደሚሰማህ ይገባኛል ። ”

“ ፖት ማንንም ጎድታ አታውቅም ኮ . . . ”

በማባበልና በማጽናናት እያግባባው ኢንስፔክተር ሻርፕ ከክፍሉ አወጣው ። ከዚያ ተመልሶ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። ከልጅቱ በድን አጠገብ ቆመ ። በጥንቃቄና በቀስታ ከጣቶቿ መካከል የሆነ ነገር አላቀቀ ።

ክፍል ሁለት

ከጀሮኒሞ ግንባር ላቡ እንደዝናብ ይወርዳል ። በፍርሃት የተጠበቡ ጥቂቱር ዓይኖቹን ከአንዱ ፊት ወደ ሌላው ያንቀዠቅዠዋል ።

“ ምንም አላየሁ . . . ምንም አልሰማሁ . . . እውነቴን ነው የምላችሁ፣ ፍጹም ምንም ነገር አላውቅም። ከማርያ ዘንድ ከወጥበቱ ነበርኩኝ . . . ሚኒስትሮኑን ጥጄ ዓይቡን ስለውሰው ነበርኩኝ . . .”

ዝርዝሩን ሻርፕ አቋረጠው ።

“ ማንም አልከሰሰህም አንተን ። ስለጊዜው ለማረጋገጥ ፈልገን ነው ይግባህ ! በመጨረሻው ሰዓት ላይ ወደ በት የገባውና የወጣውን ሰው ታውቃለህ ? ”

“ አላውቅም ። እንዴት ማወቅ እችላለሁ ? ”

“ ነገር ግን ’ኮ በቀላሉና በግልጽ ወጪና ገቢውን በወጥ - ቤቱ መስኩት መሰልከት ትችላለህ ። አትችልም ? ”

“ እ . . . ምናልባት አምን ። ”

“ በላ ንገረን ። ”

“ በዚህ ሰዓት ሁልጊዜ ይወጣሉ ይገባሉ ። ”

“ ከአሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ አሥራ ሁለት ተኩል እኛ እስከደረስንበት ከቤቱ ውስጥ የቀረ ማን ነበር ? ”

“ ከሚስተር ኒጌል፣ ሚስ ሀበርድና፣ ሚስ ሆብሐውስ በስተቀር ሁሉም ሰው ነበረ ። ”

“ መቼ ነበር እነ’ሱ የወጡት ? ”

“ ሚስ ሀበርድ ከሻይ ጊዜ በፊት ወጥታ እስካሁንም አልተመለሰች ። ”

“ እሺ ቀጥል ። ”

“ ሚስተር ኒጌል ከግማሽ ሰዓት በፊት ነው የወጣው ። ከአሥራ ሁለት ሰዓት በፊት ነበር ። ሳየው በጣም የተበሳጨ ይመስላል ። ከወጣ ይኸው አሁን አብሯችሁ መመለሱ ነው ። ”

“ አምን ትክክል ነህ ። ”

“ ወይዘሪት ቫሌሪ በአሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ነው የወጣችው ። ምልክት ፒፕ ! ፒፕ ! ፒፕ ! አለ ። በጣም ቱውባ ለኮክቴል ለብሳ ነበር ። አሁንም አልተመለሰችም ። ”

“ የተቀሩትስ ከዚህ ናቸው ? ”

“ አዎን ጌታዬ ! ሁሉም ከዚሁ ናቸው ።”

ሻርፕ ማስታወሻውን ተመለከተ ። ፖትሪሺያ የተጠራችበት ሰዓት ከማስታወሻው ሰፍሮ ነበር ። አሥራ ሁለት ሰዓት ከስምንት ደቂቃ ይላል ።

“ ሁሉም ሰው ከቢት ነበር ፣ በዚያን ጊዜ የተመለሰ አልነበረም ?”

“ ወይዘሪት ሳሊ ብቻ ናት ። ከፖስታ ሣጥኑ ደብዳቤ ይዛ ወርዳ እንደገና ተመለሰች —”

“ በስንት ሰዓት እንደተመለሰች ታውቃለህ ? ”

ጆሮኒም ቅንድቦቹን ሰበሰበ ።

“ ወሬው በመሰራጨት ላይ እያለ ነበር የደረሰችው ። ”

“ በአሥራ ሁለት ሰዓት ነበራ ? ”

“ አዎን ጌታዬ ። ”

“ እየተወራ የነበረው ስለምን ነበር ? ”

“ አላስታውሰውም ጌታዬ ። ነገር ግን ከስፖርቱ ፕሮግራም በፊት ነበር ። ዘወትር ስፖርት ሲተላለፍ ነው እኛ ምንዘጋው ። ”

ሻርፕ የቅሬታ ሣቅ ፈገግ አለ ። በጣም ሰፊ ሥራ ይጠብቃቸዋል ። ኒጌል ቻፕማን ፣ ቫሌሪ ሆብሐውሳ ፣ ሚስ ሀበርድ ሊገለሉ ይችላሉ ። በጣም አድካሚና ረጅም ምርመራ መሆኑ ነው ። ከጋራ - አዳራሹ ማን ነበረ ፣ ማን ለቀቀ ? ጣቹ ? ማን ለማን ይመሰክራል ? በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች እስያዊያኑና አፍሪካዊያኑ ወደ ውጭ ስለሚዝኑባቸውና ስለሚንከላወሱባቸው ጊዜያት በደንብ አያስታውሱም ። ይህ ተግባር በቅንዓትና ጥላቻም ላይ መመሥረት የለበትም ።

ያም ሆነ ይህ መሠራት አይኖርበትም ።

ክፍል ሦስት

ከሚስ ሀበርድ ክፍል የነበረው አየር የሀዘን ጠል አጥልቷል ። ሚስ ሀበርድ ራሷ በውጭ መውጪያ ልብሶቿ ተውባ ያ ተወዳጅ ፊቷ በጭንቀት ተወጥሮና በጥርጣሬና ፍርሃት ተዋከቦ ከሶፋው ላይ ተቀምጣለች ። ሻርፕና የሃምሳ አለቃ ኮብ ከትንሽ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀምጠዋል ።

“ ከዚህ የደወለች ይመስለኛል ፣ ” አለ ሻርፕ ። “ በአሥራ ሁለት ሰዓት ከስምንት ደቂቃ አካባቢ ብዙ ሰዎች ከጋራ - አዳራሹ ገብተዋል ። ማንም ሰው የአዳራሹ ስልክ ከጥቅም ላይ ሲውል ያየም የሰማም የለ ሊሉንም ይችላሉ ። በርግጥ የነሱ ጊዜ እንኳ የምንተማመንበት አይደለም ። ከነዚህ ሰዎች ግማሽ ያህሉ ሰዓታቸውን የሚያዩ አይመስሉም ። ብቻ በማንኛውም መንገድ ከፖሊስ ጣቢያው ለመደወል ከፈለገች እዚህ ነው ምትመጣው ። ሚስ ሀበርድ ከውጭ ነበርሽ ። ብትወጪም መዝጊያሽን ምትቆልፊ አይመስለኝም ። አይደለም ? ”

ሜስ ሀበርድ ራሷን ነቀነቀች ።

“ ሚስ ኒኮሊተስ ሁልጊዜ እንደዚያ ታደርግ ነበር ። እኔ ግን አድርጌም አላውቅ — ”

“ ፖትሪሺያ ሌን ያስታወሰችውን ሁሉ በጉጉት ለመናገር ስልክ ለመደወል ምትመጣው ከዚህ ነው ። እየተናገረች ባለችበት ወቅት በሩ ተከፍቶ ስለነበር አንድ ሰው ወደ ውስጥ ይመለከታል ፣ ወይንም ይገባል ። ፖትሪሺያ ለመናገር ስላልቻለች መነጋገሪያውን ከሥፍራው ትመልሳለች ። ምናልባት ያን ያቋረጣትን ሰው ልትናገረው የነበረው ሰው ስም መሆኑን በማወቋ ይሆን ያቋረጠችው ? ወይንስ አጠቃላይ ጥንቃቄ ለማድረግ ? ሁለቱም ሊሆን ይችላል ። እኔ ግን ወደ መጀመሪያው መላምት እዘነብላለሁ ። ”

ሚስ ሀበርድ ሀሳቡን በመቀበል ራሷን ነቀነቀች ።

“ እስከዚህ የተከተላት ማንም ይሁን ማን ምናልባት ከውጭ ሆኖ ሊያዳምጣት ይችል ይሆናል ።ከዚያም ፖት ጨርሳ ልትወጣ ስትል ወደ ውስጥ ገብቶ ሊያቆማት ይችላል ። ”

“ ከዚያስ ? ”

የቫርኮ ፊት ጽልመቱን ለበሰ ። “ ያ ሰው ከፖትሪሺያ ክፍል አብሯት በመሔድ እንደጨነኛ ሰውና እንደ ጓደኛ ያነጋግራታል ። ምናልባት ፖትሪሺያ ባይካርቦኔቱ የት እንደተወሰደ አጥብቃ ስት ጠይቅ ተጠያቂዋ ወገን የማስመሰል መልስ ሰጥታት ሊሆን ይች ላል ። ”

ሜስ ሀበርድ ኮስተር ብላ ፣

“ ለምንድነው ‘እሷ’ ብለህ ምትናገረው ? ” አለች ።

“ የሚገርም ነው ፤ ተውላጠ ስም ነው ! አስከሬኗን ባገኘነው ጊዜ ኒጌል ቻፕማን ማንም ይሁን ማን ይህን ሥራ የሠራውን ሰው ገድለዋለሁ ! ገድለዋለሁ ! ነበር ያለው ። አየሽ ? ‘እሱ’ ነበር ብሎ የጠራው ። ኔጌሉ ቻፕማን ግድያው የተፈጸመው በወንድ ነው የሚል እም ነት ነበረው ። ምክንያቱም የሀይልን ሀሳብ ያያያዘው ከወ ንድ ስለነበረ ነው ። ምናልባት ከአንድ ወንድ ላይ ልዩ ጥርጥሬ ስለነ በረውም ይሆናል ። ይህን ም ን እንዳሳሰበውም ማወቅ ይገባናል ። እኔ ግን ስናገር ሴት እንደሆነች አድርጌ ነው ። ”

“ ለምን ? ”

“ በቃ እንደዚሁ ። አንድ ሴት አብራት ከፖትሪሺያ ክፍል ገባች። አንድ በጣም የቃ ትግባባት ሴት ማለቴ ነው ። ይህ ሁኔታ ሊያመለክተን ሚችለው እንዲቷን ወይዘሪት ነው ። ወንዶቹ ለእንዳች ልዩ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ወደ ሴቶቹ መኝታ ክፍሎች አይሔዱም ። ትክ ክል ነኝ ። አይደለሁም ሚስ ሀበርድ ? ”

“ አዎን ። ይህ ሕግ እንኳ አጥብቆ የሚሠራ አይደለም ። አጠ ቃላይ በሆነ መልኩ የሚታይ ነው ።”

“ የቤቱ ሌላኛውን ወገን ከዚህኛው ወገን የተለየ ነው ከም ድሩ ወለል በስተቀር ። የኒጌልና የፖት ውይይት ተደምጦ ነበር ብለን ብናስብ ልታዳም ት ችችለው በማንኛውም መንገድ ሴት ብቻ ናት ። ”

“ አዎን ። ምን ማለት እንደፈለግህ ገብቶኛል ። አንዳንዶቹ ልጃገረዶች ግማሽ ጊዜያቸውን ሚያሳልፉት የቁልፍ ቀዳዳዎች ላይ ጆሮአቸውን ለጥፈው ነው ።”

ፊቷ ቀላ ። በትህትና እንዲህ ስትል አከለችበት ።

“ ያ ደግሞ በጣም መጨቆን ይሆናል ። ብቻ እነዚህ ቢቶች ም ንም እንኳ በጥንካሬ ቢገነቡም የተከፋፋፈና የተቆራረጡ ናቸው ። እነ

ዚህ አዳዲሶቹ ግርዶሾች በጣም ስለ ከመሆናቸውም በላይ እንደ ወረ ቀት ናቸው ። በውስጥ ድምጽ መስማት ይቻላል ። ጄን ብዙ ጊዜ እን ዲህ ያለ የማዳመጥ ሥራ ትወዳለች ። በቃ አፈጣጠሯ ነው ። በመንገድ ላይ እንዳለች በርግጥ ጄኔቬይቭ ኒጌል ለፖት አባቱ እናቱን እንደገ ደሉ ሲናገር ቆማ ማዳመጧ የማይካድ ነው ። ''

ኢንስፔክተሩ ራሱን ነቀነቀ ። ሳሊ ፊንችንና የጄን ቶሚል ሰንን እንዲሁም የጄኔቬይቭን የምሥክርነት ቃል ሰምቷል ።

'' ከፖትሪሺያ በሁለቱም በኩል ያሉትን ክፍሎች የያዙዋቸው እነማን ናቸው ? '' ሲል ጠየቀ ።

'' ጄኔቬይቭ ከበላይ ናት ። የ'ርሷ ግን አብሮ የተሠራ የግንብ ግድግዳ ነው ። ከሌላኛው በኩል የሃ ትኖረው ኤልሳቤጥ ጆሀንስተን ናት ። ከደረጃዎቹ አጠገብ ማለት ነው ። ያ ተራ ፣ የተቆራረጠ ፣ በኋላ ላይ የተሠራ መለያ ግድግዳ ነው ። ''

'' አዎን ትንሽ ያጠብበዋል ፣ '' አለ ኢንስፔክተሩ ።

''ፈረንሣይቱ ልጃገረድ የሰማችው የውይይቱን መጨረሻ ነው ። ሳሊ ፊንች ይብዳቢዋን ለመክተት ቀደም ብላ ነበር የወጣችው ። ነገር ግን የ'ነዚህ ሁለት ልጃገረዶች ከ'ዚያ መኖር ማንንም ወሬ ለመስማት ሚያስፈስፍ ሰው መገኘት ያስወግዳል ። ለአጭር ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ማለቴ ነው ። ከኤልሳቤጥ ጆሀንስተን በስተቀር ከመኝታ ክፍሉ ብትኖር ሌላ ማን ማዳመጥ ይችል ነበር ። በስሱ ግድግዳ ማለቴ ነው ። ነገር ግን ከጋራ - አዳራሹ መሆኗ ፣ ሳሊ ፊንች ወደ ፖስታው በሔደችበት ሰዓት ጉዳዩን ግልጽ ያደርገዋል ። ''

'' ከጋራ - አዳራሹ አልቆየችም ነበር ? ''

'' የለም አንድ የረሣችውን መጽሐፍ ለመውሰድ እንደገና ወደ ላይ ወጥታ ነበር ። ያው እንደቸለመደው ማንም ቢሆን እንዲህ ባለ ጊዜ ብሎ መናገር አይችልም ። ''

'' አንዳቸው ሊሆኑ ይችላሉ ፣ '' አለች ሚስ ሀበርድ ምትናገረው ጨንቋት ተስፋ በመቁረጥ ።

''እንደተናገሩት ከሆነ አዎን — ነገር ግን ትንሽ ተጨማሪ መረጃ አግኝተናል ። ''

አንዲት ትንሽ የታጠፈች የወረቀት ፓኬት ከኪሱ አወጣ ።

'' ምንድነው ? '' አለች ሚስ ሀበርድ ።

ሻርፕ ፈገግ አለ ።

“ ጥንድ ጸጉሮች ናቸው ። ከፖትሪሺያ ሌን ጣቶች መካከል የወ ለድኩት ነው ። ”

“ ምትለኝ . . . ”

በሩ ተንኳኳ ።

“ ይግቡ ! ” አለ ኢንስፔክተሩ ።

በሩ ሲከፈት ሚስተር አኪቦዎ ገባ ። ከበር መልስ ፈገግታ ውን ከዘያ ጥቁር ፊቱ አድምቆታል ።

“ እባካችሁ ፣ ” አለ ።

“ አበት ሚስተር አም ፣ ምንድነው ? ” አለ በችኮላ ኢንስፔ ክተር ሻርፕ ።

“ እንደማስበው ፣ እባካችሁ አንድ መስጠት የሚገባኝ ቃል አለ። አሳዛኝና አስከፊ ሁኔታዎችን ለማብራራት በመጀመሪያ ደረጃ የሚ ታይ ቁም ነገር ነው ” የያዝኩት አለ ።

18

“ በል እስኪ ሚስተር አኪቦምኮ ፣ ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ያለ አንዳች ተቃውሞ ፣ “ የያዝከው ጉዳይ ምን እንደሆነ እንስማዋ ! ”

ለሚስተር አኪምቦምቦ ወንበር ቀረበለት ። በጉጉት ከሚያዩት ሰዎች ፊት ለፊት ነበር የተቀመጠው ።

“ አመሰግናለሁ ። ልቀጥል ? ”

“ አዎን ይቻላል ። ”

“ መልካም ፣ አንዳች ነገር ከሆዴ ውስጥ መረበሽ ከጀመረኝ ትንሽ ጊዜ ቆይቷል ። ”

“ እንዴት ? ”

“ ሆዴን አሞኝ ነበር ። እንደዚያ ነው ወይዘሪት ሳሊ የምትለው። ነገር ግን እንደምታዩት አልታመምኩም ፣ አላስታወኩም ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ እነዚህ የህክምና ዝርዝር ጉዳዮች እስኪ ብራሩ እንደምንም ጠበቀ ።

“ አዎን ፣ አዎን ፣ ” አለ ። “ በጣም አዝናለሁ ፣ እውነቴን ነው ። ግን ዋናውን ቁም ነገር እንድትነግረን ያስፈልጋል — ” ።

“ ምናልባት ያለመድኩት ምግብ ሆኖብኝ ይሆናል ። ከዚህ ሥፍራ በጣም የሞላ ይመስለኛል ። ” ሚስተር አኪምቦምቦ ሥፍራውን በ‘ጁ አመለከታቸው ። “ለኔ ግን ሚስማኝ በቂ ሥጋ ካለማ ግኘትና ብዙ ይኼ ካርዶሀይድሬት ምትሉት ነገር ከመውሰድ ይመስለኛል ” አለ ።

“ካርቦሀይድሬት ማለትህ ነው ? ” ሲል ኢንስፔክተሩ አረመውና “ ግን እኔ አይመስለኝም — ” አለ ።

“ አንዳንዴ ትናንሽ እንክብሎች የሶዳ እንስላል ወይንም አልፎ አልፎ የሆድ ዱቄት (ፓውደር) እወስዳለሁኝ ። ምን የመሆኑ ጉዳይ አይደለም ትልቁ ችግር ። መቀመጫ መከዳ የሚያህል አየር ይወ

ጣኛል - እንደዚህ . . . '' ሚስተር አኪቦምቦ በጣም የሚከብድ ግሳት አገሣ ። '' ከዚያ በኋላ ፣ '' አለ ልክ በውበትና በደስታ ፣ '' በጣም ይሻለኛል ፣ በእጅጉ ይሻለኛል '' አለ ።

የኢንስፔክተሩ ፊት በደም ፍላት ወደ ሐምራዊ ተለም ተቀየረ ። ሚስ ሀበርድ በበላይነት መንፈሥ ፣

''ያ ሁላችንም ገብቶናል ። በል ሁለተኛውን ክፍል ቀጥል ''አለችው ።

'' እሞን ። በትክክል ። እንዳልኩት ይህ የጀመረኝ አስቀድሞ ባለ ፈው ማታ ንት ነበረ ። ተኑን በትክክል አላስታውሰውም ። በጣም ጥሩ ማካሮኒ ስለነበረ እኔም ብዙ በላሁ ። ከዚያ በኋላ በጣም አሙመኝ ። ለፕሮፌሰሬ ሥራ ሶመሥራት ሞክርኩኝ። ነገር ግን ሆዴ እንደዚህ ሞልቶ ማሰብ አልቻልኩም ። (አኪቦምቦ እንደገና ሆዱን በጣቱ አመ ለከተ ።) ከ'ራት በኋላ ከጋራ - አዳራሽ ተቀምጠን ነበር ። ኤልሳቤጥ ብቻ ነበረች ። እኔም ባክሽን ባይካርቦኔት ወይንም የሆድ ፖውደር እንዳለሽ እኔ የራሴን ስለጨረስኩኝ ነው ፣ አልኳት ። እ'ፏም ፣ ' የለኝም ' ፣ አለ ችኝና ፣ ቀጥላም ፣ ' አንድ የተዋስኳትን መሀረብ ስመልስ ከፖት መሣ ቢያ ጥቂት አይቼ ነበር ። አመጣልሃለሁ ። ፖትግድ የላትም ፣ ' አለችኝ ። ከዚያ በኋላ ወደ ላይ በመውጣት የሶዳ ባይ ካርቦኔት ጠርሙስ ይዛ ተመ ለሰች ። በጣም ትንሽ ነበር የቀረው ። በግምት ከቂጡ ላይ ነበር ። በቃ ባዶ ነበረ ማለት ይቻላል ። አመሰግኛት ወደ መታጠቢያ ቤቱ ይዤው ሔድኩኝ ። አንድ የሻይ ማንኪያ ያህል ነበር ። ሁለቱንም አደባልቄ ጠጣሁት ። ''

'' አንድ ሻይ ማንኪያ ? አንድ የሻይ ማንኪያ ! ያንተ ያለህ ! ''

ኢንስፔክተሩ በመደነቅና በመገረም ይመለከተዋል ። የሃምሳ አለቃ ኮብ በአግራሞት ገጽታ ከጠረጴዛው አሰገገ ። ሚስ ሀበርድ በተደበቀ አንዳች ከበድ ያለ ስሜት ፣

'' ልባሴ — ሥጋ ጅብድ ይቅ.ል ይኼ ነው ! ያንተ ያለህ ! '' አለች ።

'' አንድ የሻይ ማንኪያ ሞርፊያ ዋጥክ ? ''

'' እኔ ባይካርቦኔት ነው ሚመስለኝ ። ''

'' ገባኝ ፣ ገባኝ ። ነገር ግን ያልገባኝ አሁን ከዚህ ሥፍራ ለም ንድነው የተቀመጥከው ! ''

'' በቃ ከዚያ ታመምኩኝ ። እውነቴን ነው ታምሜ ነበርኩ ። የሆድ መቀርተት ብቻ ሳይሆን አንዳች የህመም ስሜት ከሆዴ ውስጥ ይሰማኛል ። ''

“ ግራ ሚገባውና ያልተረዳሁት ግን እንዴት ሶመሞት ያሶመቻ ልህን ነው ። ”

“ልባሴ-ሥጋ ጀብድ ይሏል ይኼ ነው!” አለች ሚስ ሀበርድ። “መር ዙን እየደጋገሙ ሰጥተውታል ፣ ስለተለማመደው አልገደለውም !”

አኪቦምቦ ንግግሩን ቀጠለ ።

“ በነጋታው ሲሻለኝ ጠርሙሱንና የቀረኝን ትንሽ ፖውደር ይዤ ከቀማሚው ዘንድ በመሔድ ይህን መድሐኒት ወስጄው በጣም ሆዴን ስላመመኝ ፃ ንነቱን እንድትነግረኝ አልኩት ። ”

“ እናስ ? ”

“ ‘በኋላ እንድትመጣና’ አለኝና።‘አይድነቅህ! ይህ ባይካርቦኔት አይደለም ። ቦሪ - ሲክ ነው ። ቦራሲክ አሲድ ። ከዓይኖችህ ልታደ ደርገው ትችላለህ ። አዎን ። ነገር ግን አንድ የሻይ ማንኪያ ከዋጥክ እንደትታመም ያደርግሀል ’ አለኝ ” አለ ።

“ ቦራሲክ ? ” አለ ኢስርፔክተሩ ግራ በመጋባት እየተመለከ ተው ። “ ግን ፣ ቦራሲኩ እንዴት ከጠርሙሱ ሊገባ ቻለ ? ሞርፊያው ምን ሆነ ?” ቦረጅሙ ተነፈሰና በንዴት “ ጥምብ — ርኩሱ የወጣ ጉዳይ ! ” ሲል ተናገረ ።

“ እያሰብኩኝ ነበርኩ ። ገባችሁ ? ” ሲል አኪቦምቦ ቀጠለ ።

“እያሰብክ ነበርክ!” አለ ሻርፕ።“ፃን ነበር ስታስብ የነበርከው?”

“ ሳስብ የነበርኩት ወይዘሪት ሴሊያ እንዴት እንደሞተች ነበር ። እ‘ሷ ከሞተች በኋላ አንድ ሰው ከክፍሏ በመግባት ባዶውን የሞርፊያ ቢልቃጥና ራሷን ገደለች ሚለውን ቁራጭ ወረቀት ጥሎ ሙውጣቱን ነበር — ” ።

አኪምቦምቦ ዝም ሲል ኢንስፔክተሩ ራሱን ነቀነቀ ።

“ እና ለ‘ራሴ ማንነው እንደዚያ ሊያደርግ የሚችል ? ብዬ ጥያቄ አቀረብኩኝ ። እንደሚመስለኝ ከልጃገረዶቹ አንዷ ብትሆን የቀ ለለ ይሆናል ። ለወንዶቹ ትንሽ ይከብዳል ። ወንድ ከሆነ ከወንዶቹ መኖሪያ ቤት ከሌላኛው ሀንዳ ከጋራ ወለሉ ለመግባት ደረጃውን መው ረድ ይኖርበታል ። ከላይ ከእንቅልፍ ነቅቶ አንድ ሰው ሊያዳምጠው ይችላል ብዬ ገመትኩ ። ከ‘ኛ መኖሪያ ከሆነ ከወይዘሪት ሴሊያ በሚ ቀጥለው ክፍል ሆነ እንጅ ገባችሁ ? እ‘ሷ ያለችው ከወዲያኛው ቤት ነው ። ከወንዶቹ ቤት መስኩት ደግሞ በረንዳ አለ ። ከ‘ርሷም መስ

ኩት እንዲሁ በረንዳ አለ ። በዚህ ላይ ለጤንነቷ በማሰብ መስኩቷን ከፍታ ልትተኛ ትችላለች ። ስለዚህ ደህና ሰውነት ያለውና አትሌቲክ አካል ያለው ጠንካራ ሰው ከሆነ ዘሎ መግባት ይቻለዋል ብዬ አስባለሁ ። ''

'' ወዲያኛው በት በኩል ከሴሊያ ክፍል ቀጥሎ ያለ ክፍል ፣'' አለች ሚስ ሀበርድ ። '' ቆይ እስኪ ፣ የኔጌል — እና የ. . . ''

'' የሊን ባትሰን ነው ፣ '' አለ ኢንስፔክተሩ ። በጣቱ ከእጁ ያለውን የተጣጠፈ ወረቀት እየነካ ። '' ሊን ባትሰን '' አለ በድጋሚ ።

'' በጣም ጥሩ ሰው ነው አዎን ፣ '' አለ አኪቦምቦ በሀዘን ። ''ለኔ በተለይ በጣም ጥሩ ወዳጄ ነው ። ነገር ግን በሳይኮሎጂያዊ አስተሳሰብ ከከፍተኛ ሥፍራ ያለውን ነገር ማንም ማወቅ አይቻለውም ። ይህ ነው ጉዳዩ ፣ አይደለም ? ይህ ዘመናዊ ንድፈ-ሀሳብ ነው ። ሚስ ተር ቻንድራ ላል ለዓይኑ ሚጠቀምበት ቦራሲክ ሲጠፋበት በጣም ብስጭት ተሰምቶት ነበር ። በኋላ ግን ስጠይቀው በሊን ባትሰን መወሰዱ እንደተነገረው ነገረኝ . . . ''

'' ሞርፊያው ከኒጌል መጣቢያ ተወሰዶ በፖትኩ ቦራሲክ ተተክቶበት ነበር ። ከዚያ ፖትሪሺያ ሌን መጥታ እ'ሷ ሞርፊያ ነው ብላ ባሰበችው በውነት ግን ቦራሲክ ፓውደር በነበረው ምትክ ሶዳ ባይካርቦኔቱን ቀየረችው . . . ገባኝ . . . ገባኝ . . . ''

'' ረድቻችኋለሁ አይደል ? '' አለ አኪቦምቦ በትሕትና ።

'' አዎን በጣም ባለውለተኞችን ነህ ። ስለዚህ ጉዳይ ምንም ፍንጭ እንዳታወጣ ። ''

'' የለም ጌታዬ ። በጣም ጠንቃቃ ሰው ነኝ ። ''

ሚስተር አኪቦምቦ በትህትና እጅ በመንሳት ክፍሉን ለቆ ወጣ ።

'' ሊን ባትሰን ፣ '' አለች ሚስ ሀበርድ በሀዘንና ተስፋ በቆረጠ ድምጽ ። '' እንዴ ? የለም ! ''

ሻርፕ ተመለከታት ።

'' ሊን ባትሰን መሆኑን አትፈልጊም ? ''

'' ያን ልጅ ወደዋለሁ ። በርግጥ ንዴተኛ ነው አውቃለሁ ። ነገር ግን ምንጊዜም ጥሩ ልጅ ነው ሚመስለኝ ። ''

'' ለአያሌ የተረገሙ ወንጀለኞች እንደዚህ ተብሎ ተወርቶላቸው ነበር '' አለ ሻርፕ ።

በርጋታ የያዛትን ትንሽ የወረቀት ፖኬት ዘረጋት ። በጥቅሻ ያመ ለከታት ስለገባት ሚስ ሀበርድ ሊመመልከት ወደፊት አስገገች ። ከነጭ ወረቀት ላይ ሁለት ቀይ አጫጭር ሉጫ ጸጉሮች ነበሩ . . .

‘‘ ወይኔ ! የኔ ወለላ ! ’’ አለች ሚስ ሀበርድ በሀዘን ።

‘‘ አዎን ፥ ’’ አለ ሻርፕ ያለፈ ልፎ ዱን እያስታወሰ ። ‘‘ከልምድ እንዳገኘሁት ነፍስ - ገዳይ ሁልጊዜ አንድ ሥህተት መሥራቱ የማይ ቀር ነው ’’ ሲል ተናገረ ።

19

ክፍል አንድ

“ ግን‘ኮ ወዳጄ በጣም ውብ ነው ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት በአድናቆት ። “ በጣም ግልጽ - እጅግ በውበት የጠራ ። ”

“ ስለ ሾርባ የምታወራ ይመስላል ፣ ” አለ ኢንስፔክተሩ ። “ ለአንተ ንጹህ ጠንከር ያለ የሾርባ ሥጋ ሊሆንልህ ይችላል! ... ለ‘ኔ ግን ዶሮ ማታ ሆኖብኛል ። ”

“ አሁን ግን አይደለም።ሁሉም እንደየወቅቱና ቦታው ነው ።”

“ እንደዚህ እንኳ . . . ”

ለሚስ ሀበርድ እንዳደረገው ሁሉ ኢንስፔክተር ሻርፕ እነዚያን ሁለት ቀያይ ጸጉሮች አውጥቶ አሳየው ።

የፖይሮት መልስ ሻርፕ ከተጠቀመበት ቃል የተለየ አልነበረም።

“ አህ! አዎን ፣ ” አለ ፖይሮት ። “ በሬዲዮ ምንድነው እ’ሱ ምትሉት ? ሆነ ተብሎ ሚሠራ ሥህተት ነው? ”

የሁለቱም ዐይኖች ተገጣጠሙ ።

“ ማንም ሰው ፣ ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ፣ “እ’ሱ እንደሚያስበው ብልህ የሆነ የለም ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ ‘ሔርኩሌ ፖይሮትም እንኳ ቢሆን ?’ ለማለት ቃጥቶት ነበር ግን ራሱን አመቀው ።

“ ለሌላኛውስ ጊዜው ቀጠሮ ተይዞለታል ? ”

“ አዎን ነገ ፊኛው ሚመጥቅበት ቀን ነው ፤ ”

“ ራስህ ነህ ምትመጥቀው ?፤ ”

“ የለም እኔ ፕሮግራም የተያዘልኝ ከቁጥር 26 ሒኮሪ ጎዳና ነው ፤ ሀላፊነቱ የኮብ ነው ። ”

የግድ ሆኖበት ሔርኩሌ ፖይሮት ብርጭቆውን አነሳ ። ከሪም ደ ሜንት ይዟል ።

ኢንስፔክተር ሻርፕ የዊስኪውን ብርጭቆ አነሳ ። “ ለመልካም ምኞት ! ” አለ ።

ክፍል ሁለት

"እንዲህ ዓይነቶቹ ሥፍራዎች አቤት ማሳመሩን ሲያውቁበት፣" አለ የሃ፫ ሳ አለቃ ኮብ ።

የሳብሪናን የተንጣለለ የናሙና ዕቃዎች በጉጉትና በአድናቆት ይመለከታል ። በጣም ውድ በሆነ የባለመሥታወት-ኪነጥበብ ዙሪያዋን ቲቀንብባ ተሸሞንሙናለች ። በአረንጓዴው መርዕይ ሳይሆን አስቲላ ላፊ ሞገድ ሳብሪና በጣም በከፍተኛ ጥራት የተሠራ የውስጥ ልብስ ቁምጣ ብቻ ለብሳ በደስታ በተለያዩ የታሸጉ መዋቢያዎች አሸብርቃ አምራ በጎን ቲጋድማለች ። ከፖንቱ በተጨማሪ የተለያዩ የጥንታዊ ባህላዊ ጌጣጌጦችን አጊጣለች ።

ሥውር ወንጀል ተከታታዩ የፖሊስ ሀላፊ አለመስማማቱን በንቀት ምልክት አመለከተ ።

" ርግምት ብዬዋለሁ ! ሳብሪና ሚልቲን ነው ። እንደዚያ ነው ..."

" ሚልቲን እኮ መጽሐፍ ቅዱስ አይደለም ወዳጄ ። "

"ያበቀላት ገነት ! ስለ አዳምና ሔዋን ስለ ኤደን የአትክልት ሥፍራና ስለ ሞላ ሠይጣን ገሃነም አይደለም ብለህ ትክዳለህ ! ታዲያ ምን ሊሆን ነው ? "

የሃምሳ አለቃ ኮብ ከነዚህ አወዛጋቢ ክርክሮች ውስጥ አልገባም ነበር ። በቆራጥነት ወደ ድርጅቱ ተጓዘ ። ይህን ቆፍጣና የፖሊስ ሀላፊ ሚመልሰው ነገር የለም ። ከጓንጉልማው ሐምራዊ የሳብሪና መደብር የሃምሳ አለቃና ቲከታዩ ችሎታና ጥንቃቄ ከሚፈለግበት ሥፍራ ላይ ቁጣ እንደሚቀናው ክፉ ሰው መስለው ታዩ ።

አንዲት ይህ ቀረሽ የማትባል ሐምራዊ ውብ ዐሣ መሳይ ሴት እየ ሩን እየቀዘፈች መጣች ። እግሮቿ ወለሉን የሚነኩትም አይመስሉም ።

የሃምሳ አለቃ ኮብ፣ "እመቤት እንደምን አድረሻል?" በማለት ሰላምታ ከሶጣት በኋላ ደብዳቤውን አሳያት ። ውቧ ፍጡር ቲመልሳ ሌላይቱ በውበት ምትስተካከላት ነገር ግን ትንሽ ከ'ሷ ጠና ምትል ፍጡር ብቅ አለች ። በተራዋ የከተሜ መሥፍኒት የፈገግታ ጮራ

ጸዳል ከዳር ዳር በመልቀቅ ያን ግራጫ ጸጉሯንና እንደ እንጉዳይ የለሰለሱ ጉንጮቿን በፈገግታዋ በሠራችው ገጽታ አስዋበችው ።

“ ይህ ፍጹም ያልተለመደ ነገር ነው ፣ ” አለች እመቤቲቱ ኮስ ተር ብላ ። “ ካላችሁ ግን እሺ ተከተሉኝ ። ”

ከአንድ አራት ማዕዘን ሳሎን ከመካከሉ ጋዜጦችና መጽሔቶች በግድየለሽነት ከተከመሩበት ክብ ጠረጴዛ መራቻቸው ። ግድግዳዎቹ ዙሪያቸውን ተጋርደዋል ። በመጋረጃዎቹ አሾልቆ ሚመልከት ሚቻለው በኒያ ቀልጣፋ እጆቻቸው ሐምራዊ ካባዎችን የደረቡት ሴት ቀሳውስት በጀርባቸው የተንጋለሉትን ወይዛዝርት ሲያስውባቸው ደብዘዝ ያለ ትዕይንት ነበር ።

መሥፍኒቱ የፖሊስ ሙከራዎቹን ከአንድ ረጅም ውብ ዴስክና ማለፊያ ወንበሮች ካሉበት የሥራ ሥፍራ ከሚመስል አፓርትሜንት ይዛቸው ገባች ። ሰሚናዊቱን የብርሃን ጮራ መከላከል አይሞክርም ።

“ ሚስ ሉቃስ የዚህ ድርጅት ባለቤት ነኝ ። ” አለቻቸው ። “ጓደኛዬ ወይዘሪት ሆብሐውስ ዛሬ ከዚህ ሥፍራ የለችም ” አለች በድጋሚ ።

“ የለም እመቤት ፣ ” አለ የሃምሳ አለቃ ኮብ ዜናውን እንደ ዜና ሳያየው ። ንግግሩን ሳይጨርስ ፣

“ ይህ የፍተሻ ትዕዛዛችሁ በጣም ትምክህተኛነት የወጠረው መስሎ ይሰማኛል ፣ ” አለች ሚስ ሉቃስ ። “ ይህ የወይዘሪት ሆብ ሐውስ የግል ጽሕፈት ቦት ነው ። በትክክል ተስፋ እንደማደርገው ደምበኞቻችንን መረባበሽ ሰናንተ ጥሩ አይመስለኝም ። ”

“ እስከዚህም ሚያስጨንቅሽ ጉዳይ የለም ” አለ ኮብ ። “እኛ ሰዎች ከሚስተናገዱበት ሥፍራ የምንፈልገው ምንም ነገር የለም ።”

ካለፍላጐቷ እስክትወጣ ድረስ በትህትና ጠበቀ ። የቫሌሪ ሆብ ሐውስን ጽሕፈት ቤት ተመለከተ ። በጣም የጠበበው መስኮት በኋላ ያለውን የሌሎች መደብሮችንና ድርጅቶች ህንጻ ያሳያል ። ግድግዳዎቹ በገረጡ ግራጫ የመስኮት መሸፈኛዎች ተውበዋል ። ከም ድሩ ወለል ማለፊያ የፐርሺያ ምንጣፍ ተነጥፏል ። ዓይኖቹ ከግድግዳው ካለች ትንሽ ካዝና ወደ ትልቁ ዴስክ ተቅበዘበዙ ።

“ከካዝናው አይኖርም ፡” አለ ኮብ ። “ ግልጽ ነው! ” አለ በድጋሚ ።

ከሩብ ሰዓት በኋላ ካዝናውና የዴስኩ መሣቢያዎች ያለ የሌለ ሚስጥራቸውን ችሩአቸው ።

“ ምንም ነገር የለው ባዶ ነው ” አለ ማክክሬ በተፈጥሮው ሎቶ የመረታት ጸባይ የሌለውና ኮስታራው ሰው ።

“ ግና መጀመራችን ነው ፣ ” አለ ኮብ ።

መሣቢያዎቹን ከውስጣቸው ያለውን በመላ ካነጹ በኋላ በሥነ ሥርዓት ደራረቡት ። ሌሎቹን መሣቢያዎችም በማውጣት ገለበጧቸው።

ሳያስበው የደስታ ሲቃውን ተነፈሰ ።

“ ይኸው የድካማችን ውጤት ወዳጄ ! ” አለ ።

ከውስጠኛው የመሣቢያው ክፍል በማጣበቂያ ተያይዞ ወደ ስድስት የሚሆኑ ጥቁር ሠማያዊ መጽሐፎች በወርቅማ ጽሑፍ የተቀረጹ ባቸው ይታያሉ ።

“ ፓስፖርቶች ! ” አለ የሃምሳ አለቃ ኮብ ። “ በግርማዊት ንግሥት የውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት የተሰጠ ። አምላክና ይሀን እምነት ሚያሳድር ልብ ይቅር ይበላቸው ! ”

ማክክሬ ኮብ ፓስፖርቶቹን እየከፋፈተ ርስ በ‘ርስ ሲያወዳድራቸው ማለትም የተለጠፉባቸውን ሲያስተያይ በጉጉት አሰግጎ ተመለከተው ።

“ አንድ ሴት ናት ማለቱ በጣም ያስቸግራል ። ለመለየት ትችላለህ ? ” አለ ማክክሬ ።

ፓስፖርቶቹ የሚስዳ ሲልቫ የወይዘሪት ኢሪን ፍሬንች ፣ የሚስ አልጋ ኮሽን የወይዘሪት ኒና ያሊ መሲር የሚስ ግላዲስ ቶማስ እና የወይዘሪት ሞይራ አ ኒሊ ነበሩ ። በአጠቃላይ አንዲት ከሀያ አምስት እስከ አርባ የምትገመት ሴት የሚወክሉ ነበሩ ።

“ የተየለያየው የጸጉር አሠራር ነው በተለያየ ጊዜ ሥራውን የሚሠራ ፣ ” አለ ኮብ ። “ ጉትዮ ፣ ለሥላሳ ፣ ቀጥታ ቁርጥ ፣ ጋሜ ፣ ወዘተ ። አልጋ ኮሽንን መሆን ስትፈልግ አፍንጫዋን የሆነ ነገር ታደርገዋለች ፣ ለሚስ ቶማስ ደግሞ ጉንጯን ትነፋዋለች ። ይኸው ደግሞ ሁለት ሌሎች የውጭ ፓስፖርቶች ፣ እመቤት ማህሙዳ አልጄሪያዊትና በሊያ ዶናሻን ኢሪ ። በነዚህ በተለያዩ ስሞች የባንክ ሒሳብ ከፍታለች ማለት ችላለሁ ። ”

“ ትንሽ የተወሳሰበ አይመስልም ? ”

“ መወሳሰብ አለበት ወዳጄ ። የሀገር ውስጥ ገቢ ሁልጊዜ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይከታተላል ። ዕቃዎችን አስርጎ በማ

ስገባት ባለ ብዙ ገንዘብ መሆን እስከዚህም አይከብድም — ነገር ግን ባገኘህ ጊዜ ነው ችግሩ ። ይህ ትንሽ ከሚይፌየር ያለው የቁማር ክለብ በወይዘሪቷ የተጀመረው ለ'ዚሁ ሲባል ይመስለኛል ። በቁማር ገንዘብ ማግኘትን የገቢ ታክስ ኢንስፔክተሩ ሊከታተለው ማይችለው ነገር ነው ። ከገንዘቡ አብዛኛው የዝርፊያው ክፍል ከአልጄሪያና ፊረ ንሣይ ባንኮች እንዲሁም ከኤር ካዝናዎች ይቀመጣል ። በአጠቃላይ በሥርዓት የተቀናበረ ሥራ ነው ። እንግዲህ አንድ በቀን እነዚህን የሐሰት ፖስፖርቶች በእጅዋ ከቁጥር ሀያ ስድስት ሒኮሪ ጎዳና እንደ ያዘች ያቺ ምስኪን ትንሽ ልጅ ፣ ሲሊያ አይታታለች ማለት ነው ። ”

CITY - HALL LIBRARY
OF
ADDIS ABABA

20

“ የወይዘሪት ሆብሐውስ ብልህ ሀሳብ ነበር ” አለ ኢንስፔክተር ሻርፕ ። ድምጹ የረጋና አባታዊ መንፈሥ ያደመጥበታል ።

ካርዶች እንደሚበውዝ ሰው ሁሉ ፖስፖርቶቹን ከአንዱ እጁ ወደ ሌላው አዘዋወራቸው ።

“የተወሳሰበ የገንዘብ ጉዳይ ነው” አለ። “እንግዲህ ከአንዱ ባንክ ወደ ሌላው ስንዛወር ልንከርም ነዋ! ሚስጥሯን በሚገባ ነው የሸፈነችው ። የገንዘብ ግንኙነቷን በተለይ ማወቅ ያስቸግራል! በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሁሉንም ነገር ጨራርሳ ወደ ውጭ ሀገር በመሔድ የተንደላቀቀ ኑሮ ለመኖር ስላሰበች ነው ። በሠይጣናዊ መንገድ በተገኘው የሚሉት?በዚህ በሰበሰበችው ገንዘብ ማለቴ ነው።ብዙም የተሰወረ ነገር የለውም ። የተከለከሉ አልማዞች ፣ ሠማያዊ ሉሎች ወዘተ... ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የተሠረቁ ነገሮች ደግሞ ከሀገር ይወጣሉ።በሌላም በኩል የአደንዛዥ ዕጾችም ንግድ ይጧጧፋል ። በሚገባ የተቀናጀ የተደራጀ ነው ። በ‘ራሷ ሥም’ና በተለያዩ ሌሎች ስሞች ወደ ውጭ ትጓዛለች ። ግን እከታተላ አይደለም ። አስርጎ በድብቅ ማስገባቱ ሁልጊዜም ቢሆን በአንድ የሆነ ሰው አማካኝነት ይካሔዳል ። ከውጭ የጀርባ ሻንጣዎችን በሌሎች ተመሳሳይ ሻንጣዎች በአስፈላጊው ጊዜ የሚለውጡላት ወኪሎች አሏት ። አዎን ፣ በጣም ብልህነት የተመላውና የረቀቀ ዘዴ ነው ። ለ‘ዚህ ሁሉ ፍሬያማ ውጤት ያበቃንን ሔርኩሌ ፖይሮትን ማመስገን ይገባናል ። ለምስኪኗ ትንሽ ልጅ ለሲሊያ ይህን ሳይኮሎጂያዊ የሥርቆት መሣሪያ ዘዴ መምከሯ በጣም ብልህ የሚያሰኛት ነው ። ይህን ለማወቅ አፍታም ጊዜ አልወሰደብህም ። አይደለም እንዴ መሴ ፖይሮት ?”

ፖይሮት ግን አልተቀበለውም ። ፊቷ በፈገግታ ፈክቶ ሚስ ሀበርድ በአድናቆት ተመለከተቻው ። ውይይቱ በወረቀት ላይ ሳይሰፍር ከሚስ ሀበርድ ክፍል በጥንቃቄ በቃል ብቻ ነበር የተካሔደው ።

“ እንደዚያ ያደረጋት ለገንዘብ መንሰፍሰፍ ነበር ። በፖትሪሺያ ሌን የአልማዝ ቀለበት አዕምሮዋን ሳቱት ። ሞኝነቷ የከበሩ ደንጊያዎች ከዚያ በፊት እንደምትይዝ በዚህ መጋለጧን አላጤነችውም ።

አልማዙን ከሥፍራው በማውጣት በዚርኮን (ጨረቃ አልማዝ) ጫቱ ካቱን ማለቴ ነው። አዎን፡ ያ ነው በትክክል ስለ ቫሌሪ ሆብሐውስ ሀሳብ የሰጠኝ ። በጣም ጎበዝ ናት ። ምንም እንኳ ስለ ሴሊያ በጠየቅኋት ጊዜ በጣም እንዳዘነች ላት አድርጋ ብትንግረኝም ነቃሁባት'' አለ ፖይሮት።

'' ግን'ኮ ነፍስ ማጥፋት !'' አለች ሚስ ሀበርድ። ''በቀዝቃዛ መን ፈሥ፣ በጭካኔ ሰው ጨግደል! አሁንም ፍጹም ለማመን አይቻለኝም !''

ኢንስፔክተር ሻርፕ ፊቱ ደምኗል ።

''አሁን በሴሊያ አውስቲን ሞት ልንወነጅላት ገና ጊዜው አይፈ ቅድልንም '' አለ ። '' በማስረጉ ንግድ ብትሉ እንኳ እስማማለሁ ። ስለዚያ ምንም ችግር አይኖርም ። የግድያው ጉዳይ ግን በጣም ሸሩ የረቀቀ ነው።የሕግ ጠበቃው እንደዚህ ባለመንገድ አያየውም ። በርግጥ ለዚህ ጉዳይ የገፋፋት መንስኤ ይኖራል ። አጋጣሚውም ጭምር ማለቴ ነው ። ምናልባት ስለ ውርርዱና ከኒጌል እጅ ሞርፊያ ስለመኖሩም ታውቅ ይሆናል ። ለዚህ ተጨባጭ ማስረጃ የለንም ። በዚህ ላይ ከጉ ዳዩ የሚገቡ ሁለት ግድያዎችም አሉ ። ይሁን፣ ሚስ ኒኮሊተስን ልት ጠርዛት ትችላለች፣ በሌላ መልኩ ግን ፖትሪሺያ ሌንን ስለመግደል ማረጋገጥ አይቻልም ። በወቅቱ በምንም ነገር ልትጠየቅ የማትችል ሰው 'ርሷ ብቻ ናት ። ጀሮኒሞም በአሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ቤቱን ለቃ መውጣቷን መስክሮላታል ። በዚያ ላይ ነው ድርቅ ያለው ። በገ ንዘብ ታታልለው አታታልለው የማውቀው ጉዳይ የለም ። ''

'' የለም ! '' አለ ፖይሮት ራሱን እየነቀነቀ ። '' ፍጹም አላታ ለለችውም ። ''

''ከመንገዱ መጨረሻ ላይ የተሰጠን የቀማሚውም ማስረጃ አለን። በሚገባ ያውቃታል ። በአሥራ ሁለት ከአምስት በመምጣት የፊት ፓውደርና አስፕሪን እንደገዛች ስልኩንም እንደተጠቀመች ነግሮ ናል ። መደብሩን በአሥራ ሁለት ከሩብ በመልቀቅ ከውጭ ታክሲ ተሳፍራ መሔዷንም ጭምር ገልጾልናል ። ''

ፖይሮት ከወንበሩ ቀጥ ብሎ ተቀመጠ ።

'' ያ በጣም ታላቅ ቁም ነገር ያለው ጉዳይ ነው ! የምንፈልገው ጉዳይ ነው ! ''

'' በፈጠረህ ምንድነው የምታወራው ? ''

'' ከቀማሚው መደብር ስልክ መደወሏን ማለቴ ነው ። ''

ኢንስፔክተር ሻርፕ በንዴት ተመለከተው ።

“እስኪ አድምጠኝ መሴ ፖይሮት ? ጎላ ያሉትንና የምናውቃቸውን ነጥቦች እንውሰድ ። አሥራ ሁለት ሰዓት ከስምንት ደቂቃ ላይ ፓት ሪሺያሌን ከ‘ዚህ ክፍል በሕይወት ሆና በመደወል ላይ ነበረች ። በዚህ ትስማማለህ ? ”

“ ከዚህ ክፍል ሞደወሏን መናገር አልችልም ። ”

“ መልካም ከታችኛው ወለል ከአዳራሹስ ። ”

“ ከአዳራሹም አይመስለኝም ። ”

ኢንስፔክተር ሻርፕ በረጅሙ ተነፈሰ ።

“ ለፖሊስ - ጣቢያው መደወሏን የምትክድ ሞስሎ አይታየኝም። አይደሰም ሃ ሳ አለቃዬ? የፖሊስ ሀላፊውና ኒጌል ቻፕማን የወል-ሰውን ቃኘዎች መስለው አይታዩህም ? ”

“ በትክክል አይደሉም ። ጥሩ ! ስልክ ተደርጎላችኋል ። በማምት ከቀማሚው መደብር ካለው የሕዝብ ስልክ የተላለፈ ጥሪ ነበር ብዬ አስባለሁ ። ”

የኢንስፔክተር ሻርፕ ገጽታ በአፍታ ተለዋወጠ ።

“ ቫሌሪ ሆብሐውስ ናት የደወለችው ማለትህ ነው ? እንደ ፓት ሪሺያ ሌን አስመስላ ተናገረች ነው የምትለው ? ፖትሪሺያ ሌን አስ ቀደማ ሞታለች ነው ? ”

“ አዎን እንደዚያ ነው ያልኩት ! ”

ኢንስፔክተሩ ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ ጡጫውን ከጠ ረጴዛው ላይ አሳረፈው ።

“ ለማመን አልችልም ! ድምጿን - ራሴ ሰምቼዋለሁ ! ”

“ አዎን ፡ ሰምተኸዋል ። የሴት ልጅ ድምጽ ነው ። ድምጹ ቁርጥ ቁርጥ የሚል ፍርሃት የዋጠው ፡ ነገር ግን የ‘ርሷ ድምጽ ነው ። ማለት የፖትሪሺያ ሌንን ድምጽ ፍጹም አታውቀውም ። ”

“ ምናልባት አለየሁት ይሆናል ። ነገር ግን ጥሪውን ያነሳው ኒጌል ቻፕማን ነበረ ። ኒጌል ቻፕማን ሊታሰል ይችላል ብለህ ልትነግረኝ አትችልም ። በስልክ ድምፅን መደበቅ በጣም ቀላል ነገር ነው ። ወይ ንም የአንድ የሆነ ሰውን ማስመሰል የሚያስቸግር አይደለም ። የፖት ድምጽ ባይሆን ኖሮ ኒጌል ቻፕማን በሚገባ ይለየው ነበር ። ”

“አዎን” አለ ፖይሮት ። “ኒጌል ቻፕማን ሊያውቅ ይችል ነበር ። ነገር ግን ቻፕማን ፖትሪሺያ አለመሆኗን በሚገባ ያውቃል ! ከ‘ርሱ

የተሻለ ማን ሊያውቅ ይቻለዋል ፣ ማለት ከጥቂት ጊዜ አስቀድሞ ከ‘ራሷ ላይ በመደብደብ እስከገደላት ድረስ ማለቱ ነው ። ”

ኢንስፔክተሩ ለመናገር እስከሚችል ጥቂት ጊዜ ወሰደበት ።

“ ኒጌል ቻፕማን ፣ ኒጌል ቻፕማን ፣ ሞታ ባገኘናት ጊዜ’ኮ በጣም ነው እዬዬ ያለው እንደ ህጻን ልጅ ነው ያለቀሰው ። ”

“ ያቺን ልጅ ማንኛውም ሰው እንደሚወደው ሁሉ ይወዳታል ። ነገር ግን ያለው ፍቅር ሊያድናት አልቻለም ። ጥቅሙን እስከነካች በት ፍቅር አይደለም እላለሁ ። እንግዲህ ይሀን ሁሉ ጊዜ ሊሆን የሚችል ተጠርጣሪ ሆኖ የቆየው ማነው ፣ ኒጌል ቻፕማን ። ከ‘ጁ ሞርፊያ ይዞ የነበረው ማን ነው ፣ ኒጌልቻ ፕማን ። ጠለቅ ያለ የረቀቀ የማቀድ ችሎታ ሊኖረው የሚችል ማን ነው ፣ ኒጌልቻፕማን ። ለማጭበርበርና ሰው ለመ ግደል ቆራጥነት ያለውስ ማን ነው ፣ ኒጌል ቻፕማን ። ከምናውቃቸው ሁሉ ራሱን ከፍ አድርጎ የሚመለከትና ሞኳኔ ያለው ሰው ማን ነው ፣ ኒጌል ቻፕማን ። የነፍስ ገዳይ ባህርያት ያሉት ‘ርሱ ብቻ ነው ። የአ ብሾው ስሜት ፣ የሰው ንቀቱ ፣ እያደገ የመጣው ግድየለሽነቱ በማንኛ ውም መንገድ ራሱን እንዳያጪን ያደረገው ሁኔታ ፣ ያን አረንጓዴ የብዕር ቀለም በሚያስገርምና በየዋህነት መንገድ እንደማይጠረጠር አድርጎ በመጠቀም መጨረሻ ላይ ደግሞ የሌን ባትሰንን ፀጉር ከፖት ሪሺያ ጣቶች መካከል በሥህተት በመተው መጀጀሉና ፖትሪሺያ ከበ ስተኃላዋ በተመታችበት ወቅት የገዳይዋን ፀጉር ለመንጪት እንደማት ችል አለማሰቡ ናቸው ። እነዚህ ነፍስ ገዳዮች ሁልጊዜ እንደዚህ ናቸው ። በራስ ወዳድነት ፣ ራሳቸውን በማድነቅ ፣ በግል ደስታቸው ይቅበዘ በዛሉ ፣ ይከንፋሉ ። ኒጌል አንድ ደስታ አለው ቢባል የሚያሳዝንና የተ በላሸ የልጅነት ጊዜ ብቻ ነው — የማያድግ ፣ ያላደገ ህጻንና አንድ ነገር ብቻ የሚታየው ፣ ማለትም ራሱና ‘ርሱ የሚፈልገው ነገር ብቻ ! ”

“ ግን ለምን መሴ ፖይሮት ፣ ግድያውስ ለምን ፣ ሴሊያ አውስቲ ንስ ምናልባት እሺ ይሁን ፣ ግን ፖትሪሺያ ሌንን ለምን ? ”

“ ያንን ” አለ ፖይሮት “ እኛ ሞፈለግ ያለብን ጉዳይ ነው ። ”

21

“ለረጅም ጊዜ አላየሁህም ” አለ ሽማግሌው ሚስተር ኢንዲኮት ሔርኩሌ ፖይሮትን በንጹህ ስሜት እየተመለከተው ። “ መምጣ ትህ በጣም ነው ያስደሰተኝ ” አለው በድጋሚ ።

“የለም ፣ በ‘ውነት ለሌላ እንኳ ሳይሆን ” አለ ሔርኩሊ ፖይሮት ። “ እንድ ነገር ፈልጌ ነው ። ”

“ እንደምታውቀው ባለው ለተኛዬ ነህ ። ያን አስከፊ የአበርኒዚ ጉዳይ ያታለልክልኝ አንተ ነበርክ ፣ ከጉድ አውጥተኸኛል ። ”

“ከዚህ ሥፍራ ሳይህ በጣም ነው የተገረምኩት። ጡረታ የወጣህ መስሎኝ ነበር ። ”

ሽማግሌው ጠበቃ ፈገግ አለ ። የ‘ርሱ ድርጅት የተከበረና ብዙ ዕደ ሚ ያለው ነው ።

“ ዛሬ የመጣሁት የቆዬ ደምበኛዬን ለመጠየቅ ነበር ። አሁንም የአንድ ሁለት የቆዩ ወዳጆቼን ጉዳይ እከታተላለሁ ። ”

“ሰር አርተር ስታንሊ የቆዬ ወዳጄና ደንበኛየም ነው።አልነበረም?”

“ አዎን ፣ እንዴታ ! ወጣት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ የሕግ ጉዳዮቹን በመላ ስናካሔድለት ቆይተናል ። በጣም ትልቅ ጭንቅላት ያለው ሰው ነው ፖይሮት ። የተለየ አዕምሮ ነበር የያዘው ። ”

“ ዜና - ረፍቱ ትላንት በአሥራ ሁለት ሰዓት ነበር የተላለፈው ፣ ርግጠኛ ነኝ ። ”

“ አዎን ፤ ቀብሩም ዓርብ እለት ነው ። ለጥቂት ጊዜ ሲሰቃይ ነበር ። እንደሚመስለኝ ነቀርሣ ወጥቶበት ነው ። ”

“ክብርት ስታንሊይም የሞተችው‘ኮ ከጥቂት ዓመታት በፊት ነበር ። አይደለም ? ”

“ አዎን ፣ በግምት ሁለት ዓመታት ተኩል ይሆናታል ። ”

በጣም ከበዙትና እጅብ ካሉት ቅንድቦች ሥር ያሉት ብልህ ዓይኖች ፖይሮትን ትኩር ብለው ተመለከቱት ።

“ እንዴት ነበር የሞተችው ? ”

ጠበቃው እጥጋቢ መልስ መለሰለት ።

“ የሕግ ውሳኔው የሚያስረዳው በአጋጣሚ መድሐኒቱን እንደ ወሰደችው አድርጎ ነው ። ”

“ በእውነት እንደዚያ ነው ያደረገችው ? ”

ሚስተር ኢንዲኮት ለጥቂት ጊዜ ፀጥ - አለ ።

“ ይህን ተናገርክ ብዬ በርግጥ አልጠላህም ” አለው ። “ ይህን ለመ ጠየቅ ጥሩ ምክንያት እንዳለህ ፍጹም አልጠራጠርም ። ሚዲናል አደገኛ መድሐኒት ነው ይገባኛል ። ምክንያቱም በሚያድንና በሚገል መጠኑ መ ካከል ብዙም ልዩነት የሌለውም ነገር ነው። በሽተኛዋ በማንኮላጀት የወ ሰደችውን መጠን በመርሳት ሌላ ከደገመች ውጤቱ እደገኛ ይሆናል ። ”

ፖይሮት ራሱን ነቀነቀ ።

“ እንደዚያ ነበር ያደረገች ? ”

“ ካለጥርጥር ! ራሰን በራስ የማጥፋት ሁኔታ ወይንም ራስን በራስ የመግደል ዝንባሌ ፍጹም የለም ። ”

“ ሌላ ምንም የተለየ አስተያየት አልነበረም ? ”

ያ ሰውነትን ቀዶ የሚገባ የሚመስለው አስተያዬት እንደገና ከሔር ኩሌ ፖይሮት ላይ ተተኮሰ ።

“ ባሏ እኮ ምሥክርነት ሰጥቷል ። ”

“ ምን ነበር ያለው ? ”

“ አንዳንድ ጊዜ ግራ እንደሚገባትና በተለይ የማታ መድሐኒ ቷን ከወሰደች በኋላ በድጋሚ ሌላ እንደምትጠይቅ ግልጽ አድርጎ አስረድቷል ። ”

“ መዋሸቱ ነበር ? ”

“በ‘ውነት ፖይሮት ምን ዓይነት የሚዘገንን ጥያቄ ነው የምትጠ ይቀኝ ? እኔን ያውቃል ብለህ ለደቂቃስ ቢሆን እንዴት ታስባለህ ? ”

ፖይሮት ፈገግ አለ ። ያ የውሸት ገጽታው ሊያታልለው አልቻ ለም ።

“ ወዳጄ ፡ አንተ በሚገባ ‘ ምታውቀው ይመስለኛል ። ለጊዜው ግን ምን እንደምታውቅ በመጠየቅ አላስቸግርህም ። በምትኩ

አስተያየትህን ብጠይቅህ ይሻለኛል ። አንድ ሰው ስለሌላው ያለ ውን አስተያየት ማለት ነው ። አርተር ስታንሊ ሌላ ሴት ለማግባት ሲል የራሱን ሚስት ‘ ሚያስወግዳት ዓይነት ሰው ይመስልሃል ? ’’

ሚስተር ኢንዲኮት በትንኝ እንደተወጋ ሁሉ ዘለለ ።

‘‘ መሠረተ - ቢስ ነው !’’ አለ በቁጣ ። ‘‘ ፍጹም ምክንያት የለሽ ነው ! ሌላ ሴት ፍጹም አልነበረችውም ። ስታሊን ለሚስቱ ሚች ነው !’’

‘‘ አዎን ’’ አለ ፖይሮት ። ‘‘ እኔም እንደዚሁ ነበር ያሰብኩት ። አሁን ወደ አንተ የመጣሁበትን ጉዳይ ለመግለጽ እወዳለሁ ። የአር ተር ስታንሊይ የኑዛዜ ሰነድ ያዘጋጀህ ነገር ፊጅ ነህ ፣ ጉዳይ ፊጻ ሚውም ጭምር ። ’’

‘‘ ትክክል ! ’’

‘‘ አርተር ስታንሊ ልጅ ነበረው ። ልጁ እናቱ በሞተችበት ወቅት ከአባቱ ይጣላል ። ተጣልቶም ቤቱን ለቅቆ ይወጣል ። ስሙን እስከ መቀየር ደረጃ ይደርሳል ። ’’

‘‘ ያን እኔ አላውቅም ። ማን ብሎ ነው ራሱን የሚጠራው ? ’’

‘‘እርሱን እንደርስበታለን ። ወደዚያ ከመሔዳችን በፊት ግን መላ ምቶቻችንን እንሞክር ። ትክክል ከሆንኩኝ ፣ ምናልባት እውነቱን ትቀበለኝ ይሆናል ። እንደሚመስለኝ አርተር ስታንሊይ የታሸገና የታተመበት ደብዳቤ ካንተ ዘንድ ትቶ ሊሆን ይችላል ። አንድ በሆነ ሁኔታ ወይንም ከሞቱ በኋላ የሚከፈት ደብዳቤ ማለት ነው ። ’’

‘‘በ’ውነት ነው‘ምልህ ፖይሮት ! በመካከለኛው ዘመን ቢሆን በቀጥታ በ‘ሳት ነበር ‘ምትቃጠለው ። የምትሠራቸውን ሥራዎች እንዴት ማወቅ ይቻልሃል ? ’’

ንግግሩን አቋረጠ ። ሌላኛውም አልተነፈሰም ።

‘‘ መሀሪው አምላክ ! ’’ አለ ፖይሮት በተጠንቀቅ ። ‘‘ አጥፍ ቼዋለሁ እንዳትለኝ ብቻ — ’’ ።

ሚስተር ኢንዲኮት በተቃውሞ ራሱን ሲነቀንቅ ነፍሱ ተመ ለሰች ።

‘‘ ለማንኛውም መቸኮል የለብንም ’’ አለ ሰውዬው ። ‘‘ ራሴን ለማላመንና ርካታ ለማግኘት ሁሉንም ነገር መጠየቅ ይኖርብኛል ።’’

ፀጥ አለ ። ‘‘ ይህ ጉዳይ ’’ አለ ኮስተር ብሎ ፣ ‘‘ ከፍተኛ ሚስ ጥር ነው ። ለአንተም ቢሆን ፖይሮት — ’’ አለና ራሱን ነቀነቀ ።

‘‘እንድትነግረኝ የሚያበቃህ በቂ የሆነ ምክንያት ብለጥህስ ? ’’

“ያ የእንተ ፈንታ ነው ። ከዚህ ከምንነጋገረው ጉዳይ የተያያዘ በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነገር እንዴት መፍጠር እንደምትችል ለመ ረዳት አልችልም ። ”

“ አላውቅም ፣ ስለዚህ መገመት ይኖርብኛል ። ግምቱ ትክክ ለኛ ከሆነ ማለቱ ነው ። ”

“ ሊሆን የሚችል አይመስለኝም ” አለ ሚስተር ኢንዲኮት እጁን በማወዛወዝ ። ፖያሮት በረጅሙ ተነፈሰ ።

“ በጣም ጥሩ ። ከአዕምሮዬ ያለው መመሪያ እንደዚህ ነው ። ስር እርተር በሞተበት በዚህ ወቅት ልጁን ኒጌልን ለማግኘት፣ የት እን ደሚኖር ለማወቅ፣ እንዴት እንደሚኖርና በተለይ በወንጀል ተግባር ላይ መሣተፍ ወይንም አለመሳተፉን ማወቅ ይገባሃል ። ”

ያ ሊናወጥ የማይችለው የሚስተር ኢንዲኮት የሕግ ርጋታ ሥን ጥርጥሩ ወጣ ። ጥቂት ብቻ ሊደመጡ የቻሉ ማዳነቆችን ከከንፈሩ ፈታቸው ።

“ እውነተኛው ነገር ከ‘ጅህ እስካለ ፣” የምትጠይቀኝን በመላ ለመመለስ ዝግጁ ነኝ ። እንደገባኝ ሙያህ በፈጠረው አጋጣሚ አግኝ ተኸው ከወጣቱ ኒጌል ዘንድ የመጣህ ይመስለኛል ። ለመሆኑ ያ ወጣት ዲያብሎስ እስካሁን ከየት ነበር?” ሲል ጠየቀው ።

“ ታሪኩ እንደዚህ ይመስለኛል ። ከቤት ከወጣ በኋላ ስሙን ለወጠ ። ለማንኛውም ለማወቅ ለፈለገ ሁሉ ልክ እንደኑዛዜ አድርጎ ነበር የሚገልጸው ። ከጥቂት አጭበርባሪ ሰዎች፣ የአደንዛዥ ዕጽና የጌጣጌጥ አስራጊ ኮንትራባንዲስቶች ጋር ተቀላቀለ ። ይህ የማጭበ ርበር ሥራ የመጨረሻውን ቅርጽ ያገኘው በ‘ርሱ ጥረት ይመስለኛል። በጣም ተወዳዳሪ የማይገኝለት የዋህና ምንም የማያውቁ ተማሪዎችን የሚጠቀም ድርጅት ነበር ። አጠቃላዩ ሂደት የሚካሄደው በሁ ለት ሰዎች ነው ። ኒጌል ቻፕማን ብሎ አሁን ራሱን በሚጠራውና በአንዲት ቫሌሪ ሆብሐውስ በተባለች ወጣት ሴት ነበረ ። በ‘ኔ አስተ ሳሰብ ይህች ሴት ሳትሆን አትቀርም በመ ጀመሪያ ወደዚህ ነገር የሳበ ችው። አነስተኛ የግል ድርጅት ነው። የሚሠሩት በኮሚሽን ነው። ነገር ግን ከሚገባው በላይ ትርፍ የሚያጋብስ ድርጅት ነው። ዕቃዎቹ የከፋ ደት ሙጠናቸው ሲታይ በጣም ትናንሽ ነው ። ነገር ግን በሺህ ፓውን ዶች የሚቆጠሩ የከበሩ ደንጊያዎችና አደንዛዥ ዕጾች ሊይዙ የሚ ችሉት በጣም ትንሽ ሥፍራ ነው ። ከእነዚህ ሊታዩ ከማይችሉት አጋጣሚዎች አንዱ እስከተፈጠረ ድረስ ሁሉም ነገር ያለችግር ሲከ ናወን ቆየ ። አንድ ቀን አንድ የፖሊስ ሾኩንን ካምብሪጅ ተደርጎ

ከነበረ የሰው ግድያ በተያያዘ ጉዳይ ከተማሪዎቹ ሆስቱል አስፈላጊ ምርመራ ለማድረግ ሔደ ። ያ የተለየ ፍንጭ ኒጌልን ለምን እንዳርበደበደበው ምክንያቱን የምታውቀው ይመስለኛል። ፖሊሶች የሚከታተሉት መስለው ። ከቤቱ ውስጥ ጥቂት አፖፑሎችን ፊታ ። ያህን ያደረገው ፍርሃት ስለያዘው መልኩ እንዳይታይና የጀርባ ሻንጣ ይዞ ከቤቱ በኋላ በመውጣት አደንዛዥ ዕጹ ከሻንጣው ሥር በተሠራ ልዩ ሥፍራ ስለነበረ ምናልባት ፍንጭ ሊገኝበት ይችላል በማለት ተልተሎ ጣለው።

“ ፍርሃቱ እንኳ መሠረተ - ቢስ ነበር ። ፖሊሱ የመጣው የሆነ እስያዊ - አውሮፓዊ ተማሪ ለመፈለግ ነበር። ከልጃገረዶቹ አንዷ ይህን ሻንጣ ይዞ ወጥቶ በሚበጣጥስበት ወቅት እንደ አጋጣሚ አይታዋለች ። ያ ወዲያውኑ የሞት ውሳኔዋን አላጸናባትም ነበር ። በዚያ ፈንታ ራሷ ራሷን እንድታጠፋ የሚገፋፋትና ለዚህ የሚያደርሳትን የደያቡ ጥቃቅን ሥራዎችን እንድትሠራ በጣም እንዲሰማት የሚያደርግ እቅድ ተቀነባበረ ። ነገር ግን እቅዱን በጣም አወሳሰቡት ። በመካከሉ እኔ ተጠራሁ ። እኔም በነገሩ ፖሊስ እንዲገባበት ምክር አቀረብኩ ። ልጅቷ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰች ። ራሷን ዘነጋች ። ስለዚህ እንዲህ ያለ ሥራ ፈጽሚያለሁ ብላ አጋለጠች።ራሷን ያጋለጠችው ለሠራቻቸው ነገሮች ነበረ ። ነገር ግን እንደሚመስለኝ ቀጥላ ወደ ኒጌል ሔደች ። የሻንጣውን ጉዳይና ከአንዲት ተማሪ ጓደኛው ጽሑፍ ላይ ቀለም ማፍሰሱን እንዲያጋልጥ ገፋፍችው ። ኒጌል ወይንም ሌሎቹ ባልደረቦቹ ለሻንጣው እንጠራለን የሚል ግምት አልነበራቸውም ነበር።እንግዲህ አጠቃላይ የዘመቻ እቅዳቸው አደጋ ላይ መውደቁ ነው። ከዚህም በላይ ሴሊያ ይህቺው በአጠያየቂ ሁኔታ ላይ ያለችው ልጅ ሌላ አደገኛ የሆነና የምታውቀውን ሚስጥር እኔ ከዚያ ቤት ራት በበላሁበት ምሽት ትገልጸለች ። ኒጌል በትክክል ማን እንደነበር ታውቅ ነበር።”

“ ነገር ግን በርግጥ - ” አለ ሚስተር ኢንዲኮት ኩስተር ብሎ ።

“ኒጌል ከአንዱ ዓለም ወደ ሌላው ተዘዋውሯል ። ማንኛውም ባልንጀራው እሱን የሚያውቀው በአሁኑ ወቅት ቻፕማን ብሎ ነው። ነገር ግን ምን እንደሚሠራ ምንም አያውቅም ። ከሆቴሉ ማንም ሰው ቢሆን እውነተኛ ስሙ ስታንሊይ መሆኑን የሚያውቅ የለም ነገር ግን ሴሊያ በድንገት በሁለቱም እንደምታውቀው ገለጸችለት ። በተጨማሪ በአጋጣሚ ቫሌሪ ሆብሐውስ ወደ ውጭ በሀሰተኛ ፓስፖርት ደርሳ ሙምጣቷን ታውቅ ነበር ። ብዙ ሌሎች ጉዳዮችም ታውቅ ነበር ። በተከታዩ ምሽት በቀጠሮ ከአንድ ሥፍራ ታገኘዋለች ። መጠጥ ወይንም ቡና ይጋብዛታል ። ነገር ግን ሞርፊያ ነበረበት ። ከመኝታዋ በእንንቅልፍ እንዳለች ትሞታለች ። ሁሉም ነገር ራሷን በራሷ እንዳጠፋች ለማስመሰል ሲባል የተዘጋጀ ነበረ ። ”

‹‹ ነገር ግን ይህ መጨረሻው አይደለም ›› አለ ፖይሮት ። ‹‹ እነዚህን የሆስቴል ቁርኝት በባለቤትነት የምታካሔደው ሴትዮ የጥርጣሬው ሁኔታ እንደተጠናከረ ሞተች ። ቀጥሎ የመጨረሻውና አረመኔያዊ የሆነው ወንጀል ተፈጸመ ። ፓትሪሺያ ሌንኒጌልን በጣም ታፈቅር የነበረና ራሱም የሚወዳት ወጣት ከጉዳዩ ገብታ ችግር ከመፍጠር አባቱ ከመሞቱ በፊት መታረቅ እንደሚገባው ትገፋፋዋለች ። ብዙ ሐሰት ነገሮችን ይነግራታል ። ነገር ግን የመጀመሪያውን ደብዳቤም ቢቀዳድዳት ሁለተኛ ደብዳቤ መጻፏ እንደማይቀር ሀሳብ ያሳድርበታል ። እንደሚመስለኝ ወዳጄ ከርሱ አመለካከት ሊፈጠር የሚችል አደገኛው ነገር ያ መሆኑን ልትነግረኝ ትችል ይሆናል . . . ››

ሚስተር ኢንዲኮት ከመቀመጫው ተነስቶ ቆመ ። ከቤቱ ጥግ ያለውን ካዝና ከፈተው ። ከዚያም አንድ ረጅም ኤንቨሎፕ በእጁ እንደያዘ ተመለሰ ። ከበስተጀርባው ቀይ ማህተም አርፎበታል ። ሁለት ወረቀቶችን በማውጣትም ከፖያሮት ፊት አኖረው ።

ውድ ኢንዲኮት

ይህን የምትከፍተው ከሞትኩኝ በኋላ ነው ። ልጄ ኒጌልን ካለበት ፈልገህ የሠራው የወንጀል ድርጊት ወይንም ሌላም ጉዳይ ቢኖር እንድትረዳው ነው ።

እኔ የምነግርህ እውነት ከ‘ኔ ዘንድ ብቻ ሚስጥር ሆኖ የቆየ ነው ። ኒጌል ምንጊዜም በባህሪው ፍጹም የማይረባ ሆኖ ነበር የቆየው ። ሁለት ጊዜ ያህል ስሜን በቼክ ላይ ሲያጭበረብር ያዝኩት።በእያንዳንዱ አጋጣሚ ሪርማውን እኔው ራሴ ተቀብዬዋለሁ ። ነገር ግን ያጣሜ እንደማላደርገው አስጠንቅቄው ነበር ። በሶስተኛው ጊዜ የእናቱን ስም ነበር ያጭበረበረበት። ‘ሮሷም ያዛ ጠየቀችው ፡ ተቆጣችውም።እንዳትናገር ለመናት ። አልተቀበለችውም ። እኔና‘ርሷ ተነጋገርንበት ፡ ለ‘ኔ ልትገልጽልኝ እንደተዘጋጀች ሁሉ ግልጽ አደረገችው ። በዚያ ወቅት ማታ የመኝታ ዝግጅት ሲያዘጋጅላት ነበር፡ከፍተኛ መጠን ያለው መድሐኒት ሊሰጣት የቻለው ። መድሐኒቱ ከመሥራቱ በፊት ከመኝታ ክፍሌ መጥታ ሁሉንም ነገር ነግራኛለች ። በተከታዩም ቀን ሞታ ስናገኛት ማን እንዳደረገው አውቄ ነበር ።

ኒጌልን በጣም ከወቀስኩት በኋላ አጠቃላዩን ጉዳይ ለፖሊስ እንደማስረዳ ገለጽኩለት ። ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ ለመነኝ ። እንተ ብትሆን ምን ማድረግ ትችል ነበር ኢንዲኮት?ስለልጄ የተሳሳተ ሀሳብ የለኝም። ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ በሚገባ አውቃለሁ ። ሕሊናም ሆነ ርሕ

ራሔ የሌለው ጨካኝ ሰው ነመ ። ላድነው ሀሳብ አልነበረኝም ። ነገር ግን የወድ ሚስቴ ትውስት ሀሳቤን ቀየረው ። ፍትህን እንድሻላት ትፈልግ ነበር ? መልሱን የማወቀው ይመስለኛል ። ልጅዋ ከመሰቀያው ገመድ እንዲድንላት ትፈልጋለች ። የእኔ ሰውነት እንዳለቀ ሁሉ በስግችን መጥፋት የ'ርሷም ሰውነት እንደኔው ማለቁ አይቀርም ነበር ። ነገር ግን ሌላ ግምትም ነበረኝ ። በመጨረሻ ላይ አንድ ጊዜ ነፍሰ ገዳይ የሆነ ሰው ሁልጊዜም ነፍሰ ገዳይ መሆኑን አመንኩኝ። ለወደፊቱ ሌሎች ከዚሁ ሸረኛ እጅ ሊወድቁ የሚችሉ ይኖሩ ይሆናል ። ከልጇ ጋር ድርድር አደረግሁኝ ። ትክክልም ሆነ ሥህተት ምን እንደ ሠራሁ አላውቅም ። ከኔ ዘንድ እንዲቆይ የሠራውን ሥራ በማጋለጥ እንዲጽፈው አደረግሁት ። ቤቴን ለቆ እንዲሔድና እንደገና እንዳይ መለስ የራሱን አዲስ ሕይወት እንዲጀምር ወሰንን ። ለሁለተኛ ጊዜ እድል ልሰጠው እችላለሁ ። ለእናቱ የሚደርሳት ገንዘብ በቀጥታ የ'ርሱ ነው ። ጥሩ ትምህርት አለው ። ራሱን ለማሻሻል ሁሉንም ዓይነት እድል የታደለ ነው ።

ነገር ግን በማናቸውም ዓይነት የወንጀል ተግባር ከተያዘ ከ'ኔ ዘንድ የተወው ራሱን ያጋለጠበት ደብዳቤ ለፖሊስ መቅረብ ይገባዋል ። ራሴንም ከጉዳዩ የቆጠብኩት የኔም ሞት ቢሆን ችግሩን እንደ ማይፈታው በመረዳት ነው ።

የቆየህ ባልንጀራዬ ነህ ። ከትከሻህ የማሽከምህ ከፍተኛ ሀላፊነት ነው ። ነገር ግን ጓደኛህ በሆነችው በሞተችው ሴት ስም ነው የምጠይ ይቅህ ። ኒጌልን ፈልገው ። ምንም ጉዳይ ውስጥ ያልገባ ንጹህ ሰው ከሆነ ይህን ደብዳቤና ከውስጥ ያለውን ውሸንብር አቃጥለው ። ካል ሆነ ግን ፍትህ መረጋገጥ አለባት ።

ውድ ባልንጀራህ ፣

ለርተር ስታንሊይ

"አህ ! " አለና ፖይሮት ! በረጅሙ ተነፈሰ ።

ከውስጥ የነበረውን ወረቀት ዘረጋው ።

ከዚህ ላይ እንዳስፈርኩት ውድ እናቴን ከመጠን በላይ የሆነ የሚዲናል መድሐኒት ሰጥቼ ሀዳር 18,195...መግደሌን አረጋግጣለሁ።

ኒጌል ስታንሊይ ።

22

‘‘ ያለኽበትን ሁኔታ ለመሆኑ በደንብ ተገንዘበኽዋል ወይዘሪት ሆብሐውስ ? አስቀድሜ አስጠንቅቄኻለሁ ። ’’

ቫሌሪ ሆብሐውስ ሳይጨርስ አቋረጠችው ።

‘‘ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አውቃለሁ ። የምናገረው ሁሉ በማስረጃነት እንደሚያዝ አስጠንቅቀኽኛል ። ለዚያም ተዘጋጅቻለሁ። በአስራጊነት ተከስሻለሁ ። ተስፋ አለኝ ፣ ማለት የረጅም ጊዜ እሥራት ይጠብቀኛል ። ሌላኛው ክስ ደግሞ በግድያ ተባባሪነት የሚያስጠይቀኝ ይሆናል ። ’’

‘‘ ቃልኽን መስጠቱ ይጠቅምኽ ይሆናል።እኔ ግን ምንም ቃል አልገባልኽም ፣ አላስገድድኽምም ። ’’

‘‘ ጥንቃቄ ማድረጌን አላውቀውም ። እንደመልካም ፍጻሜ ሁሉ ያው ከወህኒ ገብቶ ለዓመታት መማቀቅ ነው ። ቃሌን እሰጣለሁ ። የምትሉትን የግድያ ተባባሪ መሆን እችል ይሆናል ። ነገር ግን ነፍሰ ገዳይ አይደለሁም ። የምፈልገው ግን በኒዬል ላይ ግልጽ የሆነ ክስ ሥመሥረት እንደሚገባው ነው ። ...

‘‘ ሴሊያ ብዙ ታውቅ ነበር።ያንን እንደምንም እወጣው ነበር ። ነገር ግን ኒዬል ምንም ጊዜ አልሰጠኝም ። ወደ ውጭ በቀጠሮ እንዲገናኙ ጠራት ። ስለቀለሙና ሻንጣው ራሱን እንደሚያጋልጥ ነግሯት ሳታይ ከቡናው ውስጥ ሞርፊያውን ጨመረበት ። ለሚስ ሀበርድ የጻፈችውን ደብዳቤዋን አስቀድሞ አግኝቶት ነበር ። ቀድዶ በመውሰድ ቁም ነገር ያለው ‘ራስን-በራስ ማጥፋት’የሚል ቃል አስፈረበት ። ይህንንም ወረቀትና ባዶ የሞርፊያ ቢልቃጥ (የጣለ መስሎ ያቆየውን) ከአልጋዋ አጠገብ አስቀመጠው ። ለጥቂት ጊዜ ይህንኑ ግድያ ሲያምሰለስል እንደነበር አሁን ተረድቼዋለሁ ። ከኔ ዘንድ በመምጣት ምን እንደፈጸመ ነገረኝ ። ለራሴው ብዬ ከ‘ርሱ ጋር መቆም ነበረብኝ ።

‘‘ በሚስ ኒክም ላይ የተፈጸመው ተመሳሳይ ሁኔታ ነው ። መጠጣቷን አወቀ ። ወደ ቤቷ ስትሔድ ከመንገድ ሊያገኛት ተዘጋጀ ፣ አገኛት እብሯት ከመጠጥ ቤቱ ተከትሏትገባ ።መጠጧን መረዘው ። ለ‘ኔ

ግን ካደኝ። አልነገረኝም።ነገር ግን እንደዚያ ማድረጉን ነቅቼበት ነበር። ቀጥሎ የፖት ግድያ ተፈጸመ ። ወደ መኝታ ቤቴ በመምጣት ዘርዝሮ አስረዳኝ። በበኩሌ ምን መፈጸም እንደሚገባኝ አስረዳኝ።ስለዚህ ሁለታችን አንዳችን በአንዳችን ጉዳይ እንደምንጠየቅና ይህን ማስወገድ እንደ ማይቻል ገባኝ ። በጊዜው ከ'ጂ ንጹህ ትርፍ ነበረ ። ነገር ግን ምንም መውጫ መንገድ የለኝም ነበር... ባትያዙኝ ኖሮ ከአንዱ ሀገር ወደ ውጭ በመሔድ አዲስ ሕይወት እጀምር ነበር ። ነገር ግን ያዛችሁኝ... አሁን አንድ ነገር ብቻ ነው ሚያስጨንቀኝ። ይህን አረመኔ ፈገግ ያለ ዲያብሎስ ተሰቅሎ ማየት ፈልጋለሁ ። ''

ኢንስፔክተር ሻርፕ በረጅሙ ተነፈሰ ። ይህ ሁሉ ያልተጠበቀ ርካታን 'ሚሰጥ ነበር ። የማይታመን እጣ-ፈንታ ! ነገር ግን አንዳች ጥርጣሬም እያስጨነቀው ነበር ።

ፖሊስ ሀላፊው ርሳሱን ቀረጸው ።

'' ነገሩን መረዳቴን ርግጠኛ አይደለሁም '' ብሎ ሻርፕ ቢጀምርም እርሷ ግን አቋረጠችው ።

''የለም!መረዳት አያስፈልግህም፡የራሴ ምክንያቶች አሉኝ'' አለች።

ሔርኩሌ ፖይሮት በርጋታ ፡

'' ሚስ ኔኮሊተስን ነው ? '' ሲል ጠየቃት ።

ትንሩ ቁርጥ ፡ ቁርጥ ሲል ይሰማታል ።

'' ነበረች! አይደለም? — እናትሽ አልነበረችም ? ''

'' አዎን '' አለች ቫሌሪ ሆብሐውስ '' እናቴ ነበረች... '' አለች ።

23

ክፍል አንድ

“ ሊገባኝ አይችልም ! ” አለ ሚስተር አኪቦምቦ በግልጽ ዓይኖቹን ከአንዱ ወዳንዱ ባለቀይ ጸጉር ያቅበዘብዛል ።

ሳሊ ፊንችና ሊን ባትሰን ከሚስተር አኪምቦምቦ በመነጋገር ላይ ቢሆኑም አኪምቦም ሊረዳቸው አልተቻለውም ።

“ አንተ የመሰለህ ኒጌል እኔ ወይንም አንተ እንድንጠረጠር ማድረጉን ነው ? ”

“ ከሁለት አንዳችንን ማለት እችላለሁ ” ሲል ሊን መለሰለት ። ቀጥሎም “ ጸጉሩን የወሰደው ከብሩሹ ላይ ነበር ” አለ ።

“ እባካችሁን ልረዳው አልቻልኩም” አለ ሚስተር አኪቦምቦ ። “ የፎቁን በረንዳ የዘለለው ኒጌል ነበር ? ” ሲል ጥያቄ አቀረበ ።

“ኒጌል እንደ ድመት መዝለል የሚችል ሰው ነው።ምን ያግደዋል? እኔ ግን መዝለል አልችልም ። ሰውነቴ በጣም ወፍራም ነው ” አለው ።

“ በከፍተኛ አክብሮትና ትህትና ምንም መሠረት ስለሌለው ጥርጣሬዬ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ”

“ ግድየለም ” አለ ሊን ።

“ ብቻ ብዙ ረድተሃል ” አለች ሳሊ ። “ ስለ ቦራሲኩ የነበረህን ሀሳብ ማለቴ ነው ” በማለት በድጋሚ ገለጸች ።

አኪቦምቦ ፈገግ አለ ።

“ አንድ ሰው ይህ ኒጌል ተፈጥሮው የተበላሸና ችግር ያለበት መሆኑን መገንዘብ አያዳግተውም ” አለ ሊን ።

“ የፈጣሪ ያለህ! ልክ እንደኮሊን ነው የምታወራው።ኒጌል ሁልጊዜም ቢሆን ትክሻዬን ይከብደኝ ነበር—በመጨረሻ ላይ ግን ለምን እንደ ነበረ መረዳት ችያለሁ ። ይገባሃል ሊንሰር አርተር ስታሊ ስሜታቸው

አሸንፏቸው ባይተውትና ኒጌልን በቀጥታ ለፖሊስ አሳልፈው ቢሰጡ ኖሮ ሦስቱ ሰዎች ዛሬ ይኖሩ እንደነበር ? ነገሩን አርቄ ሳስበው እንደ ዚያ ይመስለኛል ። ''

'' አሁንም ቢሆን አንድ ሰው የተሰማውን መገንዘብ ይቻለ ዋል ። ''

'' ሚስ ሳሊ ? ''

'' አቤት አኪምቦምቦ ? ''

'' ዛሬ ማታ ፕሮፌሰሬን ከዩኒቨርስቲው ፓርቲ ላይ ካገኘሽው እባክሽን ደህና ማሰቤን አስረድልኝ ። ዘወትር የማደረባና ደደብ የሆ ሳብ ስልት ነው ያለህ ይለኛል ። ''

'' ምን ቸግሮኝ አናግረዋለሁ ። ''

ሊን ባትሰን የደመነውን ምስል አስተዋለ ።

'' በአንድ ሣምንት ውስጥ ወደ አሜሪካ መመለስሽ ነው፡'' አላት። ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ።

'' ተመልሼመጣለሁ '' አለች ሳሊ ። '' ወይንም አንተ ከዚያ በመምጣት አንድ ኮርስ ልታጠና ትችላለህ '' አለችው ።

'' ምን ጥቅም አለው ? ''

'' አኪምቦምቦ ! '' አለች ሳሊ ። '' አንድ ቀን ከሠርግ ላይ ሚዜ ሆነህ መገኘት ትፈልጋለህ ? ''

'' ሚዜ ምንድነው እባክሽ ? ''

'' ሙሽርና ማለት ነው ። ሊን ለምሳሌ አንድ የጣት ቀለበት ይሰ ጥህና ሁለታችሁ በአማረ ልብስ ተሽሞንሙናችሁ ወደ ቤተክርስቲያን ትሔዳላችሁ ። በትክክለኛው ሰዓት የጣት ቀለበቱን ይጠይቅህና ከጣቴ ያጠልቀዋል ። የቤተክርስቲያኑ አርጋን የሠርጉን ሙዚቃ ያንረዋል ። ሁሉም ሰው ልቅሶ በልቅሶ ይሆናል ፡ እዚያ ላይ ያበቃልናል ። ''

'' አንቺና ሚስተር ሊን ትጋባላችሁ ማለት ነው ? ''

'' አዎን ፡ እንደዚያ ማለቴ ነው ።''

'' ሳሊ ! ''

'' ሊን ሀሳቡን ከተቀበለው ። ''

'' ሳሊ ! ስለ አባቴ ምንም አታውቂምኮ — ''

" ታዲያ ምን ይሁን ? አውቃለሁ ! አባትህ እብድ ቢሆኑም ግድ የለም ፣ ብዙ ሰዎች እብድ አባቶች አሉዋቸውና ። "

" በደም የሚተላለፍ ጭንቀት ሕመም አይደለም ።ያን በሚገባ እረጋግጥልሻለሁ ሳሊ ። ምን ያህል በእንቺ ምክንያት እንዳዘንኩ ብታውቂ ኖሮ — "

" እምን ትንሽ ጥርጣሬ ነበረኝ . . . "

" በአፍሪካ ውስጥ " አለ ሚስተር አኪቦምቦ " በድሮ ጊዜ ከአቶሚክ ዘመንና ከሣይንሣዊ አስተሳሰብ በፊት የጋብቻ ባህል በጣም የሚያስደስትና ጥንቃቄ የተመላው ነበር፣አጫውታችኋለሁ ።"

" ባታወራን ይሻላል ! " አለች ሳሊ ። " እኔንና ሊንን ታሳፍረናለህ ብዬ አስባለሁ ። ቀዩን ፀጉር ባየህ ወቅት አንተም ሀፍረት እንደተሰማህ ያስታውቅብህ ነበር ። አልነበረም ? "

ክፍል ሁለት

ሔርኩሌ ፖይሮት ወይዘሪት ሊመን ከፊቱ ያቀረበችለትን የመ ጨረሻ ደብዳቤዎች ፈረመ ።

“ በጣም ጥሩ ” አለ እየከበደው ። “ ቅንጣት እንኳ ሥህተት የለውም አላት ። ”

ወይዘሪት ሊመን ትንሽ እንደተሰማት ያስታውቅባታል ።

“ ዘወትር እንደማልሳሳት ተስፋ አደርጋለሁ ” አለች ።

“ ዘወትር አይደለም ። አንድ ጊዜ ግን ተሳስተሽ ነበር ። እህትሽ ለመሆኑ እንዴት ናት ? ”

“ በመርከብ ወደ ሰሜን መዲናዎች ለመጓዝ እያሰበች ነው ።”

“ አሀ ! ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ።

በመርከብ — የሚቻል መሆኑን — በሀሳቡ አምሰለሰለ —

ርሱ እንደሆን የባህር ጉዞ አያደርግም ፣ አድርጎም አያውቅ በምንም ዓይነት ቢሆን... ከኃላውያለው ሰዓት ሰባት ላይ ደወለ ።

“ ሰዓቱ ሰባት ቆጣሪ ፣

ዓይጧ ከታች ተሽከርካሪ ፣

ከሒኮሪ ጎዳና ዳካሪ ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ።

“ ምናልክ መሴ ፖይሮት ? ”

“ ምንም ! ” አለ ሔርኩሌ ፖይሮት ።

Addis Ababa City Government Culture & Information Bureau Zone 4 Public Library

ፌስቡክ/2000

በተርጓሚዎቹ በተከታታይ የሚቀርቡ
የአጋታ ክርስቲ ሥራዎች

1. ENDLESS NIGHT
   የማይነጋ ለሊት

2. MURDER ON THE ORIENT EXPRESS
   ወንጀል በምሥራቁ ባቡር

3 MURDsR IN MESOPOTAMIA
   ግድያ በሜሶፖታሚያ

4 TEN LITTLE NIGGERS
   አሥሩ

5 SLEEPING MURDER-
   በእንቅልፍ ግድያ

6 THE MOVING FINGER
   ሰላቢው ጣት

7 THE MURDER OF ROGER ACKOYD
   የሮገር አኮይድ ግድያ

* * * *

ሌሎች ሥራዎች (በጊታቸው መኩንን)

1. DOGS OF WAR — ሞርጥ - ምርጡን ለኛ
2. እንከን — II



አጋታ ክርስቲ

‘በዲቴክቲቭ የፈጠራ ሥራችው በመላው ዓለም
አንቱ የተሰኙ ልዕልት’

አብዘርቨር

ፍቅር ይዞህ ነበር ! ”
ኛለ ። ”
መሆኑ በልጅቷ ሞት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ምን ያህል ሀዘንተኛ ነህ ?”
. ማለቴ ..እ..መልካም በእውነት መሌ...ፖይሮት...”

ፖይሮት አቀራረብና የምርመራ ጥያቄዎች ሚላግችውን ሊመቱ በሚ
ጥበብ የተቀየሱ ናቸው ። ”

ዴይሊ ቴሌግራም

* * * *

ፖይሮት በሂኮሪ ዲኮሪ ዶክ (በጉዳናው) ከሚጠበቅበት በላይ የቱ
ወደ የዲቴክቲቭ ተግባሩን ተወጥቷል ። ”

ዴይሊ ሚይል

* * * *

ፖይሮት የአሳዛኟን ወጣት ሞት ፊልፍሉ ለማውጣት ተወንጀዩን ሳይ
ማዘናናት ነበረበት ። ስለሆነም አንባቢን በመስክ ላይ ኩልል
እንደሚፈስ ወንዝ መንፈሱ ሳይሸበር እንዲንዝ አድርጉታል ። ”

ታይምስ ሊትረሪ ሰፕሊሜንት

* * * *

እስፔየር ፣ ግላስጐ ሔራልድ የተባሉና ሌሎችም ዝነኛ ጋዜጦችና
ች ረቂቅ የምርመራ ጥበቡን በጉዳናው የተወጣውን ፖይሮትንም
ታ ክርስቲን በማድነቅ ጽፈዋል ። ይህንን ረቂቅ የምርመራ ጥበብ ለመ
ሚቻለው ግን በማልቢያ ንባብ ሳይሆን በትዕግሥትና በልዩ ትኩ
። ”

ጐርጐርዮስ

ዋጋው :— ስምንት ብር

ሦ ፊት